# የብሉይ እና የሐዲስ ኪዳን መጻሕፍት ማውጫ

| ምሕፃረ ቃል | የመጽሐፉ ሙሉ ስም |
|---|---|
| ዘፍ. | ኦሪት ዘፍጥረት |
| ዘፀ. | ኦሪት ዘፀአት |
| ዘሌ. | ኦሪት ዘሌዋውያን |
| ዘኍ. | ኦሪት ዘኍልቍ |
| ዘዳ. | ኦሪት ዘዳግም |
| ኢያ. | መጽሐፈ ኢያሱ |
| መሳ. | መጽሐፈ መሳፍንት |
| ሩት. | መጽሐፈ ሩት |
| ፩ ሳሙ. | መጽሐፈ ሳሙኤል ቀዳማዊ |
| ፪ ሳሙ. | መጽሐፈ ሳሙኤል ካልዕ |
| ፩ ነገ. | መጽሐፈ ነገሥት ቀዳማዊ |
| ፪ ነገ. | መጽሐፈ ነገሥት ካልዕ |
| ፩ ዜ.መ. | መጽሐፈ ዜና መዋዕል ቀዳማዊ |
| ፪ ዜ.መ. | መጽሐፈ ዜና መዋዕል ካልዕ |
| ዕዝ. | መጽሐፈ ዕዝራ |
| ነህ. | መጽሐፈ ነህምያ |
| አስ. | መጽሐፈ አስቴር |
| ኢዮብ | መጽሐፈ ኢዮብ |
| መዝ. | መዝሙረ ዳዊት |
| ምሳ. | መጽሐፈ ምሳሌ |
| ተግ. | መጽሐፈ ተግሣጽ |
| መኃ. | መጽሐፈ መኃልይ |
| ኢሳ. | ትንቢተ ኢሳያስ |
| ኤር. | ትንቢተ ኤርምያስ |
| ሰ.ቆ. | ሰቆቃው ኤርምያስ |
| ሕዝ. | ትንቢተ ሕዝቅኤል |
| ዳን. | ትንቢተ ዳንኤል |
| ሆሴ. | ትንቢተ ሆሴዕ |
| አሞ. | ትንቢተ አሞጽ |
| ሚክ.. | ትንቢተ ሚክያስ |
| ኢዩ. | ትንቢተ ኢዩኤል |
| አብ. | ትንቢተ አብድዩ |
| ዮና. | ትንቢተ ዮናስ |
| ናሆ. | ትንቢተ ናሆም |
| ዕን. | ትንቢተ ዕንባቆም |
| ሶፎ. | ትንቢተ ሶፎንያስ |
| ሐጌ. | ትንቢተ ሐጌ |
| ዘካ. | ትንቢተ ዘካርያስ |

| | |
|---|---|
| ሚል. | ትንቢተ ሚልክያስ |
| ዕዝ.ሱቱ. | መጽሐፈ ዕዝራ ሱቱኤል |
| ዕዝ.ካል. | መጽሐፈ ዕዝራ ካልዕ |
| ጦቢ. | መጽሐፈ ጦቢት |
| ዮዲ. | መጽሐፈ ዮዲት |
| አስ. | መጽሐፈ አስቴር |
| ፩ መቃ. | መጽሐፈ መቃብያን ቀዳማዊ |
| ፪ መቃ. | መጽሐፈ መቃብያን ካልዕ |
| ፫ መቃ. | መጽሐፈ መቃብያን ሣልስ |
| ሲራ. | መጽሐፈ ሲራክ |
| ምና. | ጸሎተ ምናሴ |
| ተረ.ኤር. | ተረፈ ኤርምያስ |
| ሶስና | ሶስና |
| ባሮክ | መጽሐፈ ባሮክ |
| ጥበ. | መጽሐፈ ጥበብ |
| ሠ.ደ. | መዝሙረ ሠለስቱ ደቂቅ |
| ተ.ዳ. | ተረፈ ዳንኤል |
| ኩፋ. | መጽሐፈ ኩፋሌ |
| ሄኖ. | መጽሐፈ ሄኖክ |

---

| | |
|---|---|
| ማቴ. | የማቴዎስ ወንጌል |
| ማር | የማርቆስ ወንጌል |
| ሉቃ. | የሉቃስ ወንጌል |
| ዮሐ. | የዮሐንስ ወንጌል |
| የሐዋ. | የሐዋርያት ሥራ |
| ሮሜ. | ወደ ሮሜ ሰዎች |
| ፩ ቆሮ. | ወደ ቆሮንቶስ ሰዎች ፩ |
| ፪ ቆሮ. | ወደ ቆሮንቶስ ሰዎች ፪ |
| ገላ. | ወደ ገላትያ ሰዎች |
| ኤፌ. | ወደ ኤፌሶን ሰዎች |
| ፊል. | ወደ ፊልጵስዩስ ሰዎች |
| ቈላ. | ወደ ቈላስይስ ሰዎች |
| ፩ ተሰ. | ወደ ተሰሎንቄ ሰዎች ፩ |
| ፪ ተሰ. | ወደ ተሰሎንቄ ሰዎች ፪ |
| ፩ ጢሞ. | ወደ ጢሞቴዎስ ሰዎች ፩ |
| ፪ ጢሞ. | ወደ ጢሞቴዎስ ሰዎች ፪ |
| ቲቶ. | ወደ ቲቶ |
| ፊል. | ወደ ፊልሞና |
| ዕብ. | ወደ ዕብራውያን |
| ፩ ጴጥ. | የጴጥሮስ መልእክት ፩ |
| ፪ ጴጥ. | የጴጥሮስ መልእክት ፪ |
| ፩ ዮሐ. | የዮሐንስ መልእክት ፩ |
| ፪ ዮሐ. | የዮሐንስ መልእክር ፩ |
| ፫ ዮሐ. | የዮሐንስ መልእክት ፫ |
| ያዕ. | የያዕቆብ መልእክት |
| ይሁዳ | የይሁዳ መልእክት |
| ራእ. | የዮሐንስ ራእይ |

# ኦሪት ዘፍጥረት

## ምዕራፍ ፩

### የፍጥረት ታሪክ

[፩]በመጀመሪያ እግዚአብሔር ሰማይንና ምድ
ርን ፈጠረ። [፪]ምድር ግን ባዶ ነበረች፤ አትታ
ይምም[፩] ነበር፤ የተዘጋጀችም አልነበረችም፤
ጨለማም በውኃው ላይ ነበረ፤ የእግዚአብሔ
ርም መንፈስ በውኃው ላይ ይሰፍፍ ነበር።
[፫]እግዚአብሔርም፥ "ብርሃን ይሁን" አለ፤ ብር
ሃንም ሆነ።
[፬]እግዚአብሔርም ብርሃኑ መልካም እንደ
ሆነ አየ፤ እግዚአብሔርም በብርሃኑና በጨለ
ማው መካከል ለየ። [፭]እግዚአብሔርም ብርሃ
ኑን "ቀን፥" ጨለማውንም "ሌሊት" ብሎ
ጠራው። ማታም ሆነ፤ ጥዋትም ሆነ፤ አንደኛ
ቀንም ሆነ። [፮]እግዚአብሔርም፥ "በውኃው
መካከል ጠፈር ይሁን፤ በውኃና በውኃ መካከ
ልም ይለይ" አለ፤ እንዲሁም ሆነ።
[፯]እግዚአብሔርም ጠፈርን አደረገ፤ ከጠፈር
በላይና ከጠፈር በታች ያሉትንም ውኆች ለየ።
[፰]እግዚአብሔር ያን ጠፈር "ሰማይ" ብሎ
ጠራው። እግዚአብሔርም ያ መልካም እንደ
ሆነ አየ። ማታም ሆነ፤ ጥዋትም ሆነ፤ ሁለተ
ኛም ቀን ሆነ።
[፱]እግዚአብሔርም ከሰማይ በታች ያለው
ውኃ በአንድ ስፍራ ይሰብሰብ፥ የብሱም ይገ
ለጥ አለ፤ እንዲሁም ሆነ። ከሰማይ በታች
ያለው ውኃም በመጠራቀሚያው ተሰበሰበ፤
የብሱም ተገለጠ። [፲]እግዚአብሔርም የብሱን
"ምድር" ብሎ ጠራው፤ የውኃ መጠራቀሚያ
ውንም "ባሕር" ብሎ ጠራው። እግዚአብሔ
ርም ያ መልካም እንደሆነ አየ። [፲፩]እግዚአብሔ
ርም "ምድር በየዘሩ፥[፪] በየወገኑና በየመልኩ
ዘር የሚሰጥ ቡቃያን፥ በምድርም ላይ በየወ
ገኑ ዘሩ በውስጡ የሚገኝውንና ፍሬ የሚያፈ
ራውን ዛፍ ታብቅል" አለ፤ እንዲሁም ሆነ።
[፲፪]ምድርም በየዘሩ፥[፫] በየወገኑና በየመልኩ የሚ
ዘራ ቡቃያን፥ በምድር ላይ በየወገኑ ዘሩ በው
ስጡ የሚገኝውንና ፍሬ የሚያፈራውን ዛፍ አበ
ቀለች። እግዚአብሔርም ያ መልካም እንደሆነ
አየ። [፲፫]ማታም ሆነ፤ ጥዋትም ሆነ። ሦስተኛም
ቀን ሆነ።
[፲፬]እግዚአብሔርም አለ፥ "በምድር ላይ ያበሩ
ዘንድ፥ በቀንና በሌሊትም ይለዩ ዘንድ ብር
ሃናት በሰማይ ጠፈር ይሁኑ፤ ለምልክቶች፥
ለዘመናት፥ ለዕለታት፥ ለዓመታትም ይሁኑ።
[፲፭]በምድር ላይ ያበሩ ዘንድ፥ በሰማይ ጠፈር
ለማብራት ይሁኑ፤" እንዲሁም ሆነ። [፲፮]እግዚ
አብሔርም ሁለት ታላላቅ ብርሃናትን አደረገ፤
ትልቁ ብርሃን ቀንን እንዲመግብ፥ ትንሹ ብር
ሃንም ከከዋክብት ጋር ሌሊትን እንዲመግብ
አደረገ። [፲፯]እግዚአብሔርም በምድር ላይ ያበሩ
ዘንድ በሰማይ ጠፈር አኖራቸው፤ [፲፰]መዓልት
ንና ሌሊትንም እንዲመግቡ፥ በመዓልትና በሌ
ሊትም መካከል እንዲለዩ፤ እግዚአብሔርም ያ
መልካም እንደሆነ አየ። [፲፱]ማታም ሆነ፤ ጥዋ
ትም ሆነ፤ አራተኛም ቀን ሆነ።
[፳]እግዚአብሔርም አለ፥ "ውኃ የሕይወት እስት
ንፋስ ያላቸውን ተንቀሳቃሾችና በምድር ላይ ከሰ
ማይ በታች የሚበርሩ[፬] አዕዋፍን ታስገኝ፥" እንዲ
ሁም ሆነ። [፳፩]እግዚአብሔርም ታላላቅ አንበሪዎ
ችን፥ ውኃ ያስገኘውን ተንቀሳቃሽ ሕያው ፍጥ
ረትን ሁሉ በየወገኑ፥ የሚበርሩ አዕዋፍንም ሁሉ

---

፩ "አትታይም" በግሪክ ሰባ. ሊ. የለም።

፪ "በየዘሩ" በግሪክ ሰባ. ሊ. የለም።

፫ "በየዘሩ" በግሪክ ሰባ. ሊ. የለም።

፬ ዕብ. "አዕዋፍም ይብረሩ" ይላል።

በየወገናቸው ፈጠረ። እግዚአብሔርም ያ መልካም
እንደሆነ አየ። ፳፪እግዚአብሔርም እንዲህ ብሎ ባረ
ካቸው፥ "ብዙ፥ ተባዙም፥ የባሕርንም ውኃ ሙሉ
አት፤ ወፎችም በምድር ላይ ይብዙ።" ፳፫ማታም
ሆነ፤ ጥዋትም ሆነ፤ አምስተኛም ቀን ሆነ።

፳፬እግዚአብሔርም አለ፥ "ምድር ሕያዋን ፍጥረ
ታትን እንደ ወገኑ፥ እንስሳትንና ተንቀሳቃሾችን፥
የምድር አራዊትንም እንደየወገኑ ታውጣ፥" እንዲ
ሁም ሆነ። ፳፭እግዚአብሔርም የምድር አራዊትን
እንደየወገኑ፥ እንስሳትንም እንደየወገኑ፥ በምድር
የሚንቀሳቀሰውንም ሁሉ እንደየወገኑ አደረገ፤ እግ
ዚአብሔርም ያ መልካም እንደሆነ አየ።

፳፮እግዚአብሔርም አለ፥ "ሰውን በአርአያች
ንና በአምሳላችን እንፍጠር፤ የባሕር ዓሣዎች
ንና የምድር አራዊትን፥[፭] የሰማይ ወፎችን፥ እን
ስሳትንና ምድርን ሁሉ፥ በምድርም ላይ የሚን
ቀሳቀሱትን ሁሉ ይግዛ።" ፳፯እግዚአብሔርም
ሰውን በእግዚአብሔር አምሳል ፈጠረው። ወን
ድና ሴት አድርጎ ፈጠራቸው። ፳፰እግዚአብሔ
ርም ባረካቸው፤ እንዲህም አላቸው፥[፮] "ብዙ፤
ተባዙ፤ ምድርንም ሙሉአት፤ ግዙአትም፤ የባ
ሕርን ዓሣዎችንና የምድር አራዊትን፥[፯] የሰማይ
ወፎችንና እንስሳትንም ሁሉ፥ በምድር ላይ
የሚንቀሳቀሱትንም ሁሉ ግዙአቸው።"

፳፱እግዚአብሔርም አለ፥ "እነሆ፥ መብል
ይሆናችሁ ዘንድ በየዘሩ የሚዘራውንና የሚበቅ
ለውን፥ በምድር ሁሉ ላይ የምትዘሩትን የእህል
ፍሬ፥ ዘሩ በውስጡ ያለውን ቡቃያ፥ በየፍሬ
ውም የሚዘራውን ዛፍ ሁሉ ሰጠኋችሁ። ፴ለም
ድር አራዊት ሁሉ፥ ለሰማይም ወፎች ሁሉ፥
ሕያው ነፍስ ላላቸው ለምድር ተንቀሳቃሾችም
ሁሉ ሐመልማሉ ሁሉ መብል ይሁንላችሁ።"
እንዲሁም ሆነ። ፴፩እግዚአብሔርም የፈጠረውን
ሁሉ እጅግ መልካም እንደሆነ አየ። ማታም
ሆነ፤ ጥዋትም ሆነ፤ ስድስተኛም ቀን ሆነ።

## ምዕራፍ ፪

፩ሰማይና ምድር ዓለማቸውም ሁሉ ተፈ
ጸሙ። ፪እግዚአብሔርም የሠራውን ሥራ በስ
ድስተኛው ቀን ፈጸመ፤ እግዚአብሔርም በሰባ
ተኛው ቀን ከሠራው ሥራ ሁሉ ዐረፈ። ፫እግዚ
አብሔር ሰባተኛዋን ቀን ባረካት፤ ቀደሳትም፤
ሊፈጥረው ከጀመረው ሥራ ሁሉ በእርስዋ ዐር
ፎአልና።

፬እግዚአብሔር አምላክ ሰማይንና ምድርን
በፈጠረበት ቀን፥ በተፈጠሩ ጊዜ የሰማይና
የምድር ፍጥረት[፰] ይህ ነው። ፭የሜዳ ቍጥቋጦ
ሁሉ በምድር ላይ ከመኖሩ በፊት፥ የሜዳውም
ቡቃያ ሁሉ ከመብቀሉ በፊት፥ አዳምም ከመ
ፈጠሩ በፊት፥[፱] እግዚአብሔር አምላክ በም
ድር ላይ አላዘነበም ነበር፤ ምድርንም የሚሠራ
ባት ሰው አልነበረም። ፮ነገር ግን የውኃ ምንጭ
ከምድር ይወጣ ነበር፤ የምድርንም ፊት ሁሉ
ያጠጣ ነበር። ፯እግዚአብሔር አምላክም ሰውን
ከምድር አፈር ፈጠረው፤ በፊቱም የሕይወት
እስትንፋስን እፍ አለበት፤ ሰውም ሕያው ነፍስ
ያለው ሆነ።

### አዳም በኤዶም ገነት

፰እግዚአብሔር አምላክም በኤዶም በስተ
ምሥራቅ ገነትን ተከለ፤ የፈጠረውንም ሰው
በዚያ አኖረው። ፱እግዚአብሔር አምላክም ለማ
የት ደስ የሚያሰኘውን፥ ለመብላትም መልካም
የሆነውን ዛፍ ሁሉ ደግሞ ከምድር አበቀለ፤
በገነትም መካከል የሕይወትን ዛፍ፥ መልካም
ንና ክፉን የሚያሳየውንና የሚያስታውቀውንም
ዛፍ አበቀለ። ፲ወንዝም ገነትን ያጠጣ ዘንድ
ከኤዶም[፲] ይወጣ ነበር፤ ከዚያም ለዐራት መዓ
ዝን ይከፈል ነበር። ፲፩የአንደኛው ወንዝ ስም
ኤፌሶን[፲፩] ነው፤ እርሱም ወርቅ የሚገኝበትን
የኤውላጥ ምድርን ይከብባል። ፲፪የዚያችም
ምድር ወርቅ ጥሩ ነው። ፲፫በዚያም የሚያበራ
ዕንቍና የሚያብረቀርቅ ዕንቍ አለ። የሁለተኛ
ውም ወንዝ ስም ግዮን ነው፤ እርሱም የኢትዮ
ጵያን ምድር ሁሉ ይከብባል፤ ፲፬የሦስተኛውም
ወንዝ ስም ጤግሮስ ነው፤ እርሱም በአሶር ላይ
የሚሄድ ነው። አራተኛውም ወንዝ ኤፍራጥስ
ነው። ፲፭እግዚአብሔር አምላክም ሰውን ወስዶ

---

፭ "አራዊትን" የሚለው በግሪክ ሰባ. ሊ. እና በዕብ. የለም።

፮ ዕብ. "እግዚአብሔርም አላቸው" ይላል።

፯ ግሪክ ሰባ. ሊ. እና ዕብ. "አራዊትን" አይጽፍም።

፰ ግሪክ ሰባ. ሊ. "የሰማይና የምድር የልደት መጽሐፍ ነው" ይላል።

፱ ግሪክ ሰባ. ሊ. "አዳም ከመፈጠሩ በፊት" አይልም።

፲ በግእዙ "ኤዶም" አይልም።

፲፩ በግሪክ ሰባ. ሊ. እና በዕብ. "ፊሶን" ይላል።

ያበጃትም፥ ይጠብቃትም ዘንድ በኤዶም ገነት
አኖረው። ፲፮እግዚአብሔር አምላክም አዳምን
እንዲህ ብሎ አዘዘው፥ “በገነት ካለው ዛፍ
ሁሉ ብላ፤ ፲፯ነገር ግን መልካምንና ክፉን ከሚ
ያሳየውና ከሚያስታውቀው ዛፍ አትብላ፤ ከእ
ርሱ በበላህ ቀን ሞትን ትሞታለህና።”
፲፰እግዚአብሔር አምላክም አለ፥ “ሰው ብቻ
ውን ይኖር ዘንድ መልካም አይደለም፤ የሚረ
ዳውን ጓደኛ እንፍጠርለት እንጂ።” ፲፱እግዚአ
ብሔር አምላክም የምድር አራዊትንና የሰማይ
ወፎችን ሁሉ ደግሞ ከምድር ፈጠረ፤ በምን
ስም እንደሚጠራቸውም ያይ ዘንድ ወደ አዳም
አመጣቸው፤ አዳምም ሕያው ነፍስ ላለው ሁሉ
በስሙ እንደጠራው ስሙ ያው ሆነ። ፳አዳምም
ለእንስሳት ሁሉ፥ ለሰማይ ወፎችም ሁሉ፥ ለም
ድር አራዊትም ሁሉ ስም አወጣላቸው። ነገር
ግን ለአዳም እንደ እርሱ ያለ ረዳት አልተገኘ
ለትም ነበር። ፳፩እግዚአብሔር አምላክም በአ
ዳም ላይ እንቅልፍን አመጣ፤ አንቀላፋም፤ ከጎ
ኑም አጥንቶች አንድ አጥንትን ወስዶ ስፍራ
ውን በሥጋ መላው። ፳፪እግዚአብሔር አምላ
ክም[፭] ከአዳም የወሰዳትን አጥንት ሴት አድርጎ
ሠራት፤ ወደ አዳምም አመጣት። ፳፫ያን ጊዜም
አዳም አለ፥ “ይህች አጥንት ከአጥንቴ ናት፤
ሥጋዋም ከሥጋዬ ናት፤ እርስዋ ከባልዋ ተገ
ኝታለችና ሚስት ትሁነኝ።”[፮] ፳፬ስለዚህ ሰው
አባቱንና እናቱን ይተዋል፤ ሚስቱንም ይከተ
ላል፤ ሁለቱም አንድ ሥጋ ይሆናሉ። ፳፭አዳ
ምና ሚስቱም ዕራቁታቸውን ነበሩ፤ አይተፋ
ፈሩም ነበር።

## ምዕራፍ ፫

### የሰው አለመታዘዝ

፩እባብም እግዚአብሔር አምላክ ከፈጠራቸው
ከምድር አራዊት ሁሉ ይልቅ ተንኰለኛ ነበር።
እባብም ሴቲቱን “እግዚአብሔር በገነት ካለው
ዛፍ ሁሉ አትብሉ ያላችሁ ለምንድን ነው?”
አላት። ፪ሴቲቱም ለእባቡ አለችው፥ “በገነት
መካከል ካለው ከሚያፈራው ዛፍ ፍሬ እንበላ
ለን፤ ፫ነገር ግን በገነት መካከል ካለው ከዛፉ
ፍሬ፥ እግዚአብሔር አለ፦ እንዳትሞቱ ከእርሱ
አትብሉ፤ አትንኩትም።” ፬እባብም ለሴቲቱ
አላት፥ “ሞትን አትሞቱም፤ ፭ከእርስዋ በበላ
ችሁ ቀን፥ ዐይኖቻችሁ እንዲከፈቱ፥ እንደ እግ
ዚአብሔርም እንደምትሆኑ፥ መልካምንና ክፉን
እንደምታውቁ እግዚአብሔር ስለሚያውቅ ነው
እንጂ።” ፮ሴቲቱም ዛፉ ለመብላት ያማረ እን
ደሆነ፥ ለዐይንም ለማየት እንደሚያስጎመጅ፥
መልካምንም እንደሚያሳውቅ ባየች ጊዜ፥ ከፍ
ሬው ወሰደችና በላች፤ ለባልዋም ደግሞ ሰጠ
ችው፤ እርሱም ከእርስዋ ጋር በላ። ፯የሁለ
ቱም ዐይኖች ተከፈቱ፤ እነርሱም ዕራቁታቸ
ውን እንደ ሆኑ ዐወቁ፤ አፈሩም፤[፯] የበለስንም
ቅጠሎች ሰፍተው ለእነርሱ ለራሳቸው ግል
ድም አደረጉ። ፰እነርሱም ቀኑ በመሸ ጊዜ የእ
ግዚአብሔርን የአምላክን ድምፅ በገነት ውስጥ
ሲመላለስ ሰሙ፤ አዳምና ሚስቱም ከእግዚአ
ብሔር ከአምላክ ፊት በገነት ዛፎች መካከል
ተሸሸጉ።
፱እግዚአብሔር አምላክም አዳምን ጠርቶ፥
“አዳም፥ ወዴት አለህ?” አለው። ፲አዳምም
አለ፤ “በገነት ስትመላለስ ድምፅህን ሰማሁ፤
ዕራቁቴንም ስለሆንሁ ፈራሁ፤ ተሸሸግሁም።”
፲፩እግዚአብሔርም አለው፥ “ዕራቁትህን እንደ
ሆንህ ማን ነገረህ? ከእርሱ እንዳትበላ ካዘዝሁህ
ዛፍ በውኑ በላህን?” ፲፪አዳምም አለ፥ “ከእኔ
ጋር እንድትሆን የሰጠኸኝ ሴት እርስዋ ከዛፉ
ሰጠችኝና በላሁ።” ፲፫እግዚአብሔር አምላክም
ሴቲቱን፤ “ይህን ለምን አደረግሽ?” አላት።
ሴቲቱም አለች፥ “እባብ አሳተኝና በላሁ።”

### የእግዚአብሔር ፍርድ

፲፬እግዚአብሔር አምላክም እባቡን አለው፤
“ይህን ስላደረግህ ከእንስሳት ሁሉ፥ ከምድር
አራዊትም ሁሉ ተለይተህ አንተ የተረገምህ
ሁን፤ በደረትህና በሆድህም ትሄዳለህ፤ በሕይ
ወትህም ዘመን ሁሉ አፈርን ትበላለህ። ፲፭በአ
ንተና በሴቲቱ መካከል፥ በዘርህና በዘርዋም
መካከል ጠላትነትን አደርጋለሁ፤ እርሱ ራስ
ህን ይቀጠቅጣል፤ አንተም ሰኰናውን ትነድ
ፋለህ።” ፲፮ለሴቲቱም እግዚአብሔር አላት፥
“ጭንቅሽን እጅግ አበዛለሁ፤ በጭንቅ ትወል
ጃለሽ፤ ከወለድሽም በኋላ ፈቃድሽ ወደ ባልሽ

---

፭ ምዕ. ፪ ቁ. ፬፤ ፭፥ ፮፤ ፯፥ ፰፥ ፱፤ ፲፥ ፲፭፥ ፲፮ ዕብ. እና ግሪክ ሰባ. ሊ. “እግዚአብሔር አምላክ” ሲሉ፤ ግእዙ “እግዚአብሔር” ብቻ ይላል።

፮ በዕብ. እና በግሪክ ሰባ. ሊ. “እርስዋ ከወንድ ተገኝታለችና ሴት ትባል” ይላል።

፯ “አፈሩም” የሚለው በዕብ. እና በግሪክ ሰባ. ሊ. የለም።

ይሆናል፤ እርሱም ይገዛሻል።” ፲፯እግዚአብሔ
ርም አዳምን አለው፥ “የሚስትህን ቃል ሰም
ተሃልና፥ ከእርሱ እንዳትበላ ከአዘዝሁህ ከዚያ
ዛፍም በልተሃልና ምድር በሥራህ የተረገመች
ትሁን፤ በሕይወት ዘመንህም ሁሉ በድካም
ከእርስዋ ትበላለህ፤ ፲፰እሾህንና አሜከላን ታበቅ
ልብሃለች፤ የምድርንም ቡቃያ ትበላለህ። ፲፱ወደ
ወጣህበት መሬት እስክትመለስ ድረስ በፊትህ
ወዝ እንጀራህን ትበላለህ፤ አፈር ነህና ወደ
አፈርም ትመለሳለህና።” ፳አዳምም ለሚስቱ
“ሔዋን” ብሎ ስም አወጣ፤ የሕያዋን ሁሉ
እናት ናትና። ፳፩እግዚአብሔር አምላክም ለአዳ
ምና ለሚስቱ የቁርበትን ልብስ አደረገላቸው፥
አለበሳቸውም።

## አዳምና ሔዋን ከገነት እንደ ወጡ

፳፪እግዚአብሔር አምላክም አለ፥ “እነሆ፥
አዳም መልካምንና ክፉን ለማወቅ ከእኛ እንደ
አንዱ ሆነ፤ አሁንም እጁን እንዳይዘረጋ፥ ደግ
ሞም ከሕይወት ዛፍ ወስዶ እንዳይበላ፥ ለዘለ
ዓለምም ሕያው ሆኖ እንዳይኖር፥” ፳፫ስለዚህ
የተገኘባትን መሬት ያርስ ዘንድ እግዚአብሔር
አምላክ ደስታ ከሚገኝባት ገነት[፪] አስወጣው።
፳፬አዳምንም አስወጣው፤ ደስታ በሚገኝባት በገ
ነት አንጻርም አኖረው፤ ወደ ሕይወት ዛፍ የሚ
ወስደውንም መንገድ ለመጠበቅ የምትገለባበጥ
የነበልባል ሰይፍን በእጃቸው የያዙ ኪሩቤልን[፫]
አዘዛቸው።

## ምዕራፍ ፬

## ቃየልና አቤል

፩አዳምም ሚስቱን ሔዋንን ዐወቃት፤ ፀነ
ሰችም፤ ቃየልንም ወለደችው። ፪እርስዋም
“ወንድ ልጅ ከእግዚአብሔር አገኘሁ” አለች።
ደግሞም ወንድሙን አቤልን ወለደችው። አቤ
ልም በግ ጠባቂ ሆነ፤ ቃየልም ምድርን የሚ
ያርስ ሆነ። ፫ከብዙ ቀን በኋላም እንዲህ ሆነ፤
ቃየል ከምድር ፍሬ ለእግዚአብሔር መሥዋዕ
ትን አቀረበ፤ ፬አቤልም ደግሞ ከበጎቹ መጀ
መሪያ የተወለደውንና ከሰቡት አቀረበ። እግ
ዚአብሔርም ወደ አቤልና ወደ መሥዋዕቱ
ተመለከተ፤ ፭ወደ ቃየልና ወደ መሥዋዕቱ
ግን አልተመለከተም። ቃየልንም እጅግ አሳ
ዘነው፤ ፊቱም ጠቈረ። ፮እግዚአብሔር አምላ
ክም ቃየልን አለው፥ “ለምን ታዝናለህ? ለም
ንስ ፊትህ ጠቈረ? ፯በእውነት ያመጣህልኝ አይ
ደለም፤ አግባብስ በእውነት ታመጣልኝ ዘንድ
ነበር። በደልህ፤ እንግዲህ ዝም በል፤ የወንድ
ምህ መመለሻው ወደ አንተ ነው፤ አንተም
ትሰለጥንበታለህ።” ፰ቃየልም ወንድሙን አቤ
ልን፥ “ና ወደ ሜዳ እንሂድ” አለው። በሜ
ዳም ሳሉ ቃየል በወንድሙ በአቤል ላይ ተነሣ
በት፤ ገደለውም።

፱እግዚአብሔርም[፬] ቃየልን አለው፥ “ወን
ድምህ አቤል ወዴት ነው?” ቃየልም አለ፥
“አላውቅም፤ በውኑ የወንድሜ ጠባቂው እኔ
ነኝን?” ፲እግዚአብሔርም አለው፥ “ቃየል!
ምን አደረግህ? የወንድምህ የአቤል የደሙ
ድምፅ ከምድር ወደ እኔ ይጮሃል። ፲፩አሁንም
የወንድምህን ደም ከእጅህ ለመቀበል አፍዋን
በከፈተች በምድር ላይ አንተ የተረገምህ ነህ።[፭]
፲፪ምድርንም ባረስህ ጊዜ እንግዲህ ኀይልዋን
አትሰጥህም፤ በምድር ላይ ኰብላይና ተቅበዝ
ባዥ ትሆናለህ።” ፲፫ቃየልም እግዚአብሔርን
አለው፥ “ኀጢአቴ ይቅር የማትባል ታላቅ
ናትን? ፲፬እነሆ፥ ዛሬ ከምድር ፊት ከአሳደድ
ኸኝ፥ ከፊትህ እሰወራለሁ፤ በምድርም ላይ
ኰብላይና ተቅበዝባዥ እሆናለሁ፤ የሚያገኘኝም
ሁሉ ይገድለኛል።” ፲፭እግዚአብሔርም አለው፥
“እንዲህ አይደለም፤ እንግዲህ ቃየልን የገደለ
ሁሉ ሰባት እጥፍ ይበቀልበታል።” እግዚአብ
ሔርም ቃየልን ያገኘው ሁሉ እንዳይገድለው
ምልክት አደረገለት።

## የቃየል ትውልድ

፲፮ቃየልም ከእግዚአብሔር ፊት ወጣ፤ በኤ
ዶም አንጻር ባለችው ኖድ በምትባለው ምድ
ርም ኖረ። ፲፯ቃየልም ሚስቱን ዐወቃት፤
ፀነሰችም፤ ሄኖሕንም ወለደች። ከተማም
ሠራ፤ የከተማይቱንም ስም በልጁ ስም
“ሄኖሕ” አላት። ፲፰ሄኖሕም ጋይዳድን[፮]

---

፪ ዕብ. “ኤደን ገነት” ይላል።

፫ ዕብ. “ኪሩቤልንና ሰይፍን በኤደን ምሥራቅ አስቀመጠ” ይላል።

፬ ግሪኩ “እግዚአብሔር አምላክ” ይላል።

፭ ግእዙ “አፍዋን የከፈተች ምድር የተረገመች ትሁን” ይላል።

፮ ዕብ. “ኢራድ” ይላል።

ወለደ፤ ጋይዳድም ሜኤልን ወለደ፤ ሜኤ
ልም ማቱሳኤልን ወለደ፤ ማቱሳኤልም ላሜ
ሕን ወለደ። ፲፱ላሜሕም ለራሱ ሁለት ሚስ
ቶችን አገባ፤ የአንዲቱ ስም ዓዳ፥ የሁለተኛ
ይቱ ስም ሴላ ነበር። ፳ዓዳም ዮቤልን ወለ
ደች፤ እርሱም በድንኳን የሚቀመጡት የዘላ
ኖች አባት ነበረ። ፳፩የወንድሙም ስም ኢዮ
ቤል ነበር፤ እርሱም በገናንና መሰንቆን አስ
ተማረ። ፳፪ሴላም ደግሞ ቶቤልን ወለደች።
እርሱም ናስና ብረትን የሚሠራ ሆነ። የእኅ
ቱም ስም ኖኤም ነበረ። ፳፫ላሜሕም ለሚስ
ቶቹ ለዓዳና ለሴላ አላቸው፥ "እናንት የላ
ሜሕ ሚስቶች ቃሌን ስሙ፤ ነገሬንም አድ
ምጡ፤ እኔ ጕልማሳውን ስለ መቍሰሌ፤
ብላቴናውንም ስለ መወጋቴ ገድየዋለሁና፤
፳፬ቃየልን ሰባት እጥፍ ይበቀሉታል፤ ላሜ
ሕን ግን ሰባ ጊዜ ሰባት።"

## ሴትና ሄኖስ

፳፭አዳምም ዳግመኛ ሚስቱን ዐወቃት፤ ፀነ
ሰችም፤ ወንድ ልጅንም ወለደች። ስሙንም
ቃየል በገደለው በአቤል ፈንታ እግዚአብሔር
ሌላ ዘር ተክቶልኛል ስትል ሴት አለችው።
፳፮ሴትም ወንድ ልጅ ወለደ። ስሙንም ሄኖስ
አለው፤ እርሱም የእግዚአብሔርን ስም መጥ
ራት የጀመረ ነው።፬

## ምዕራፍ ፭

### የአዳም ትውልድ

(፩ዜ.መ. ፩፡ ፩-፬)

፩የሰዎች የትውልድ መጽሐፍ ይህ ነው።
እግዚአብሔር አዳምን በፈጠረ ቀን በእግዚ
አብሔር ምሳሌ አደረገው፤ ፪ወንድና ሴት
አድርጎ ፈጠራቸው፤ ባረካቸውም። እነርሱ
ንም በፈጠረበት ቀን ስሙን አዳም ብሎ
ጠራው። ፫አዳምም ሁለት መቶ ሠላሳ ዓመት
ኖረ፤ ልጅንም እንደ ምሳሌው እንደ መልኩ
ወለደ፤ ስሙንም ሴት ብሎ ጠራው። ፬አዳ
ምም ሴትን ከወለደ በኋላ የኖረው ሰባት
መቶ ዓመት ሆነ፤ ወንዶችንም፥ ሴቶችንም
ወለደ። ፭አዳምም የኖረበት ዘመን ሁሉ
ዘጠኝ መቶ ሠላሳ ዓመት ሆነ፤ ሞተም።

፮ሴትም ሁለት መቶ አምስት ዓመት ኖረ፤
ሄኖስንም ወለደ፤ ፯ሴትም ሄኖስን ከወለደ በኋላ
ሰባት መቶ ሰባት ዓመት ኖረ፤ ወንዶችንም፥
ሴቶችንም ወለደ። ፰ሴትም የኖረበት ዘመን
ሁሉ ዘጠኝ መቶ ዐሥራ ሁለት ዓመት ሆነ፤
ሞተም።

፱ሄኖስም መቶ ዘጠና ዓመት ኖረ፤ ቃይናን
ንም ወለደ፤ ፲ሄኖስም ቃይናንን ከወለደ በኋላ
ሰባት መቶ ዐሥራ አምስት ዓመት ኖረ። ወን
ዶችንም፥ ሴቶችንም ወለደ። ፲፩ሄኖስም የኖረ
በት ዘመን ሁሉ ዘጠኝ መቶ አምስት ዓመት
ሆነ፤ ሞተም።

፲፪ቃይናንም መቶ ሰባ ዓመት ኖረ፤ መላል
ኤልንም ወለደ፤ ፲፫ቃይናንም መላልኤልን ከወ
ለደ በኋላ ሰባት መቶ አርባ ዓመት ኖረ፤ ወን
ዶችንም፥ ሴቶችንም ወለደ። ፲፬ቃይናንም የኖ
ረበት ዘመን ሁሉ ዘጠኝ መቶ ዐሥር ዓመት
ሆነ፤ ሞተም።

፲፭መላልኤልም መቶ ስድሳ አምስት ዓመት
ኖረ፤ ያሬድንም ወለደ፤ ፲፮መላልኤልም ያሬ
ድን ከወለደ በኋላ ሰባት መቶ ሠላሳ ዓመት
ኖረ፤ ወንዶችንም፥ ሴቶችንም ወለደ። ፲፯መላ
ልኤልም የኖረበት ዘመን ሁሉ ስምንት መቶ
ዘጠና አምስት ዓመት ሆነ፤ ሞተም።

፲፰ያሬድም መቶ ስድሳ ሁለት ዓመት ኖረ፤
ሄኖክንም ወለደ፤ ፲፱ያሬድም ሄኖክን ከወለደ
በኋላ ስምንት መቶ ዓመት ኖረ፤ ወንዶች
ንም፥ ሴቶችንም ወለደ። ፳ያሬድም የኖረበት
ዘመን ሁሉ ዘጠኝ መቶ ስድሳ ሁለት ዓመት
ሆነ፤ ሞተም።

፳፩ሄኖክም መቶ ስድሳ አምስት ዓመት
ኖረ፤ ማቱሳላንም ወለደ፤ ፳፪ሄኖክም እግዚ
አብሔርን ደስ አሰኘው፤ ሄኖክም ማቱሳላን
ከወለደ በኋላ ሁለት መቶ ዓመት ኖረ፤ ወን
ዶችንም፥ ሴቶችንም ወለደ። ፳፫ሄኖክም የኖረ
በት ዘመን ሁሉ ሦስት መቶ ስድሳ አምስት
ዓመት ሆነ። ፳፬ሄኖክም እግዚአብሔርን ደስ
ስላሰኘው አልተገኘም፤ እግዚአብሔር ሰው
ሮታልና።

፳፭ማቱሳላም መቶ ሰማንያ ሰባት፭ ዓመት
ኖረ፤ ላሜሕንም ወለደ፤ ፳፮ማቱሳላም ላሜ
ሕን ከወለደ በኋላ ሰባት መቶ ሰማንያ ሁለት፮
ዓመት ኖረ፤ ወንዶችንም፥ ሴቶችንም ወለደ።

---

፬ ዕብ. "በዚያን ጊዜ ሰዎች የእግዚአብሔርን ስም መጥራት ጀመሩ" ይላል።
፭ ግሪክ ሰባ. ሊ. "መቶ ስድሳ ሰባት" ይላል።
፮ ግሪክ ሰባ. ሊ. "ስምንት መቶ ሁለት" ይላል።

፳፯ማቱሳላም የኖረበት ዘመን ሁሉ ዘጠኝ መቶ
ስድሳ ዘጠኝ ዓመት ሆነ፤ ሞተም።
፳፰ላሜሕም መቶ ሰማንያ ሁለት[፫] ዓመት ኖረ፤
ልጅንም ወለደ። ፳፱ስሙንም ከሥራዬ፥ ከእጆ
ድካምና እግዚአብሔር ከረገማት ምድር ይህ ያሳ
ርፈኝ ዘንድ አለው ሲል "ኖኅ" ብሎ ጠራው።
፴ላሜሕም ኖኅን ከወለደ በኋላ አምስት መቶ
ስድሳ አምስት ዓመት[፬] ኖረ፤ ወንዶችንም ሴቶ
ችንም ወለደ። ፴፩ላሜሕም የኖረበት ዘመን ሁሉ
ሰባት መቶ አርባ ሰባት[፭] ዓመት ሆነ፤ ሞተም።
፴፪ለኖኅም አምስት መቶ ዓመት ሆነው፤
ኖህም ሦስት ልጆችን ወለደ፤ እነርሱም ሴም፥
ካምና ያፌት ናቸው።

## ምዕራፍ ፮

### የሰዎች ክፋት

፩እንዲህም ሆነ፤ ሰዎች በምድር ላይ መብዛት
በጀመሩ ጊዜ መልከ መልካሞች ሴቶች ልጆች
ተወለዱላቸው፤ ፪የእግዚአብሔር ልጆችም የሰውን
ሴቶች ልጆች መልካሞች እንደሆኑ አዩ፤ ከመረ
ጡአቸውም ሁሉ ሚስቶችን ለራሳቸው ወሰዱ።
፫እግዚአብሔርም፥ "መንፈሴ በሰው ላይ ለዘለዓ
ለም አይኖርም፤ እነርሱ ሥጋ ናቸውና፤ ዘመናቸ
ውም መቶ ሃያ ዓመት ይሆናል" አለ። ፬በእነዚያም
ወራት ረዓይት በምድር ላይ ነበሩ። ከዚያም በኋላ
የእግዚአብሔር ልጆች ወደ ሰው ሴቶች ልጆች
በገቡ ጊዜ ልጆችን ወለዱላቸው፤ እነርሱም በዱሮ
ዘመን ስማቸውን ያስጠሩ ኀያላን ሰዎች ሆኑ።
፭እግዚአብሔርም የሰዎች ክፉ ሥራ በምድር
ላይ እንደበዛ፥ የልባቸው ዐሳብ ምኞትም ሁል ጊዜ
ፈጽሞ ክፉ እንደሆነ አየ። ፮እግዚአብሔርም ሰውን
በምድር ላይ በመፍጠሩ ተጸጸተ፤ በልቡም አዘነ።
፯እግዚአብሔርም፥ "የፈጠርሁትን ሰው ከምድር
ላይ አጠፋለሁ፤ ከሰው እስከ እንስሳና አራዊት፥
እስከ ተንቀሳቃሽም፥ እስከ ሰማይ ወፍም ድረስ፤
ስለ ፈጠርኋቸው ተጸጽቻለሁና" አለ። ፰ኖኅ ግን
በእግዚአብሔር ፊት ሞገስን አገኘ።

### ኖኅ

፱የኖኅ ትውልድ እንዲህ ነው። ኖኅም በትው
ልዱ ጻድቅ፥ ፍጹምም ሰው ነበረ፤ ኖኅም እግ
ዚአብሔርን ደስ አሰኘው።[፮] ፲ኖኅም ሦስት ልጆ
ችን ሴምን፥ ካምን ያፌትንም ወለደ። ፲፩ምድ
ርም በእግዚአብሔር ፊት ተበላሸች፤ ምድርም
ግፍን ተመላች። ፲፪እግዚአብሔርም ምድርን
እንደ ተበላሸች፥ ሥጋን የለበሱ ሁሉም በም
ድር ላይ መንገዳቸውን እንደ አበላሹ አየ።
፲፫እግዚአብሔር አምላክም ኖኅን አለው፥ "የሰው
ሁሉ ጊዜው በፊቴ ደርሶአል፤ ከእነርሱ የተነሣ
ምድር በግፍ ተመልታለችና፤ እኔም እነሆ፥ ከም
ድር ጋር አጠፋቸዋለሁ። ፲፬ባለ አራት መዓዝን የዕን
ጨት መርከብን ለአንተ ሥራ፤ በመርከቢቱም ክፍ
ሎችን አድርግ፤ በውስጥም፥ በውጭም በቅጥራን
ለቅልቃት። ፲፭መርከብዋንም እንዲህ ታደርጋታለህ፤
የመርከቢቱ ርዝመት ሦስት መቶ ክንድ፥ ወርድዋ
አምሳ ክንድ፥ ከፍታዋ ሠላሳ ክንድ ይሁን። ፲፮ለመ
ርከቢቱም መስኮትን ታደርጋለህ፤ ከቁመቷም ክንድ
ሙሉ ትተህ ጨርሳት፤ የመርከቢቱንም በር በጎንዋ
አድርግ፤ ታችኛውንም፥ ሁለተኛውንም፥ ሦስተኛ
ውንም ደርብ ታደርግላታለህ። ፲፯እኔም እነሆ፥ ከሰ
ማይ በታች የሕይወት ነፍስ ያለውን ሥጋ ሁሉ ለማ
ጥፋት በምድር ላይ የጥፋት ውኃን አመጣለሁ፤
በምድር ያለው ሁሉ ይጠፋል። ፲፰ቃል ኪዳኔንም
ከአንተ ጋር አጸናለሁ፤ ወደ መርከብም አንተ ልጆ
ችህንና ሚስትህን፥ የልጆችህንም ሚስቶች ይዘህ
ትገባለህ። ፲፱ከእንስሳ ሁሉ፥ ከተንቀሳቃሽ አራዊ
ትም ሁሉ፥ ሥጋ ካለው ሁሉ ከአንተ ጋር ትመግ
ባቸው ዘንድ ከሁሉም ሁለት ሁለት ወደ መርከብ
ታገባለህ፤ ተባትና እንስት ይሁን። ፳ከወፎች ሁሉ
በየወገናቸው፥ ከእንስሳም ሁሉ በየወገናቸው፥ በም
ድር ላይ ከሚሳቡ ተንቀሳቃሾች ሁሉ በየወገናቸው
ከአንተ ጋር ይመገቡ ዘንድ ከሁሉም ሁለት ሁለት
ወንድና ሴት እየሆኑ ወደ አንተ ይግቡ። ፳፩ከሚበላ
ውም የመብል ዓይነት ሁሉ ለአንተ ውሰድ፤ ወደ
አንተ ትሰበስባለህ፤ እርሱም ለአንተ፥ ለእነርሱም
መብል ይሆናል።" ፳፪ኖኅም እግዚአብሔር አምላክ
ያዘዘውን ሁሉ አደረገ፤ እንዲሁ አደረገ።

## ምዕራፍ ፯

### ማየ አይኅ

፩እግዚአብሔር አምላክም ኖኅን አለው፥
"አንተ ቤተሰቦችህን ሁሉ ይዘህ ወደ መር

---

፫ ግሪክ ሰባ. ሊ. "መቶ ሰማንያ ስምንት" ይላል።
፬ ዕብ. "አምስት መቶ ዘጠና አምስት" ይላል።
፭ ግሪክ ሰባ. ሊ. "ሰባት መቶ ሃምሳ ሦስት" ዕብ. "ሰባት መቶ ሰባ ሰባት" ይላል።
፮ ዕብ. "ኖኅም አካሄዱን ከእግዚአብሔር ጋር አደረገ" ይላል።

ከብ ግባ፤ በዚህ ትውልድ በፊቴ ጻድቅ ሆነህ
አይቼሃለሁና። ፪ከንጹሕ እንስሳ ሁሉ ሰባት
ሰባት ተባትና እንስት፥ ንጹሕ ካልሆነም እን
ስሳ ሁለት ሁለት ተባትና እንስት፤ ፫ከንጹሕ
የሰማይ ወፍ ደግሞ ሰባት ሰባት ተባትና እን
ስት፥ ንጹሕ ካልሆነ የሰማይ ወፍም ሁለት
ሁለት ተባትና እንስት እያደረግህ በምድር ላይ
ለምግብና ለዘር ይቀር ዘንድ ለአንተ ትወስ
ዳለህ። ፬ከሰባት ቀን በኋላ አርባ ቀንና አርባ
ሌሊት በምድር ላይ ዝናብ አዘንባለሁና፤ የፈ
ጠርሁትንም ፍጥረት ሁሉ ከምድር ሁሉ ላይ
አጠፋለሁና።” ፭ኖኅም እግዚአብሔር አምላክ
ያዘዘውን ሁሉ አደረገ። ፮ኖኅም የጥፋት ውኃ
በምድር ላይ በሆነ ጊዜ የስድስት መቶ ዓመት
ዕድሜ ነበረ።

፯ኖኅም ስለ ጥፋት ውኃ ልጆቹንና ሚስቱን፥
የልጆቹንም ሚስቶች ይዞ ወደ መርከብ ገባ።
፰ከንጹሓን ወፎችና ንጹሓን ካልሆኑ ወፎች፥
ከንጹሕ እንስሳ፥ ንጹሕም ካልሆነው እንስሳ፥
በምድር ላይ ከሚንቀሳቀሰው ሁሉ፥ ፱እግዚአብ
ሔር ኖኅን እንዳዘዘው፥ ሁለት ሁለት ተባትና
እንስት እየሆኑ ወደ ኖኅ ወደ መርከብ ውስጥ
ገቡ። ፲ከሰባት ቀን በኋላም የጥፋት ውኃ በም
ድር ላይ ሆነ። ፲፩በኖኅ ዕድሜ በስድስተኛው
መቶ ዓመት በሁለተኛው ወር ከወሩም በዐሥራ
ሰባተኛው ዕለት፥[፩] በዚያው ቀን የታላቁ ቀላይ
ምንጮች ሁሉ ተነደሉ፤ የሰማይ መስኮቶችም
ተከፈቱ፤ ፲፪ዝናቡም አርባ ቀንና አርባ ሌሊት
በምድር ላይ ሆነ።

፲፫በዚያውም ቀን ኖኅ ወደ መርከብ ገባ፤
የኖኅ ልጆችም ሴም፥ ካም፥ ያፌትና የኖኅ
ሚስት፥ ሦስቱም የልጆቹ ሚስቶች ከእርሱ
ጋር ገቡ። ፲፬አራዊትም ሁሉ በየወገናቸው፥ እን
ስሳትም ሁሉ በየወገናቸው፥ በምድር ላይ የሚ
ንቀሳቀሱ ተንቀሳቃሾችም ሁሉ በየወገናቸው፥
ወፎችም ሁሉ በየወገናቸው፥ የሚበሩ ወፎችም
ሁሉ፥ ፲፭ሥጋ ያላቸው ሕያዋን ሁሉ ሁለት
ሁለት እየሆኑ ወደ ኖኅ መርከብ ውስጥ ገቡ።
፲፮ሥጋ ካለው ሁሉ የገቡትም ተባትና እንስት
እግዚአብሔር ኖኅን እንዳዘዘው ገቡ፤ እግዚአብ
ሔር አምላክም መርከብዋን በስተውጭ ዘጋት።
፲፯የጥፋት ውኃ በምድር ላይ አርባ ቀንና አርባ
ሌሊት ነበረ፤ ውኃውም በዛ፤ መርከቢቱንም
አነሣ፤ ከምድርም ወደ ላይ ከፍ ከፍ አለች።
፲፰ውኃውም አሸነፈ፤ በምድር ላይም እጅግ
በዛ፤ መርከቢቱም በውኃ ላይ ተንሳፈፈች።
፲፱ውኃውም በምድር ላይ እጅግ በጣም አሸ
ነፈ፤ ከሰማይ በታች ያሉ ረዣዥም ተራሮችን
ሁሉ ሸፈነ። ፳ውኃው ወደ ላይ ዐሥራ አም
ስት ክንድ ከፍ ከፍ አለ፤ ረዣዥም ተራሮች
ንም ሸፈነ። ፳፩በምድር ላይ ሥጋ ያለው የሚን
ቀሳቀሰው ሁሉ ወፉም፥ እንስሳውም፥ አራዊ
ቱም፥ በምድር ላይ የሚርመሰመሰው ተንቀሳ
ቃሹምሁሉ፥ ሰውም ሁሉ ጠፋ። ፳፪የሕይወት
እስትንፋስ ያለው ሁሉ፥ በየብስም ያለው ሁሉ
ሞተ። ፳፫በምድር ላይ የነበረውም ሁሉ ከሰው
ጀምሮ እስከ እንስሳ፥ እስከሚርመሰመሰውም
ሁሉ ድረስ፥ እስከ ሰማይ ወፍም ድረስ ተደመ
ሰሰ፤ ከምድርም ተደመሰሱ። ኖኅም አብረውት
በመርከብ ከነበሩት ጋር ብቻውን ቀረ። ፳፬ውኃ
ውም መቶ አምሳ ቀን በምድር ላይ ሞላ።

## ምዕራፍ ፰

### የማየ አይኅ መጕደል

፩እግዚአብሔርም ኖኅን፥ በመርከብም ከእ
ርሱ ጋር የነበረውን አራዊቱን ሁሉ፥ እንስሳ
ውንም ሁሉ፥ አዕዋፍንም ሁሉ፥ የሚንቀሳቀስ
ውንም ሁሉ ዐሰበ፤ እግዚአብሔርም በምድር
ላይ ነፋስን አመጣ፤ ውኃውም ጐደለ፤ ፪የቀ
ላዩም ምንጮች፥ የሰማይም መስኮቶች ተደ
ፈኑ፤ ዝናብም ከሰማይ ተከለከለ፤ ፫ውኃውም
ከምድር ላይ እያደር እየቀለለ ይሄድ ጀመረ፤
ከመቶ አምሳ ቀንም በኋላ ውኃው ጐደለ።
፬መርከቢቱም በሰባተኛው ወር ከወሩም በሃያ
ሰባተኛው ቀን በአራራት ተራሮች ላይ ተቀመ
ጠች። ፭ውኃውም እስከ ዐሥረኛው ወር ድረስ
ይጐድል ነበር፤ በዐሥራ አንደኛው ወር ከወ
ሩም በመጀመሪያው ቀን የተራሮቹ ራሶች ተገ
ለጡ።

፮ከአርባ ቀን በኋላም ኖኅ የሠራውን የመርከ
ቢቱን መስኮት ከፈተ፤ ፯ከምድርም ላይ ውኃዉ
ጐድሎ እንደሆን ያይ ዘንድ ቁራውን ላከው፤ እር
ሱም ሄደ፤ ነገር ግን ውኃው ከምድር ላይ እስኪ
ደርቅ ድረስ አልተመለሰም። ፰ርግብንም ውኃው
ከምድር ፊት ጐድሎ እንደ ሆነ እንድታይ ከእርሱ
በኋላ ላካት። ፱ነገር ግን ርግብ እግርዋን የምታ
ሳርፍበት ስፍራ አላገኘችም፤ ወደ እርሱም ወደ
መርከብ ተመለሰች፤ ውኃው በምድር ላይ ሁሉ
ነበረና፤ እጁን ዘረጋና ተቀበላት፤ ወደ እርሱም

፩ ግዕዙ “አመ ፲ወ፯ ለጽልመት” ግሪክ ሰባ. ሊ. “በሃያ ሰባተኛው ዕለት” ይላል።

ወደ መርከብ ውስጥ አገባት። ፲ከዚያም በኋላ
ደግሞ ሰባት ቀን ቆይቶ፥ ርግብን እንደገና ከመ
ርከብ ላካት። ፲፩ርግብም በማታ ጊዜ ወደ እርሱ
ተመለሰች፤ በአፍዋም እነሆ፥ የለመለመ የወይራ
ቅጠል ይዛ ነበር። ኖኅም ከምድር ላይ ውኃው
እንደ ጐደለ ዐወቀ። ፲፪ደግሞ ሰባት ቀን ቆይቶ፥
ርግብን ላካት፤ ዳግመኛም ወደ እርሱ አልተመ
ለሰችም።

፲፫በኖኅ ዕድሜ በስድስት መቶ አንድ ዓመት
በመጀመሪያው ወር ከወሩም በመጀመሪያው ቀን
ውኃው ከምድር ላይ ደረቀ፤ ኖኅም የሠራትን
የመርከቢቱን ክዳን አነሣ፤ እነሆም፥ ውኃው ከም
ድር ፊት እንደ ደረቀ አየ። ፲፬በሁለተኛውም ወር
ከወሩም በሃያ ሰባተኛው ቀን ምድር ደረቀች።

፲፭እግዚአብሔርም ለኖኅ እንዲህ ብሎ ነገ
ረው፤ ፲፮"አንተ ሚስትህንና ልጆችህን፥ የል
ጆችህንም ሚስቶች ይዘህ ከመርከብ ውጣ።
፲፯ከአንተ ጋር ያሉትን አራዊት ሁሉ፥ ሥጋ ያላ
ቸውን ሁሉ፥ ወፎችንና እንስሶችን ሁሉ፥ በም
ድር ላይ የሚንቀሳቀሱትንም ሁሉ ከአንተ ጋር
አውጣቸው፤ በምድርም ላይ ብዙ፤ ተባዙ።
ምድርንም ሙሉአት።"[፩] ፲፰ኖኅም ሚስቱን፥
ልጆቹንና የልጆቹንም ሚስቶች ከእርሱ ጋር
ይዞ ወጣ፤ ፲፱አራዊት ሁሉ፥ እንስሳም ሁሉ፥
ወፎችም ሁሉ፥ በምድር ላይ የሚርመሰመሰው
ሁሉ በየወገናቸው ከመርከብ ወጡ።

## ኖኅ መሥዋዕት እንደ አቀረበ

፳ኖኅም ለእግዚአብሔር መሠውያዉን ሠራ፤
ከንጹሕም እንስሳ ሁሉ፥ ከንጹሓን ወፎችም ሁሉ
ወሰደ፤ በመሠውያውም ላይ መሥዋዕትን አቀረበ።
፳፩እግዚአብሔር አምላክም መልካሙን መዓዛ አሸ
ተተ፤ እግዚአብሔርም በልቡ አለ፥ "ምድርን
ዳግመኛ ስለ ሰዎች ሥራ አልረግምም፤ በሰው
ልብ ከታናሽነቱ ጀምሮ ክፉት ሁል ጊዜ ይኖ
ራል፤ ደግሞም ከዚህ ቀደም እንዳደረግሁት ሕያ
ዋንን ሁሉ እንደገና አልመታም። ፳፪በምድር ዘመን
ሁሉ መዝራትና ማጨድ፥ ብርድና ሙቀት፥
በጋና ክረምት፥ ቀንና ሌሊት አያቋርጡም።"

## ምዕራፍ ፱

## እግዚአብሔር ለኖኅ የሰጠው ቃል ኪዳን

፩እግዚአብሔርም ኖኅንና ልጆቹን ባረካቸው፤
እንዲህም አላቸው፥ "ብዙ፤ ተባዙ፤ ምድር
ንም ሙሉአት፤ ግዙአትም። ፪አስፈሪነታችሁና
አስደንጋጭነታችሁ በምድር አራዊት፥ በሰማይ
ወፎች፥ በምድር ላይ በሚንቀሳቀሱትም፥ በባ
ሕር ዓሦችም ሁሉ ላይ ይሁን፤ እነርሱንም በእ
ጃችሁ ሰጠኋችሁ። ፫ሕይወት ያለው ተንቀሳ
ቃሽ ሁሉ መብል ይሁናችሁ፤ ሁሉንም እንደ
ለመለመ ቡቃያ ሰጠኋችሁ። ፬ነገር ግን ደመ
ነፍስ ያለበትን ሥጋ አትብሉ፤ ፭ነፍሳችሁ ያለ
ችበትን ደማችሁን ከአራዊት ሁሉ እጅ እሻዋ
ለሁ፤ ከሰውም እጅ፥ ከሰው ወንድም እጅ፥
የሰውን ነፍስ እሻለሁ። ፮የሰውን ደም የሚያፈ
ስስ ሁሉ ስለዚያ ደም ፈንታ ደሙ ይፈስሳል፤
ሰውን በእግዚአብሔር መልክ ፈጥሬዋለሁና።
፯እናንተም ብዙ፤ ተባዙ፤ ምድርንም ሙሉ
አት፤ ግዙአትም።"

፰እግዚአብሔርም ለኖኅ፥ ከእርሱም ጋር ለል
ጆቹ እንዲህ ብሎ ተናገረ፦ ፱"እኔም እነሆ፥
ቃል ኪዳኔን ከእናንተ ጋር፥ ከእናንተም በኋላ
ከዘራችሁ ጋር አጸናለሁ፤ ፲ከእናንተ ጋር ላሉ
ትም፥ ሕያው ነፍስ ላላቸው ሁሉ፥ ከእና
ንተ ጋር ከመርከብ ለወጡት ለወፎች፥ ለእን
ስሳትም፥ ለምድር አራዊትም ሁሉ፥ ለማንኛ
ውም ለምድር አራዊት ሁሉ ይሆናል። ፲፩ቃል
ኪዳኔንም ከእናንተ ጋር አጸናለሁ፤ ሥጋ ያለ
ውም ሁሉ ዳግመኛ በጥፋት ውኃ አይጠፋም፤
ምድርንም ለማጥፋት ዳግመኛ የጥፋት ውኃ
አይሆንም።" ፲፪እግዚአብሔር አምላክም ለኖኅ
አለው፥ "በእኔና በእናንተ መካከል፥ ከእናን
ተም ጋር ባለው በሕያው ነፍስ ሁሉ መካከል፥
ለዘለዓለም ትውልድ የማደርገው የቃል ኪዳኔ
ምልክት ይህ ነው፤ ፲፫ቀስቴን በደመና አኖራ
ለሁ፤ የቃል ኪዳኔም ምልክት በእኔና በምድር
መካከል ይሆናል። ፲፬በምድር ላይ ደመናን በጋ
ረድሁ ጊዜ ቀስቴ በደመናው ትታያለች፤ ፲፭በእ
ኔና በእናንተ መካከል፥ ሕያው ነፍስ ባለውም
ሥጋ ሁሉ መካከል ያለውን ቃል ኪዳኔን አስ
ባለሁ፤ ሥጋ ያለውንም ሁሉ ያጠፋ ዘንድ ዳግ
መኛ የጥፋት ውኃን አላመጣም። ፲፮ቀስቴም
በደመና ትሆናለች፤ በእኔና በምድር መካከል፥
በምድር ላይ በሚኖር ሥጋ ባለው በሕያው
ነፍስ ሁሉ መካከል ያለውን የዘለዓለም ቃል
ኪዳን ለማሰብ አያታለሁ።" ፲፯እግዚአብሔርም
ኖኅን፥ "በእኔና በምድር ላይ በሚኖር፥ ሥጋ
ባለው ሁሉ መካከል ያጸናሁት የቃል ኪዳን
ምልክት ይህ ነው" አለው።

---

፩ ዕብ. "በምድር ላይ ይርመስመሱ፤ ይዋለዱ፥ በምድርም ላይ ይብዙ" ይላል።

## ኖኅና ልጆቹ

፲፰ከመርከብ የወጡት የኖኅ ልጆችም እነዚህ
ናቸው፤ ሴም፥ ካም፥ ያፌት፤ ካምም የከነ
ዓን አባት ነው። ፲፱በምድር ሁሉ ላይ የተበተኑ
የኖኅ ልጆች እነዚህ ሦስቱ ናቸው።
፳ኖኅም ገበሬ መሆን ጀመረ፤ ወይንም
ተከለ። ፳፩ከወይን ጠጁም ጠጣና ሰከረ፤ በድን
ኳኑም ውስጥ ዕራቁቱን ሆነ። ፳፪የከነዓን አባት
ካምም የአባቱን ዕራቁትነት አየ፤ ወደ ውጭም
ወጥቶ ለሁለቱ ወንድሞቹ ነገራቸው። ፳፫ሴምና
ያፌትም ልብስ ወስደው በጫንቃቸው ላይ አደ
ረጉ፤ የኋሊትም ሄደው የአባታቸውን ዕራቁት
ነት አለበሱ፤ ፊታቸውም ወደ ኋላ ነበር፤ የአ
ባታቸውንም ዕራቁትነት አላዩም። ፳፬ኖኅም ከወ
ይኑ ስካር በነቃ ጊዜ፥ ታናሹ ልጁ ያደረገበ
ትን ዐወቀ።
፳፭ኖኅም እንዲህ አለ፥ "ከነዓን ርጉም
ይሁን፤ ለወንድሞቹም የባሪያዎች ባሪያ
ይሁን።" ፳፮እንዲህም አለ፥ "የሴም አም
ላክ እግዚአብሔር ይባረክ፤ ከነዓንም ለእርሱ
ባሪያ ይሁን። ፳፯እግዚአብሔር የያፌትን ሀገር
ያስፋ፤ በሴምም ድንኳን ይደር፤ ከነዓንም ለእ
ርሱ ባሪያ ይሁን።"
፳፰ኖኅም ከጥፋት ውኃ በኋላ ሦስት
መቶ አምሳ ዓመት ኖረ። ፳፱ኖኅም የኖረበት
ዘመን ሁሉ ዘጠኝ መቶ አምሳ ዓመት ሆነ፤
ሞተም።

## ምዕራፍ ፲

### የኖኅ ልጆች ትውልድ

(፩ዜ.መ. ፩፡ ፭-፳፫)

፩የኖኅ ልጆች የሴም፥ የካምና፥ የያፌት ትው
ልድ ይህ ነው፤ ከጥፋት ውኃም በኋላ ልጆች
ተወለዱላቸው።

### የያፌት ትውልድ

፪የያፌት ልጆች ጋሜር፥ ማጎግ፥ ማዴ፥ ይህ
ያን፥ ይልሳ፥ ቶቤል፥ሞሳሕ፥ ቴራስ ናቸው።
፫የጋሜርም ልጆች አስከናዝ፥ ሪፋት፥ ቴርጋማ
ናቸው። ፬የይህያንም ልጆች ኤልሳ፥ ተርሴስ፥
ኬቲም፥ ሮድኢ[፩] ናቸው። ፭ከእነዚህም የአሕዛብ
ደሴቶች ሁሉ በየምድራቸው፥ በየቋንቋቸው፥
በየነገዳቸው፥ በየሕዝባቸው ተከፋፈሉ።

### የካም ትውልድ

፮የካምም ልጆች ኩሽ፥ ምስራይም፥ ፉጥ፥
ከነዓን ናቸው። ፯የኩሽም ልጆች ሳባ፥ ኤው
ላጥ፥ ሰብታ፥ ሬጌም፥ ሰበቅታ ናቸው። የሬ
ጌም ልጆችም ሳባ፥ ዮድዳን ናቸው። ፰ኩሽም
ናምሩድን ወለደ፤ እርሱም በምድር ላይ ኀያል
መሆን ጀመረ። ፱እርሱም በእግዚአብሔር ፊት
ኀያል አዳኝ ነበረ፤ ስለዚህም በእግዚአብሔር
ፊት ኀያል አዳኝ እንደ ናምሩድ ተባለ። ፲የግ
ዛቱም መጀመሪያ በሰናዖር ሀገር ባቢሎን፥
ኦሬክ፥ አርካድ፥ ካሌድን ናቸው። ፲፩አሦርም
ከዚያች ሀገር ወጣ፤ ነነዌን፥ ረሆቦት የተባለች
ውን ከተማ ካለህን፥ ፲፪በነነዌና በካለህ መካከ
ልም ዳስን[፪] ሠራ፤ እርስዋም ታላቂቱ ከተማ
ናት። ፲፫ምስራይምም ሉዲምን፥ ኢኒሜቲምን፥
ላህቢምን፥ ንፍታሌምን፥ ጳጥሮሶኒምን፥ ፲፬ከእ
ነርሱ የፍልስጥኤም ሰዎች የወጡባቸውን ከስ
ሎሂምንና ቀፍቶሪምንም ወለደ።
፲፭ከነዓንም የበኵር ልጁን ሲዶንን፥ ኬጤ
ዎንን፥ ፲፮ኢያቡሴዎንን፥ አሞሬዎንን፥ ጌርጌ
ሴዎንን፥ ፲፯ኤዌዎንን፥ አሩቄዎንን፥ ኤሴኒዎ
ንን፥ ፲፰አራዲዎንን፥ ሰማርዮንን፥ አማቲንን[፫]
ወለደ። ከዚህም በኋላ የከነዓናውያን ነገድ ተበ
ተኑ። ፲፱የከነዓናውያንም ወሰን ከሲዶን እስከ
ጌራራና ጋዛ ድረስ ነው፤ ወደ ሰዶምና ወደ
ገሞራ፥ ወደ አዳማና ወደ ሴባዮም እስከ ላሳ
ይደርሳል። ፳የካም ልጆች በየነገዳቸውና በየቋ
ንቋቸው፥ በየምድራቸውና በየሕዝባቸው እነ
ዚህ ናቸው።

### የሴም ትውልድ

፳፩ለሴምም ደግሞ ልጆች ተወለዱለት፤ እር
ሱም የያፌት ታላቅ ወንድምና የዔቦር ልጆች
ሁሉ አባት የሆነው ነው። ፳፪የሴምም ልጆች
ኤላም፥ አሦር፥ አርፋክስድ፥ ሉድ፥ አራም፥
ቃይናን።[፬] ፳፫የአራምም ልጆች ዑፅ፥ ሁል፥
ጋቴር፥ ሞሳሕ ናቸው። ፳፬አርፋክስድም ቃይ
ናንን ወለደ፤ ቃይናንም ሳላን፥ ሳላም ዔቦ

---

፩ ዕብ. "ዶዳኒም" ይላል።

፪ ዕብ. "ሬሴን" ይላል።

፫ ዕብ. ምዕ. ፲ ከቍ. ፲፫ እስከ ፲፰ ያለውን በብዙ ቍጥር ይጽፋል።

፬ "ቃይናን" በግእዙ እና በዕብ. የለም።

ርን ወለደ። ፳፭ለዔቦርም ሁለት ልጆች ተወለ
ዱለት፤ የአንደኛው ስሙ ፋሌቅ ነው፤ ምድር
በዘመኑ ተከፋፍላለችና፤ የወንድሙም ስም ዮቅ
ጣን ነው። ፳፮ዮቅጣንም ኤልሞዳድን፥ ሳሌፍ
ንም፥ ሐስረሞትንም፥ ያራሕንም፥ ፳፯ሀዶራም
ንም፥ አዚላንም፥፰ ደቅላንም፥ ፳፰ዖባልንም፥
አቤማኤልንም፥ ሳባንም፥ ፳፱ኦፊርንም፥ ኤው
ላጥንም፥ ዮባብንም ወለደ፤ እነዚህ ሁሉ የዮ
ቅጣን ልጆች ናቸው። ፴ስፍራቸውም ከማሲ
አንስቶ ወደ ስፋር ሲል እስከ ምሥራቅ ተራራ
ድረስ ነው። ፴፩የሴም ልጆች በየነገዳቸውና በየ
ቋንቋቸው፥ በየምድራቸውና በየሕዝባቸው እነ
ዚህ ናቸው።
፴፪የኖኅ የልጆቹ ነገዶች እንደ ትውልዳቸው
በየሕዝባቸው እነዚህ ናቸው። ከእነዚህም ከጥ
ፋት ውኃ በኋላ ሕዝቦች በምድር ላይ ተዘሩ።

## ምዕራፍ ፲፩

### የሰናዖር ግንብ

፩የዓለም ሁሉ ቋንቋ አንድ፥ ንግግሩም አንድ
ነበረ። ፪እንዲህም ሆነ፤ ከምሥራቅም ተነሥ
ተው በሄዱ ጊዜ በሰናዖር ምድር አንድ ሜዳ
አገኙ፤ በዚያም ተቀመጡ። ፫እርስ በርሳቸ
ውም፥ "ኑ ጡብ እንሥራ፤ በእሳትም እንተኩ
ሰው" ተባባሉ። ጡባቸውም እንደ ድንጋይ፥
ጭቃቸውም እንደ ዝፍት ሆነላቸው። ፬እርስ
በርሳቸውም፥ "ኑ ለእኛ ከተማና ራሱ ወደ
ሰማይ የሚደርስ ግንብ እንሥራ፤ በምድር ፊት
ሁሉ ላይ ሳንበተን ስማችንን እናስጠራው"
ተባባሉ። ፭እግዚአብሔርም የሰዎች ልጆች የሠ
ሩትን ከተማና ግንብ ለማየት ወረደ። ፮እግዚ
አብሔርም አለ፥ "እነሆ፥ እነርሱ አንድ ወገን
ናቸው፤ ለሁሉም አንድ ቋንቋ አላቸው፤ ይህ
ንም ለማድረግ ጀመሩ፤ አሁንም ያሰቡትን
ሁሉ መሥራትን አይተዉም። ፯ኑ እንውረድ፤
አንዱ የሌላውን ነገር እንዳይሰማው ቋንቋቸውን
በዚያ እንደባልቀው።" ፰እግዚአብሔርም ቋን
ቋቸውን ለያየ፤፩ ከዚያም በምድር ፊት ሁሉ
ላይ በተናቸው፤ ከዚያም በኋላ ከተማዪቱንና
ግንቡን መሥራትን ተዉ። ፱ስለዚህም ስምዋ
ባቢሎን ተባለ፤ እግዚአብሔር በዚያ የምድ
ርን ቋንቋ ሁሉ ደባልቆአልና፤ ከዚያም እግዚ
አብሔር በምድር ሁሉ ፊት ላይ እነርሱን በት
ኖአቸዋል።

### የሴም ትውልድ

(፩ዜ.መ. ፩፥ ፳፬-፳፯)

፲የሴም ትውልድ ይህ ነው። ሴም ከጥ
ፋት ውኃ በኋላ በሁለተኛው ዓመት አርፋክ
ስድን በወለደ ጊዜ የመቶ ዓመት ሰው ነበረ።
፲፩ሴምም አርፋክስድን ከወለደ በኋላ አምስት
መቶ ዓመት ኖረ፤ ወንዶችንም፥ ሴቶችንም
ወለደ፤ ሞተም።
፲፪አርፋክስድም መቶ ሠላሳ አምስት ዓመት
ኖረ፤ ቃይናንንም ወለደ፤ ፲፫አርፋክስድም ቃይ
ናንን ከወለደ በኋላ አራት መቶ አርባ ዓመት፪
ኖረ፤ ወንዶችንም፥ ሴቶችንም ወለደ፤ ሞተም።
ቃይናንም መቶ ሠላሳ ዓመት ኖረ፤ ሳላንም
ወለደ፤ ቃይናንም ሳላን ከወለደ በኋላ አራት
መቶ ሠላሳ፫ ዓመት ኖረ፤ ወንዶችንም፥ ሴቶች
ንም ልጆች ወለደ፤ ሞተም።
፲፬ሳላም መቶ ሠላሳ ዓመት ኖረ፤ ዔቦርንም
ወለደ፤ ፲፭ሳላም ዔቦርን ከወለደ በኋላ አራት
መቶ ሠላሳ፬ ዓመት ኖረ፤ ወንዶችንም ሴቶች
ንም ወለደ፤ ሞተም።
፲፮ዔቦርም መቶ ሠላሳ አራት ዓመት ኖረ፤
ፋሌቅንም ወለደ፤ ፲፯ዔቦርም ፋሌቅን ከወለደ
በኋላ አራት መቶ ሠላሳ፭ ዓመት ኖረ፤ ወንዶ
ችንም፥ ሴቶችንም ወለደ፤ ሞተም።
፲፰ፋሌቅም መቶ ሠላሳ ዓመት ኖረ፤ ራግው
ንም ወለደ፤ ፲፱ፋሌቅም ራግውን ከወለደ በኋላ
ሁለት መቶ ዘጠኝ ዓመት ኖረ፤ ወንዶችንም፥
ሴቶችንም ወለደ፤ ሞተም።
፳ራግውም መቶ ሠላሳ ሁለት ዓመት ኖረ፤
ሴሮሕንም ወለደ፤ ፳፩ራግውም ሴሮሕን ከወለደ
በኋላ ሁለት መቶ ሰባት ዓመት ኖረ፤ ወንዶች
ንም ሴቶችንም ወለደ፤ ሞተም።
፳፪ሴሮሕም መቶ ሠላሳ ዓመት ኖረ፤ ናኮር
ንም ወለደ፤ ፳፫ሴሮሕም ናኮርን ከወለደ በኋላ

---

፰ በግሪክ ሰባ. ሊ. "ኤቢል" በዕብ. "አውዛል" ይላል።
፩ "እግዚአብሔርም ቋንቋቸውን ለያየ" የሚለው በዕብ. እና በግሪክ ሰባ. ሊ. የለም።
፪ ግሪክ ሰባ. ሊ. "አራት መቶ ሠላሳ" ዕብ. "አራት መቶ" ይላል።
፫ ዕብ. "ሦስት መቶ ሠላሳ" ይላል።
፬ ዕብ. እና ግሪክ ሰባ ሊ. "ሦስት መቶ ሠላሳ" ይላል።
፭ ግሪክ ሰባ. ሊ. "ሦስት መቶ ሰባ" ይላል።

ሁለት መቶ ዓመት ኖረ፤ ወንዶችንም፥ ሴቶች
ንም ወለደ፤ ሞተም።
፳፬ናኮርም መቶ ዘጠኝ፯ ዓመት ኖረ፤ ታራ
ንም ወለደ፤ ፳፭ታራንም ከወለደ በኋላ ናኮር
መቶ ሀያ ዘጠኝ ዓመት ኖረ፤ ወንዶችንም፥
ሴቶችንም ወለደ፤ ሞተም።

## የታራ ትውልድ

፳፮ታራም መቶ፰ ዓመት ኖረ፥ አብራምንና
ናኮርን፥ አራንንም ወለደ። ፳፯አራንም ሎጥን
ወለደ።፱ ፳፰አራንም በተወለደባት ሀገር በከለ
ዳውያን ምድር፲ በአባቱ በታራ ፊት ሞተ።
፳፱አብራምና ናኮርም ሚስቶችን አገቡ፤ የአብ
ራም ሚስት ስምዋ ሦራ ነው፤ የናኮርም ሚስት
የአራን ልጅ ሚልካ ናት፤ አራንም የሚልካና
የዮስካ አባት ነው። ፴ሦራም መካን ነበረች፤
ልጆችም አልነበሩአትም። ፴፩ታራም ልጁን አብ
ራምንና የልጅ ልጁን የአራንን ልጅ ሎጥን፥
የልጁንም የአብራምን ሚስት ምራቱን ሦራን
ወሰደ፤ ከእርሱም ጋር ወደ ከነዓን ምድር
ይሄዱ ዘንድ ከከለዳውያን ምድር አወጣቸው።
ወደ ካራንም መጡ፤ በዚያም ተቀመጡ።
፴፪ታራም በካራን ምድር የኖረበት ዘመን ሁለት
መቶ አምስት ዓመት ሆነ፤ ታራም በካራን
ሞተ።

## ምዕራፍ ፲፪

### እግዚአብሔር አብራምን እንደ ጠራው

፩እግዚአብሔርም አብራምን አለው፥ “ከሀ
ገርህ፥ ከዘመዶችህም፥ ከአባትህም ቤት ተለ
ይተህ ውጣ፤ እኔ ወደማሳይህም ምድር ሂድ።
፪ታላቅ ሕዝብም አደርግሃለሁ፤ እባርክሃለሁ፤
ስምህንም ከፍ ከፍ አደርጋለሁ፤ ቡሩክም ትሆ
ናለህ፤ የሚባርኩህንም እባርካለሁ፤ ፫የሚረግ
ሙህንም እረግማለሁ፤ የምድር ነገዶችም ሁሉ
በአንተ ይባረካሉ።” ፬አብራምም እግዚአብ
ሔር እንደ ነገረው ሄደ፤ ሎጥም ከእርሱ ጋር
ሄደ፤ አብራምም ከካራን በወጣ ጊዜ ሰባ አም
ስት ዓመት ሆኖት ነበረ። ፭አብራምም ሚስ
ቱን ሦራንና የወንድሙን ልጅ ሎጥን፥ ያገኙ
ትን ከብት ሁሉና በካራን ያገኙአቸውን ሰዎች
ይዞ ወደ ከነዓን ምድር ለመሄድ ወጣ፤ ወደ ከነ
ዓንም ምድር ገቡ። ፮አብራምም እስከ ሴኬም
ስፍራ እስከ ታላቁ ዛፍ፲፩ ድረስ በዚያች ምድር
አለፈ፤ የከነዓን ሰዎችም በዚያን ጊዜ በዚያች
ምድር ነበሩ። ፯እግዚአብሔርም ለአብራም ተገ
ለጠለትና፥ “ይህችን ምድር ለዘርህ እሰጣለሁ”
አለው። አብራምም ለእርሱ ለተገለጠለት ለእግ
ዚአብሔር በዚያ መሠውያን ሠራ። ፰ከዚያም
በቤቴል ምሥራቅ ወዳለው ተራራ ወጣ፤ በዚ
ያም ቤቴልን ወደ ምዕራብ፥ ጋይን ወደ ምሥ
ራቅ አድርጎ ድንኳኑን ተከለ፤ በዚያም ለእግዚ
አብሔር መሠውያን ሠራ፤ የእግዚአብሔርንም
ስም ጠራ። ፱አብራምም ከዚያ ተነሣ፤ እየተጓ
ዘም ወደ አዜብ ሄደ፤ በዚያም ኖረ።

### የአብራም እንግድነት በግብፅ

፲በምድርም ራብ ሆነ፤ አብራምም በዚያ በእ
ንግድነት ይቀመጥ ዘንድ ወደ ግብፅ ወረደ፤
በምድር ራብ ጠንቶ ነበረና። ፲፩እንዲህም ሆነ፤
አብራም ወደ ግብፅ ለመግባት በቀረበ ጊዜ
ሚስቱን ሦራን እንዲህ አላት፥ “አንቺ መልከ
መልካም ሴት እንደ ሆንሽ እነሆ እኔ አውቃ
ለሁ፤ ፲፪የግብፅ ሰዎች ያዩሽ እንደ ሆነ ሚስቱ
ናት ይላሉ፤ እኔንም ይገድሉኛል፤ አንቺንም
በሕይወት ይተዉሻል። ፲፫እንግዲህ በአንቺ ምክ
ንያት መልካም ይሆንልኝ ዘንድ፥ ስለ አንቺም
ነፍሴ ትድን ዘንድ እኅቱ ነኝ በዪ።” ፲፬እንዲ
ህም ሆነ፤ አብራም ወደ ግብፅ በገባ ጊዜ የግ
ብፅ ሰዎች ሴቲቱን እጅግ ውብ እንደ ሆነች
አዩ፤ ፲፭የፈርዖንም አለቆች አዩአት፤ በፈርዖ
ንም ፊት አደነቁአት፤ ወደ ፈርዖን ቤትም ወሰ
ዱአት። ፲፮ለአብራምም ስለ እርስዋ መልካም
አደረጉለት፤ ለእርሱ በጎችም፥ በሬዎችም፥ አህ
ዮችም፥ በቅሎዎችም፥፲፪ ወንዶችና ሴቶች ባሪ
ያዎችም፥ ግመሎችም ነበሩት። ፲፯እግዚአብሔ
ርም በአብራም ሚስት በሦራ ምክንያት ፈርዖ
ንንና የቤቱን ሰዎች በታላቅ መቅሠፍት መታ።
፲፰ፈርዖንም አብራምን ጠርቶ አለው፥ “ይህ

---

፯ ግሪክ ሰባ. ሊ. “መቶ ሰባ ዘጠኝ” ይላል።

፰ ግሪክ ሰባ. ሊ. “ሰባ” ይላል።

፱ ዕብ. “የታራም ትውልድ ይህ ነው ታራ አብራምንና ናኮርን፥ አራንንም ወለደ” ይላል።

፲ ዕብ. “ዑር” ይላል።

፲፩ ዕብ. “እስከ ታላቁ የሞሬ ዛፍ” ይላል።

፲፪ “በቅሎዎችም” በዕብ. የለም።

ያደረግህብኝ ምንድን ነው? እርስዋ ሚስትህ
እንደ ሆነች ለምን አልገለጥህልኝም? ፲፱ለም
ንስ 'እኅቴ ናት' አልህ? ለእኔ ሚስት ትሆንኝ
ዘንድ ወስጃት ነበር። አሁንም እኅኳት፥ ሚስ
ትህ በፊትህ ናት፤ ይዘሃትም ሂድ።" ፳ፈርዖ
ንም ሰዎቹን ስለ አብራም አዘዘ፤ እርሱንም፥
ሚስቱንም፥ የነበረውንም[፫] ሁሉ ሸኙአቸው።

## ምዕራፍ ፲፫

### የአብራምና ሎጥ መለያየት

፩አብራምም ከግብፅ ወጣ፤ እርሱና ሚስቱ፥
ለእርሱ የነበረውም ሁሉ፥ ሎጥም ከእርሱ ጋር
ወደ አዜብ ወጡ። ፪አብራምም በከብት፥ በብ
ርና በወርቅ እጅግ በለጸገ። ፫ከአዜብ ባደረ
ገው በጕዞውም ወደ ቤቴል ሄደ፤ ያም ስፍራ
አስቀድሞ በቤቴልና በጋይ መካከል ድንኳን
ተክሎበት የነበረው ነው፤ ፬ስፍራውም አስቀ
ድሞ መሠውያ የሠራበት ነው፤ በዚያም አብ
ራም የእግዚአብሔርን ስም ጠራ። ፭ከአብራም
ጋር የሄደው ሎጥ ደግሞ የላምና የበግ መንጋ
ድንኳኖችም ነበሩት። ፮በአንድነትም ይቀመጡ
ዘንድ ምድር አልበቃቸውም፤ ንብረታቸው
ብዙ ነበርና፤ ስለዚህም ባንድነት ይቀመጡ
ዘንድ ምድር አልበቃቻቸውም። ፯በአብራምና
በሎጥ መንጎች ጠባቆች መካከልም ጠብ ሆነ፤
በዚያ ዘመን ከነዓናውያንና ፌርዛውያን በዚ
ያች ምድር ተቀምጠው ነበር። ፰አብራምም
ሎጥን አለው፥ "እኛ ወንድማማች ነንና በእ
ኔና በአንተ፥ በእረኞቼና በእረኞችህ መካከል
ጠብ አይሁን። ፱እነሆ፥ ምድር ሁሉ በፊትህ
አይደለችምን? ከእኔ ትለይ ዘንድ እለምንሃ
ለሁ፤ አንተ ወደ ግራው ብትሄድ እኔ ወደ
ቀኝ እሄዳለሁ፤ አንተም ወደ ቀኙ ብትሄድ
እኔ ወደ ግራ እሄዳለሁ።" ፲ሎጥም ዓይኖቹን
አነሣ፤ በዮርዳኖስ ዙሪያ ያለውንም ሀገር ሁሉ
ውኃ የሞላበት መሆኑን አየ፤ እግዚአብሔር
ሰዶምንና ገሞራን ከማጥፋቱ አስቀድሞ እስከ
ሴጎር ድረስ እንደ እግዚአብሔር ገነትና እንደ
ግብፅ ምድር እንደ ነበረ አየ። ፲፩ሎጥም ለራሱ
በዮርዳኖስ ዙሪያ ያለውን ሀገር ሁሉ መረጠ፤
ሎጥም ወደ ምሥራቅ ተጓዘ፤ አንዱም ከሌላው
እርስ በርሳቸው ተለያዩ። ፲፪አብራም በከነዓን
ምድር ተቀመጠ፤ ሎጥም በጎረቤት ሕዝቦች
ከተማ ተቀመጠ፤ ድንኳኑንም በሰዶም ተከለ፤[፬]
፲፫የሰዶም ሰዎች ግን ክፉዎችና በእግዚአብሔር
ፊት እጅግ ኀጢአተኞች ነበሩ።

### አብራም ወደ ኬብሮን እንደ ሄደ

፲፬ሎጥ ከተለየው በኋላም እግዚአብሔር አብ
ራምን አለው፥ "ዐይንህን አንሣና አንተ ካለ
ህበት ስፍራ ወደ መስዕና ወደ አዜብ፥ ወደ
ምሥራቅና ወደ ምዕራብ እይ፤ ፲፭የምታያትን
ምድር ሁሉ ለአንተና ለዘርህ ለዘለዓለም እሰጣ
ለሁና። ፲፮ዘርህንም እንደ ባሕር አሸዋ[፭] አደርጋ
ለሁ፤ የባሕር አሸዋን ይቈጥር ዘንድ የሚችል
ሰው ቢኖር ዘርህ ደግሞ ይቈጠራል። ፲፯ተነሣ፤
በምድር በርዝመቷም፥ በስፋቷም ዙር፤ እርስ
ዋን ለአንተና ለዘርህ ለዘለዓለም እሰጣለሁና።"
፲፰አብራምም ድንኳኑን ነቀለ፤ መጥቶም በኬ
ብሮን ባለው የመምሬ ዛፍ ተቀመጠ፤ በዚያም
ለእግዚአብሔር መሠውያን ሠራ።

## ምዕራፍ ፲፬

### አብራም ሎጥን ከምርኮ እንደ መለሰው

፩በሰናዖር ንጉሥ በአሚሮፌል፥ በእላሳር
ንጉሥ በአርዮክ፥ በኤላም ንጉሥ በኮሎዶጎ
ሞር፥ በአሕዛብ ንጉሥ በቴሮጋል ዘመን እን
ዲህ ሆነ፤ ፪ከሰዶም ንጉሥ ከባላ፥ ከገሞራ
ንጉሥ ከበርሳ፥ ከአዳማ ንጉሥ ከሰናአር፥ ከሲ
ባዮ ንጉሥ ከሲምቦር፤ ሴጎር ከተባለች ከባላ
ንጉሥም ጋር ጦርነት አደረጉ። ፫እነዚህ ሁሉ
በኤሌቄን ሸለቆ ተሰብስበው ተባበሩ፤ ይኸውም
የጨው ባሕር ነው። ፬ዐሥራ ሁለት ዓመት ለኮ
ሎዶጎሞር ተገዙ፤ በዐሥራ ሦስተኛውም ዓመት
ዐመፁ። ፭በዐሥራ አራተኛውም ዓመት ኮሎዶጎ
ሞርና ከእርሱ ጋር የነበሩት ነገሥታት መጡ፤
ረዐይትን በአስጣሮት ቃርናይም፥ ከእነርሱም
ጋር ጽኑዓን ሰዎችንና አሚዎስን በሴዊ ከተማ
ገደሉአቸው፤ ፮በሴይር ተራራዎች ያሉ የኬሬ
ዎስ ሰዎችንም በበረሃ አጠገብ እስከ አለችው
እስከ ፋራን ዛፍ ድረስ መቱአቸው። ፯ተመልሰ
ውም ቃዴስ ወደ ተባለች ወደ ፍርድ ምንጭ
መጡ፤ የአማሌቅን አለቆች ሁሉና በአሳሶን
ታማር የሚኖሩ አሞራውያንንም ገደሉአቸው።

---

፫ ግሪክ ሰባ. ሊ. "ሎጥንም" ይላል።
፬ ግእዙ "ወደ ሰዶም ተጓዘ" ይላል።
፭ ግሪክ ሰባ. ሊ. እና ዕብ. "እንደ ምድር አሸዋ" ይላል።

፰የሰዶም ንጉሥና የገሞራ ንጉሥ፥ የአዳማ ንጉ
ሥና የሲባዮን ንጉሥ፥ ሴጎር የተባለች የባላቅ
ንጉሥም ወጡ፤ እነዚህ ሁሉ በጨው ሸለቆ
በእነርሱ ላይ ለሰልፍ ወጡ፤ ፱ከኤላም ንጉሥ
ከኮሎዶጎሞር፥ ከአሕዛብ ንጉሥ ከቴሮጋል፥
ከሰናዖር ንጉሥ ከአሜሮፌል፥ ከእላሳር ንጉሥ
ከአርዮክ ጋር ተጋጠሙ። እነዚህ አራቱ ነገሥ
ታት ከአምስቱ ነገሥታት ጋር ተዋጉ። ፲ያም
የጨው ሸለቆ የዝፍት ጕድጓዶች ነበሩበት። የሰ
ዶም ንጉሥና የገሞራ ንጉሥም ሸሹና በዚያ
ወደቁ፤[፩] የቀሩትም ወደ ተራራማው ሀገር
ሸሹ። ፲፩የሰዶምንና የገሞራን ፈረሶች ሁሉ፥
ስንቃቸውንም ሁሉ ይዘው ሄዱ። ፲፪እነርሱም
የአብራምን የወንድም ልጅ ሎጥንና ገንዘቡን
ይዘው ሄዱ። እርሱ በሰዶም ይኖር ነበርና።
፲፫ከአመለጡትም አንድ ሰው መጣ፤[፪] ለዕብራ
ዊው ለአብራምም ነገረው፤ እርሱም የኤስኮል
ወንድምና የአውናን ወንድም በሆነ በአሞራ
ዊው የመምሬ ዛፍ ይኖር ነበር፤ እነዚያም ከአ
ብራም ጋር ቃል ኪዳን ገብተው ነበር። ፲፬አብ
ራምም የወንድሙ ልጅ ሎጥ እንደ ተማረከ
በሰማ ጊዜ ወገኖቹንና ቤተሰቦቹን ሁሉ ቈጠ
ራቸው፤ እነርሱም ሦስት መቶ ዐሥራ ስምንት
ሆኑ፤ እስከ ዳን ድረስ ተከትሎ አሳደዳቸው።
፲፭እርሱም ከብላቴኖቹ ጋር በሌሊት ደረሰባ
ቸው፤ መታቸውም፤ በደማስቆ ግራ እስካለች
ውም እስከ ሖባ ድረስ አሳደዳቸው። ፲፮የሰዶ
ምን ፈረሶች ሁሉ አስመለሰ፤ ደግሞም የወንድ
ሙን ልጅ ሎጥንና ንብረቱን፥ ሴቶችንና ሕዝ
ቡንም አስመለሰ።

## መልከጼዴቅ አብራምን እንደ ባረከው

፲፯ኮሎዶጎሞርንና ከእርሱ ጋር የነበሩትን
ነገሥታት ወግቶ ከተመለሰም በኋላ የሰዶም
ንጉሥ የንጉሥ ሜዳ በሆነ በሴዊ ሸለቆ ሊቀበ
ለው ወጣ። ፲፰የሳሌም ንጉሥ መልከ ጼዴቅም
እንጀራንና የወይን ጠጅን አወጣ፤ እርሱም የል
ዑል እግዚአብሔር ካህን ነበረ። ፲፱አብራምንም
ባረከው፤ "አብራም ሰማይንና ምድርን ለፈ
ጠረ ለልዑል እግዚአብሔር የተባረከ ነው፤
፳ጠላቶችህን በእጅህ የጣለልህ ልዑል እግዚ
አብሔርም ቡሩክ ነው" አለው። አብራምም
ከሁሉ ዐሥራትን ሰጠው። ፳፩የሰዶም ንጉሥም
አብራምን፥ "ሰዎቹን ስጠኝ፤ ፈረሶቹን[፫] ግን
ለአንተ ውሰድ" አለው። ፳፪አብራምም የሰዶ
ምን ንጉሥ አለው፥ "ሰማይንና ምድርን ወደ
ፈጠረ ወደ ልዑል እግዚአብሔር እጄን ከፍ
አደርጋለሁ፤ ፳፫አንተ፦ አብራምን ባለጠጋ አደ
ረግሁት እንዳትል፥ ከአንተ ገንዘብ ሁሉ ፈት
ልም ቢሆን፥ የጫማ ማዘቢያም ቢሆን እንዳል
ወስድ፥ ፳፬ብላቴኖች ከበሉት እህልና ከእኔ ጋር
ከመጡት ድርሻ በቀር፥ አውናን፥ ኤስኮልም፥
መምሬም እነርሱ ድርሻቸውን ይውሰዱ።"

## ምዕራፍ ፲፭

### እግዚአብሔር ለአብራም ቃል ኪዳንን እንደ ሰጠው

፩ከዚህም ነገር በኋላ የእግዚአብሔር ቃል
በራእይ ወደ አብራም መጣ፤ እንዲህ ሲል፥
"አብራም ሆይ፥ አትፍራ፤ እኔ ጋሻ እሆንሃ
ለሁ፤ ዋጋህም በእኔ ዘንድ እጅግ ብዙ ነው።"
፪አብራምም፥ "አቤቱ እግዚአብሔር ሆይ፥
ምን ትሰጠኛለህ? እነሆ፥ ልጅ ሳልወልድ እሞ
ታለሁ፤ የቤቴም ወራሽ ከዘመዴ ወገን የሚ
ሆን የደማስቆ ሰው የማሴቅ ልጅ ይህ ኢያው
ብር[፬] ነው" አለ። ፫አብራምም፥ "ለእኔ ዘር
አልሰጠኸኝም፤ የዘመዴ ልጅ እርሱ ይወርሰ
ኛል" አለ። ፬ያን ጊዜም የእግዚአብሔር ቃል
ወደ አብራም እንዲህ ሲል መጣ፤ "እርሱ አይ
ወርስህም፤ ነገር ግን ከአብራክህ የሚወጣው
እርሱ ይወርስሃል።" ፭ወደ ሜዳም አወጣውና
"ወደ ላይ ወደ ሰማይ ተመልከት፤ ልትቈጥራ
ቸው ትችል እንደሆነ ከዋክብትን ቍጠራቸው።
ዘርህም እንደዚሁ ነው" አለው። ፮አብራምም
በእግዚአብሔር አመነ፤ ጽድቅም ሆኖ ተቈጠ
ረለት። ፯"ይህችን ምድር ትወርሳት ዘንድ እን
ድሰጥህ ከከለዳውያን ምድር ያወጣሁህ አምላ
ክህ እግዚአብሔር እኔ ነኝ" አለው። ፰"አቤቱ
እግዚአብሔር ሆይ፥ እንደምወርሳት በምን አው
ቃለሁ?" አለው። ፱እርሱም አለው፥ "የሦስት
ዓመት ላም፥ የሦስት ዓመት ፍየልም፥ የሦስት
ዓመት በግም፥ ዋኖስም፥ ርግብም አምጣ፤ እኒ
ህንም ሁሉ አምጥተህ ከሁለት ከሁለት ቍረጣ

---

[፩] ግእዙ "በዚያም ገደሉአቸው" የሚል አለው።
[፪] ግእዙ በብዙ ቍጥር ይጽፋል።
[፫] ግእዙ "ጥሪትን" ይላል።
[፬] ግሪክ ሰባ. ሊ. እና ዕብ. "ኤሊዔዘር" ይላል።

ቸው፤ ወፎችን ግን አትቍረጣቸው።”[፱] ፲እንዲ
ሁም እነዚህን ሁሉ ወሰደለት፤ በየሁለትም ከፈ
ላቸው፤ የተከፈሉትንም በየወገኑ ትይዩ አደረጋ
ቸው፤ ወፎችን ግን አልቈረጣቸውም። ፲፩አሞ
ራዎችም በተቈረጠው ሥጋቸው ላይ ወረዱ፤
አብራምም በእነርሱ ዘንድ ተቀምጦ አባረራ
ቸው።

፲፪ፀሐይም በገባ ጊዜ በአብራም ድንጋጤ[፲]
መጣበት፤ እነሆም፥ የሚያስፈራ ጽኑዕ ጨለማ
መጣበት፤ ፲፫እግዚአብሔርም አብራምን አለው፥
“ዘርህ ለእነርሱ ባልሆነች ምድር ስደተኞች እን
ዲሆኑ በእርግጥ ዕወቅ፤ አራት መቶ ዓመታትም
ባሪያዎች አድርገው ይገዙአቸዋል፤ ያሠቃዩአቸ
ዋል፤ ያስጨንቋቸዋልም። ፲፬ደግሞም የሚያሠቃ
ዩአቸውን እኔ እፈርድባቸዋለሁ። ከዚህም በኋላ
ከብዙ ገንዘብ ጋር ወደዚህ ይወጣሉ። ፲፭አንተ
ግን ወደ አባቶችህ በሰላም ትሄዳለህ፤ በመልካም
ሽምግልናም ትቀበራለህ። ፲፮በአራተኛው ትው
ልድ ግን ወደዚህ ይመለሳሉ፤ እስከ ዛሬ ድረስ
የአሞራውያን ኀጢአት አልተፈጸመምና።” ፲፯እን
ዲህም ሆነ፤ ፀሐይም በገባ ጊዜ ነበልባል መጣ፤
የእሳት መብራትና የሚጨስ ምድጃም መጣ፤
በዚያም በተከፈለው መካከል አለፈ። ፲፰በዚያ
ችም ቀን እግዚአብሔር ለአብራም ተስፋ ያደ
ረገለትን ቃል ኪዳን አጸና፤ እንዲህም አለው፥
“ከግብፅ ወንዝ ጀምሮ እስከ ትልቁ ወንዝ እስከ
ኤፍራጥስ ወንዝ ድረስ ይህችን ምድር ለዘርህ
እሰጣታለሁ፤ ፲፱ቀኔዎሳውያንን፥ ቄኔዜዎሳውያ
ንን፥ ቄኔሚሎሳውያንን፥ ፳ኬጤዎናውያንንም፥
ፌርዜዎናውያንንም፥ ፈራዮናውያንንም፤[፲፩] ፳፩አሞ
ሬዎናውያንንም፥ ከናኔዎናውያንንም፥ ጌርጌሴዎ
ናውያንንም፥[፲፪] ኢያቡሴዎናውያንንም።”

## ምዕራፍ ፲፮

## አጋርና ይስማኤል

፩የአብራም ሚስት ሦራ ግን ልጅ አልወለደችለ
ትም ነበር፤ ስምዋ አጋር የተባለ ግብፃዊት አገል
ጋይም ነበረቻት። ፪ሦራም አብራምን፥ “እነሆ፥
እንዳልወልድ እግዚአብሔር ዘጋኝ፤ ከእርስዋ
ትወልድ ዘንድ ወደ አገልጋዬ ሂድ” አለችው።
አብራምም የሚስቱን የሦራን ቃል ሰማ። ፫አብ
ራምም በከነዓን ምድር ዐሥር ዓመት ከተቀመጠ
በኋላ፥ የአብራም ሚስት ሦራ ግብፃዊት አገልጋ
ይዋን አጋርን ወስዳ ለአብራም ሚስት ትሆነው
ዘንድ ሰጠችው። ፬አብራምም ወደ አጋር ገባ፤
ፀነሰችም፤ እንደ ፀነሰችም ባየች ጊዜ እመቤቷን
ማክበርዋን ተወች። ፭ሦራም አብራምን፥ “ከአ
ንተ የተነሣ እገፋለሁ፤ እኔ አገልጋዬን በብብትህ
ሰጠሁህ፤ እንደ ፀነሰችም ባየች ጊዜ እኔን ማክበ
ርን ተወች፤ እግዚአብሔር በእኔና በአንተ መካ
ከል ይፍረድ” አለችው። ፮አብራምም ሚስቱን
ሦራን፥ “እነሆ፥ አገልጋይሽ በእጅሽ ናት፤ እንደ
ወደድሽ አድርጊባት” አላት። ሦራም አጋርን
አሠቃየቻት፤ ከእርስዋም ኰበለለች።

፯የእግዚአብሔር መልአክም በውኃ ምንጭ
አጠገብ በሱር በረሃ በመንገድ አገኛት። ፰የእግ
ዚአብሔርም መልአክ፥ “የሦራ አገልጋይ አጋር
ሆይ፥ ከወዴት መጣሽ? ወዴትስ ትሄጂያለሽ?”
አላት። እርስዋም፥ “እኔ ከእመቤቴ ከሦራ ፊት
እኰበልላለሁ” አለች። ፱የእግዚአብሔር መልአ
ክም፥ “ወደ እመቤትሽ ተመለሺ፤ ከእጅዋም
በታች ራስሽን ዝቅ አድርጊ” አላት። ፲እግዚ
አብሔርም[፲፫] “ከብዛቱ የተነሣ እስከማይቈጠር
ድረስ ዘርሽን እጅግ አበዛለሁ፥” አላት። ፲፩የእ
ግዚአብሔር መልአክም አላት፥ “እነሆ፥ አንቺ
ፀንሰሻል፤ ወንድ ልጅንም ትወልጃለሽ፤ ስሙ
ንም ይስማኤል ብለሽ ትጠሪዋለሽ፤ እግዚአብ
ሔር ሥቃይሽን ሰምቶአልና። ፲፪እርሱም የበረሃ
ሰው ይሆናል፤[፲፬] እጁ በሁሉ ላይ ይሆናል፤ የሁ
ሉም እጅ ደግሞ በእርሱ ላይ ይሆናል፤ እር
ሱም በወንድሞቹ ሁሉ ፊት ይኖራል።” ፲፫አጋ
ርም ይናገራት የነበረውን የእግዚአብሔርን ስም[፲፭]
ጠራች፤ “አቤቱ የራራህልኝ አንተ ነህ፤ የተገለ
ጠልኝን በፊቱ አይቸዋለሁና።” ፲፬ስለዚህም የዚ
ያን ጕድጓድ ስም “በፊቱ የተገለጠልኝ የእርሱ

---

[፱] “ይህንም ሁሉ አምጥተህ ከሁለት ከሁለት ቍረጣቸው፥ ወፎችን ግን አትቍረጣቸው” የሚለው በግሪክ ሰባ. ሊ. እና በዕብ. የለም።

[፲] ዕብ. “ከባድ ዕንቅልፍ” ይላል።

[፲፩] ግሪክ ሰባ. ሊ. እና ዕብ. “ራፋይምን” ይላል።

[፲፪] በግሪክ ሰባ. ሊ. “ኤዌዎናውያን” የሚል አለ።

[፲፫] ግሪክ ሰባ. ሊ. እና ዕብ. “የእግዚአብሔር መልአክ” ይላል።

[፲፬] ዕብ. “እርሱ የምድረ በዳ አህያን የሚመስል ሰው ይሆናል” ይላል።

[፲፭] ዕብ. “ኤልሮኢ ብላ” ይላል።

ጕድጓድ” ብላ ጠራችው፤ እርሱም በቃዴስና
በባሬድ መካከል ነው። አጋርም ተመለሰች።[ፀ]
፲፭ከዚህም በኋላ አጋር ለአብራም ወንድ
ልጅን ወለደችለት፤ አብራምም አጋር የወለደ
ችለትን የሕፃኑን ስም ይስማኤል ብሎ ጠራው።
፲፮አጋር ይስማኤልን በወለደችለት ጊዜ አብራም
የሰማንያ አምስት[ፁ] ዓመት ሰው ነበረ።

## ምዕራፍ ፲፯

### ግዝረት የቃል ኪዳን ምልክት ሆኖ መሰጠቱ

፩ከዚህም በኋላ አብራም የዘጠና ዘጠኝ ዓመት
ሰው በሆነ ጊዜ እግዚአብሔር ለአብራም ተገ
ለጠለት፤ እንዲህም አለው “በፊትህ የሄድሁ
ፈጣሪህ[ፂ] እግዚአብሔር እኔ ነኝ፤ በፊቴ መል
ካም አድርግ፤ ንጹሕም ሁን፤ ፪ቃል ኪዳኔንም
በእኔና በአንተ መካከል አጸናለሁ፤ እጅግም
አበዛሃለሁ።” ፫አብራምም በግንባሩ ወደቀ፤
እግዚአብሔርም አብራምን እንዲህ አለው፡-
፬“እነሆ፥ ቃል ኪዳኔን በእኔና በአንተ መካ
ከል አጸናለሁ፤ ለብዙ አሕዛብም አባት ትሆ
ናለህ። ፭እንግዲህ ስምህ አብራም አይባልም
‘አብርሃም’ ይባላል እንጂ፤ ለብዙ አሕዛብ
አባት አድርጌሃለሁና። ፮እጅግም በጣም አበ
ዛሃለሁ፤ ሕዝብም፥ ነገሥታትም ከአንተ እን
ዲወጡ አደርግሃለሁ። ፯ቃል ኪዳኔንም በእኔና
በአንተ መካከል፥ ከአንተም በኋላ በዘርህ መካ
ከል በትውልዳቸው ለዘለዓለም ኪዳን አቆማ
ለሁ፤ ለአንተና ከአንተም በኋላ ለዘርህ አምላክ
እሆን ዘንድ። ፰በውስጥዋ የምትኖርባትን ይህ
ችን ምድር፥ የከነዓንን ምድር ሁሉ፥ ለዘለዓ
ለም ይገዙአት ዘንድ ለዘርህ እሰጣለሁ፤ አምላ
ክም እሆናቸዋለሁ።”
፱እግዚአብሔርም አብርሃምን አለው፥ “አንተ
ደግሞ ቃል ኪዳኔን ትጠብቃለህ፤ አንተ፥ ከአን
ተም በኋላ ዘርህ በትውልዳቸው። ፲በእኔና በአ
ንተ መካከል፥ ከአንተም በኋላ በዘርህ መካከል
የምትጠብቋት ቃል ኪዳኔ ይህች ናት፤ ከእ
ናንተ ወንድ ሁሉ ይገረዝ። ፲፩የሰውነታችሁን
ቍልፈት ትገረዛላችሁ፤ በእኔና በእናንተ መካ
ከል ላለውም ቃል ኪዳን ምልክት ይሆናል።
፲፪ሕፃኑንም በስምንተኛው ቀን ትገርዙታላችሁ፤
በቤት የተወለደ ወይም ከዘራችሁ ያይደለ፥ በብ
ርም ከእንግዳ ሰው የተገዛ ወንድ ሁሉ በትውል
ዳችሁ ይገረዝ። ፲፫በቤትህም የተወለደ፥ በብርም
የተገዛ ፈጽሞ ይገረዝ።[ፃ] ቃል ኪዳኔም በሥጋ
ችሁ የዘለዓለም ቃል ኪዳን ይሆናል። ፲፬በስም
ንተኛው ቀን የሥጋውን ቍልፈት ያልተገረዘ፥
ያች ነፍስ ከወገንዋ ተለይታ ትጥፋ፤ ቃል ኪዳ
ኔን አፍርሳለችና።”
፲፭እግዚአብሔርም አብርሃምን አለው፥
“ሚስትህ ሦራ እንግዲህ ሦራ ተብላ አትጠ
ራም፤ ስምዋ ‘ሣራ’ ይሆናል እንጂ። ፲፮እባ
ርካታለሁና፥ ከአንተም ልጅችን እሰጣታለ
ሁና፤[ፄ] አሕዛብና የአሕዛብ ነገሥታት ከእርስዋ
ይወጣሉ።”[ፅ] ፲፯አብርሃምም በግንባሩ ወደቀ፤
ሳቀም፤ በልቡም እንዲህ ብሎ አሰበ፥ “የመቶ
ዓመት ሰው ስሆን በውኑ እኔ ልጅ እወልዳለ
ሁን? ዘጠና ዓመት የሆናትም ሣራ ትወልዳለ
ችን?” ፲፰አብርሃምም እግዚአብሔርን አለው፥
“ይህ ይስማኤል ብቻ በፊትህ ይኖርልኝ ዘንድ
አቤቱ፥ እማልድሃለሁ።” ፲፱እግዚአብሔርም
አብርሃምን አለው፥ “እሺ እነሆ፥ ሚስትህ
ሣራ ወንድ ልጅን ትወልድልሃለች፤ ስሙንም
ይስሐቅ ብለህ ትጠራዋለህ፤ ለእርሱና ከእርሱ
በኋላ ለዘሩ አምላክ እሆን ዘንድ ቃል ኪዳኔን
ለዘለዓለም ቃል ኪዳን ከእርሱ ጋር አቆማለሁ።
፳ስለ ይስማኤልም እነሆ፥ ሰምቼሃለሁ፤ እባ
ርከዋለሁ፤ አበዛዋለሁ፤ እጅግም አበዛዋለሁ፤
ዐሥራ ሁለት አለቆችንም ይወልዳል፤ ታላቅ
ሕዝብም አደርገዋለሁ። ፳፩ቃል ኪዳኔን ግን
በሚመጣው ዓመት በዚሁ ጊዜ ሣራ ከምትወ
ልድልህ ከይስሐቅ ጋር አቆማለሁ።”
፳፪እግዚአብሔርም ንግግሩን ከእርሱ ጋር በፈ
ጸመ ጊዜ ከአብርሃም ተለይቶ ወጣ። ፳፫አብር
ሃምም ልጁን ይስማኤልን፥ በቤቱም የተወለዱ
ትን ሁሉ፥ በወርቅም የገዛውን ወንድ ሁሉ፥
ከቤተ ሰቡም ወንዶቹን ሁሉ ወሰደ። የሥጋቸ

---

[ፀ] “አጋርም ተመለሰች” የሚለው በግሪክ ሰባ. ሊ. እና በዕብ. የለም።

[ፁ] ዕብ. እና ግሪክ ሰባ. ሊ. “ሰማንያ ስድስት” ይላል።

[ፂ] “በፊትህ የሄድሁ” የሚለው በግሪክ ሰባ. ሊ. እና በዕብ. የለም።

[ፃ] በግሪክ ሰባ. ሊ. እና በዕብ. ብቻ።

[ፄ] ግሪክ ሰባ. ሊ. “ከእርስዋ ልጆች እሰጥሀለሁ” ይላል።

[ፅ] ግሪክ ሰባ. ሊ. “እባርካታለሁ ከእርስዋም ልጅን እሰጥሃለሁ እባርከውማለሁ ሕዝብም ይሆናል የአሕዛብ ነገሥታ
ትም ከእርሱ ይወጣሉ” ይላል።

ውንም ቍልፈት እግዚአብሔር እንዳለው በዚ
ያው ቀን ገረዘ። ፳፬አብርሃምም የሥጋውን ቍል
ፈት በተገረዘ ጊዜ ዘጠና ዘጠኝ ዓመት ሆኖት
ነበረ፤ ፳፭ልጁ ይስማኤልም የሥጋውን ቍል
ፈት በተገረዘ ጊዜ ዐሥራ ሦስት ዓመት ሆኖት
ነበረ። ፳፮በዚያም ቀን አብርሃም ተገረዘ፤ ልጁ
ይስማኤልም። ፳፯በቤት የተወለዱትና በብር ከእ
ንግዶች የተገዙት፥ የቤቱ ወንዶች ሁሉ ከእ
ርሱ ጋር ተገረዙ።

## ምዕራፍ ፲፰

### እግዚአብሔር ለአብርሃም እንደ ተገለጠ

፩በቀትርም ጊዜ አብርሃም በድንኳኑ ደጃፍ
ተቀምጦ ሳለ እግዚአብሔር በመምሬ ዛፍ ሥር
ተገለጠለት። ፪ዐይኑንም በአነሣ ጊዜ እነሆ፥
ሦስት ሰዎች በፊቱ ቆመው አየ፤ ባያቸ
ውም ጊዜ ሊቀበላቸው ከድንኳኑ ደጃፍ ተነ
ሥቶ ሮጠ፤ ወደ ምድርም ሰገደ፤ ፫እንዲህም
አለ፥ "አቤቱ በፊትህስ ባለሟልነትን አግኝቼ
እንደ ሆነ ባሪያህን አትለፈው፤ ፬ውኃ እናም
ጣላችሁ፤ እግራችሁንም እንጠባችሁ። ፭ከዛ
ፉም ሥር ዕረፉ፤ እንጀራም እናምጣላችሁና
ብሉ፤ ከዚያም በባሪያችሁ ዘንድ ከአረፋችሁ
በኋላ፥ ወደ ዐሰባችሁት ትሄዳላችሁ።" እነር
ሱም፥ "እንዳልህ እንዲሁ አድርግ" አሉት።
፮አብርሃምም ወደ ድንኳን ወደ ሚስቱ ወደ
ሣራ ፈጥኖ ገባና፥ "ሦስት መስፈሪያ የተሰለቀ
ዱቄት ፈጥነሽ ለውሺ፤ እንጎቻም አድርጊ"
አላት። ፯አብርሃምም ወደ ላሞቹ ሮጠ፤ እጅግ
የሰባም ታናሽ ጥጃ ያዘና ለብላቴናው ሰጠው፤
ያዘጋጅም ዘንድ ተቻኮለ። ፰እርጎና መዓር፥[፩]
ያን ያዘጋጀውንም ጥጃ አመጣ፤ በፊታቸውም
አቀረበው፤ እርሱም ከዛፉ በታች በፊታቸው
ቆሞ ያሳልፍላቸው ነበር፤ እነርሱም በሉ።

### ለአብርሃም ወንድ ልጅ እንደሚወለድለት የተሰጠው ተስፋ

፱እርሱም፥ "ሚስትህ ሣራ ወዴት ናት?"
አለው። እርሱም፥ "በድንኳኑ ውስጥ ናት"
አለው። ፲እርሱም፥ "የዛሬ ዓመት እንደ
ዛሬው ወደ አንተ ተመልሼ እመጣለሁ፤ ሚስ
ትህ ሣራም ልጅን ታገኛለች" አለ። ፲፩ሣራም
በድንኳኑ ደጃፍ በስተኋላው ቆማ ሳለች ይህን
ሰማች። አብርሃምና ሣራም በዕድሜያቸው ሸም
ግለው ፈጽመው አርጅተው ነበር፤ በሴቶች
የሚሆነውም ልማድ ከሣራ ተቋርጦ ነበር።
፲፪ሣራም ለብቻዋ በልብዋ እንዲህ ስትል
ሳቀች፥ "እስከ ዛሬ ገና ነኝን? ጌታዬም ፈጽሞ
ሸምግሎአል።" ፲፫እግዚአብሔርም አብርሃምን
አለው፥ "ሣራን ለብቻዋ በልብዋ ምን አሳ
ቃት? እስከ ዛሬ ገና ነኝን? በእውነትስ እወል
ዳለሁን? ጌታዬም አርጅትዋል[፪] እነሆ፥ እኔም
አርጅቻለሁ ብላለችና። ፲፬በውኑ ለእግዚአብ
ሔር የሚሳነው ነገር አለን? የዛሬ ዓመት እንደ
ዛሬው ጊዜ ወደ አንተ እመለሳለሁ፤ ሣራም
ልጅን ታገኛለች።" ፲፭ሣራም ስለ ፈራች "አል
ሳቅሁም" ብላ ካደች። እርሱም፥ "አይደለም፥
ሳቅሽ እንጂ" አላት።

### አብርሃም ለሰዶም እንደ ማለደ

፲፮እነዚያም ሰዎች ከዚያ ተነሥተው ወደ ሰዶ
ምና ወደ ገሞራ[፫] አቀኑ፤ አብርሃምም ሊሸኛ
ቸው አብሮአቸው ሄደ፤ አብርሃምም ተመልሶ
በእግዚአብሔር ፊት ቆመ።[፬] ፲፯እግዚአብሔርም
አለ፥ "እኔ የማደርገውን ከወዳጄ አብርሃም
አልሰውርም፤ ፲፰አብርሃም በእውነት ታላቅና
ብርቱ ሕዝብ ይሆናልና፤ የምድር ሕዝቦችም
ሁሉ በእርሱ ይባረካሉና። ፲፱ጽድቅንና ፍርድን
በማድረግ የእግዚአብሔርን መንገድ ይጠብቁ
ዘንድ፥ ልጆቹንና ቤቱን ያዝዛቸው ዘንድ እን
ዳለው አውቃለሁና፤ ይህም እግዚአብሔር ለአ
ብርሃም የተናገረውን ሁሉ ያደርግላቸው ዘንድ
ነው።" ፳እግዚአብሔርም ለአብርሃም አለው፥
"የሰዶምና የገሞራ ጩኸት በእኔ ዘንድ በዛ፤
ኀጢአታቸውም እጅግ ከበደች፤ ፳፩እንግዲህስ
ወደ እኔ እንደ መጣች እንደ ጩኸቷ ይፈጽሙ
አት እንደ ሆነ አይ ዘንድ እወርዳለሁ፤ እንዲ
ሁም ባይሆን አውቃለሁ።"
፳፪ሰዎቹም ከዚያ በተመለሱ ጊዜ ወደ ሰዶም
መጡ፤ አብርሃም ግን በእግዚአብሔር ፊት
ገና ቆሞ ነበር። ፳፫አብርሃምም ቀረበ፤ አለም፥
"አቤቱ፥ ጻድቃንን ከኃጥአን ጋር አታጥፋ፤
ጻድቁ እንደ ኃጥኡ አይሁን። ፳፬አምሳ ጻድቃን

---

፩ ግሪክ ሰባ. ሊ. እና ዕብ. "ቅቤና ወተት" ይላል።

፪ "እስከ ዛሬ ገና ነኝን ጌታዬም አርጅትዋል" የሚለው በግሪክ ሰባ. ሊ. እና በዕብ. የለም።

፫ "ገሞራ" በዕብ. የለም።

፬ "አብርሃምም ተመልሶ በእግዚአብሔር ፊት ቆመ" የሚለው በዕብ. እና በግሪክ ሰባ. ሊ. የለም።

በከተማዪቱ ውስጥ ቢገኙ በውኑ ሁሉን ታጠፋ
ለህን? ከተማዪቱንስ በእርስዋ ስለሚገኙ አምሳ
ጻድቃን አትምርምን? ፳፭አቤቱ ይህ ለአንተ
አግባብ አይደለም፤ ይህን ነገር አታድርግ፤ ጻድ
ቃንን ከኃጥአን ጋር አታጥፋ፤ ምድርን ሁሉ
የምትገዛ ይህን ፍርድ ታደርግ ዘንድ ለአንተ
አግባብ አይደለም።” ፳፮እግዚአብሔርም አብር
ሃምን አለው፥ “በሰዶም ከተማ ውስጥ አምሳ
ጻድቃን ባገኝ ከተማውን ሁሉ ስለ እነርሱ
አድናለሁ።” ፳፯አብርሃምም መለሰ፤ አለም፥
“እኔ አፈርና አመድ ስሆን ከጌታዬ ከእግዚ
አብሔር ጋር እናገር ዘንድ አሁን ጀመርሁ፤
፳፰ከእነዚያ አምሳ ጻድቃን አምስት ቢጐድሉ
ከተማዪቱን ሁሉ በጐደሉት በአምስቱ ምክን
ያት ታጠፋለህን?” እግዚአብሔርም፥ “ከዚያ
አርባ አምስት ባገኝ ስለ እነርሱ አላጠፋትም”
አለው። ፳፱አብርሃምም አለው፥ “ከዚያ አርባ
ቢገኙሳ?” እግዚአብሔርም፥ “ለአርባው ስል
አላጠፋትም” አለው። ፴አብርሃምም እንደገና
ነገሩን ደገመ፤ እንዲህም አለው፥ “ከዚያ ሠላሳ
ቢገኙሳ?” እርሱም፥ “ስለ ሠላሳው አላጠፋ
ትም” አለው። ፴፩ደግሞም፥ “እነሆ፥ ከጌታዬ
ከእግዚአብሔር ጋር እነጋገር ዘንድ ባለሚል
ነትን ካገኘሁ ከዚያ ሃያ ቢገኙሳ?” አለው።
እርሱም፥ “ስለ ሃያው አላጠፋትም” አለው።
፴፪አብርሃምም አለው፥ “አቤቱ እንደገና እና
ገር ዘንድ ፍቀድልኝ፤ ከዚያ ዐሥር ቢገኙሳ?”
እርሱም፥ “ስለ ዐሥሩ አላጠፋትም” አለው።[፭]
፴፫እግዚአብሔርም ከአብርሃም ጋር ንግግሩን
በጨረሰ ጊዜ ሄደ፤ አብርሃምም ወደ ስፍራው
ተመለሰ።

## ምዕራፍ ፲፱

### የሰዶም ኀጢአት

፩ሁለቱም መላእክት በመሸ ጊዜ ወደ ሰዶም
ደረሱ፤ ሎጥም በሰዶም ከተማ በር ተቀምጦ
ነበር። ሎጥም ባያቸው ጊዜ ሊቀበላቸው
ተነሣ፤ ፊቱንም ወደ ምድር ደፍቶ ሰገደላ
ቸው፤ ፪አላቸውም፥ “ጌቶች ሆይ፥ ወደ ባሪ
ያችሁ ቤት ገብታችሁ እደሩ፤ እግራችሁንም
ታጠቡ፤ ነገም ማልዳችሁ መንገዳችሁን ትሄ
ዳላችሁ።” እነርሱም፥ “በአደባባዩ እናድራለን
እንጂ፥ አይሆንም” አሉት። ፫እርሱም ግድ አላ
ቸው፤ ወደ እርሱም አቀኑ፤ ወደ ቤቱም ገቡ፤
ቂጣንም አስጋገረላቸው፤ እነርሱም በሉ። ፬ገና
ሳይተኙም የዚያች ከተማ ሰዎች፥ ታናሹም፥
ታላቁም ቤቱን በአንድነት ከበቡት። ፭ሎጥንም
ጠርተው እንዲህ አሉት፥ “በሌሊት ወደ አንተ
የገቡት ሰዎች ወዴት ናቸው? እናውቃቸው
ዘንድ ወደ እኛ አውጣቸው።” ፮ሎጥም ወደ
እነርሱ ወደ ደጅ ፊት ለፊት ወጣ፤ መዝጊ
ያውንም በስተኋላው ዘጋው፤ ፯እንዲህም አላ
ቸው፥ “ወንድሞች ሆይ፥ ለእናንተ አግባባ
ችሁ አይደለም፤ በእነዚህ ላይ ክፉ አታድርጉ፤
፰እነሆ፥ ወንድን ያላወቁ ሁለት ሴቶች ልጆች
አሉኝ፤ እነርሱን ላውጣላችሁ፤ እንደ ወደዳ
ችሁም አድርጉአቸው፤ በእነዚህ ሰዎች ብቻ
ምንም በደል አታድርጉ፤ እነርሱ በቤቴ ጥላ
ሥር ገብተዋልና።” ፱እነርሱም፥ “ወዲያ ሂድ፤
ከእኛ ጋር ልትኖር መጣህ እንጂ ልትገዛን አይ
ደለም፤ አሁንም ከእነርሱ ይልቅ አንተን እና
ሠቃይሃለን” አሉት። ፲እጅግም ተጋፉት፤ የደ
ጁንም መዝጊያ ለመስበር ቀረቡ። እነዚያም
ሰዎች እጃቸውን ዘርግተው ሎጥን ወደ እነ
ርሱ ዘንድ ወደ ቤት ስበው አገቡት፤ መዝጊ
ያውንም ዘጉት። ፲፩በቤቱ ደጃፍ የነበሩትንም
ሰዎች ከታናሻቸው ጀምሮ እስከ ታላቃቸው
ድረስ ዐይናቸውን አሳወሩአቸው፤ ደጃፉንም
ሲፈልጉ ደከሙ፤ አጡትም።[፮]

### ሎጥ ሰዶምን ትቶ እንደ ወጣ

፲፪እነዚያም መላእክት[፯] ሎጥን አሉት፥
“ከዚህ ሌላ ማን አለህ? አማችም ቢሆን፥
ወንድ ልጅም ቢሆን፥ ሴት ልጅም ብትሆን፥
በዚህ ከተማ የምታውቀው ወዳጅ ቢኖርህ ያለ
ህን ሁሉ ከዚህ ስፍራ አስወጣቸው፤ ፲፫እኛ ይህ
ችን ስፍራ እናጠፋታለንና፥ ጩኸታቸው በእ
ግዚአብሔር ፊት ትልቅ ሆኖአልና፤ እናጠፋ
ትም ዘንድ እግዚአብሔር ልኮናል።” ፲፬ሎጥም
ወጣ፤ ልጆቹን ለሚያገቡት ለአማቾቹም አላ
ቸው፥ “ተነሡ፤ ከዚች ስፍራ ውጡ፤ እግዚ
አብሔር ይህችን ከተማ ያጠፋታልና።” ለአማ
ቾቹ ግን የሚያፌዝባቸው መሰላቸው። ፲፭ኀህም

---

[፭] ምዕ. ፲፰ ቍ. ፴ እና ፴፪ ላይ በግሪክ ሰባ. ሊ. “ጌታዬ ሆይ እንደ ገና አንድ ጊዜ ብናገር በእኔ ላይ አንዳች ነገር ይሆናልን?” ይላል።

[፮] “አጡትም” የሚለው በግሪክ ሰባ. ሊ. እና በዕብ. የለም።

[፯] በግእዙ “እነዚያ መላእክት” የሚለው በግሪክ ሰባ. ሊቃ. እና በዕብ. “ሁለቱ ሰዎች” ይላል።

በቀደደ ጊዜ መላእክት ሎጥን፥ “ተነሣ፤ ሚስ
ትህንና ከዚህ ያሉትን ሁለቱን ሴቶች ልጆች
ህን ውሰድ፤ አንተም በከተማዪቱ ሰዎች ኀጢ
አት እንዳትጠፋ” እያሉ ያስቸኩሉት ነበር።
፲፮እርሱም በዘገየ ጊዜ እነዚያ መላእክት የእር
ሱን እጅ፥ የሚስቱንም እጅ፥ የሁለቱን ሴቶች
ልጆቹንም እጅ ይዘው አወጡአቸው፤ እግዚአ
ብሔር ራርቶላቸዋልና። ፲፯ወደ ሜዳም በወጡ
ጊዜ እንዲህ አሉት፥ “ራስህን አድን፤ ወደ
ኋላም አትመልከት፤ አንተንም መከራ እንዳ
ታገኝህ በዚች ሀገር በዳርቻዋና በተራራዋ አት
ቁም።”[፫] ፲፰ሎጥም አላቸው፥ “ጌቶች ሆይ፥
በጀ በሉኝ፤ ፲፱እነሆ፥ ባሪያህ በፊትህ ምሕረትን
አግኝቷ እንደሆነ፥ ሰውነቴንም ታድናት ዘንድ፥
ቸርነትህን አብዝተህልኝ እንደ ሆነ፥ መከራ አግ
ኝቶኝ እንዳልጠፋ ወደ ተራራ ሸሽቼ ራሴን
ማዳን አልችልም። ፳እነሆ፥ ይህች ከተማ ወደ
እርስዋ ሸሽቶ ለማምለጥ ቅርብ ናት፤ እርስዋም
ትንሽ ናት፤ ነፍሴን ለማዳን ወደ እርስዋ ሸሽቼ
ራሴን ላድን፤ ሰውነቴም ከዳነች ትንሽ አይደለ
ችም፤”[፬] ፳፩እርሱም አለው፥ “ስለ እርስዋ የነ
ገርኸኝን ያችን ከተማ እንዳላጠፋት እነሆ፥ እን
ዳልኸው ልመናህን ተቀብዬሃለሁ፤ ፳፪እንግዲህ
ፍጠንና በዚያ ራስህን አድን፤ ወደዚያ እስክትደ
ርስ ድረስ ምንም አደርግ ዘንድ አልችልምና።”
ስለዚህም የዚያች ከተማ ስም ሴጎር ተባለ።

### የሰዶምና የገሞራ መጥፋት

፳፫ፀሐይ በምድር ላይ ወጣች፤ ሎጥም ወደ
ሴጎር ገባ። ፳፬እግዚአብሔርም በሰዶምና በገ
ሞራ ላይ ከእግዚአብሔር ዘንድ ከሰማይ እሳ
ትና ዲን አዘነበ፤ ፳፭እነዚያንም ከተሞች፥ በዙ
ሪያቸው ያለውንም ሁሉ፥ በከተሞችም የሚ
ኖሩትን ሁሉ፥ የምድሩንም ቡቃያ ሁሉ ገለ
በጠ። ፳፮የሎጥም ሚስት ወደ ኋላዋ ተመለከ
ተች፤ የጨው ሐውልትም ሆነች። ፳፯አብርሃ
ምም በእግዚአብሔር ፊት ቆሞ ወደ ነበረበት
ስፍራ ለመሄድ ማልዶ ተነሣ፤ ፳፰ወደ ሰዶምና
ገሞራ፥ ወደ አውራጃዎችዋም ሁሉ ተመለከተ፤
እነሆም፥ ነበልባል ከምድር እንደ ምድጃ ጢስ
ሲወጣ አየ።

፳፱እግዚአብሔርም እነዚያን ከተሞችና ሎጥ
የሚኖርባቸውን አውራጃዎችዋን ሁሉ ባጠፋ
ጊዜ አብርሃምን ዐሰበው፤ ሎጥንም ከጥፋት
መካከል አወጣው።

### የሞአባውያንና የአሞናውያን መወለድ

፴ሎጥም ከሴጎር ወጣ፤ ከሁለቱም ሴቶች
ልጆቹ ጋር በተራራ ተቀመጠ፤ በሴጎር መቀመ
ጥን ፈርቶአልና እርሱና ሁለቱ ሴቶች ልጆቹ
በዋሻ ተቀመጡ። ፴፩ታላቂቱም ታናሺቱን አለ
ቻት፥ “አባታችን ሽማግሌ ነው፤ በምድርም
ሁሉ እንዳለው ልማድ ሊገናኘን የሚችል ሰው
በምድር ላይ የለም። ፴፪ነዪ፥ አባታችንን ወይን
እናጠጣውና ከእርሱ ጋር እንተኛ፤ ከአባታች
ንም ዘር እናስቀር።” ፴፫በዚያችም ሌሊት አባ
ታቸውን ወይን አጠጡት፤ ታላቂቱም ገባች፤
በዚያችም ሌሊት ከአባቷ ጋር ተኛች፤ እር
ሱም ስትተኛም፥ ስትነሣም አላወቀም። ፴፬በነ
ጋውም ታላቂቱ ታናሺቱን አለቻት፥ “እነሆ፥
ትናንት ከአባቴ ጋር ተኛሁ፤ ዛሬ ሌሊት ደግሞ
ወይን እናጠጣው፤ አንቺም ግቢና ከእርሱ ጋር
ተኚ፤ ከአባታችንም ዘር እናስቀር።” ፴፭አባታቸ
ውንም በዚያች ሌሊት ደግሞ ወይን አጠጡት፤
ታናሺቱም ገብታ ከአባቷ ጋር ተኛች፤ እር
ሱም ስትተኛም ስትነሣም አላወቀም። ፴፮የሎ
ጥም ሁለቱ ሴቶች ልጆች ከአባታቸው ፀነሱ።
፴፯ታላቂቱም ወንድ ልጅ ወለደች፤ ስሙንም
ሞዓብ ብላ ጠራችው፤ ይህም ከአባቴ የወለድ
ሁት ማለት ነው። እርሱም እስከ ዛሬ የሞዓባ
ውያን አባት ነው። ፴፰ታናሺቱም ደግሞ ወንድ
ልጅ ወለደች፤ ስሙንም የወገኔ ልጅ ስትል
አሞን[፭] ብላ ጠራችው፤ እርሱም እስከ ዛሬ የአ
ሞናውያን አባት ነው።

## ምዕራፍ ፳

### አብርሃምና አቤሜሌክ

፩አብርሃምም ከዚያ ተነሥቶ ወደ አዜብ
ምድር አቅጣጫ ሄደ፤ በቃዴስና በሱር መካከ
ልም ኖረ፤ በጌራራም በእንግድነት ተቀመጠ።
፪አብርሃምም ሚስቱን ሣራን “እኅቴ ናት” አላ
ቸው፤ የከተማዪቱ ሰዎች ስለ እርስዋ እንዳይ
ገድሉት “ሚስቴ” ናት ማለትን ፈርቶአልና፤
የጌራራ ንጉሥ አቤሜሌክም ላከና ሣራን ወሰ
ዳት። ፫በዚያች ሌሊትም አቤሜሌክ ተኝቶ ሳለ

---

፫ በግሪክ ሰባ. ሊ. “በተራራው ራስህን አድን” ይላል።
፬ ዕብ. “እርስዋ ትንሽ ከተማ አይደለችምን?” ይላል።
፭ ግሪክ ሰባ. ሊ. “አማን” ይላል።

እግዚአብሔር በሕልም ወደ እርሱ መጣ፤ እን
ዲህም አለው፥ "እነሆ፥ አንተ ስለ ወሰድሃት
ሴት ትሞታለህ፤ እርስዋ ባለ ባል ናትና።"
፬አቢሜሌክ ግን አልቀረባትም ነበር፤ አቤሜሌ
ክም እንዲህ አለ፥ "አቤቱ ያላወቀውን ሕዝብ
በእውነት ታጠፋለህን? ፭እኅቴ ናት ያለኝ እርሱ
አይደለምን? እርስዋ ደግሞ ራስዋ ወንድሜ
ነው አለች፤ በልቤ ቅንነትና በእጄ ንጹሕነት
ይህን አደረግሁት።" ፮እግዚአብሔርም በሕ
ልም አለው፥ "ይህን በልብህ ቅንነት እንዳደ
ረግህ እኔ ዐወቅሁ፤ እኔም ደግሞ በፊቴ ኀጢ
አትን እንዳትሠራ ጠበቅሁህ፤ ስለዚህም ትቀ
ርባት ዘንድ አልተውሁህም። ፯አሁንም የሰው
የውን ሚስት መልስ፤ ነቢይ ነውና፥ ስለ አን
ተም ይጸልያል፤ ትድናለህም። ባትመልሳት ግን
አንተ እንድትሞት፥ ለአንተ የሆነውም ሁሉ
እንዲሞት በርግጥ ዕወቅ።" ፰አቤሜሌክም በጥ
ዋት ተነሣ፤ ብላቴኖቹንም ሁሉ ጠራ፤ ይህ
ንም ነገር ሁሉ በጆሮአቸው ተናገረ፤ ቤተ ሰዎ
ቹም ሁሉ እግዚአብሔርን እጅግ ፈሩ። ፱አቤ
ሜሌክም አብርሃምን ጠርቶ አለው፥ "ይህ ያደ
ረግህብን ምንድን ነው? ምንስ ክፉ ሠራሁ
ብህ? በእኔና በመንግሥቴ ላይ ትልቅ ኀጢአት
አውርደሃልና፤ ማንም የማያደርገው የማይገባ
ሥራ በእኔ ሠራህብኝ።" ፲አቤሜሌክም አብ
ርሃምን አለው፥ "ይህን ነገር ማድረግህ ምን
አይተህ ነው?" ፲፩አብርሃምም አለ፥ "ምንአ
ልባት በዚህ ስፍራ እግዚአብሔርን መፍራት
ስለሌለ በሚስቴ ምክንያት ይገድሉኛል ብዬ
ነው። ፲፪እርስዋም ደግሞ በእናቴ ወገን አይ
ደለችም እንጂ በእውነት በአባቴ ወገን እኅቴ
ናት፤ ለእኔም ሚስት ሆነች። ፲፫እግዚአብሔርም
ከአባቴ ቤት ባወጣኝ ጊዜ አልኋት፥ "ይህን
ጽድቅ አድርጊልኝ፤ በገባንበት ሀገር ሁሉ ወን
ድሜ ነው በዪ።" ፲፬አቤሜሌክም አንድ ሺህ
ምዝምዝ ብርን፩ በጎችንና ላሞችን፥ ወንዶ
ችና ሴቶች ባሪያዎችን አመጣ፤ ለአብርሃምም
ሰጠው፤ ሚስቱን ሣራንም መለሰለት። ፲፭አቤ
ሜሌክም አብርሃምን አለው፥ "እነሆ፥ ምድሬ
በፊትህ ናት፤ በወደድኸው ተቀመጥ።" ፲፮ሣራ
ንም አላት "እነሆ፥ ለወንድምሽ አንድ ሺህ
ምዝምዝ ብር ሰጠሁት፤ ይህም ለፊትሽ ክብር
ይሁንሽ፤ በሁሉም እውነትን ተናገራት።"
፲፯አብርሃምም ወደ እግዚዘብሔር ጸለየ፤ እግዚ
አብሔርም አቤሜሌክን፥ ሚስቱንም፥ ሴቶች
ልጆቹንም፥ በቤቱ ውስጥ ያሉ ሴቶች አገልጋ
ዮቹንም ፈወሳቸው፤ እነርሱም ወለዱ፤ ፲፰እግ
ዚአብሔር በአብርሃም ሚስት በሣራ ምክንያት
በአቤሜሌክ ቤት ማኅፀኖችን ሁሉ በፍጹም
ዘግቶ ነበርና።

## ምዕራፍ ፳፩

### የይስሐቅ ልደት

፩እግዚአብሔርም እንደ ተናገረው ሣራን ጐበ
ኛት፤ እግዚአብሔርም እንደ ተናገረው ለሣራ
አደረገላት። ፪ሣራም ፀነሰች፤ እግዚአብሔ
ርም በተናገረው ወራት ለአብርሃም በእርጅ
ናዋ ወንድ ልጅን ወለደችለት። ፫አብርሃምም
ሣራ የወለደችለትን የልጁን ስም ይስሐቅ ብሎ
ጠራው። ፬አብርሃምም ልጁን ይስሐቅን እግ
ዚአብሔር እንዳዘዘው በስምንተኛው ቀን ገረ
ዘው። ፭አብርሃምም ልጁ ይስሕቅ በተወለደ
ለት ጊዜ መቶ ዓመቱ ነበረ። ፮ሣራም፥ "እግ
ዚአብሔር ደስ አሰኘኝ፤ ይህን የሚሰማ ሁሉ
በእኔ ምክንያት ደስ ይሰኛልና" አለች። ፯ደግ
ሞም ሣራ "በእርጅናዋ የወለደችውን ሕፃን እን
ድታጠባ ለአብርሃም ማን በነገረው?" አለች።
፰ሕፃኑም አደገ፤ ጡትንም አስጣሉት፤ አብር
ሃምም ይስሐቅን ጡት ባስጣለበት ቀን ትልቅ
ግብዣን አደረገ።

### የአጋርና የይስማኤል መባረር

፱ሣራም ግብፃዊቱ አጋር ለአብርሃም የወለደ
ችለትን ልጅ ይስማኤልን ከልጅዋ ከይስሐቅ
ጋር ሲጫወት አየችው። ፲ሣራም አብርሃምን
አለችው፥ "ይህችን ባሪያ ከነልጅዋ አባርራት፤
የዚህች ባሪያ ልጅ ከልጄ ከይስሐቅ ጋር አይ
ወርስምና።" ፲፩ይህም ነገር በአብርሃም ዘንድ
ስለ ልጁ እጅግ ችግር ሆነበት። ፲፪እግዚአብሔ
ርም አብርሃምን አለው፥ "ስለዚች አገልጋይ
ህና ስለ ሕፃኑ አትዘን፤ ሣራም የምትነግርህን
ቃል ሁሉ ስማ፤ በይስሐቅ ዘር ይጠራልሃልና።
፲፫የባሪያዪቱን ልጅ ደግሞ ታላቅ ሕዝብ አደር
ገዋለሁ፤ ዘርህ ነውና።" ፲፬አብርሃምም ማልዶ
ተነሣ፤ እንጀራንም ወሰደ፤ የውኃ አቍማዳ
ንም ለአጋር በትከሻዋ አሸከማት፤ ሕፃኑንም
ሰጥቶ አስወጣት፤ እርስዋም ሄደች፤ በዐዘቅተ
መሐላም በኩል ባለው ምድረ በዳ ተቅበዘበ
ዘች። ፲፭ውኃውም ከአቍማዳው አለቀ፤ ሕፃ

---

፩ "አንድ ሺህ ምዝምዝ ብርን" የሚለው በዕብ. የለም።

ኑንም ከአንድ ቊጥቋጦ ሥር ጥላው ሄደች፤
፲፮ልጄ ሲሞት አላየውም ብላ ቀስት ተወርውሮ
የሚደርስበትን ያህል ርቃ በአንጻሩ እየተመለ
ከተች፥ ፊት ለፊት ተቀመጠች፤ ቃልዋንም
አሰምታ አለቀሰች።[፩]። ፲፯እግዚአብሔርም የሕፃ
ኑን ጩኸት ሰማ፤ የእግዚአብሔርም መልአክ
ከሰማይ አጋርን እንዲህ ሲል ጠራት፥ "አጋር
ሆይ፥ ምን ሆንሽ? እግዚአብሔር የልጅሽን
ድምፅ ባለበት ስፍራ ሰምቶአልና አትፍሪ።
፲፰ተነሺ፤ ልጅሽንም አንሺ፤ በእጅሽም አጽ
ኚው፤ ትልቅ ሕዝብ አደርገዋለሁና። ፲፱እግዚ
አብሔርም ለአጋር ዐይንዋን ከፈተላት፤ የውኃ
ጉድጓድንም አየች፤ ሄዳም አቊማዳውን በውኃ
ሞላች፤ ልጅዋንም አጠጣችው። ፳እግዚአብሔ
ርም ከዚያ ሕፃን ጋር ነበረ፤ አደገም፤ በም
ድረ በዳም ተቀመጠ፤ ቀስተኛም ሆነ። ፳፩በፋ
ራን ምድረ በዳም ተቀመጠ፤ እናቱም ከምድረ
ግብፅ ሚስት ወሰደችለት።

## በአብርሃምና በአቤሜሌክ መካከል የተደረገ ስምምነት

፳፪በዚያ ዘመን አቤሜሌክ፥ ሚዜው አኮዘትና
የሠራዊቱ አለቃ ፋኮል ወደ አብርሃም ሄደው
አሉት፥ "በምታደርገው ሁሉ እግዚአብሔር
ከአንተ ጋር ነው፤ ፳፫አሁንም በእኔም፥ በል
ጄም፥ በወገኔም፥ ከእኔም ጋር ባለ ክፉ እንዳታ
ደርግብኝ በእግዚአብሔር ማልልኝ፤ ነገር ግን
በእንግድነት መጥተህ ለአንተ ቸርነት እንዳደረ
ግሁ አንተም ለእኔ፥ ለተቀምጥህባትም ምድር
ቸርነትን ታደርጋለህ።" ፳፬አብርሃምም፥ "እሺ
እኔ እምላለሁ" አለ። ፳፭አብርሃምም አቤሜሌ
ክን ብላቴኖቹ በቀሙት በውኃ ጉድጓድ ምክ
ንያት ወቀሰው። ፳፮አቤሜሌክም አለ፥ "ይህን
ነገር ማን እንዳደረገው አላወቅሁም፤ አንተም
ደግሞ ምንም አልነገርኸኝም፤ እኔም ከዛሬ
በቀር አልሰማሁም።" ፳፯አብርሃምም በጎችንና
ላሞችን አምጥቶ ለአቤሜሌክ ሰጠው፤ ሁለ
ቱም ቃል ኪዳን አደረጉ። ፳፰አብርሃምም ሰባ[፪]
ቄቦች በጎችን ለብቻቸው አቆመ። ፳፱አቤሜሌ
ክም አብርሃምን፥ "ለብቻቸው ያቆምሃቸው
እነዚያ ሰባ[፫] ቄቦች በጎች ምንድን ናቸው?"
አለው። ፴እርሱም፥ "እኔ ይህችን የውኃ ጉድ
ጓድ እንደቈፈርሁ ምስክር ይሆኑልኝ ዘንድ
እነዚህን ሰባ ቄቦች በጎች ከእጄ ትወስዳለህ"
አለው። ፴፩ስለዚህም ያን ጉድጓድ ዐዘቅተ
መሐላ ብሎ ጠራው፤ በዚያ እርስ በርሳቸው
ተማምለዋልና። ፴፪በዐዘቅተ መሐላ አጠገብም
ቃል ኪዳንን አደረጉ። አቤሜሌክና ሚዜው
አኮዘት፥ የሠራዊቱ አለቃ ፋኮልም ተነሥተው
ወደ ፍልስጥኤም ምድር ተመለሱ። ፴፫አብርሃ
ምም በዐዘቅተ መሐላ አጠገብ የተምር ዛፍን
ተከለ፤ በዚያም የዘለዓለሙን አምላክ የእግዚአ
ብሔርን ስም ጠራ። ፴፬አብርሃምም በፍልስጥ
ኤም ምድር ብዙ ቀን እንግዳ ሆኖ ተቀመጠ።

## ምዕራፍ ፳፪

## አብርሃም ልጁን ለመሥዋዕት ማቅረቡ

፩ከእነዚህም ነገሮች በኋላ እንዲህ ሆነ። እግ
ዚአብሔር አብርሃምን ፈተነው፤ እንዲህም
አለው፥ "አብርሃም! አብርሃም ሆይ፥" እር
ሱም፥ "እነሆ፥ አለሁ" አለ። ፪"የምትወድደ
ውን አንድ ልጅህን ይስሐቅን ይዘህ ወደ ከፍ
ተኛው ተራራ[፬] ሂድ፤ እኔም በምነግርህ በአንድ
ተራራ ላይ በዚያ መሥዋዕት አድርገህ ሠዋው"
አለው። ፫አብርሃምም በማለዳ ተነሥቶ አህያ
ውን ጫነ፤ ሁለቱንም ሎሌዎቹንና ልጁን ይስ
ሐቅን ከእርሱ ጋር ወሰደ፤ ዕንጨትንም ለመሥ
ዋዕት ሰነጠቀ፤ ተነሥቶም እግዚአብሔር ወዳ
ለው ቦታ ሄደ፤ በሦስተኛውም ቀን ደረሰ።
፬አብርሃምም ዐይኑን አነሣና ቦታውን ከሩቅ
አየ። ፭አብርሃምም ሎሌዎቹን አላቸው፥ "አህ
ያውን ይዛችሁ በዚህ ቈዩ፤ እኔና ልጄ ወደዚያ
ተራራ ሄደን እንሰግዳለን፤ ሰግደንም ወደ እና
ንተ እንመለሳለን።" ፮አብርሃምም የመሥዋዕቱን
ዕንጨት አንሥቶ ለልጁ ለይስሐቅ አሸከመው፤
እርሱም እሳቱንና ቢላዋዉን በእጁ ያዘ፤ ሁለ
ቱም አብረው ሄዱ። ፯ይስሐቅም አባቱን አብ
ርሃምን ተናገረው፥ "አባቴ ሆይ፥" አለ፤ እር
ሱም፥ "ልጄ፥ ምንድን ነው?" አለው። "እሳ
ቱና ዕንጨቱ ይኸው አለ፤ የመሥዋዕቱ በግ ግን
ወዴት አለ?" አለው። ፰አብርሃምም፥ "ልጄ
ሆይ፥ የመሥዋዕቱን በግ እግዚአብሔር ያዘጋ
ጃል" አለው፤ ሁለቱም አብረው ሄዱ።

---

፩ ግሪክ ሰባ. ሊ. "ሕፃኑ ቃሉን አሰምቶ አለቀሰ" ይላል።

፪ ዕብ. "ሰባት" ይላል።

፫ ዕብ. "ሰባት" ይላል።

፬ ዕብ. "ሞሪያ" ይላል።

፱እግዚአብሔር ወዳለውም ወደዚያ ቦታ
ደረሱ፤ አብርሃምም በዚያ መሠዊያዉን ሠራ፤
ዕንጨትንም ረበረበ፤ ልጁን ይስሐቅንም አስሮ
በመሠዊያዉ በዕንጨቱ ላይ በልቡ አስተኛው።
፲አብርሃምም እጁን ዘረጋ፤ ልጁንም ያርድ ዘንድ
ቢላዋ አነሣ። ፲፩የእግዚአብሔር መልአክም ከሰ
ማይ ጠራና፥ “አብርሃም! አብርሃም” አለው፤
እርሱም፥ “እነሆኝ” አለ። ፲፪እርሱም፥ “በብላ
ቴናው ላይ እጅህን አትዘርጋ፤ አንዳችም አታ
ድርግበት፤ ለምትውድደው ልጅህ ከእኔ አል
ራራህለትምና አንተ እግዚአብሔርን የምትፈራ
እንደሆንህ አሁን ዐውቄአለሁ” አለው። ፲፫አብ
ርሃምም ዐይኖቹን አቅንቶ በተመለከተ ጊዜ፥
በኋላው እነሆ፥ አንድ በግ ቀንዶቹ በዕፀ ሳቤቅ
ተይዞ አየ፤[፱] አብርሃምም ሄዶ በጉን ወሰደው፤
በልጁ በይስሐቅ ፈንታም ሠዋው። ፲፬አብርሃ
ምም ዛሬ በዚህ ተራራ እግዚአብሔር ፈጽሞ
ታየኝ ሲል ያን ቦታ “ራእየ እግዚአብሔር”[፲]
ብሎ ጠራው። ፲፭የእግዚአብሔር መልአክም አብ
ርሃምን ከሰማይ ሁለተኛ ጊዜ ጠራው፤ እንዲ
ህም አለው፦ ፲፮“እግዚአብሔር በራሴ ማልሁ
ይላል፤ ይህን ነገር አድርገሃልና፥ ለምትወድደው
ልጅህም ከእኔ አልራራህምና መባረክን እባር
ክሃለሁ፤ ፲፯ዘርህንም እንደ ሰማይ ከዋክብትና
በባሕር ዳር እንዳለ አሸዋ ፈጽሞ አበዛዋለሁ፤
ዘርህም የጠላት ሀገሮችን ይወርሳሉ፤ ፲፰የምድር
አሕዛብ ሁሉም በዘርህ ይባረካሉ፤ ቃሌን ሰምተ
ሃልና። ፲፱አብርሃምም ወደ ብላቴኖቹ ተመለሰ፤
ተነሥተውም ወደ ዐዘቅተ መሐላ አብረው ሄዱ፤
አብርሃምም በዐዘቅተ መሐላ ተቀመጠ።

## የናኮር ትውልድ

፳እንዲህም ሆነ፤ ከዚህ ነገር በኋላ ለአብርሃም
እንዲህ ተብሎ ተነገረ፥ “እነሆ፥ ሚልካ ደግሞ
ለወንድምህ ለናኮር ልጆችን ወለደች፤ ፳፩እነር
ሱም በኵሩ ዑፅ፥ ወንድሙ በዋክሲ፤ የአራም[፲፩]
አባት ቀማኤል፥ ፳፪አኮዛት፥ ኤዝራው፥ ፌል
ዳስ፥ ዮፋትና ባቱኤል” ናቸው። ፳፫ባቱኤልም
ርብቃን ወለደ፤ ሚልካ ለአብርሃም ወንድም
ለናኮር የወለደችለት ስምንቱ ልጆች እነዚህ
ናቸው። ፳፬ሬሕማ የሚሉአት ዕቅብቱ ደግሞ
ጥባህን፥ ቤካን፥ ጠኮንና ሜካን ወለደች።

## ምዕራፍ ፳፫

### የሣራ መሞትና አብርሃም
### የመቃብር ቦታ መግዛቱ

፩የሣራም ዕድሜ መቶ ሃያ ሰባት ዓመት ሆነ።
፪ሣራም በቈላ ውስጥ ባለች አርባቅ በምትባል
ከተማ ሞተች፤ እርስዋም በከነዓን ምድር ያለች
ኬብሮን ናት፤ አብርሃምም ለሣራ ሊያዝንላ
ትና ሊያለቅስላት ተነሣ። ፫አብርሃምም ከሬሳው
አጠገብ ተነሣ፤ ለኬጢ ልጆችም እንዲህ ሲል
ተናገረ፦ ፬“እኔ በእናንተ ዘንድ ስደተኛና መጻ
ተኛ ነኝ፤ በእናንተ ዘንድ እንድገዛ የመቃብር
ርስት ስጡኝ፤ ሬሳዬንም እንደ እናንተ ልቅ
በር።” ፭የኬጢ ልጆችም ለአብርሃም መለሱ፤
አሉትም፦ ፮“አይሆንም፥ ጌታ ሆይ፥ ስማን፤
አንተ ከእግዚአብሔር ዘንድ ለእኛ ንጉሥ ነህና
ከመቃብር ስፍራችን በመረጥኸው ቦታ ሬሳ
ህን ቅበር፤ ሬሳህን በዚያ ትቀብር ዘንድ ከእኛ
መቃብሩን የሚከለክልህ የለም።” ፯አብርሃምም
ተነሣ፤ በሀገሩ ሕዝብ ፊትም ለኬጢ ልጆች
ሰገደ። ፰እንዲህም አላቸው፥ “ሬሳዬን ከፊቴ
አርቄ እንድቀብር ከወደዳችሁስ ስሙኝ፤ ለሰ
ዓር ልጅ ለኤፍሮንም ስለ እኔ ንገሩት፤ ፱በእር
ሻው ዳር ያለችውን ድርብ ክፍል ያላትን ዋሻ
ውን ይስጠኝ፤ መቃብሩ የእኔ ርስት እንዲሆን
በሚገባው ዋጋ በመካከላችሁ ይስጠኝ፤ ከእር
ሱም እገዛለሁ።” ፲ኤፍሮንም በኬጢ ልጆች
መካከል ተቀምጦ ነበር፤ የኬጢ ሰው ኤፍሮ
ንም የኬጢ ልጆችና ወደ ከተማ የሚገቡ ሁሉ
ሲሰሙ ለአብርሃም እንዲህ ሲል መለሰለት፦
፲፩“አይደለም፥ ጌታዬ፥ ቀርበህ ስማኝ፤ እር
ሻውን፥ በውስጡም ያለውን ዋሻውን ሰጥቼ
ሃለሁ፤ በወገኔ ልጆች ፊት ሰጥቼሃለሁ፤ ሬሳ
ህን ቅበር።” ፲፪አብርሃምም በሀገሩ ሕዝብ ሁሉ
ፊት ሰገደ፤ ፲፫የሀገሩ ሕዝብም ሲሰሙ ለኤፍ
ሮን እንዲህ ሲል ተናገረ፥ “ከእኔ ቅርብ ነህና
ስማኝ፤ የእርሻህንም ዋጋ ከእኔ ውሰድ፤ ሬሳዬ
ንም በዚያ እቀብራለሁ።” ፲፬ኤፍሮንም ለአብ
ርሃም እንዲህ ሲል መለሰለት፥ “አይሆንም፤
ጌታዬ ሆይ፥ እኔን ስማኝ፤ ፲፭የአራት መቶ
ምዝምዝ ብር ዋጋ ምድር በእኔና በአንተ መካ

---

[፱] ዕብ. “በዱር ውስጥ በዕፀ ሳቤቅ ተይዞ አየ” ይላል።

[፲] ግሪክ ሰባ. ሊ. “አብርሃምም ያን ቦታ እግዚአብሔር አየ ብሎ ጠራው፤ ዛሬ እግዚአብሔር በዚህ ተራራ ታይቶ ነበር ይሉ ዘንድ” ይላል።

[፲፩] ግሪክ ሰባ. ሊ. “የሶርያውያን” ይላል።

ከል ምንድን ነው? እንግዲህ ሬሳህን በዚያ ቅበር።” ፲፮አብርሃምም የኤፍሮንን ነገር ሰማ፤ አብርሃምም በኬጢ ልጆች ፊት የነገረውንና ተቀባይነት ያለውን ግብዝ ያይደለ አራት መቶ ምዝምዝ ብር መዝኖ ለኤፍሮን ሰጠው።

፲፯በመምሬ ፊት ያለው ባለ ድርብ ክፍል የሆነው የኤፍሮን እርሻም ለአብርሃም ጸና፤ እርሻው፥ በእርሱም ያለ ዋሻው፥ በእርሻውም ውስጥ በዙሪያውም ያለው ዕንጨት ሁሉ፤ ፲፰በኬጢ ልጆችና በከተማዪቱ በር በሚገቡ ሁሉ ፊት ለአብርሃም ርስቱ ሆነ። ፲፱ከዚህም በኋላ አብርሃም ኬብሮን በምትባል በመምሬ ፊት በከነዓን ምድር ባለው እርሻ ባለ ድርብ ክፍል በሆነው ዋሻ ውስጥ ሚስቱን ሣራን ቀበረ። ፳እርሻውና በእርሱ ያለው ዋሻም በኬጢ ልጆች ዘንድ ለአብርሃም የመቃብር ርስት ሆኖ ጸና።[፩]

## ምዕራፍ ፳፬

### የይስሐቅና ርብቃ ጋብቻ

፩አብርሃምም ሸመገለ፤ ዘመኑም አለፈ፤ እግዚአብሔርም አብርሃምን በሁሉ ባረከው። ፪አብርሃምም ሎሌውን፥ የቤቱን ሽማግሌ፥ የከብቱን ሁሉ አዛዥ አለው፡- ፫“እጅህን በእጄ ላይ አድርግ፤ እኔም አብሬ ከምኖራቸው ከከነዓን ሴቶች ልጆች ለልጄ ለይስሐቅ ሚስት እንዳት ወስድለት በሰማይና በምድር አምላክ በእግዚአብሔር አምልሃለሁ፤ ፬ነገር ግን ወደ ተወለድሁበት ወደ ሀገሬና ወደ ተወላጆች ሂድ፤ ለልጄ ለይስሐቅም ከዚያ ሚስትን አምጣለት።” ፭ሎሌውም፥ “ሴቲቱ ምናልባት ወደዚህ ሀገር ከእኔ ጋር ለመምጣት ባትወድድስ ልጅህን ወደ መጣህበት ሀገር ልመልሰውን?” አለው። ፮አብርሃምም አለው፥ “ልጄን ወደዚያ እንዳትመልስ ተጠንቀቅ፤ ፯ከአባቴ ቤት፥ ከተወለድሁባት ምድር ያወጣኝ፡- ‘ይህችንም ምድር ለአንተና ለዘርህ እሰጥሃለሁ’ ብሎ የነገረኝና የማለልኝ የሰማይና የምድር አምላክ እግዚአብሔር፥ እርሱ መልአኩን በፊትህ ይሰድዳል፤ ከዚያም ለልጄ ሚስትን ትወስዳለህ። ፰ሴቲቱም ከአንተ ጋር ወደዚች ምድር ለመምጣት ባትፈቅድ አንተ ከዚህ መሐላ ንጹሕ ነህ፤ ልጄን ግን ወደ ዚያ እንዳትመልሰው ተጠንቀቅ።” ፱ሎሌውም በጌታው በአብርሃም እጅ ላይ እጁን አደረገ፤ ስለዚሁም ነገር ማለለት።

፲ሎሌውም ከጌታው ግመሎች መካከል ዐሥር ግመሎችን ወሰደ፥ ከጌታውም ዕቃ መልካም መልካሙን ይዞ ተነሣ፤ ተነሥቶም ወደ ሦርያ ወንዞች መካከል[፪] ወደ ናኮር ከተማ ሄደ። ፲፩ሲመሽም ውኃ ቀጂዎች ውኃ ሊቀዱ በሚመጡበት ጊዜ ከከተማዪቱ ውጪ በውኃ ጕድጓድ አጠገብ ግመሎቹን አሳረፈ። ፲፪እንዲህም አለ፥ “የጌታዬ የአብርሃም አምላክ እግዚአብሔር ሆይ፥ እማልድሃለሁ፤[፫] መንገዴን ዛሬ በፊቴ አቅናልኝ፤ ለጌታዬም ለአብርሃም ምሕረትን አድርግ። ፲፫እነሆ፥ በውኃው ጕድጓድ አጠገብ ቆሜአለሁ፤ የከተማዋ ሰዎች ሴቶች ልጆችም ውኃውን ሊቀዱ ይወጣሉ፤ ፲፬እንስራሽን አዘንብለሽ ውኃ አጠጭኝ የምላት እርስዋም፡- ‘አንተ ጠጣ፥ ግመሎችህን ደግሞ እስኪረኩ አጠጣለሁ’ የምትለኝ ድንግል፥ እርስዋ ለባሪያህ ለይስሐቅ ያዘጋጀሃት ትሁን፤ በዚህም ለጌታዬ ለአብርሃም ምሕረትን እንዳደረግህ አውቃለሁ።” ፲፭እንደዚህ በልቡ ያሰበውን መናገሩን ሳይፈጽም እንዲህ ሆነ፡- የአብርሃም ወንድም የናኮር ሚስት የሚልካ ልጅ የባቱኤል ሴት ልጅ ርብቃ እነሆ፥ መጣች፥ እንስራዋንም በጫንቃዋ ተሸክማ ነበር። ፲፮ብላቴናይቱም መልክዋ እጅግ ያማረ፥ ወንድ የማታውቅ ድንግል ነበረች። ወደ ውኃው ጕድጓድም ወረደች፤ ውኃም ቀዳች፤ እንስራዋንም ሞልታ ወጣች። ፲፯ያም ሰው ሊገናኛት ሮጠና፥ “ከእንስራሽ ጥቂት ውኃ አጠጪኝ” አላት። ፲፰እርስዋም፥ “ጌታዬ ሆይ፥ ጠጣ” አለችው፤ ፈጥናም እንስራዋን ከጫንቃዋ በእጅዋ አውርዳ እስኪረካ አጠጣችው። ፲፱እርሱንም ከአጠጣች በኋላ፡-[፬] “ለግመሎችህ ደግሞ ሁሉም እስኪረኩ ድረስ ውኃ እቀዳለሁ” አለችው። ፳ፈጥናም ውኃውን ከእንስራዋ በማጠጫው ውስጥ ገለበጠችው፤ ደግሞም ልትቀዳ ወደ ጕድጓዱ ሮጠች፤ ለግመሎቹም ሁሉ ውኃ ቀዳች። ፳፩ሰውየውም ትክ ብሎ ይመለከታት ነበር፤ እግዚአብሔር መንገዱን አቅንቶለት እንደ ሆነ

---

፩ ምዕ. ፳፫ ቍ. ፳ ላይ የሚነበበው በግሪክ ሰባ. ሊ. እና በዕብ. ብቻ ያለ ነው።

፪ ግሪክ ሰባ. ሊ. እና ዕብ. “መስጴጦምያ” ይላል።

፫ “እማልድሃለሁ” የሚለው በግሪክ ሰባ. ሊ. የለም።

፬ “እርሱንም ካጠጣች በኋላ” የሚለው በዕብ. ብቻ ነው።

ወይም እንዳልሆነ ለማወቅም ዝም አለ። ፳፪ግመ
ሎቹም ከጠጡ በኋላ እንዲህ ሆነ፤ ሰውዬው
አንድ አንድ ወቄት የሚመዝን የወርቅ ጉትቻ፥
ለእጆችዋም ዐሥር ወቄት የሚመዝን ጥንድ
የወርቅ አምባር አወጣ፤ ፳፫ጠርቶም እንዲህ
አላት፥ “አንቺ የማን ልጅ ነሽ? በአባትሽ ቤት
የምናድርበት ስፍራ እንዳለ እስኪ ንገሪኝ፤”
፳፬አለችውም፥ “እኔ ሚልካ ለናኮር የወለደች
ለት የባቱኤል ልጅ ነኝ። ፳፭በእኛ ዘንድ ለግመ
ሎችህ ሣርና ገለባ የሚበቃ ያህል አለ፤ ማደሪ
ያም አለን።” ፳፮ሰውየውም ደስ አለው፤ ለእግ
ዚአብሔርም ሰገደ። ፳፯እንዲህም አለ፥ “ቸር
ነቱንና እውነቱን ከጌታዬ ያላራቀ የጌታዬ የአ
ብርሃም አምላክ እግዚአብሔር ይመስገን፤ ለእ
ኔም ወደ ጌታዬ ወደ አብርሃም ወንድም ቤት
መንገዴን አቀናልኝ።”

፳፰ብላቴናዪቱም ሮጠች፥ ለእናቷም ቤት
ይህን ሁሉ ነገር ተናገረች። ፳፱ለርብቃም ስሙ
ላባ የተባለ ወንድም ነበራት፤ ላባም ወደ ውጪ
ወደ ውኃው ጉድጓድ ወደ ሰውዬው ሮጠ።
፴ጉትቻውንና አምባሮቹን በእኅቱ እጅ ባየ
ጊዜ፥ የእኅቱንም የርብቃን ነገር፦ ያ ሰው እን
ዲህ አለኝ ያለችውን በሰማ ጊዜ፥ እርሱ ወደ
ዚያ ሰው መጣ፤ እነሆም በውኃው ጉድጓድ
አጠገብ ከግመሎቹ ዘንድ ቆሞ ነበር። ፴፩እር
ሱም አለው፥ “አንተ የእግዚአብሔር ቡሩክ፥
ግባ ስለምን አንተ በውጪ ቆመሃል? እኛም
ቤትን፥ ለግመሎችህም ማደሪያን አዘጋጅተ
ናል።”፬ ፴፪ሰውዬውም ወደ ቤት ገባ፤ ግመ
ሎቹንም አራገፈ፤ ለግመሎቹም ሣርና ገለባ
አቀረቡላቸው፤ እግሩን ይታጠብ ዘንድ ውኃ
አመጡለት፤ ከእርሱ ጋር ላሉ ሰዎችም አመ
ጡላቸው። ፴፫ይበላም ዘንድ እንጀራን አቀረቡ
ለት፥ እርሱ ግን “ነገሬን እስክናገር ደረስ አል
በላም” አለ። እነርሱም “ተናገር” አሉት።
፴፬እርሱም አለ፥ “እኔ የአብርሃም ሎሌ ነኝ።
፴፭እግዚአብሔርም ጌታዬን እጅግ ባረከው፤ አገ
ነነውም፤ ላሞችንና በጎችን፥ ወርቅንና ብርን፥
ወንዶች ባሪያዎችንና ሴቶች ባሪያዎችን፥ ግመ
ሎችንና አህዮችንም ሰጠው። ፴፮የጌታዬ የአብር
ሃም ሚስት ሣራም በእርጅናዋ፭ ለጌታዬ ወንድ
ልጅን ወለደች፤ የነበረውንም ሁሉ ሰጠው።”
፴፯ጌታዬ እንዲህ ሲል አማለኝ፥ “እኔ ካለሁ
በት ሀገር ከከነዓናውያን ሴቶች ልጆች ለልጄ
ሚስትን አትውሰድ፤ ፴፰ነገር ግን ወደ አባቴ
ቤት ወደ ወገኔም ሂድ፤ ለልጄም ከዚያ ሚስ
ትን ውሰድለት። ፴፱ጌታዬንም ሴቲቱ ምናልባት
ከእኔ ጋር መምጣትን ባትፈቅድስ አልሁት።
፵እርሱም አለኝ፦ አካሄዴን በፊቱ ያደረግሁለት
እግዚአብሔር መልአኩን ከአንተ ጋር ይልካል።
መንገድህንም ያቀናል፤ ለልጄም ከወገኖች ከአ
ባቴም ቤት ሚስትን ትወስዳለህ፤ ፵፩የዚያን
ጊዜ ከመሐላዬ ንጹሕ ትሆናለህ፤ ወደ ዘመ
ዶች ሄደህ እነርሱ ባይሰጡህ ካማልሁህ መሐላ
ንጹሕ ትሆናለህ።” ፵፪ዛሬም ወደ ውኃው ጉድ
ጓድ መጣሁ፤ እንዲህም አልሁ፥ “የጌታዬ የአ
ብርሃም አምላክ እግዚአብሔር ሆይ፥ ዛሬ የም
ሄድበትን መንገዴን ብታቀናልኝ፥ ፵፫እነሆ፥ እኔ
በውኃው ጉድጓድ አጠገብ ቆሜአለሁ፤ የከተ
ማዋ ሰዎች ሴቶች ልጆችም ውኃን ሊቀዱ
ይወጣሉ፤ ጥቂት ውኃ ከእንስራሽ አጠጪኝ
ስላት፥ ፵፬እርስዋም ፦ ‘አንተ ጠጣ፤ ደግሞም
ለግመሎችህ እቀዳለሁ’ የምትለኝ ድንግል፥
እግዚአብሔር ለጌታዬ ልጅ ለባሪያዉ ለይስ
ሐቅ ያዘጋጃት ሚስት እርስዋ ትሁን። በዚህም
ለጌታዬ ምሕረትን እንዳደረግህ አውቃለሁ።”፮
፵፭እኔም በልቤ ያሰብሁትን ሳልፈጽም እንዲህ
ሆነ፤ ያን ጊዜ ርብቃ እንስራዋን በትከሻዋ
ተሸክማ ወጣች፥ ወደ ምንጭም ወርዳ ውኃ
ቀዳች፤ እኔም “እስቲ ውኃ አጠጪኝ” አል
ኋት። ፵፮ፈጥናም እንስራዋን ከትከሻዋ አወረደ
ችና፥ “አንተ ጠጣ፤ ግመሎችህን ደግሞ አጠ
ጣለሁ” አለችኝ፤ እኔም ጠጣሁ፤ ግመሎችንም
ደግሞ አጠጣች። ፵፯እኔም “አንቺ የማን ልጅ
ነሽ? ንገሪኝ” ብዬ ጠየቅኋት። እርስዋም፥
“ሚልካ የወለደችለት የናኮር ልጅ የባቱኤል
ልጅ ነኝ” አለችኝ፤ ፵፰ይህንም ነገር ከአንደበቷ
በሰማሁ ጊዜ እጅግ ደስ አሰኘችኝ።፯ ለጆሮዎ
ችዋም ጉትቻዎችን ለእጆችዋም አምባሮችን
አድርጌ አስጌጥኋት። ደስ ባሰኘችኝም ጊዜ፥
ለእግዚአብሔር ሰገድሁ፤ የጌታዬን የወንድሙን
ልጅ ለልጁ እወስድ ዘንድ በቀና መንገድ የመ
ራኝን የጌታዬን የአብርሃምን አምላክ እግዚአ
ብሔርን አመሰገንሁ። ፵፱አሁንም ቸርነትንና

---

፬ ግሪክ ሰባ. ሊ. እና ዕብ. “እኔም ቤቱን፥ ለግመሎችህም ገፈራን አዘጋጅቻለሁ” ይላል።

፭ ግሪክ ሰባ. ሊ. “በእርጅናው” ይላል።

፮ “በዚህም ለጌታዬ ምሕረትን እንዳደረግህ አውቃለሁ” የሚለው በዕብ. የለም።

፯ “ይህንም ነገር ከአንደበቷ በሰማሁ ጊዜ እጅግ ደስ አሰኘችኝ” የሚለው በግሪክ ሰባ. ሊ. እና በዕብ. የለም።

እውነትን ለጌታዬ ትሠሩ እንደ ሆነ ንገሩኝ፤
ይህም ባይሆን ንገሩኝ፤ ወደ ቀኝ ወይም ወደ
ግራ እመለስ ዘንድ። ፶ባቱኤልና ላባም መለሱ፤
እንዲህም አሉ፥ "ነገሩ ከእግዚአብሔር ዘንድ
መጥቶአል፤ ክፉ ወይም በጎ ልንመልስልህ አን
ችልም። ፶፩ርብቃ እንኋት፤ በፊትህ ናት፤ ይዘ
ሃት ሂድ፥ እግዚአብሔር እንደ ተናገረ ለጌታህ
ልጅ ሚስት ትሁን።" ፶፪የአብርሃምም ሎሌ ነገ
ራቸውን በሰማ ጊዜ ወደ ምድር ወድቆ ለእግ
ዚአብሔር ሰገደ። ፶፫ሎሌውም የብርና የወርቅ
ጌጥ፥ ልብስም አወጣ፤ ለርብቃም ሰጣት፤ ዳግ
መኛም ለአባቷና ለእናቷ፰ እጅ መንሻ ሰጣ
ቸው። ፶፬ከዚህም ሁሉ በኋላ እርሱ፥ ከእርሱ
ጋር ያሉትም በሉ፤ ጠጡም፤ በዚያም አደሩ፤
በማለዳም ተነሥቶ፥ "ወደ ጌታዬ እሄድ ዘንድ
አሰናብቱኝ" አላቸው። ፶፭አባቷ እናቷና ወንድ
ምዋ፡-፱ "ብላቴናዪቱ ዐሥር ቀን ያህል እንኳ
በእኛ ዘንድ ትቀመጥ፤ ከዚያም በኋላ ትሄዳ
ለች" አሉ። ፶፮እርሱም፥ "እግዚአብሔር መን
ገዴን አቅንቶልኝ ሳለ አታዘግዩኝ፤ ወደ ጌታዬ
እሄድ ዘንድ አሰናብቱኝ" አላቸው። ፶፯እነር
ሱም፥ "ብላቴናዪቱን እንጥራና ከአፍዋ እንጠ
ይቅ" አሉ። ፶፰ርብቃንም ጠርተው፥ "ከዚህ
ሰው ጋር ትሄጃለሽን?" አሉአት። እርስዋም፥
"አዎን እሄዳለሁ" አለች። ፶፱እኅታቸውንም
ርብቃን ሞግዚቷንም፲ ከገንዘብ ጋር፥ የአብር
ሃምን ሎሌና ሰዎቹንም አሰናበቱአቸው። ፷እኅ
ታቸው ርብቃንም መረቁአትና፥ "አንቺ እኅታ
ችን፥ እልፍ አእላፋት ሁኚ፤ ዘርሽም የጠላት
ሀገሮችን ይውረስ" አሉአት።

፷፩ርብቃም ተነሣች፤ ደንገጥሮችዋም፥ በግመ
ሎችዋ ላይ ተቀምጠው ከሰውዬው ጋር አብ
ረው ሄዱ፤ ሎሌውም ርብቃን ተቀብሎ ሄደ።
፷፪ይስሐቅም በዐዘቅተ ራእይ በኩል ወደ ምድረ
በዳ ይመለከት ነበር፤ በአዜብ በኩል ባለው
ምድር ተቀምጦ ነበርና። ፷፫ይስሐቅም በመሸ
ጊዜ በልቡ እያሰላሰለ ወደ ሜዳ ወጥቶ ነበር፤
ዓይኖቹንም አቀና፤ እነሆም ግመሎች ሲመጡ
አየ። ፷፬ርብቃም ዓይኖችዋን አቀናች፤ ይስሐ
ቅንም አየች፤ ከግመልም ወረደች። ፷፭ሎሌው
ንም፥ "ሊቀበለን በሜዳ የሚመጣ ይህ ሰው
ማነው?" አለችው። ሎሌውም፥ "እርሱ ጌታዬ
ነው" አላት፤ እርስዋም ቀጸላዋን ወስዳ ተከና
ነበች። ፷፮ሎሌውም ያደረገውን ነገር ሁሉ ለይ
ስሐቅ ነገረው። ፷፯ይስሐቅም ወደ እናቱ ቤት
ገባ፤ ርብቃንም ወሰዳት፤ ሚስትም ሆነችው፤
ወደዳት፤ ይስሐቅም ስለ እናቱ ስለ ሣራ ተጽ
ናና።

## ምዕራፍ ፳፭

### አብርሃም ከኬጡራ የወለዳቸው ልጆች

(፩ዜ.መ. ፩፥ ፴፪-፴፫)

፩አብርሃምም ደግሞ ስምዋ ኬጡራ የተባ
ለች ሚስት አገባ። ፪እርስዋም ዘንበሪን፥ ዮቃ
ጤንን፥ ሜዳንን፥ ዮብቅን፥ ምድያምንና ሴሂን
ወለደችለት። ፫ዮቃጤንም ሶቤቅን፥ ቴማንንና
ድዳንን ወለደ። የድዳንም ልጆች ራጉኤል፥
ንበከዝ፥ እስራኦምና ሎአም ናቸው። ፬የምድ
ያምም ልጆች ጌፌር፥ ዔፉር፥ ሄኖኅ፥ አቢሮ
ንና ቲያሮስ ናቸው። እነዚህም ሁሉ የኬጡራ
ልጆች ናቸው። ፭አብርሃምም በሕይወቱ ሳለ
ገንዘቡን ሁሉ ለልጁ ለይስሐቅ ሰጠው፤ ፮አብ
ርሃምም ለቁባቶቹ ልጆች ሀብትን ሰጣቸው፤
እርሱም ገና በሕይወቱ ሳለ ከልጁ ከይስሐቅ
ለይቶ ወደ ምሥራቅ ሀገር ሰደዳቸው።

### የአብርሃም ሞት

፯አብርሃምም የኖረበት የዕድሜው ዓመታት
እነዚህ ናቸው፤ መቶ ሰባ አምስት ዓመት ኖረ።
፰አብርሃምም መልካም ሽምግልናን ሽምግሎ፥
ዘመኑንም ፈጽሞ ሞተ፤ ወደ ወገኖቹም ተጨ
መረ። ፱ልጆቹ ይስሐቅና ይስማኤልም በመምሬ
ፊት ለፊት ባለው በኬጢያዊው በሰዓር ልጅ
በኤፍሮን እርሻ ላይ ባለ ድርብ ክፍል በሆነው
ዋሻ ውስጥ ቀበሩት። ፲ይህም አብርሃም ከኬጢ
ልጆች የገዛው እርሻ ነው፤ አብርሃምንና ሚስ
ቱን ሣራን በዚያ ቀበሩአቸው። ፲፩እንዲህም ሆነ፥
አብርሃምም ከሞተ በኋላ እግዚአብሔር ልጁን
ይስሐቅን ባረከው፤ ይስሐቅም ዐዘቅተ ራእይ
ተብሎ በሚጠራው ምንጭ አጠገብ ኖረ።

### የይስማኤል ትውልድ

(፩ዜ.መ. ፩፥ ፳፰-፴፩)

፲፪የሣራ ባሪያ ግብፃዊቱ አጋር ለአብርሃም የወ
ለደችለት የአብርሃም ልጅ የይስማኤል ትውልድ

---

፰ ዕብ. "ወንድምዋ እና እናቷ" ይላል።

፱ ግሪክ ሰባ. ሊ. "ወንድሞችዋና እናቷ" ይላል ዕብ. "ወንድምዋና እናቷ" ይላል።

፲ "ሞግዚቷንም" የሚለው በግሪክ ሰባ. ሊ. የለም።

ይህ ነው፤ ፲፫የይስማኤልም የልጆቹ ስም በየስማ
ቸውና በየትውልዳቸው እንዲህ ነው። ፲፬የይስማ
ኤል የበኵር ልጁ ናቡአት፥ ቄዳር፥ ነብዳኤል፥
መብሳን፥ ፲፭ማሴሜ፥ ዱማ፥ ማሜን፥ ኩዳን፥
ቴማን፥ ኤያጤር፥ ናፌስ፥ ቄድን። ፲፮የይስማ
ኤል ልጆች እነዚህ ናቸው፤ ስማቸውም በየመ
ንደራቸውና በየሰፈራቸው ይህ ነው፤ በየወገናቸ
ውም ዐሥራ ሁለት አለቆች ናቸው። ፲፯እርሱም
ከኤውላጥ አንሥቶ በግብፅ ፊት ለፊት እስከም
ትገኝ እስከ ሴይር ባለው ሀገር ኖረ፤ ወደ አሦር
ዮንም ደረሰ፤ እንዲህም ከወንድሞቹ ሁሉ ፊት
ተቀመጠ። ፲፰ይስማኤልም የኖረበት የዕድሜው
ዘመን መቶ ሠላሳ ሰባት ዓመት ነው፤ ሸምግሎ
ሞተ፤ ወደ ወገኖቹም ተጨመረ።[፩]

## የዔሳውና የያዕቆብ መወለድ

፲፱የአብርሃም ልጅ የይስሐቅ ትውልድም
ይህ ነው፤ አብርሃም ይስሐቅን ወለደ፥ ፳ይስሐ
ቅም ሚስት ትሆነው ዘንድ የሶርያዊውን የላባን
እኅት፥ የሶርያዊውን የባቱኤልን ልጅ ርብቃን
ከሁለቱ ከሶርያ ወንዞች መካከል በወሰዳት ጊዜ
አርባ ዓመት ሆኖት ነበር። ፳፩ይስሐቅም ስለ
ሚስቱ ርብቃ ወደ እግዚአብሔር ለመነ፤ መካን
ነበረችና፤ እግዚአብሔርም ሰማው፤ ሚስቱ ርብ
ቃም ፀነሰች። ፳፪ልጆችዋም በሆድዋ ውስጥ
ይንቀሳቀሱ ነበር፤ እርስዋም፥ "እንዲህ እሆን
ዘንድ ካለኝ ይህ ለእኔ ምኔ ነው?" አለች። ወደ
እግዚአብሔርም ትለምን ዘንድ ሄደች። ፳፫እግዚ
አብሔርም አላት፥ "ሁለት ሕዝቦች በማኅፀንሽ
አሉ፤ ሁለቱም ሕዝብ ከሆድሽ ይወለዳሉ፤ ሕዝ
ብም ከሕዝብ ይበረታል፤ ታላቁም ለታናሹ ይገ
ዛል።" ፳፬የምትወልድበትም ወራት ተፈጸመ፤
በማኅፀንዋም መንታ ነበሩ። ፳፭የበኵር ልጅዋም
ወጣ፤ እንደ ጽጌረዳም ቀይ ነበረ፤ ሁለንተና
ውም ጠጕራም ነበር፤ ስሙንም ዔሳው ብላ
ጠራችው። ፳፮ከዚያም በኋላ ወንድሙ ወጣ፤
በእጁም የዔሳውን ተረከዝ ይዞ ነበር፤ ስሙንም
ያዕቆብ ብላ ጠራችው። ርብቃ ዔሳውንና ያዕቆ
ብን በወለደቻቸው ጊዜ ይስሐቅ ስድሳ ዓመት
ሆኖት ነበር።

## ዔሳው ብኵርናውን እንደ ሰጠ

፳፯ብላቴኖቹም አደጉ፤ ጐለመሱም፤ ዔሳ
ውም አደን የሚያውቅ የበረሃ ሰው ሆነ፤ ያዕ
ቆብ ግን ጭምት ሰው ነበረ፤ በቤትም ይቀ
መጥ ነበር። ፳፰ይስሐቅም ዔሳውን ይወድ
ነበር፤ እርሱ ከአደነው ይበላ ነበርና። ርብቃ
ግን ያዕቆብን ትወድ ነበረች። ፳፱ለያዕቆብም
የምስር ንፍሮ ቀቀለችለት፤[፪] ዔሳውም ደክሞ
ከበረሃ ገባ፤ ፴ዔሳውም ያዕቆብን፥ "ከምስር
ንፍሮህ አብላኝ፤ እኔ እጅግ ደክሜአለሁና"
አለው፤ ስለዚህም ስሙ ኤዶም ተባለ። ፴፩ያዕ
ቆብም ዔሳውን፥ "ዛሬ ብኵርናህን ስጠኝ"
አለው። ፴፪ዔሳውም፥ "እነሆ፥ እኔ ልሞት ነኝ፤
ይህች ብኵርና ለምኔ ናት?" አለ። ፴፫ያዕቆ
ብም፥ "ብኵርናህን ትሰጠኝ ዘንድ እስኪ ዛሬ
ማልልኝ" አለው። ዔሳውም ማለለት፤ ብኵር
ናውንም ለያዕቆብ ሸጠ። ፴፬ያዕቆብም ለዔሳው
እንጀራና የምስር ንፍሮ ሰጠው፤ በላ፥ ጠጣ፥
ተነሥቶም ሄደ፤ ዔሳውም ብኵርናውን አቃ
ለላት።

## ምዕራፍ ፳፮

## ይስሐቅ ወደ ጌራራ መሄዱ

፩በምድርም ቀድሞ በአብርሃም ዘመን ከሆ
ነው ራብ ሌላ ራብ ሆነ፤ ይስሐቅም ወደ ፍል
ስጥኤም ንጉሥ ወደ አቤሜሌክ ወደ ጌራራ
ሄደ። ፪እግዚአብሔርም ተገለጠለት፤ እንዲህም
አለው፥ "ወደ ግብፅ አትውረድ፤ እኔ በምልህ
ምድር ተቀመጥ። ፫በዚህች ምድር ተቀመጥ፤
ከአንተ ጋርም እሆናለሁ፤ እባርክሃለሁም፤ ይህ
ችን ምድር ሁሉ ለአንተም፥ ለዘርህም እሰ
ጣለሁና፥ ለአባትህም ለአብርሃም የማልሁለ
ትን መሐላ ከአንተ ጋር አጸናለሁ። ፬ዘርህንም
እንደ ሰማይ ከዋክብት አበዛዋለሁ፤ ይህችንም
ምድር ሁሉ ለዘርህ እሰጣለሁ፤ የምድርም ሕዝ
ቦች ሁሉ በዘርህ ይባረካሉ፤ ፭አባትህ አብርሃም
ቃሌን ሰምቶአልና፤ ትእዛዜንና ፍርዴን፥ ሥርዐ
ቴንና ሕጌንም ጠብቆአልና።" ፮ይስሐቅም በጌ
ራራ ተቀመጠ። የዚያም ስፍራ ሰዎች ስለ
ሚስቱ ስለ ርብቃ ጠየቁት፤ እርሱም፥ "እኅቴ
ናት" አላቸው፤ ፯የዚህ ስፍራ ሰዎች ለርብቃ
ሲሉ እንዳይገድሉኝ ብሎ ሚስቴ ናት ማለ
ትን ፈርቶአልና፤ እርስዋም ውብ ነበረችና።
፰በዚያም ብዙ ቀን ተቀመጠ። የፍልስጥኤም
ንጉሥ አቤሜሌክም በመስኮት ሆኖ በተመለከተ
ጊዜ ይስሐቅን ከሚስቱ ከርብቃ ጋር ሲጫወት

---

[፩] ምዕ. ፳፭ ቁ. ፲፯ እና ፲፰ በዕብ. እና በግሪክ ሰባ ሊ. ተዘዋውረዋል።
[፪] ዕብ. እና ግሪክ ሰባ. ሊ. "ያዕቆብም የምስር ንፍሮ ቀቀለ" ይላል።

አየው። ፱አቤሜሌክም ይስሐቅን ጠራ፤ እንዲ
ህም አለው፥ "እነሆ፥ ሚስትህ ናት፤ እንዴትስ
እርስዋን፦ 'እኅቴ ናት' አልህ?" ይስሐቅም፥
"በእርስዋ ምክንያት እንዳልሞት ብዬ ነው"
አለው። ፲አቤሜሌክም አለ፥ "ይህ ያደረግህብን
ምንድን ነው? ከሕዝቡ አንዱ ባለማወቅ ከሚስ
ትህ ጋር ሊተኛ ጥቂት በቀረው ነበር፤ ኀጢአት
ንም ልታመጣብን ነበር።" ፲፩አቤሜሌክም ሕዝ
ቡን ሁሉ፥ "ይህን ሰው፥ ሚስቱንም የሚነካ
ፍርዱ ክፉ ሞት ነው" ብሎ አዘዘ።
፲፪ይስሐቅም በዚያች ምድር ዘርን ዘራ፤ በዚ
ያች ዓመትም መቶ እጥፍ ገብስ አገኘ፤ እግዚ
አብሔርም ባረከው። ፲፫ከፍ ከፍም አለ፤ እጅ
ግም ታላቅ እስኪሆን ድረስ እየጨመረ ይበዛ
ነበር፤ ፲፬ወንዶችና ሴቶች አገልጋዮችን፥ ብዙ
በጎችንና ላሞችን፥ የእርሻ መሬትንም ገዛ፤ የፍ
ልስጥኤም ሰዎችም ቀኑበት። ፲፭በአባቱ በአብ
ርሃም ዘመን የአባቱ ሎሌዎች የማሱአቸውን
ጒድጓዶች ሁሉ የፍልስጥኤም ሰዎች ደፈኑአ
ቸው፤ አፈርንም ሞሉባቸው። ፲፮አቤሜሌክም
ይስሐቅን፥ "ከእኛ ተለይተህ ሂድ፤ ከእኛ
ይልቅ እጅግ በርትተሃልና" አለው። ፲፯ይስሐ
ቅም ከዚያ ሄደ፤ በጌራራም ሸለቆ ሰፈረ፤ በዚ
ያም ተቀመጠ።
፲፰ይስሐቅም የአባቱ የአብርሃም አገልጋዮች
ቈፍረዋቸው የነበሩትን የውኃ ጒድጓዶች ደግሞ
አስቈፈረ፤ አባቱ አብርሃም ከሞተ በኋላ የፍ
ልስጥኤም ሰዎች ደፍነዋቸው ነበርና፤ አባቱም
አብርሃም ይጠራቸው በነበረው ስም ጠራ
ቸው። ፲፱የይስሐቅ ሎሌዎችም በጌራራ ሸለቆ
ውስጥ ጒድጓድ ቈፈሩ፤ በዚያም ጣፋጭ
የውኃ ምንጭ አገኙ። ፳የጌራራ እረኞች ከይ
ስሐቅ እረኞች ጋር፥ "ውኃው የእኛ ነው"
ሲሉ ተጣሉ፤ የዚያችንም ጒድጓድ ስም "ዐዘ
ቅተ ዐመፃ" ብሎ ጠራት፤ እነርሱ በድለው
ታልና። ፳፩ይስሐቅም ከዚያ ሄደ በዚያም ሌላ
ጒድጓድ ማሰ፥ ስለ እርስዋም ደግሞ ተጣሉት፤
ስምዋንም "ጽልእ" ብሎ ጠራት። ፳፪ከዚያም
እልፍ ብሎ ሌላ ጒድጓድ ቈፈረ፤ ስለ እርስ
ዋም አልተጣሉትም፤ ስምዋንም "መርኅብ"
ብሎ ጠራት፤ እንዲህ ሲል፥ "አሁን እግዚአብ
ሔር አሰፋልን፤ በምድርም አበዛን።"
፳፫ከዚያም ወደ ዐዘቅተ መሐላ ሄደ። ፳፬በዚ
ያችም ሌሊት እግዚአብሔር ተገለጠለት፤ እን
ዲህም አለው፥ "እኔ የአባትህ የአብርሃም አም
ላክ ነኝ፤ አትፍራ፤ እኔ ከአንተ ጋር ነኝና፤ እባ
ርክሃለሁ፤ ስለ አባትህ ስለ አብርሃም ዘርህን
አበዛዋለሁ።" ፳፭በዚያም ለአምላኩ ለእግዚአ
ብሔር መሠውያን ሠራ፤ የእግዚአብሔርንም
ስም ጠራ፤ በዚያም ድንኳን ተከለ፤ የይስሐ
ቅም ሎሌዎች በዚያ ጒድጓድ ማሱ።

### በይስሐቅና በአቤሜሌክ መካከል
### የተደረገ ስምምነት

፳፮አቤሜሌክና ሚዜው አኮዘት፥ የሠራዊቱም
አለቃ ፋኮል ከጌራራ ወደ እርሱ ሄዱ። ፳፯ይስ
ሐቅም፥ "ለምን ወደ እኔ መጣችሁ? እናንተ
ጠልታችሁኛል፤ ከእናንተም ለይታችሁ አሳድ
ዳችሁኛልና" አላቸው። ፳፰እነርሱም አሉት፥
"እኛ የጠላንህ አይደለም፤ በመልካም አኑረን፥
በመልካም አሰናበትንህ እንጂ፤ አሁንም አንተ
ለአምላክህ ለእግዚአብሔር ቡሩክ ነህ። ፳፱አም
ላክህ እግዚአብሔርም ከአንተ ጋር እንደ አለ
በአየን ጊዜ በአንተና በእኛ መካከል መሐላ
ይሁን፤ አንተ በእኛ ላይ ክፉ እንዳታደርግ፤
እኛም በአንተ ላይ ክፉ እንዳናደርግ እንማማ
ላለን።" ፴ይስሐቅም ማዕድ አቀረበላቸው፤
በሉም፤ ጠጡም። ፴፩ማልደውም ተነሡ፤
እርስ በርሳቸውም ተማማሉ፤ ይስሐቅም አሰና
በታቸው፤ ከእርሱም በደኅና ሄዱ። ፴፪በዚያም
ቀን የይስሐቅ ሎሌዎች መጡ፤ ስለ ቈፈሩአ
ትም ጒድጓድ፥ ውኃ አገኘን ብለው ነገሩት።
፴፫ስምዋንም "መሐላ" ብሎ ጠራት፤ ስለዚ
ህም የከተማዪቱ ስም እስከ ዛሬ ድረስ "ዐዘ
ቅተ መሐላ" ይባላል።

### ዔሳው ከከነዓን ሚስቶችን እንደ አገባ

፴፬ዔሳውም አርባ ዓመት ሲሆነው የኬጢያ
ዊው የብኤልን ልጅ ዮዲትን፤ የኬጢያዊው
የኤሎንን ልጅ ቤሴሞትንም ሚስቶች አድርጎ
አገባ፤ ፴፭እነርሱም ይስሐቅንና ርብቃን ያሳ
ዝኑ ነበር።

## ምዕራፍ ፳፯

### ይስሐቅ ያዕቆብን እንደ ባረከ

፩እንዲህም ሆነ፦ ይስሐቅ ፈጽሞ ከአረጀ
በኋላ ዐይኖቹ ፈዝዘው አያይም ነበር። ታላ
ቁን ልጁን ዔሳውንም ጠርቶ፥ "ልጄ ሆይ፥"
አለው፤ እርሱም፥ "እነሆ አለሁ" አለው።
፪እርሱም አለው፥ "እነሆ እኔ አረጀሁ፤ የም
ሞትበትን ቀን አላውቅም። ፫አሁንም ማደኛ
ህን የፍላጻህን አፎትና ቀስትህን ውሰድ፤ ወደ
ምድረ በዳም ውጣ፤ አደንም አድንልኝ፤ ፬ሳል

ሞትም ነፍሴ እንድትባርክህ እኔ እንደምወደው
መብል አዘጋጅተህ አበላ ዘንድ አምጣልኝ።”
፭ርብቃም ይስሐቅ ለልጁ ለዔሳው እንደዚህ
ሲነግር ትሰማ ነበር። ዔሳውም ለአባቱ አደን
ሊያድን ወደ ምድረ በዳ ሄደ። ፮ርብቃም ታናሹ
ልጅዋን ያዕቆብን እንዲህ አለችው፦ ፯“እነሆ፥
አባትህ ለወንድምህ ለዔሳው፦ እንዲህ ሲለው
ሰማሁ፤ ‘ሂድና ከአደንኸው መብል አዘጋጅ
ተህ አምጣልኝ፤ ሳልሞትም በልቼ በእግዚአ
ብሔር ፊት ልባርክህ።’ ፰አሁንም ልጄ ሆይ፥
እኔ እንደማዝዝህ ስማኝ፤ ፱ወደ በጎቻችን ሄደህ
ሁለት መልካም ጠቦቶች አምጣልኝ፤ እነርሱ
ንም ለአባትህ እንደሚወደው መብል አደርጋ
ቸዋለሁ፤ ፲ለአባትህም ሳይሞት እንዲባርክህ፥
ይበላ ዘንድ ትወስድለታለህ።” ፲፩ያዕቆብም እና
ቱን ርብቃን፥ “እነሆ ዔሳው ወንድሜ ጠጉ
ራም ሰው ነው፥ እኔ ግን ለስላሳ ነኝ፤ ፲፪ምናል
ባት አባቴ ቢዳስሰኝ በፊቱ እንደምንቀው እሆ
ናለሁ፤ መርገምን በላዬ አመጣለሁ፤ በረከት
ንም አይደለም።” ፲፫እናቱም አለችው፥ “ልጄ
ሆይ፥ መርገምህ በእኔ ላይ ይሁን፥ ቃሌን ብቻ
ስማኝ፤ ሂድና ያልሁህን አምጣልኝ።” ፲፬ሄዶም
አመጣ፤ ለእናቱም ሰጣት፤ እናቱም መብልን
አባቱ እንደሚወድደው አደረገች። ፲፭ርብቃም
ከእርስዋ ዘንድ በቤት የነበረውን የታላቁን ልጅ
ዋን የዔሳውን መልካሙን ልብስ አመጣች፤
ለታናሹ ልጅዋ ለያዕቆብም አለበሰችው፤ ፲፮የጠ
ቦቶችንም ለምድ በእጆቹና በለስላሳው አንገቱ
ላይ አደረገች፤ ፲፯ያን የሠራችውን መብልና እን
ጀራውን ለልጅዋ ለያዕቆብ በእጁ ሰጠችው።
፲፰ወደ አባቱም አግብቶ፥ “አባቴ ሆይ፥”
አለው፦ እርሱም፥ “እነሆኝ፤ ልጄ ሆይ፥
አንተ ማን ነህ?” አለ። ፲፱ያዕቆብም አባቱን
አለው፥ “የበኵር ልጅህ እኔ ዔሳው ነኝ፤ እንዳ
ዘዝኸኝ አደረግሁ፤ ነፍስህ ትባርከኝ ዘንድ ቀና
ብለህ ተቀመጥ፤ ካደንሁትም ብላ።” ፳ይስሐ
ቅም ልጁን፥ “ልጄ ሆይ፥ ፈጥነህ ያገኘኸው
ይህ ምንድን ነው?” አለው። እርሱም፥ “አም
ላክህ እግዚአብሔር በፊቴ የሰጠኝ ነው” አለ።
፳፩ይስሐቅም ያዕቆብን፥ “ልጄ ሆይ፥ አንተ
ልጄ ዔሳው እንደ ሆንህ ወይም እንዳልሆንህ
ቅረበኝና ልዳስስህ” አለው። ፳፪ያዕቆብም ወደ
አባቱ ወደ ይስሐቅ ቀረበ፤ ዳሰሰውም፤ እን
ዲህም አለው፥ “ይህ ድምፅ የያዕቆብ ድምፅ
ነው፥ እጆች ግን የዔሳው እጆች ናቸው”
አለው። ፳፫እርሱም አላወቀውም ነበር፤ እጆቹ
እንደ ወንድሙ እንደ ዔሳው እጆች ጠጉራም
ነበሩና፤ ይስሐቅም ባረከው ። ፳፬አለውም፥
“አንተ ልጄ ዔሳው ነህን?” እርሱም፥ “እኔ
ነኝ” አለ። ፳፭እርሱም፥ “ልጄ ሆይ፥ ከአደ
ንኸው እንድበላና ነፍሴ እንድትባርክህ አም
ጣልኝ” አለው። አቀረበለትም፤ በላም፤ ወይ
ንም አመጣለት፤ እርሱም ጠጣ። ፳፮አባቱ ይስ
ሐቅም፥ “ልጄ ሆይ፥ ወደ እኔ ቅረብ፤ ሳመ
ኝም” አለው። ፳፯ወደ እርሱም ቀረበ፤ ሳመ
ውም፤ የልብሱንም ሽታ አሸተተ፤ ባረከውም፤
እንዲህም አለ፥ “የልጄ ሽታ እግዚአብሔር
እንደ ባረከው የእርሻ ሽታ ነው፤ ፳፰እግዚአብ
ሔርም ከሰማይ ጠል፥ ከምድርም ስብ፥ የእ
ህልንም፥ የወይንንም፥ የዘይትንም ብዛት ይስ
ጥህ፤ ፳፱አሕዛብ ይገዙልህ፤ አለቆችም ይስገ
ዱልህ፤ ለወንድምህ ጌታ ሁን፤ የአባትህም[፩]
ልጆች ይስገዱልህ፤ የሚረግምህ እርሱ ርጉም
ይሁን፤ የሚባርክህም ቡሩክ ይሁን።”

### ዔሳው ከይስሐቅ በረከትን መለመኑ

፴ይስሐቅም ያዕቆብን ባርኮ ከፈጸመ በኋላ፥
ያዕቆብ ከአባቱ ከይስሐቅ ፊት ወጣ፥ ወን
ድሙ ዔሳውም ከአደኑ መጣ፤ ፴፩እርሱም
ደግሞ መብል አዘጋጀ፥ ለአባቱም አመጣ፤ አባ
ቱንም፥ “አባቴ ተነሥ፤ ነፍስህም ትባርከኝ
ዘንድ ልጅህ ከአደነው ብላ” አለው። ፴፪አባቱ
ይስሐቅም፥ “አንተ ማን ነህ?” አለው። እር
ሱም፥ “እኔ የበኵር ልጅህ ዔሳው ነኝ”
አለው። ፴፫ይስሐቅም እጅግ ደነገጠ፤ እንዲህም
አለ፥ “ያደነውን አደን ወደ እኔ ያመጣው ማን
ነው? አንተ ሳትመጣም ከሁሉ በላሁ፤ ባረክ
ሁትም፤ እርሱም የተባረከ ነው።” ፴፬ዔሳውም
የአባቱን ቃል በሰማ ጊዜ ታላቅ፥ እጅግም
መራራ ጩኸት ጮኸ፤ አባቱንም፥ “አባቴ
ሆይ፤ እኔንም ደግሞ ባርከኝ” አለው። ፴፭ይስ
ሐቅም ዔሳውን አለው፥ “ወንድምህ በተንኰል
መጥቶ በረከትህን ወሰደብህ።” ፴፮ዔሳውም
አለ፥ “በእውነት ስሙ ያዕቆብ ተባለ፤ ሁለት
ጊዜ አሰናክሎኛልና፤ መጀመሪያ ብኵርናዬን
ወሰደ፤ አሁንም እነሆ በረከቴን ወሰደ።” ዔሳ
ውም አባቱን አለው፥ “ደግሞም አባቴ ሆይ፥
ለእኔ በረከትን አላስቀረህልኝምን?” ፴፯ይስሐ
ቅም መለሰ ዔሳውንም አለው፥ “እነሆ ጌታህ
አደረግሁት፤ ወንድሞቹንም ሁሉ ለእርሱ ተገ

---

[፩] ዕብ. “የእናትህ” ይላል።

ገሮች አደረግኋቸው፤ እህሉን፥ ወይኑንና ዘይቱንም አበዛሁለት፤ ለአንተ ግን፥ ልጄ ሆይ፥ ምን ላድርግልህ?" ፴፰ዔሳውም አባቱን ይስሐቅን አለው፥ "አባቴ ሆይ፥ በረከትህ አንዲት ብቻ ናትን? አባቴ ሆይ፥ እኔንም ደግሞ ባርከኝ።" ዔሳውም ጮሆ አለቀሰ። ፴፱አባቱ ይስሐቅም መለሰ፤ አለውም፥ "እነሆ መኖሪያህ ከላይ ከሰማይ ጠል፥ ከምድርም ስብ ይሁን፤ ፵በሰይፍህም ትኖራለህ፤ ለወንድምህም ትገዛለህ፤ ነገር ግን ቀንበሩን ከአንገትህ ልትጥል ብትወድድ ከእርሱ ጋር ተስማማ።"[፬]

፵፩ዔሳውም አባቱ ስለ ባረከው በያዕቆብ ቂም ያዘበት፤ ዔሳውም በልቡ አለ፥ "ለአባቴ የልቅሶ ቀን ትቅረብ፤ ወንድሜን ያዕቆብን እገድለዋለሁ።" ፵፪ለርብቃም ታላቁ ልጅዋ ዔሳው ያለው ተነገራት፤ ታናሹን ልጅዋን ያዕቆብንም ልካ ጠራችው፤ አለችውም፥ "እነሆ ወንድምህ ዔሳው ያድድንሃል፤ ሊገድልህም ይፈልጋል። ፵፫አሁንም ልጄ ሆይ፥ ቃሌን ስማ፤ ተነሣና በሶርያ ወንዞች መካከል ወደ ካራን ምድር ወደ ወንድሜ ወደ ላባ ሂድ፤ ፵፬በእርሱም ዘንድ ጥቂት ቀን ተቀመጥ። የወንድምህ ቍጣ ከአንተ እስኪበርድ ድረስ፥ ፵፭ያደረግህበትንም እስኪረሳው ድረስ፤ በአንድ ቀን ሁለታችሁን እንዳላጣ፥ ከዚያም ልኬ አመጣሃለሁ።"

## ይስሐቅ ያዕቆብን ወደ ላባ መላኩ

፵፮ርብቃም ይስሐቅን አለችው፥ "ከኬጢ ሴቶች ልጆች የተነሣ ሕይወቴን ጠላሁት፤ ያዕቆብ ከዚህ ሀገር ሴቶች ልጆች ሚስትን የሚያገባ ከሆነ በሕይወት መኖር ለእኔ ምኔ ነው?"

## ምዕራፍ ፳፰

፩ይስሐቅም ያዕቆብን ጠራው፤ ባረከውም፥ እንዲህም ብሎ አዘዘው፥ "ከከነዓናውያን ሴቶች ልጆች ሚስትን አታግባ፤ ፪ተነሣና ወደ እናትህ አባት ወደ ባቱኤል ቤት ወደ ሁለቱ ወንዞች መካከል ሂድ፤ ከዚያም ከእናትህ ከርብቃ ወንድም ከላባ ሴቶች ልጆች ሚስትን አግባ። ፫አምላኬ[፭] ከአንተ ጋር ይሂድ፤ ከፍ ከፍም ያድርግህ፤ ይባርክህ፤ ያብዛህ፤ ብዙ ሕዝብም ሁን፤ ፬ስደተኛ ሆነህ የተቀመጥህባትን፥ እግዚአብሔር ለአብርሃም የሰጣትን ምድር ትወርስ ዘንድ የአባቴን የአብርሃምን በረከት ለአንተ ይስጥህ፤ ከአንተም በኋላ ለዘርህ።" ፭ይስሐቅም ልጁ ያዕቆብን ላከው፤ እርሱም የያዕቆብና የዔሳው እናት የርብቃ ወንድም የሚሆን የሶርያዊው ባቱኤል ልጅ ላባ ወዳለበት ወደ ሁለቱ ወንዞች መካከል ሄደ።

## ዔሳው ሌላ ሚስት ማግባቱ

፮ዔሳውም ይስሐቅ ያዕቆብን እንደ ባረከው በአየ ጊዜ ከዚያም ሚስትን ያገባ ዘንድ ወደ ሁለቱ የሶርያ ወንዞች መካከል እንደ ላከው፥ በባረከውም ጊዜ፥ "ከከነዓን ሴቶች ልጆች ሚስትን አታግባ" ብሎ እንዳዘዘው፥ ፯ያዕቆብም የአባቱንና የእናቱን ቃል ሰምቶ ወደ ሁለቱ ወንዞች መካከል እንደ ሄደ፥ ፰የከነዓናውያንም ሴቶች ልጆች በአባቱ በይስሐቅ ፊት የተጠሉ እንደ ሆኑ ዔሳው በአየ ጊዜ፥ ፱ዔሳው ወደ ይስማኤል ሄደ፤ ቤሴሞትንም በፊት ካሉ ሚስቶቹ ጋር ሚስት ትሆነው ዘንድ ወሰዳት፤ እርስዋም የናኮር ወንድም የአብርሃም ልጅ የሆነው የይስማኤል ልጅና የናቡዓት እኅት ናት።

## ያዕቆብ በቤቴል ያየው ሕልም

፲ያዕቆብም ከአዘቅተ መሐላ ወጥቶ ወደ ካራን ሄደ። ፲፩ወደ አንድ ስፍራም ደረሰ፤ ፀሐይም ጠልቃ ነበርና በዚያ አደረ፤ ከዚያም ስፍራ ድንጋዮች አንድ ድንጋይ አነሣ፤ ከራሱም በታች ተንተርሶ በዚያ ስፍራ ተኛ። ፲፪ሕልምም አለመ፤ እነሆም መሰላል[፮] በምድር ላይ ተተክሎ፥ ራሱም ወደ ሰማይ ደርሶ፥ እነሆም የእግዚአብሔር መላእክት ይወጡበትና ይወርዱበት ነበር። ፲፫እነሆም፥ እግዚአብሔር በላዩ ቆሞበት ነበር፥ እንዲህም አለ፥ "የአባትህ የአብርሃም አምላክ የይስሐቅም አምላክ እኔ እግዚአብሔር ነኝ፤ አትፍራ፥ ይህችን አንተ የተኛህባትን ምድር ለአንተም ለዘርህም እሰጣለሁ፤ ፲፬ዘርህም እንደ ባሕር አሸዋ ይሆናል፤ እስከ ባሕርና እስከ አዜብ እስከ መስዕና እስከ ምሥራቅ ይበዛል፤ ይሞላልም፤ የምድርም ሕዝቦች ሁሉ በአንተ፥ በዘርህም ይባረካሉ። ፲፭እነሆም፥ እኔ ከአንተ ጋር እሄዳለሁ፤ በምትሄድበትም መንገድ ሁሉ እጠብቅሃለሁ፤ ወደዚያችም ምድር እመልስሃለሁ፤ የነገርሁህን ሁሉ

[፬] ግሪክ ሰባ. ሊ. እና ዕብ. "በተቃወምኸው ጊዜ ቀንበሩን ከአንገትህ ትጥላለህ" ይላል።
[፭] ዕብ. "ሁሉን የሚችል አምላክ" ይላል።
[፮] ግእዙ "ሰዋስወ ወርቅ" ይላል።

እስካደርግልህ ድረስ አልተውህምና።” ፲፮ ያዕቆ
ብም ከእንቅልፉ ተነሥቶ፥ “በእውነት እግዚ
አብሔር በዚህ ስፍራ አለ፤ እኔ አላወቅሁም
ነበር” አለ። ፲፯ ፈራ፤ እንዲህም አለ፥ “ይህ
ስፍራ እንዴት ያስፈራ፤ ይህ ስፍራ የእግዚአብ
ሔር ቤት ነው እንጂ ሌላ አይደለም፤ ይህችም
የሰማይ ደጅ ናት።”
፲፰ ያዕቆብም ማልዶ ተነሣ፤ ተንተርሷት የነ
በረችውንም ድንጋይ ወስዶ ሐውልት አድርጎ
አቆማት፥ በላይዋም ዘይትን አፈሰሰባት። ፲፱ ያዕ
ቆብም ያን ስፍራ ቤቴል ብሎ ጠራው፤ አስቀ
ድሞ ግን የዚያ ከተማ ስም ሎዛ[3] ነበረ። ፳ ያዕ
ቆብም እንዲህ ብሎ ስእለት ተሳለ፥ “እግዚአ
ብሔር ከእኔ ጋር ቢሆን፥ በምሄድባትም በዚች
መንገድ ቢጠብቀኝ፥ የምበላውንም እንጀራ፥
የምለብሰውንም ልብስ ቢሰጠኝ፥ ፳፩ ወደ አባ
ቴም ቤት በጤና ቢመልሰኝ፥ እግዚአብሔር
አምላኬ ይሆንልኛል፤ ፳፪ ለሐውልት ያቆምኋት
ይህችም ድንጋይ የእግዚአብሔር ቤት ትሆንል
ኛለች፤ ከሰጠኸኝም ሁሉ ለአንተ ከዐሥር እጅ
አንዱን እሰጥሃለሁ።”

## ምዕራፍ ፳፱

### ያዕቆብ ወደ ላባ ቤት መድረሱ

፩ ያዕቆብም በማለዳ ተነሥቶ የያዕቆብና የዔ
ሳው እናት የርብቃ ወንድም የሶርያ ሰው የባ
ቱኤል ልጅ ወደሚሆን ወደ ላባ ሄደ። ፪ በተመ
ለከተም ጊዜ በሜዳው እነሆ ጕድጓድን አየ፤
በዚያም ሦስት የበጎች መንጎች በላዩ ተመስ
ገው ነበር፤ ከዚያች ጕድጓድ በጎቹን ያጠጡ
ነበርና፤ በጕድጓድዋም አፍ ታላቅ ድንጋይ ነበ
ረች። ፫ መንጎችም ሁሉ ከዚያ በተሰበሰቡ ጊዜ
እረኞች ድንጋይዋን ከጕድጓዱ አፍ ገለል አድ
ርገው በጎቹን ያጠጡ ነበር፤ ድንጋይዋንም ወደ
ስፍራው መልሰው በጕድጓዱ አፍ እንደገና ይገ
ጥሙት ነበር። ፬ ያዕቆብም፥ “ወንድሞች ሆይ፥
እናንት ከወዴት ናችሁ?” አላቸው። ፭ እነር
ሱም፥ “እኛ ከካራን ነን” አሉት። “የናኮርን
ልጅ ላባን ታውቁታላችሁን?” አላቸው። እነር
ሱም፥ “እናውቀዋለን” አሉት። ፮ “እርሱ ደኅና
ነውን?” አላቸው። እነርሱም፥ “አዎ ደኅና
ነው፤ አሁንም ልጁ ራሔል የአባቷን በጎች
ይዛ ትመጣለች” አሉት። ፯ እርሱም፥ “ቀኑ
ገና ቀትር ነው፥ ከብቶቹ የሚሰበሰቡበት ሰዓ
ቱም ገና አልደረሰም፤ አሁንም በጎቹን አጠ
ጡና ሄዳችሁ አሰማሩአቸው” አላቸው። ፰ እነር
ሱም አሉ፥ “እረኞች ሁሉ ካልተሰበሰቡና ድን
ጋዩቱን ከጕድጓዱ አፍ ካላነሡአት በቀር አን
ችልም፤ ከዚያም በኋላ በጎቹን እናጠጣለን።”
፱ እርሱም ገና ከእነርሱ ጋር ሲነጋገር እነሆ፥
የላባ ልጅ ራሔል የአባትዋን በጎች ይዛ ደረ
ሰች፤ እርስዋ የአባቷን በጎች ትጠብቅ ነበርና።
፲ ያዕቆብም የእናቱን ወንድም የላባን ልጅ ራሔ
ልንና የአጎቱን የላባን በጎች በአየ ጊዜ ቀረበ፤
ከጕድጓዱም አፍ ድንጋዩን አነሣ፤ የአጎቱን
የላባን በጎችም አጠጣ። ፲፩ ያዕቆብም ራሔልን
ሳማት፤ ቃሉንም ከፍ አድርጎ አለቀሰ። ፲፪ ያዕ
ቆብም የአባቷ ዘመድና የርብቃ ልጅ መሆኑን
ለራሔል አስታወቃት፤ እርስዋም ሮጣ ሄዳ ለአ
ባቷ ይህን ነገር ነገረችው።
፲፫ ላባም የእኅቱን የርብቃን ልጅ የያዕቆብን
ስም[4] በሰማ ጊዜ ሊቀበለው ሮጠ፥ አቅፎም
ሳመው፥ ወደ ቤቱም አገባው። ነገሩንም ሁሉ
ለላባ ነገረው። ፲፬ ላባም ያዕቆብን፥ “በእውነት
አንተ አጥንቴ ሥጋዬም ነህ፤ ከእኔ ጋር ተቀ
መጥ” አለው። አንድ ወር የሚያህልም ከእርሱ
ጋር ተቀመጠ።

### ያዕቆብ ስለ ራሔልና ልያ ላባን ማገልገሉ

፲፭ ላባም ያዕቆብን፥ “ወንድሜ ስለሆንህ በከ
ንቱ አታገለግለኝም ደመወዝህ ምንድን ነው?
ንገረኝ” አለው ፲፮ ለላባም ሁለት ሴቶች ልጆች
ነበሩት፤ የታላቂቱ ስም ልያ የታናሺቱም ስም
ራሔል ነበረ። ፲፯ ልያም ዓይነ ልም ነበረች፤
ራሔል ግን መልከ መልካም ነበረች፥ ፊቷም
ውብ ነበረ። ፲፰ ያዕቆብም ራሔልን ወደዳት፤
ያዕቆብም ላባን እንዲህ አለው፥ “ስለ ታና
ሺቱ ልጅህ ስለ ራሔል ሰባት ዓመት እገዛልሃ
ለሁ። ሚስት ትሆነኝ ዘንድ እርስዋን ስጠኝ”[5]
አለው። ፲፱ ላባም፥ “ለሌላ ሰው ከምሰጣት
ይልቅ ለማውቅህ ለዘመዴ ለአንተ ብሰጣት
ይሻላል፤ ከእኔ ጋር ተቀመጥ” አለው። ፳ ያዕቆ
ብም ስለ ራሔል ሰባት ዓመት ተገዛ፤ እርስዋ
ንም ይወድዳት ስለነበረ በእርሱ ዘንድ ጥቂት
ቀን ሆነለት።

---

[3] ግሪክ ሰባ. ሊ. “ኡላምሉዝ” ግእዙ “ወለምሕሳ” ይላል።
[4] ዕብ. “ዜና” ይላል።
[5] “ሚስት ትሆነኝ ዘንድ እርስዋን ስጠኝ” የሚለው በግሪክ ሰባ. ሊ. እና በዕብ. የለም።

፳፩ያዕቆብም ላባን፥ “እንግዲህ ወደ እርስዋ
እገባ ዘንድ ሚስቴን ስጠኝ፥ ቀኔ ተፈጽሞአ
ልና አለው።” ፳፪ላባም የዚያን ስፍራ ሰዎች
ሁሉ ሰበሰበ፥ ሰርግም አደረገ። ፳፫በመሸም ጊዜ
ልጁን ልያን ወስዶ ወደ ያዕቆብ አስገባት፤ ያዕ
ቆብም ወደ እርስዋ ገባ። ፳፬ላባም ለልጁ ልያ
አገልጋዩቱን ዘለፋን አገልጋይ ትሆናት ዘንድ
ሰጣት። ፳፭በነጋም ጊዜ እነሆ ልያ ነበረች፤ ያዕ
ቆብም ላባን፥ “ምነው እንደዚህ አደረግህብኝ?
ያገለገልሁህ ስለ ራሔል አልነበረምን? ለምን
አታለልኸኝ?” አለው። ፳፮ላባም እንዲህ አለ፥
“በሀገራችን ታላቂቱ ሳለች፥ ታናሺቱን እንሰጥ
ዘንድ ወግ አይደለም፤ ፳፯ለዚችም ሰባት ዓመት
ፈጽም፤ ሌላ ሰባት ዓመት ደግሞ እኔን ስለም
ታገለግለኝ አገልግሎት እርስዋን ደግሞ እሰጥሃ
ለሁ።” ፳፰ያዕቆብም እንዲህ አደረገ፤ ለዚችም
ሰባት ዓመት ፈጸመ፤ ልጁን ራሔልንም ለእ
ርሱ ሚስት ትሆነው ዘንድ ሰጠው። ፳፱ላባም
ለልጁ ለራሔል አገልጋዩቱን ባላን አገልጋይ
ትሆናት ዘንድ ሰጣት። ፴ያዕቆብም ወደ ራሔል
ደግሞ ገባ። ራሔልንም ከልያ ይልቅ ወደዳት፤
ሌላ ሰባት ዓመትም ተገዛለት።

## ለያዕቆብ የተወለዱ ልጆች

፴፩እግዚአብሔርም ልያ የተጠላች መሆንዋን
በአየ ጊዜ ማኅፀንዋን ከፈተላት፤ ራሔል ግን
መካን ነበረች። ፴፪ልያም ፀነሰች፤ ወንድ ልጅንም
ወለደች፥ ስሙንም ሮቤል ብላ ጠራችው፥ “እግ
ዚአብሔር መዋረዴን አይቶአልና፥ እንግዲህስ
ወዲህ ባሌ ይወድደኛል” ስትል። ፴፫ልያም ዳግ
መኛ ፀነሰች፤ ሁለተኛ ወንድ ልጅንም ለያዕቆብ
ወለደችለት፤ “እኔ እንደ ተጠላሁ እግዚአብሔር
ስለ ሰማ ይህን ጨመረልኝ” አለች፤ ስሙንም
ስምዖን ብላ ጠራችው ። ፴፬ደግሞም ፀነሰች፤
ወንድ ልጅንም ወለደች፤ “ከእንግዲህ ወዲህስ
ባሌ ወደ እኔ ይጠጋል፤ ሦስት ወንዶች ልጆችን
ወልጄለታለሁና” አለች፤ ስለዚህም ስሙን ሌዊ
ብላ ጠራችው። ፴፭ደግሞም ፀነሰች፤ ወንድ ልጅ
ንም ወለደች፤ በዚህም ጊዜ “እግዚአብሔርን
አመሰግናለሁ” አለች፤ ስለዚህም ስሙን ይሁዳ
ብላ ጠራችው። መውለድንም አቆመች።

## ምዕራፍ ፴

፩ራሔልም ለያዕቆብ ልጅ እንዳልወለደች በአ
የች ጊዜ በእኅቷ ላይ ቀናችባት፤ ያዕቆብንም
“ልጅ ስጠኝ፤ ይህስ ከአልሆነ እሞታለሁ” አለ
ችው። ፪ያዕቆብም፥ “የማኅፀንሽን ፍሬ የምከ
ለክልሽ እኔ እንደ እግዚአብሔር ነኝን?” ብሎ
ራሔልን ተቈጣት። ፫እርስዋም፥ “ባሪያዬ ባላ
እነሆ አለች፤ ወደ እርስዋ ግባ፤ በእኔም ጭን
ላይ ትውለድ፤ የእርስዋም ልጆች ለእኔ ደግሞ
ይሁኑልኝ” አለች። ፬አገልጋይዋን ባላንም
ሚስት ትሆነው ዘንድ ለእርሱ ሰጠችው፤ ያዕ
ቆብም ወደ እርስዋ ገባ። ፭የራሔል አገልጋይ
ባላም ፀነሰች፤ ወንድ ልጅንም ለያዕቆብ ወለ
ደችለት። ፮ራሔልም፥ “እግዚአብሔር ፈረደ
ልኝ፤ ቃሌንም ደግሞ ሰማ፤ ወንድ ልጅንም
ሰጠኝ” አለች፤ ስለዚህ ስሙን ዳን ብላ ጠራ
ችው። ፯የራሔልም አገልጋይ ባላ ደግማ ፀነ
ሰች፤ ለያዕቆብም ሁለተኛ ወንድ ልጅን ወለ
ደች። ፰ራሔልም፥ “እግዚአብሔር ከፍ ከፍ
አደረገኝ፤ ብርቱ ትግልንም ከእኅቴ ጋር ታገ
ልሁ፤ አሸነፍሁም፤ እኅቴንም መሰልኋት”
አለች፤ ስሙንም ንፍታሌም ብላ ጠራችው።
፱ልያም መውለድን እንዳቆመች በአየች ጊዜ
አገልጋይዋን ዘለፋን ወሰደች፤ ሚስት ትሆነ
ውም ዘንድ ለያዕቆብ ሰጠችው፤ ያዕቆብም
ወደ እርስዋ ገባ።[፩] ፲የልያ አገልጋይ ዘለፋም
ፀነሰች፤ ወንድ ልጅንም ለያዕቆብ ወለደች።
፲፩ልያም፥ “እኔም ራሴን ብፅዕት አሰኘሁ”
ስትል ስሙን ጋድ ብላ ጠራችው። ፲፪የልያ አገ
ልጋይ ዘለፋም ዳግመኛ ለያዕቆብ ወንድ ልጅን
ወለደች። ፲፫ልያም፥ “እኔ ብፅዕት ነኝ፤ ሴቶች
ያመሰግኑኛልና” አለች፤ ስሙንም አሴር ብላ
ጠራችው።
፲፬ሮቤል ስንዴ በሚታጨድበት ወራት ወጣ፤
በእርሻም እንኮይ አገኘ፥ ለእናቱ ለልያም አመ
ጣላት። ራሔልም ልያን፥ “የልጅሽን እንኮይ
ስጪኝ” አለቻት። ፲፭ልያም፥ “ባሌን መውሰ
ድሽ አይበቃሽምን? አሁን ደግሞ የልጄን እን
ኮይ ልትወስጂ ትፈልጊያለሽን?” አለቻት።
ራሔልም “እንኪያስ ስለ ልጅሽ እንኮይ በዚ
ህች ሌሊት ከአንቺ ጋር ይደር” አለች፤ ሰጠቻ
ትም። ፲፮ያዕቆብም ሲመሽ ከዱር ገባ፤ ልያም
ልትቀበለው ወጣች፤ እንዲህም አለችው፥
“እኔ ዘንድ ታድራለህ፤ በልጄ እንኮይ በእር
ግጥ ተስማምቼሃለሁና።” ፲፯በዚያችም ሌሊት
ከእርስዋ ጋር አደረ። እግዚአብሔርም የል
ያን ጸሎት ሰማ፤ ፀነሰችም፤ አምስተኛ ወንድ
ልጅንም ለያዕቆብ ወለደች። ፲፰ልያም፥ “የል

---

፩ “ያዕቆብም ወደ እርስዋ ገባ” በግሪክ ሰባ. ሊ. ብቻ።

ጀን እንኮይ[፬] ስለ ሰጠሁ እግዚአብሔር ዋጋ
ዬን ሰጠኝ" አለች፤ ስሙንም ይሳኮር ብላ
ጠራችው። ፲፱ልያም ደግማ ፀነሰች፤ ስድስተኛ
ወንድ ልጅንም ለያዕቆብ ወለደች። ፳ልያም፥
"እግዚአብሔር መልካም ስጦታን ሰጠኝ፤ እን
ግዲህስ ከዛሬ ጀምሮ ባሌ ይወደድኛል[፭] ስድ
ስት ልጆችን ወልጄለታለሁና" አለች፤ ስሙ
ንም ዛብሎን ብላ ጠራችው። ፳፩ከዚያም በኋላ
ሴት ልጅን ወለደች፤ ስምዋንም ዲና አለቻት።
፳፪እግዚአብሔርም ራሔልን አሰባት፤ እግዚአብ
ሔርም ተለመናት፤ ማኅፀንዋንም ከፈተላት፤
ፀነሰችም፤ ፳፫ወንድ ልጅንም ለያዕቆብ ወለደ
ችና፥ "እግዚአብሔር ሽሙጤን ከእኔ አስወ
ገደ" አለች፤ ፳፬ስሙንም፥ "እግዚአብሔር ሁለ
ተኛ ወንድ ልጅን ይጨምርልኝ" ስትል ዮሴፍ
ብላ ጠራችው።

### ያዕቆብ ስለ ደመወዝ ከላባ ጋር መከራከሩ

፳፭ራሔልም ዮሴፍን ከወለደች በኋላ ያዕቆብ
ላባን እንዲህ አለው፥ "ወደ ስፍራዬ፥ ወደ ሀገ
ሬም እመለስ ዘንድ አሰናብተኝ። ፳፮ስለ እነርሱ
የተገዛሁላቸውን ሚስቶቼንና ልጆችን ስጠኝና
ልሂድ፤ የተገዛሁልህን መገዛት ታውቃለህና።"
፳፯ላባም፤ "በዐይንህ ፊት ሞገስን የማገኝ ብሆንስ
ከዚሁ ተቀመጥ፤ እግዚአብሔር በአንተ ምክንያት
እንደ ባረከኝ ተመልክቼአለሁና። ፳፰ደመወዝህን
ንገረኝ፤ እርሱንም እሰጥሃለሁ" አለው። ፳፱ያዕ
ቆብም አለው፥ "እንዴት እንዳገለገልሁህ፥ በእኔ
ዘንድ ያሉ ከብቶችህ ምን ያህል እንደ ሆኑ አታው
ቅምን? ጥቂት ሆነው አግኝቻቸዋለሁና፤ ፴አሁን
ግን ፈጽመው በዝተዋል፤ እግዚአብሔርም በእኔ
መምጣት ባርኮአቸዋል፤ አሁን ደግሞ ለቤቴ የም
ሠራው መቼ ነው?" ፴፩ላባም፥ "የምሰጥህ ምን
ድን ነው?" አለው። ያዕቆብም አለው፤ "ምንም
አትስጠኝ፤ ይህንም ነገር ብታደርግልኝ እንደገና
በጎችህን አሰማራለሁ፤ እጠብቃለሁም። ፴፪ዛሬ በጎ
ችህ ሁሉ ይለፉ፤[፮] በዚያም ከበጎችህ መካከል ዝን
ጕርጕርና ነቍጣ ያለበትን ጥቁሩንም በግ ሁሉ፥
ከፍየሎቹም ነቍጣና ዝንጕርጕር ያለበትን ለይ
ልኝ፤[፯] እነርሱም ደመወዜ ይሆናሉ። ፴፫ስለዚህም
በፊትህ ያለውን ደመወዜን ለመመልከት በመጣህ
ጊዜ ወደፊት ጻድቅነቴን ይመሰክርልኛል፤ ከፍየ
ሎች ዝንጕርጕርና ነቍጣ የሌለበት፥ ከበግ ጠቦ
ቶችም ጥቁር ያልሆኑ ሁሉ፥ እርሱ በእኔ ዘንድ
ቢገኝ እንደ ተሰረቀ ይቈጠርብኝ።"[፰] ፴፬ላባም፥
"እነሆ እንደ ቃልህ ይሁን" አለ። ፴፭በዚያም ቀን
ከተባቶቹ ፍየሎች ሽመልመሌ መሳይና ነቍጣ
ያለባቸውን፥ ከእንስቶቹ ፍየሎች ዝንጕርጕርና
ነቍጣ ያለባቸውን፥ ነጭ ያለበትን ማንኛውንም
ሁሉ፥ ከበጎቹም መካከል ጥቁሩን በግ ሁሉ ለይቶ
ለልጆቹ ሰጣቸው። ፴፮በእርሱና በያዕቆብ መካከ
ልም የሦስት ቀን መንገድ ያህል አራቃቸው፤
ያዕቆብም የቀሩትን የላባን በጎች ይጠብቅ ነበር።
፴፯ያዕቆብም ልብን፥ ለውዝ፥ ኤርሞን ከሚባሉ
ዕንጨቶች ርጥብ በትርን ወስዶ በበትሮቹ ውስጥ
ያለው ነጭ እንዲታይ ነጭ ሽመልመሌ አድርጎ
ላጣቸው። ፴፰በጎቹም ውኃ ሊጠጡ በመጡ ጊዜ
በትሮቹ በፊታቸው ይሆኑ ዘንድ የላጣቸውን በት
ሮች በውኃ ማጠጫ ገንዳው ውስጥ አኖራቸው፤
፴፱በጎቹም መጥተው በጠጡ ጊዜ ሽመልመሌ መሳ
ይና ዝንጕርጕር፥ ነቍጣም ያለበትን በበትሮቹ
አምሳል ፀነሱ። ፵ያዕቆብም ተባት በጎችንና እንስት
በጎችን ለይቶ ነጭና ሐመደ ክቦ በሆኑ አውራዎች
ፊት አቆማቸው፤[፱] መንጎቹንም ለብቻቸው አቆ
ማቸው። ከላባ በጎች ጋርም አልጨመራቸውም።
፵፩እንዲህም ሆነ፦ በጎቹ በሚፀንሱበት ወራት በበ
ትሮቹ አምሳል ይፀንሱ ዘንድ ያዕቆብ በትሮቹን
በበጎቹ ፊት በውኃ ማጠጫ ገንዳው ውስጥ ያኖራ
ቸው ነበር። ፵፪በጎችም ከወለዱ በኋላ በፊታቸው
በትሩን አያደርገውም ነበር፤ ምልክት ያላቸው ለያ
ዕቆብ፥ ምልክት የሌላቸውም ለላባ ሆኑ። ፵፫ያዕ
ቆብም እጅግ ባለጠጋ ሆነ፤ ሴቶችም ወንዶችም
አገልጋዮች፥ ብዙ ከብትም፤ ላሞችም፤ በጎችም፥
ግመሎችና አህዮችም ሆኑለት።

## ምዕራፍ ፴፩

### ያዕቆብ ከላባ መሸሹ

፩ያዕቆብም የላባ ልጆች ያሉትን ነገር፥ "ያዕ
ቆብ ለአባታችን የሆነውን ሁሉ ወሰደ፤ ይህንም

---

፬ ግሪክ ሰባ. ሊ. እና ዕብ. "ባሪያዬን ለባሌ" ይላል።
፭ ዕብ. "ባሌ ከእኔ ጋር ይኖራል" ይላል።
፮ ዕብ. "በመንጎችህ በኩል አልፋለሁ" ይላል።
፯ ዕብ. "እለያለሁ" ይላል።
፰ ምዕ. ፴ ቍ. ፴፫ በግእዙ "ዝንጕርጕር ያልሆነው፥ መልኩም ነጭ ያልሆነው ሁሉ እርሱ ለአንተ ይሁን" ይላል።
፱ ግሪክ ሰባ. ሊ. " አውራዎቹን በእንስቶቹ በጎች ፊት አቆመ" ይላል።

ሁሉ ክብር ከአባታችን ከብት አገኘ” ሲሉ
ሰማ። ፪ያዕቆብም የላባን ፊት አየ፤ እነሆም፥
ከእርሱ ጋር እንደ ዱሮው አልሆነም። ፫እግዚአ
ብሔርም ያዕቆብን፥ “ወደ አባትህና ወደ ዘመ
ዶችህ ሀገር ተመለስ፤ እኔም ከአንተ ጋር እሆና
ለሁ” አለው። ፬ያዕቆብም ልኮ ራሔልንና ልያን
ወደ በጎቹ መሰማሪያ ወደ ሜዳ ጠራቸው፤
፭እንዲህም አላቸው፥ “እነሆ፥ የአባታችሁ ፊት
እንደ ዱሮ ከእኔ ጋር እንዳልሆነ አያለሁ፤ ነገር
ግን የአባቴ አምላክ ከእኔ ጋር ነው። ፮እኔ ባለኝ
ጕልበቴ ሁሉ አባታችሁን እንዳገለገልሁ ታውቃ
ላችሁ። ፯አባታችሁ ግን አሳዘነኝ፥ ደመወዜንም
ዐሥር ጊዜ[፩] ለወጠ፤ እግዚአብሔር ግን ክፉን
ያደርግብኝ ዘንድ አልፈቀደለትም። ፰ደመወዝህ
ዝንጕርጕሮቹ ይሁኑ ቢለኝ በጎቹ ሁሉ ዝንጕ
ርጕሮችን ወለዱ፤ ነጫጮቹ ደመወዝህ ይሁኑ
ቢለኝ በጎቹ ሁሉ ነጫጮችን ወለዱ። ፱እግ
ዚአብሔርም የአባታችሁን በጎች ሁሉ ነሥቶ
ለእኔ ሰጠኝ። ፲እንዲህም ሆነ፤ በጎቹ በሚፀ
ንሱ ጊዜ ዐይኔን አንሥቼ በሕልም አየሁ፤ እነ
ሆም፥ በበጎችና በፍየሎች ላይ የሚንጠላጠሉት
የበጎችና የፍየሎች አውራዎች ነጭ፥ ዝንጕርጕ
ሮችና ሐመደ ክቦ ነበሩ። ፲፩እግዚአብሔርም[፪]
በሕልም፦ ‘ያዕቆብ ያዕቆብ’ አለኝ፤ እኔም፦
‘እነሆኝ ምንድን ነው?’ አልሁት። ፲፪እንዲህም
አለኝ፦ ዐይንህን አቅንተህ እይ፤ በበጎችና በፍ
የሎች ላይ የሚንጠላጠሉት የበጎችና የፍየሎች
አውራዎች ነጭ፥ ሐመደ ክቦና ዝንጕርጕሮች
ናቸው፤ ላባ በአንተ ላይ የሚያደርገውን አይ
ቻለሁና። ፲፫ሐውልቱን ዘይት በቀባህባት፥ በዚ
ያች ለእኔ ስእለት በተሳልህባት ሀገር የተገለጥ
ሁልህ ፈጣሪህ እግዚአብሔር እኔ ነኝ። አሁንም
ተነሥተህ ከዚህ ሀገር ውጣ፤ ወደ ተወለድህባ
ትም ምድር ተመለስ፤ እኔም ከአንተ ጋር እኖ
ራለሁ።” ፲፬ራሔልና ልያም መልሰው እንዲህ
አሉት፥ “በአባታችን ቤት ለእኛ ድርሻ ወይም
ርስት በውኑ አለን? ፲፭እኛ በእርሱ ዘንድ እንደ
ባዕድ የተቈጠርን አይደለምን? እርሱ እኛን
ሸጦ ዋጋችንን በልቶአልና። ፲፮ስለዚህም እግዚ
አብሔር ከአባታችን የነሣው ይህ ሁሉ ሀብትና
ክብር ለእኛና ለልጆቻችን ነው፤ አሁንም እግ
ዚአብሔር ያለህን ሁሉ አድርግ።”

፲፯ያዕቆብም ተነሣ፤ ልጆቹንና ሚስቶቹንም
በግመሎች ላይ አስቀመጠ። ፲፰መንጎቹንም
ሁሉ፥ የቤቱንም ዕቃ ሁሉ፥ በሁለቱ ወንዞች
መካከል ሳለ ያገኛቸውን ከብቶች ሁሉ ይዞ
ወደ አባቱ ወደ ይስሐቅ ወደ ከነዓን ምድር
ሄደ። ፲፱ላባ ግን በጎቹን ለመሸለት ሄዶ ነበር፤
ራሔልም የአባቷን ጣዖቶች ሰረቀች። ፳ያዕቆ
ብም ነገሩን ከሶርያዊው ከላባ ሰወረ፤ እንደሚሄ
ድም አልነገረውም። ፳፩እርሱም ያለውን ሁሉ
ይዞ ኰበለለ፤ ተነሥቶም ወንዙን ተሻገረ፤ በገ
ለዓድ ተራራም አደረ።

## ላባ ያዕቆብን መከታተሉ

፳፪ለሶርያዊው ላባም ያዕቆብ እንደ ኰበለለ ነገ
ሩት። ፳፫ላባም ወንድሞቹን ሁሉ ይዞ የሦስት
ቀን መንገድ ተከተላቸው፤ በገለዓድ ተራራም
ላይ አገኛቸው።[፫] ፳፬እግዚአብሔርም ወደ ሶርያ
ዊው ወደ ላባ በሌሊት በሕልም መጥቶ፥ “በባ
ሪያዬ በያዕቆብ ላይ ክፉ ነገር እንዳትናገር ተጠ
ንቀቅ” አለው። ፳፭ላባም ያዕቆብን አገኘው፤ ያዕ
ቆብም ድንኳኑን በተራራው ላይ ተክሎ ነበር፤
ላባም ወንድሞቹን በገለዓድ ተራራ አስቀመጣ
ቸው። ፳፮ላባም ያዕቆብን አለው፥ “ለምን እን
ዲህ አደረግህ? ከእኔ በስውር የኰበለልህ? ልጆ
ችንስ ሰርቀህ በሰይፍ እንደማረከ የወሰድኻቸው?
፳፯ብትነግረኝ ኑሮ በደስታና በሐሴት፥ በዘፈን፥
በከበሮና በበገና በሸኘሁህ ነበር። ፳፰ወይስ ወን
ዶቹንና ሴቶቹን ልጆችን እስም ዘንድ አይገባኝ
ምን? አሁንም ይህን እንደ አላዋቂ አደረግህ።
፳፱አሁንም በአንተ ላይ ክፉ ማድረግ በቻልሁ
ነበር፤ ነገር ግን የአባትህ አምላክ ትናንት፦ በያ
ዕቆብ ላይ ክፉ እንዳታደርግ ተጠንቀቅ ብሎ ነገ
ረኝ። ፴አሁንም የአባትህን ቤት ከናፈቅህ ሂድ፤
ነገር ግን አምላኮቼን ለምን ሰረቅህ?” ፴፩ያዕቆ
ብም መለሰ፤ ላባንም እንዲህ አለው፥ “ልጆች
ህንና ገንዘቤን ሁሉ ከእኔ የምትቀማኝ ስለመ
ሰለኝና ስለፈራሁ ይህን አደረግሁ።” ፴፪ያዕቆ
ብም አለ፥ “አምላኮችህን የምታገኝበት ሰው
ግን እርሱ ይሙት፤ ገንዘብህም በእኔ ዘንድ
ካለ በወንድሞቻችን ፊት እይ፤ ለአንተም ውሰ
ደው” አለ። ያዕቆብ ሚስቱ ራሔል እንደ ሰረ
ቀቻቸው አያውቅም ነበርና።

---

፩ ግሪክ ሰባ. ሊ. “ደመወዜን በዐሥር በጎች ዋጋ ለወጠብኝ” ይላል።

፪ ዕብ. “የእግዚአብሔር መልአክ” ይላል።

፫ ምዕ. ፴፩ ቍ. ፳፪ በዕብ. እና በግሪክ ሰባ ሊ. “በሦስተኛው ቀን የያዕቆብ መኰብለል ለላባ ተነገረው” ሲል ቍ.
፳፫ “ከወንድሞቹም ጋር ሆኖ የሰባት ቀን ያህል መንገድ ተከተለው” ይላል።

፴፫ላባም ወደ ያዕቆብ ድንኳንና ወደ ልያም
ድንኳን ገባና በረበረ፤ አላገኘምም፤ ከዚያም
ወጣና ወደ ሁለቱ ዕቁባቶቹ ድንኳን ገባ፤ ነገር
ግን አላገኘም። ወደ ራሔልም ድንኳን ገባ።
፴፬ራሔልም የአባቷን ጣዖቶች ወስዳ ከግመል
ኮርቻ በታች ሸሸገች፤ በላዩም ተቀመጠችበት።
ላባም ድንኳኑን ሁሉ ፈለገ፤ አንዳችም አላገ
ኘም። ፴፭እርስዋም አባቷን፥ "ጌታዬ በፊትህ
ለመቆም ስላልቻልሁ የአቀለልሁህ አይምሰ
ልህ፤ በሴቶች የሚደርስ ግዳጅ ደርሶብኛልና"
አለችው። ላባም የራሔልን ድንኳን በረበረ፤
ነገር ግን ጣዖቶቹን አላገኘም።

፴፮ያዕቆብም ተቈጣ፤ ላባንም ወቀሰው፤ ያዕ
ቆብም መለሰ፤ ላባንም እንዲህ አለው፥ "የበ
ደልሁህ በደል ምንድን ነው? ኀጢአቴስ ምን
ድን ነው? ይህን ያህል ያሳደድኸኝ? ፴፯አሁ
ንም ዕቃዬን ሁሉ በረበርህ፤ ከቤትህስ ዕቃ
ሁሉ ምን አገኘህ? እነርሱ በእኛ በሁለታችን
መካከል ይፈርዱ ዘንድ በወንድሞችና በወንድ
ሞችህ ፊት አቅርበው። ፴፰ሃያ አንድ ዓመት
በጎችህንና ፍየሎችህን ስጠብቅ ኖርሁ፥[፬] ከበጎ
ችህም ጠቦቶችን አልበላሁም፤ ፴፱አውሬ የሰበ
ረውንም አላመጣሁልህም ነበር፤ በቀንም ሆነ
በሌሊት የተሰረቀ ቢኖር ከእኔ እከፍልህ ነበር።
፵የቀን ሐሩር፥ የሌሊት ቍር ይበላኝ ነበር፤ ዕን
ቅልፍም ከዐይኔ ጠፋ። ፵፩ለአንተ ቤት የተገዛሁ
ልህ ዛሬ ሃያ አንድ ዓመት ነው፤ ዐሥራ አራት
ዓመት ስለ ሁለቱ ሴቶች ልጆችህ፥ ሰባት[፭]
ዓመት ስለ በጎችህ ተገዛሁልህ፤ ደመወዜንም
ዐሥር ጊዜ ለዋወጥኸው። ፵፪የአባቴ የአብርሃም
አምላክ የይስሐቅም ፍርሀት ከእኔ ጋር ባይሆ
ንስ ዛሬ ባዶ እጄን በሰደድኸኝ ነበር፤ እግዚአ
ብሔር መዋረዴንና የእጆችን ድካም አየ፤ ትና
ንትም ገሠጸህ።"

## የያዕቆብና የላባ ስምምነት

፵፫ላባም ለያዕቆብ እንዲህ ብሎ መለሰለት፥
"ሴቶቹ ልጆች ልጆች ናቸው፤ ወንዶቹም
ልጆች ልጆች ናቸው፤ መንጎቹም ከብቶች
ናቸው፤ ይህ የምታየው ሁሉ የእኔ ነው፤ የል
ጆችም ሀብት ነው፤ ዛሬም በእነዚህ በሴቶች
ልጆችና በወለዱአቸው ልጆቻቸው ላይ ምን
አደርጋለሁ? ፵፬አሁንም ና፤ አንተና እኔ ቃል
ኪዳን እንጋባ፤ በእኔና በአንተ መካከል ምስክር
ይሁን።" ፵፭ያዕቆብም ድንጋይ ወስዶ ሐውልት
አቆመ። ፵፮ያዕቆብም ወንድሞቹን፥ "ድንጋይ
ሰብስቡ" አላቸው፤ እነርሱም ድንጋይ ሰብስ
በው ከመሩ፤ በድንጋዩም ክምር ላይ በሉ።
፵፯ላባም፥ "ይህች የድንጋይ ክምር በእኔና በአ
ንተ መካከል ምስክር ትሁን" አለው። ላባም
"ወግረ ስምዕ" ብሎ ጠራት፤ ያዕቆብም እን
ዲሁ አላት። ፵፰ላባም፥ "ይህች ያቆምኋት የድ
ንጋይ ክምር በእኔና በአንተ መካከል ዛሬ ምስ
ክር ናት" አለ። ስለዚህም ስምዋ ወግረ ስምዕ
ተባለ። ፵፱ላባም አለው፥ "እኛ አንዳችን ከሌ
ላው እንለያያለንና ራእይን የገለጠልኝ እግዚአብ
ሔር በእኔና በአንተ መካከል ሆኖ ይመልከት።
፶ልጆችን ብትበድላቸው ወይም በላያቸው ላይ
ሚስቶችን ብታገባባቸው እነሆ፥ ከእኛ ጋር ያለ
ሰው እንደሌለ አስተውል፤ እግዚአብሔር በእ
ኔና በአንተ መካከል ምስክር ነው።" ፶፩ላባም
ያዕቆብን አለው፥ "እነሆ፥ ይህች የድንጋይ
ክምርና ይህችም ሐውልት ምስክሮች ናቸው።
፶፪እኔ ወደ አንተ በክፋት ባልፍ ይህች የድንጋይ
ክምር፥ ይህችም ሐውልት በክፉ ነገር ትከተ
ለኝ። ፶፫አንተም ወደ እኔ ብታልፍ የአብርሃም
አምላክ የናኮርም አምላክ በእኛ መካከል ይፍ
ረድ።" ያዕቆብም በአባቱ በይስሐቅ አምላክ
ማለ። ፶፬ያዕቆብም በተራራው ላይ መሥዋዕትን
ሠዋ፤ ወንድሞቹንም ጠራ፤ እነርሱም በሉ፤
ጠጡም፤ በዚያም በተራራው አደሩ። ፶፭ላባም
ማልዶ ተነሥቶ ወንዶችንና ሴቶችን ልጆቹን
ሳመ፤ ባረካቸውም፤ ላባም ተመልሶ ወደ ስፍ
ራው ሄደ።

## ምዕራፍ ፴፪

## ያዕቆብ ላባን ለመገናኘት እንደ ተዘጋጀ

፩ያዕቆብም መንገዱን ሄደ፤ በዐይኖቹም የእግ
ዚአብሔርን ሠራዊት ከትመው አየ፤ የእግዚአ
ብሔር መላእክትም ተገናኙት። ፪ያዕቆብም በአ
ያቸው ጊዜ፥ "እነዚህ የእግዚአብሔር ሠራዊት
ናቸው" አለ፤ የዚያንም ስፍራ ስም "ተዓ
ይን" ብሎ ጠራው።
፫ያዕቆብም ወደ ወንድሙ ወደ ዔሳው ወደ
ሴይር ምድር ወደ ኤዶም ሀገር በፊቱ መል
እክተኞችን ላከ፤ ፬እንዲህም ብሎ አዘዛቸው፥
"ለጌታዬ ለዔሳው፡- ባሪያህ ያዕቆብ እንዲህ

---

[፬] ግሪክ ሰባ. ሊ. ዕብ. "ሃያ ዓመት ሙሉ ከአንተ ጋር ነበርሁ እንስት በጎችህና ፍየሎችህም አልጨነገፉም" ይላል።
[፭] ግሪክ ሰባ. ሊ. "ስድስት" ይላል።

አለ ብላችሁ ንገሩት፡- በላባ ዘንድ በስደት
ተቀመጥሁ፤ እስከ ዛሬ ድረስ ቈየሁ፤ ፭ላሞች
ንም፥ ግመሎችንም፥ አህዮችንም፥ በጎችንም፥
ወንዶች አገልጋዮችንም፥ ሴቶች አገልጋዮች
ንም አገኘሁ፤ አሁንም በፊትህ ሞገስን አገኝ
ዘንድ ለጌታዬ ለዔሳው ለመንገር ላክሁ።” ፮የላ
ካቸው መልእክተኞችም ወደ ያዕቆብ ተመል
ሰው እንዲህ አሉት፤ “ወደ ወንድምህ ወደ
ዔሳው ሄደን ነበር፤ እርሱም ደግሞ ሊቀበልህ
ይመጣል፤ ከእርሱም ጋር አራት መቶ ሰዎች
አሉ።” ፯ያዕቆብም እጅግ ፈራ፤ የሚያደርገው
ንም አጣ። ከእርሱም ጋር ያሉትን ሰዎች ላሞ
ችንም፥ ግመሎችንም፥ በጎችንም ሁለት ወገን
አድርጎ ከፈላቸው፤ ፰ያዕቆብም እንዲህ አለ፥
“ዔሳው መጥቶ አንዱን ወገን የመታ እንደ
ሆነ የቀረው ወገን ይድናል።” ፱ያዕቆብም አለ፥
“የአባቴ የአብርሃም አምላክ ሆይ፥ የአባቴ የይ
ስሐቅ አምላክ ሆይ፥ ‘ወደ ምድርህ ወደ ተወ
ለድህበትም ስፍራ ተመለስ፤ በጎነትንም አደር
ግልሃለሁ’ ያልኸኝ እግዚአብሔር ሆይ፥ ፲ለባሪ
ያህ በአደረግኸው በምሕረትህና በእውነትህም
ሁሉ በጎውን አድርግልኝ፤ በትሬን ብቻ ይዤ
ይህን ዮርዳኖስን ተሻግሬ ነበርና፥ አሁን ግን
የሁለት ክፍል ሠራዊት ሆንሁ። ፲፩አቤቱ ከወ
ንድሜ ከዔሳው እጅ አድነኝ፤ መጥቶ እንዳያ
ጠፋኝ፥ እናትን[፩] ከልጆችዋ ጋር እንዳያጠፋ
እኔ እፈራዋለሁና። ፲፪አንተም፡- ‘በርግጥ መል
ካም አደርግልሃለሁ፥ ዘርህንም ከብዛቱ የተነሣ
እንደማይቈጠር እንደ ባሕር አሸዋ አደርጋለሁ
ብለህ ነበር።’ ”

፲፫በዚያችም ሌሊት በዚያው አደረ። ለወን
ድሙ ለዔሳውም የሚወስደውን እጅ መንሻ
አወጣ፤ ፲፬ሁለት መቶ እንስት ፍየሎችንና ሃያ
የፍየል አውራዎችን፥ ሁለት መቶ እንስት በጎ
ችንና ሃያ የበግ አውራዎችን፥ ፲፭ሃምሳ[፪] የሚያ
ጠቡ ግመሎችን ከግልገሎቻቸው ጋር፥ አርባ
ላም፥ ዐሥር በሬ፥ ሃያ እንስት አህያ፥ ዐሥ
ርም የአህያ ውርንጫዎች፤ ፲፮መንጎቹንም ለየ
ብቻ ከፍሎ ለብላቴኖቹ ሰጣቸው፤ ብላቴኖቹ
ንም፥ “በፊቴ እለፉ፤ መንጋውን ከመንጋው
አርቁ” አላቸው።

፲፯የፊተኛውንም እንዲህ ብሎ አዘዘው፥ “ወን
ድሜ ዔሳው ያገኘህ እንደ ሆነ፡- ‘አንተ የማን
ነህ? ወዴትስ ትሄዳለህ? በፊትህ ያለው ይህስ
መንጋ የማን ነው?’ ብሎ የጠየቀህም እንደ
ሆነ፥ ፲፰በዚያ ጊዜ አንተ፡- ‘ለጌታዬ ለዔሳው
እጅ መንሻ የላከው የአገልጋይህ የያዕቆብ ነው፤
እርሱም ደግሞ እነሆ ከኋላችን ተከትሎናል’
በለው።” ፲፱እንዲሁም ሁለተኛውንና ሦስተኛ
ውን፥ በፊቱ የሚሄዱትንና መንጋውን የሚነ
ዱትን ሁሉ እንዲሁ ብሎ አዘዘ፡-“ ወንድሜ
ዔሳውን ባገኛችሁት ጊዜ ይህንኑ ነገር ንገሩት፤
፳እንዲህም በሉ፡- እነሆ አገልጋይህ ያዕቆብ ከኋ
ላችን ነው። በፊቴ በሚሄደው እጅ መንሻ እታ
ረቀዋለሁ፤ ከዚያም በኋላ ምናልባት ይራራል
ኛል፤ ፊቱንም አያለሁ ብሎአልና።” ፳፩እጅ
መንሻውን ከእርሱ አስቀድሞ ላከ፤ እርሱ ግን
በዚያች ሌሊት በሰፈር አደረ።

## የያዕቆብ ትግል

፳፪በዚያችም ሌሊት ተነሣ፥ ሁለቱን ሚስ
ቶቹንና ሁለቱን ዕቁባቶቹን ዐሥራ አንዱንም
ልጆቹን ይዞ የያቦቅን ወንዝ ተሻገረ። ፳፫ወሰዳ
ቸውም፤ ወንዙንም አሻገራቸው፤ ገንዘቡንም
ሁሉ አሻገረ። ፳፬ያዕቆብ ግን ለብቻው ቀረ፤
አንድ ሰውም እስከ ንጋት ድረስ ይታገለው
ነበር። ፳፭እንዳላሸነፈውም ባየ ጊዜ የጭኑን
ሹልዳ ያዘው፤ የያዕቆብም የጭኑ ሹልዳ ሲታገ
ለው ደነዘዘ። ፳፮እንዲህም አለው፥ “ሊነጋ ጎሕ
ቀድዶአልና ልቀቀኝ።” እርሱም “ካልባረክ
ኸኝ አልለቅህም” አለው። ፳፯እንዲህም አለው፥
“ስምህ ማን ነው?” እርሱም፥ “ያዕቆብ ነኝ”
አለው። ፳፰አለውም፥ “ከእንግዲህ ወዲህ ስምህ
እስራኤል ይባል እንጂ ያዕቆብ አይባል፤ ከእግ
ዚአብሔርና ከሰው ጋር ታግለህ በርትተሃልና።”
፳፱ያዕቆብም፥ “ስምህን ንገረኝ” ብሎ ጠየቀው።
እርሱም፥ “ስሜን ለምን ትጠይቃለህ? ድንቅ
ነውና”[፫] አለው። ፴በዚያም ስፍራ ባረከው። ያዕ
ቆብም፥ “እግዚአብሔርን ፊት ለፊት አየሁ፤
ሰውነቴም ዳነች” ሲል የዚያን ቦታ ስም “ራእየ
እግዚአብሔር” ብሎ ጠራው። ፴፩ራእየ እግዚአ
ብሔርንም በተወ ጊዜ ፀሐይ ወጣችበት። እር
ሱም በጭኑ ምክንያት ያነክስ ነበር። ፴፪ስለዚ
ህም የእስራኤል ልጆች እስከ ዛሬ ድረስ የወር
ችን ሹልዳ አይበሉም፤ የያዕቆብን ጭን ይዞ የወ
ርቹን ሹልዳ አደንዝዞአልና።

---

፩ ዕብ. “እናቶችን ከልጆቻቸው ጋር” ይላል።
፪ ዕብ. “ሠላሳ” ይላል።
፫ “ድንቅ ነውና” በግሪክ ሰባ. ሊ. እና በዕብ. የለም።

## ምዕራፍ ፴፫

### ያዕቆብ ዔሳውን እንደ ተገናኘው

፩ያዕቆብም ዐይኑን አነሣ፤ እነሆም፥ ዔሳውን
ሲመጣ አየው፤ ከእርሱም ጋር አራት መቶ
ሰዎች ነበሩ፤ ልጆቹንም ከፍሎ ወደ ልያና ወደ
ራሔል ወደ ሁለቱም ዕቁባቶቹ አደረጋቸው፤
፪ዕቁባቶቹንና ልጆቻቸውንም በፊት አደረገ፤
ልያንና ልጆችዋን በኋላ፥ ራሔልንና ዮሴፍ
ንም ከሁሉ በኋላ አደረገ። ፫እርሱም በፊታ
ቸው አለፈ፤ ወደ ወንድሙ ወደ ዔሳውም እስ
ኪደርስ ድረስ ወደ ምድር ሰባት ጊዜ ሰገደ።
፬ዔሳውም ሊገናኘው ሮጠ፤ አንገቱንም አቅፎ
ሳመው፤ ሁለቱም በአንድነት አለቀሱ። ፭ዔሳ
ውም ዐይኑን አነሣና ሴቶችንና ልጆችን አየ፤
እንዲህም አለ፥ "እነዚህ ምኖችህ ናቸው?"
እርሱም፥ "እግዚአብሔር ለእኔ ለአገልጋይህ
የሰጠኝ ልጆች ናቸው" አለ። ፮ዕቁባቶቹም
ከልጆቻቸው ጋር ቀርበው ሰገዱ፤ ፯ደግሞም
ልያና ልጆችዋ ቀርበው ሰገዱለት፤ ከዚያም
በኋላ ዮሴፍና ራሔል ቀርበው ሰገዱ። ፰ዔሳ
ውም፥ "ያገኘሁት ይህ ሠራዊት ሁሉ ምንህ
ነው?" አለ። እርሱም፥ "በጌታዬ ፊት ሞገስን
አገኝ ዘንድ ያደረግሁልህ ነው" አለ። ፱ዔሳ
ውም፥ "ለእኔ ብዙ አለኝ፤ ወንድሜ ሆይ፥
የአንተ ለአንተ ይሁን" አለ። ፲ያዕቆብም አለ፥
"እንደዚህ አይደለም፤ ነገር ግን በፊትህ ሞገ
ስን አግኝቼ እንደ ሆንሁ እጅ መንሻዬን ከእጄ
ተቀበለኝ፤ የእግዚአብሔርን ፊት እንደሚያይ
ፊትህን አይቻለሁና፥ በቸርነትም ተቀብለኸኛ
ልና። ፲፩ከወደድኸኝስ ይህችን ያመጣሁልህን
በረከቴን ተቀበል፤ እግዚአብሔር ራርቶልኛ
ልና፥ ለእኔም ብዙ አለኝና።" እስኪቀበለውም
ድረስ ግድ አለው፤ ተቀበለውም። ፲፪እርሱም፥
"ተነሣና ወደ ፊት እንሂድ" አለው። ፲፫እር
ሱም አለው፥ "ጌታዬ ሆይ፥ ልጆቹ ደካሞች
እንደ ሆኑ ታውቃለህ፤ በጎችና ላሞችም ግልገ
ሎቻቸውን ያጠባሉ፤ ሰዎችም በአንድ ወይም
በሁለት ቀን በችኮላ የነዱአቸው እንደ ሆነ ከብ
ቶቹ ሁሉ ይሞታሉ። ፲፬ጌታዬ ከአገልጋዩ ፊት
ቀድሞ ይለፍ፤ እኛም እንደ ቻልን እንሄዳለን፤
በጎዳናም እንውላለን፤ ወደ ጌታችን ወደ ሴይር
እስክንደርስም በሕፃናቱ ርምጃ መጠን እንሄዳ
ለን" አለው። ፲፭ዔሳውም፥ "ከእኔ ጋር ካሉ
ሰዎች ከፍዬ ልተውልህን?" አለ። እርሱም፥
"ይህ ለምንድን ነው? በጌታዬ ዘንድ ሞገስን
ማግኘቴ ይበቃኛል" አለ። ፲፮ዔሳውም በዚያ
ቀን ወደ ሴይር ተመለሰ። ፲፯ያዕቆብ ግን በሰ
ፈሩ አደረ፤ ፩ በዚያም ለእርሱ ቤትን ሠራ፤
ለከብቶቹም ዳሶችን አደረገ፤ ስለዚህም የዚያን
ቦታ ስም ማኅደር ብሎ ጠራው።
፲፰ያዕቆብም ከሁለቱ ወንዞች መካከል በተመ
ለሰ ጊዜ በከነዓን ምድር ወዳለችው ወደ ሰቂ
ሞን ከተማ ወደ ሴሎም መጣ፤ በከተማዪቱም
ፊት ለፊት ሰፈረ። ፲፱ድንኳኑን ተክሎበት የነበ
ረውንም የእርሻ ክፍል ከሴኬም አባት ከኤሞር
ልጆች በመቶ በጎች ገዛው። ፳በዚያም መሠው
ያዉን አቆመ፤ የእስራኤልንም አምላክ ጠራ።

## ምዕራፍ ፴፬

### የኤሞር ልጅ ዲናን እንደ አስነወራት

፩ለያዕቆብ የተወለደች የልያ ልጅ ዲናም የዚ
ያን ሀገር ሴቶች ልጆችን ለማየት ወጣች።
፪የሀገሩ አለቃ የኤዊያዊው ሰው የኤሞር ልጅ
ሴኬም አያት፤ ወሰዳትም፤ ከእርስዋም ጋር
ተኛ፤ አስነወራትም። ፫ልቡናውም በያዕቆብ
ልጅ በዲና ፍቅር ተነደፈ፤ ብላቴናዪቱንም
ወደዳት፤ ልብዋንም ደስ በሚያሰኛት ነገር
ተናገራት። ፬ሴኬምም አባቱን ኤሞርን፥ "ይህ
ችን ብላቴና አጋባኝ" ብሎ ነገረው። ፭ያዕቆ
ብም ልጁን ዲናን የኤሞር ልጅ እንዳስነወራት
ሰማ፤ ልጆቹም ከከብቶቻቸው ጋር በምድረ
በዳ ነበሩ፤ ያዕቆብም ልጆቹ እስኪመጡ ድረስ
ዝም አለ። ፮የሴኬም አባት ኤሞርም ይነግረው
ዘንድ ወደ ያዕቆብ መጣ። ፯የያዕቆብም ልጆች
ከምድረ በዳ መጡ፤ ይህንም በሰሙ ጊዜ ፈጽ
መው ደነገጡ፤ የያዕቆብን ልጅ በመተኛቱ በእ
ስራኤል ላይ ኀፍረትን ስላደረገ አዘኑ፤ እጅ
ግም ተቈጡ፤ እንዲህ አይደረግምና። ፰ኤሞ
ርም እንዲህ ብሎ ነገራቸው፥ "ልጄ ሴኬም
ልጃችሁን ወዶአታልና ሚስት እንድትሆነው
እርስዋን ስጡት። ፱ጋብቾችም ሁኑን፤ ሴቶች
ልጆቻችሁን ስጡን፤ እናንተም የእኛን ሴቶች
ልጆች ለልጆቻችሁ ውሰዱ። ፲ከእኛም ጋር
ተቀመጡ፤ ምድራችንም በፊታችሁ ሰፊ ናት፤
ኑሩባት፤ ነግዱም፤ ግዙአትም።" ፲፩ሴኬምም
አባቷንና ወንድሞችዋን እንዲህ አለ፥ "በፊታ
ችሁ ሞገስን በአገኝ የምትሉትን ሁሉ እሰጣ

፩ ዕብ. "ያዕቆብ ግን ወደ ሱኮት ሄደ" ይላል።

ለሁ። ፲፪ብዙ ማጫ አምጣ በሉኝ፤ በምትጠ
ይቁኝም መጠን እሰጣለሁ፤ ይህችን ብላቴና
ግን ሚስት ትሆነኝ ዘንድ ስጡኝ።” ፲፫የያዕቆ
ብም ልጆች ለሴኬምና ለአባቱ ለኤሞር በተን
ኰል መለሱ፤ እኅታቸውን ዲናን አስነውሮአታ
ልና፤ ፲፬የዲና ወንድሞች ስምዖንና ሌዊም እን
ዲህ አሉአቸው፥ “እኅታችንን ላልተገረዘ ሰው
ለመስጠት ይህን ነገር እናደርግ ዘንድ አይቻለ
ንም፤ ይህ ነውር ይሆንብናልና። ፲፭እናንተም
እንደ እኛ ወንዶቻችሁን ሁሉ ብትገርዙ በዚህ
ብቻ እንመስላችኋለን፤ ከእናንተም ጋር እንኖ
ራለን፤ ፲፮ሴቶች ልጆቻችንንም እንሰጣችኋለን፤
የእናንተንም ሴቶች ልጆች ለሚስትነት እንወስ
ዳለን፤ አንድ ሕዝብም ሆነን ከእናንተ ጋር እን
ኖራለን። ፲፯ትገረዙ ዘንድ እኛን ባትሰሙ ግን
ልጃችንን ይዘን እንሄዳለን።”

፲፰ነገራቸውም ኤሞርንና የኤሞርን ልጅ ሴኬ
ምን ደስ አሰኛቸው። ፲፱ብላቴናውም ይህን ነገር
ያደርግ ዘንድ አልዘገየም፤ የያዕቆብን ልጅ ወድ
ዶአልና፤ እርሱም ከአባቱ ቤተ ሰብእ ሁሉ የከ
በረ ነበረ። ፳ኤሞርና ልጁ ሴኬምም ሄዱና ወደ
ከተማቸው በር ደረሱ፤ ለከተማቸውም ሰዎች
ሁሉ እንዲህ ብለው ነገሩ፦ ፳፩“እነዚህ ሰዎች
በእኛ ዘንድ የሰላም ሰዎች ናቸው፤ በምድራ
ችን ይቀመጡ፤ ይነግዱባትም፤ እነሆም፥ ምድ
ሪቱ ሰፊ ናት፤ ሴቶች ልጆቻቸውን ለሚስት
ነት እንውሰድ፤ ለእነርሱም ሴቶች ልጆቻችንን
እንስጥ። ፳፪እነርሱ እንደ እኛ ይሆኑ ዘንድ በዚህ
ብቻ እንምሰላቸው። አንድ ወገንም እንሁን፤
እነርሱ እንደሚገርዙ ወንዶቻችንን ሁሉ እንገር
ዛለን። ፳፫መንጋቸውም፥ የጋማ ከብቶቻቸውም፥
ገንዘባቸውም ሁሉ ለእኛ አይደሉምን? ነገር
ግን በዚህ ብቻ ከመሰልናቸው ከእኛ ጋር ይቀ
መጣሉ።” ፳፬በከተማዪቱም በር የሚገቡ ሁሉ
ኤሞርንና ልጁን ሴኬምን እሺ አሉ፤ ወንዶ
ችም ሁሉ የሰውነታቸውን ሸለፈት ተገረዙ።[፩]

## የዲና ወንድሞች በቀል

፳፭እንዲህም ሆነ፤ በሦስተኛው ቀን እጅግ
ቈስለው ሳሉ ሁለቱ የያዕቆብ ልጆች የዲና ወን
ድሞች ስምዖንና ሌዊ እየራሳቸው ሰይፋቸውን
ይዘው ተደፋፍረው ወደ ከተማ ገቡ፤ ወንዱ
ንም ሁሉ ገደሉ፤ ፳፮ኤሞርንና ልጁን ሴኬም
ንም በሰይፍ ገደሉ፤ እኅታቸው ዲናንም ከሴ
ኬም ቤት ይዘው ወጡ። ፳፯የያዕቆብ ልጆችም
ወደ ሞቱት ገብተው እኅታቸው ዲናን ያስ
ነወሩባትን ከተማዪቱን ዘረፉ፤ ፳፰ላሞቻቸው
ንም፥ በጎቻቸውንም፥ አህዮቻቸውንም በሜ
ዳም፥ በከተማም ያለውን ወሰዱ ። ፳፱ሎሌዎቻ
ቸውንና ሚስቶቻቸውን፥ የቤታቸውንም ቁሳ
ቍስ[፪] ሁሉ ማረኩ፤ በቤትና በከተማ ያለውንም
ሁሉ ዘረፉ። ፴ያዕቆብም ስምዖንንና ሌዊን እን
ዲህ አላቸው፥ “ክፉ አደረጋችሁብኝ፤ በዚች
ሀገር በሚኖሩ በከነዓናውያንና በፌርዜዎናው
ያን ሰዎች ዘንድ አስጠላችሁኝ። እኔ በቍጥር
ጥቂት ነኝ፤ እነርሱ በእኔ ላይ ይሰበሰቡና ይወ
ጉኛል፤ እኔና ቤቴም እንጠፋለን። ፴፩እነርሱም፥
“እኅታችንን እንደ አመንዝራ አድርገው ለምን
አዋረዷት?” አሉት።

## ምዕራፍ ፴፭

## እግዚአብሔር ያዕቆብን እንደ ባረከው

፩እግዚአብሔርም ያዕቆብን አለው፥ “ተነሥ
ተህ ወደ ቤቴል ውጣ፤ በዚያም ኑር፤ ከወንድ
ምህ ከዔሳው ፊት በሸሸህ ጊዜ ለተገለጥሁልህ
ለእኔ መሠውያን ሥራ።” ፪ያዕቆብም ለቤተ
ሰቡና ከእርሱ ጋር ላሉት ሁሉ እንዲህ አለ፥
“ከእናንተ ጋር ያሉ እንግዶች አማልክትን ከመ
ካከላችሁ አስወግዱ፤ ንጹሓንም ሁኑ፤ ልብሳች
ሁንም እጠቡ፤ ፫ተነሡና ወደ ቤቴል እንውጣ፤
በዚያም በመከራዬ ቀን ለሰማኝ፥ በሄድሁብ
ትም መንገድ ከእኔ ጋር ለነበረው፥ ከመከራም
አድኖ ላሻገረኝ ለእግዚአብሔር መሠውያን እን
ሥራ።” ፬በእጃቸው ያሉትንም እንግዶች አማ
ልክት ሁሉ፥ በጆሮአቸውም ያሉትን ጉትቾች
ለያዕቆብ ሰጡት፤ ያዕቆብም በሴቄም አጠገብ
ካለችው ዛፍ በታች ቀበራቸው። እስከ ዛሬም
ድረስ አጠፋቸው። ፭እስራኤልም ከሴቄም ሄደ፤
እግዚአብሔርንም መፍራት በዙሪያቸው ባሉት
ከተሞች ሁሉ ወደቀ፤ የእስራኤልንም ልጆች
ለማሳደድ አልተከተሉአቸውም። ፮ያዕቆብም
እርሱ፥ ከእርሱ ጋርም የነበሩት ሰዎች ሁሉ
በከነዓን ምድር ወዳለችው ወደ ሎዛ መጡ፤
እርስዋም ቤቴል ናት። ፯በዚያም መሠውያዉን
ሠራ፤ የዚያንም ቦታ ስም ቤቴል ብሎ ጠራው፤
እርሱ ከወንድሙ ከዔሳው ፊት በሸሸበት ጊዜ
እግዚአብሔር በዚያ ተገልጦለት ነበርና። ፰የር

---

፩ ዕብ. “ከከተማዪቱ አደባባይ የሚወጡት ወንዶች ሁሉ ተገረዙ” ይላል።
፪ ዕብ. “ሀብታቸውን ሁሉ፥ ሕፃናቶቻቸውን ሁሉ፥ ሴቶቻቸውንም ሁሉ” ይላል።

ብቃ ሞግዚት ዲቦራም ሞተች፤ ከቤቴል በታች
ባላን በሚባል ዛፍ ሥርም ተቀበረች፤ ያዕቆብም
ስሙን "የልቅሶ ዛፍ" ብሎ ጠራው።
፱እግዚአብሔርም ለያዕቆብ ከሁለት ወንዞች
መካከል ከሶርያ ከተመለሰ በኋላ እንደገና በሎዛ
ተገለጠለት፤ እግዚአብሔርም ባረከው። ፲እግዚ
አብሔርም አለው፥ "ስምህ ያዕቆብ አይባል፤
ስምህ እስራኤል ይባል እንጂ" ስሙንም እስራ
ኤል ብሎ ጠራው። ፲፩እግዚአብሔርም አለው፥
"አምላክህ እኔ ነኝ፤[፩] ብዛ፤ ተባዛም፤ ሕዝ
ብና የአሕዛብ ማኅበር ከአንተ ይሆናል፤ ነገሥ
ታትም ከጕልበትህ ይወጣሉ። ፲፪ለአብርሃምና
ለይስሐቅም የሰጠኋትን ምድር ለአንተ፥ ከአን
ተም በኋላ ለዘርህ እሰጣለሁ።" ፲፫እግዚአብሔ
ርም ከእርሱ ጋር ከተነጋገረበት ስፍራ ወደ ላይ
ወጣ። ፲፬ያዕቆብም እግዚአብሔር ከእርሱ ጋር
በተነጋገረበት ቦታ የድንጋይ ሐውልት ተከለ፤
የመጠጥ መሥዋዕትንም በእርሱ ላይ አፈሰሰ፤
ዘይትንም አፈሰሰበት። ፲፭ያዕቆብም እግዚአ
ብሔር ከእርሱ ጋር የተነጋገረበትን ያን ቦታ
"ቤቴል" ብሎ ጠራው።

## የራሔል ሞት

፲፮ያዕቆብም ከቤቴል ተጓዘ፤ በጋዲር ግንብ
አጠገብ ድንኳን ተከለ፤ ወደ ኤፍራታም ለመ
ድረስ በቀረበ ጊዜ ራሔልን ምጥ ያዛት፤ በም
ጡም ተጨነቀች። ፲፯በምጥ ሳለችም አዋላጂቱ፥
"አትፍሪ ይህኛው ደግሞ ወንድ ልጅ ይሆንል
ሻልና" አለቻት። ፲፰ከዚያም በኋላ ነፍስዋ ልት
ወጣ ደረሰች፤ ሞትዋ በእርሱ ሆኖአልና ስሙን
የጭንቀቴ ልጅ ብላ ጠራችው፤ አባቱ ግን ብን
ያም አለው። ፲፱ራሔልም ሞተች፤ ወደ ኤፍ
ራታም በምትወስድ መንገድ ተቀበረች፤ እር
ስዋም ቤተ ልሔም ናት። ፳ያዕቆብም በመቃ
ብርዋ ላይ ሐውልት አቆመ፤ እርስዋም እስከ
ዛሬ የራሔል የመቃብርዋ ሐውልት ትባላለች።
፳፩ከዚህም በኋላ እስራኤል በዚያች ምድር ሳለ
ሮቤል ሄደ፤ ከአባቱ ከያዕቆብ ዕቅብት ከባላ
ጋርም ተኛ፤ እስራኤልም ሰማ። በፊቱም ክፉ
ነገር ሆነ።

## የያዕቆብ ልጆች

(፩ዜ.መ. ፪፥ ፩-፪)

፳፪የያዕቆብም ልጆች ዐሥራ ሁለት ናቸው፤
፳፫የልያ ልጆች፤ የያዕቆብ በኵር ልጅ ሮቤል፥
ስምዖን፥ ሌዊ፥ ይሁዳ፥ ይሳኮር፥ ዛብሎን፤
፳፬የራሔል ልጆች፤ ዮሴፍ፥ ብንያም፤ ፳፭የራ
ሔል አገልጋይ የባላ ልጆችም፤ ዳን፥ ንፍታ
ሌም፤ ፳፮የልያ አገልጋይ የዘለፋ ልጆችም፤
ጋድ፥ አሴር፤ እነዚህ በሁለቱ ወንዞች መካከል
በሶርያ የተወለዱለት የያዕቆብ ልጆች ናቸው።

## የይስሐቅ ሞት

፳፯ያዕቆብም ወደ አባቱ ወደ ይስሐቅ፥ አብር
ሃምና ይስሐቅ እንግዶች ሆነው ወደ ተቀመጡ
ባት በአርባቅ ከተማ ወደምትገኘው ወደ መምሬ
እርስዋም ኬብሮን ወደምትባለው መጣ። ፳፰የይ
ስሐቅም ዕድሜ መቶ ሰማንያ ዓመት ሆነ።
፳፱ይስሐቅም ሸምግሎ ዕድሜንም ጠግቦ ሞተ፤
ወደ ወገኖቹም ተጨመረ፤ ልጆቹም ዔሳውና
ያዕቆብ ቀበሩት።

## ምዕራፍ ፴፮

## የዔሳው ትውልድ

(፩ ዜ.መ. ፩፥ ፴፭-፶፬)

፩ኤዶም የተባለው የዔሳው ትውልድ እን
ዲህ ነው። ፪ዔሳው ከከነዓን ልጆች ሚስቶችን
አገባ፤ የኬጢያዊውን የዔሎን ልጅ ሐዳሶን፥
የኤውያዊው የሴቤሶ ልጅ ሐና የወለዳትን ኤሌ
ባማን፥ ፫የይስማኤልን ልጅ የናቡአት እኅት
ቤሴሞትን። ፬ሐዳሶ ለእርሱ ኤልፋዝን ወለ
ደች፤ ቤሴሞትም ራጉኤልን ወለደች፤ ፭ኤሌባ
ማም የሔልን፥ ይጉሜልን፥ ቆሬንም ወለደች።
በከነዓን ምድር የተወለዱለት የዔሳው ልጆች
እነዚህ ናቸው። ፮ዔሳውም ሚስቶቹን፥ ወን
ዶች ልጆቹንና ሴቶች ልጆቹን፥ ቤተ ሰቡንም
ሁሉ፥ እንስሶቹንም ሁሉ፥ በከነዓንም ሀገር
ያገኘውን ገንዘቡን ሁሉ ይዞ ከወንድሙ ከያዕ
ቆብ ፊት ከከነዓን ሀገር ሄደ። ፯ከብታቸው ስለ
በዛ በአንድነት ይቀመጡ ዘንድ አልቻሉም፤
በእንግድነት የተቀመጡባትም ምድር ከከብታ
ቸው ብዛት የተነሣ ልትበቃቸው አልቻለችም።
፰ዔሳውም በሴይር ተራራ ተቀመጠ፤ ዔሳውም
ኤዶም ነው።
፱በሴይር ተራራ የሚኖሩ የኤዶማውያን አባት
የዔሳው ትውልድም እንዲህ ነው። ፲የዔሳው
ልጆች ስም ይህ ነው፤ የዔሳው ሚስት የሐ
ዳሶ ልጅ ኤልፋዝ፤ የዔሳው ሚስት የቤሴሞት
ልጅ ራጉኤል። ፲፩የዔሳው ልጅ የኤልፋዝ ልጅ

፩ ዕብ. "ሁሉን ቻይ አምላክ እኔ ነኝ" ይላል።

ችም እነዚህ ናቸው፤ ቴማን፥ ኤሞር፥ ሳፍር፥
ጎቶን፥ ቄኔዝ። ፲፪ቴምናሕም ለዔሳው ልጅ
ለኤልፋዝ ዕቅብት ነበረች፤ አማሌቅንም ለኤ
ልፋዝ ወለደችለት፤ የዔሳውም ሚስት የሐዳሶ
ልጆች እነዚህ ናቸው። ፲፫የዔሳው ልጅ[፩] የራጉ
ኤል ልጆችም እነዚህ ናቸው፤ ናሖት፥ ዛራ፥
ሲም፥ ሞዛህ፤ እነዚህም የዔሳው ሚስት የቤ
ሴሞት ልጆች ናቸው። ፲፬የሴቤጎን ልጅ የሐና
ልጅ የዔሳው ሚስት የኤሌባማ ልጆች እነዚህ
ናቸው፤ ለዔሳውም ዮሔልን፥ ዬጉሜልን፥
ቆሬን ወለደች።

፲፭የዔሳው ልጆች መሳፍንት እነዚህ ናቸው፤
የዔሳው የበኵር ልጅ የኤልፋዝ ልጆች፤ ቴማን
መስፍን፥ ኦሜር መስፍን፥ ሳፍር መስፍን፥
ቄኔዝ መስፍን፥ ፲፮ቆሬ መስፍን፥ ጎቶን መስ
ፍን፥ አማሌቅ መስፍን፤ በኤዶም ምድር የኤ
ልፋዝ መሳፍንት እነዚህ ናቸው፤ እነዚህ የሓ
ዳሶ ልጆች ናቸው ። ፲፯የዔሳው ልጅ የራጉኤል
ልጆች መሳፍንት እነዚህ ናቸው፤ ናሖት መስ
ፍን፥ ዛራ መስፍን፥ ሲን መስፍን፥ ሞዛህ መስ
ፍን፤ በኤዶም ምድር የራጉኤል ልጆች መሳፍ
ንት እነዚህ ናቸው፤ እነዚህም የዔሳው ሚስት
የቤሴሞት ልጆች ናቸው። ፲፰የዔሳው ሚስት
የኤሌባማ ልጆች መሳፍንት እነዚህ ናቸው፤
ዮሔል መስፍን፥ ይጉሜል መስፍን፥ ቆሬ መስ
ፍን፤ የዔሳው ሚስት የሐና ልጅ የኤሌባማ
ልጆች መሳፍንት እነዚህ ናቸው። ፲፱የዔሳው
ልጆችና መስፍኖቻቸው እነዚህ ናቸው፤ እነር
ሱም የኤዶም ልጆች ናቸው።

## የሴይር ዘሮች

(፩ ዜ.መ. ፩፥ ፴፰-፵፪)

፳በዚያች ሀገር የተቀመጡ የሖሪያዊው የሴ
ይር ልጆች እነዚህ ናቸው፤ ሎጣን፥ ሦባን፥
ሳባቅ፥ አናም፥ ፳፩ዲሶን፥ ኤሶር፥ ዲሳን፤ እነ
ዚህ በኤዶም ምድር የሖሪያዊው የሴይር ልጆች
መሳፍንት ናቸው። ፳፪የሎጣን ልጆችም እነ
ዚህ ናቸው፤ ሖሪ፥ ሃማን ናቸው፤ የሎጣንም
እኅት ትምናዕ ናት። ፳፫የሦባን ልጆችም እነዚህ
ናቸው፤ ዓልዋን፥ ማኔሐት፥ ኤቤል፥ ሳፉር፥
አውናም። ፳፬የሳባቅ ልጆችም እነዚህ ናቸው፤
ኢአ፥ ዓናን፤ ይህም ዓናን በምድረ በዳ የአባ
ቱን የሳባቅን አህዮች ሲጠብቅ ፍል ውኃዎችን[፪]
ያገኘ ነው። ፳፭የዓናን ልጆችም እነዚህ ናቸው፤
ዲሶን፤ የዓናን ሴት ልጅ ኤሌባማ። ፳፮የዲሶ
ንም ልጆች እነዚህ ናቸው፤ ሕምዳን፥ አስባን፥
ቢዖር፥[፫] ይትራን፥ ክራን። ፳፯የኤሶር ልጆችም
እነዚህ ናቸው፤ ክልሐን፥ ዛአን፥ ዓቃን። ፳፰የሪ
ሶን[፬] ልጆችም እነዚህ ናቸው፤ ዑሳ፥ አራን።
፳፱የሖሪ መሳፍንት እነዚህ ናቸው፤ ሎጣን መስ
ፍን፥ ሦባን መስፍን፥ ሳባቅ መስፍን፥ ዓናን
መስፍን፥ ፴ዲሶን መስፍን፥ ኤሶር መስፍን፥
ሪሶን መስፍን፤ በሴይር ምድር በየሹመታ
ቸው መሳፍንት የሆኑ የሖሪ መሳፍንት እነ
ዚህ ናቸው።

## የኤዶም ነገሥታት

(፩ ዜ.መ. ፩፡ ፵፫-፶፬)

፴፩በእስራኤል ልጆች ላይ ንጉሥ ከመንገሡ
በፊት በኤዶም ሀገር የነገሡ ነገሥታት እነ
ዚህ ናቸው። ፴፪በኤዶምም የቢዖር ልጅ ባላቅ
ነገሠ፤ የከተማዋም ስም ዴናባ ናት። ፴፫ባላ
ቅም ሞተ፤ በእርሱ ፈንታም የባሶራው የዛራ
ልጅ ኢዮባብ ነገሠ። ፴፬ኢዮባብም ሞተ፤ በእ
ርሱም ፈንታ የቴማኒው ሀገር ሑሳም ነገሠ።
፴፭ሑሳምም ሞተ፤ በእርሱም ፈንታ የምድያ
ምን ሰዎች በሞዓብ ሜዳ የገደለ የቢዳድ ልጅ
አዳድ ነገሠ፤ የከተማዋም ስም ዓዊት ተባለ።
፴፮ዓዳድም ሞተ፤ በእርሱም ፈንታ የምስሬ
ቃው ሠምላ ነገሠ። ፴፯ሠምላም ሞተ፤ በእር
ሱም ፈንታ በወንዝ አጠገብ ካለችው ከርኆ
ቦት ሳኦል ነገሠ። ፴፰ሳኦልም ሞተ፤ በእርሱም
ፈንታ የዓክቦር ልጅ በአልሐናን ነገሠ። ፴፱የአክ
ቦር ልጅ በአልሐናንም ሞተ፤ በእርሱም ፈንታ
አዳር ነገሠ፤ የከተማውም ስም ፎጎር ነው፤
ሚስቱም የሜዛአብ ልጅ መጥሬድ የወለደቻት
ምኤጠብኤል ትባላለች።

፵የዔሳውም የመሳፍንቱ ስም በየነገዳቸው፥
በየስፍራቸው፥ በያገራቸውና በየሕዝባቸው
ይህ ነው፤ ትምናዕ መስፍን፥ ዓልዋ መስፍን፥
ኤቴት መስፍን፥ ፵፩ኤሌባማ መስፍን፥ ኤላ
መስፍን፥ ፊኖን መስፍን፥ ፵፪ቄኔዝ መስፍን፥
ቴማን መስፍን፥ ሜብሳር መስፍን፥ ፵፫መግዳ
ኤል መስፍን፥ ኤራም መስፍን፤ እነዚህ በግ

---

፩ "የዔሳው ልጅ" በግሪክ ሰባ. ሊ. እና በዕብ. የለም።

፪ በግእዙ "ያሜን" ይላል።

፫ "ቢዖር" በግሪክ ሰባ. ሊ. እና በዕብ. የለም።

፬ በግእዙ "ዲሳን" ይላል።

ዛታቸው ምድር በየመኖሪያቸው የኤዶም መሳፍንት ናቸው። የኤዶማውያንም አባት ይህ ዔሳው ነው።

## ምዕራፍ ፴፯

### ዮሴፍና ወንድሞቹ

፩ ያዕቆብም አባቱ በስደት በኖረበት ሀገር በከነዓን ምድር ተቀመጠ። ፪ የያዕቆብም ትውልድ እንዲህ ነው። ዮሴፍ ዐሥራ ሰባት ዓመት በሆነው ጊዜ ከወንድሞቹ ጋር የአባቱን በጎች ይጠብቅ ነበር፤ እርሱም ከአባቱ ሚስቶች ከባላና ከዘለፋ ልጆች ጋር ሳለ ብላቴና ነበረ፤ ዮሴፍም የክፋታቸውን ወሬ ወደ አባታቸው ወደ እስራኤል ያመጣ ነበር።[፩] ፫ ያዕቆብም ዮሴፍን ከልጆቹ ሁሉ ይልቅ ይወድደው ነበር፤ እርሱ በሽምግልናው የወለደው ነበርና። በብዙ ኅብር ያጌጠችም ቀሚስ አደረገለት። ፬ ወንድሞቹም አባታቸው ከልጆቹ ሁሉ ይልቅ እንደሚወድደው በአዩ ጊዜ ጠሉት፤ በሰላም ይናገሩትም ዘንድ አልቻሉም።

፭ ዮሴፍም ሕልምን አለመ፤ ለወንድሞቹም ነገራቸው።[፪] ፮ እርሱም አላቸው፦ "እኔ ያለምሁትን ሕልም ስሙ፤ ፯ እነሆ፥ እኛ በእርሻ መካከል ነዶ ስናስር ነበርና፥ እነሆ፥ የእኔ ነዶ ቀጥ ብላ ቆመች፤ የእናንተም ነዶዎች በዙርያ ከብበው እነሆ፥ ለእኔ ነዶ ሰገዱ።" ፰ ወንድሞቹም፦ "በእኛ ላይ ልትነግሥብን ይሆን? ወይስ ገዢ ትሆነን ይሆን?" አሉት። እንደገናም ስለ ሕልሙና ስለ ነገሩ የበለጠ ጠሉት። ፱ ደግሞም ሌላ ሕልምን አየ፤ ለአባቱና ለወንድሞቹም ነገራቸው፤ እንዲህም አለ፦ "እነሆ፥ ደግሞ ሌላ ሕልም አለምሁ፤ ሕልሙም እንዲህ ነው:- ፀሐይና ጨረቃ ዐሥራ አንድ ከዋክብትም ይሰግዱልኝ ነበር።" ፲ አባቱም ገሠጸው፤ እንዲህም አለው፦ "ይህ ያለምኸው ሕልም ምንድን ነው? በውኑ እኔና እናትህ፥ ወንድሞችህም መጥተን በምድር ላይ እንሰግድልህ ይሆን?" ፲፩ ወንድሞቹም ቀኑበት፤ አባቱ ግን ይህን ነገር በልቡ ይጠብቀው ነበር።

### ዮሴፍን ወንድሞቹ እንደ ሸጡት

፲፪ ወንድሞቹም በሴኬም የአባታቸውን በጎች ይጠብቁ ዘንድ ሄዱ። ፲፫ እስራኤልም ዮሴፍን፦ "ወንድሞችህ በሴኬም በጎችን የሚጠብቁ አይደሉምን? ወደ እነርሱ እልክህ ዘንድ ና" አለው። እርሱም፦ "እሺ" አለው። ፲፬ እርሱም፦ "ሄደህ ወንድሞችህና በጎቹ ደኅና እንደ ሆኑ እይ፤ ወሬአቸውንም አምጣልኝ" አለው። ወደ ኬብሮንም ቆላ ላከው፤ ወደ ሴኬምም መጣ። ፲፭ እነሆም፥ በምድረ በዳ ሲቅበዘበዝ ሳለ አንድ ሰው አገኘው፤ ሰውየውም፦ "ምን ትፈልጋለህ?" ብሎ ጠየቀው። ፲፮ እርሱም፦ "ወንድሞችን እፈልጋለሁ፤ በጎቹን የሚጠብቁበት ወዴት እንደ ሆነ እባክህ ንገረኝ?" አለ። ፲፯ ሰውየውም፦ "ከዚህ ተነሥተዋል፤ ወደ ዶታይን እንሂድ ሲሉም ሰምቼአቸዋለሁ" አለው። ዮሴፍም ወንድሞቹን ተከታትሎ ሄደ፤ በዶታይንም አገኛቸው።

፲፰ እነርሱም ወደ እነርሱ ሳይቀርብ ከሩቅ አስቀድመው አዩት፥ ይገድሉትም ዘንድ በእርሱ ላይ ተማከሩ። ፲፱ አንዱም ለአንዱ እንዲህ አለው፦ "ያ ባለ ሕልም ይኸው መጣ። ፳ ኑ፥ እንግደለውና በአንድ ጕድጓድ ውስጥ እንጣለው፤ ክፉ አውሬም በላው እንላለን፤ ሕልሞቹም ምን እንደሚሆኑ እናያለን።" ፳፩ ሮቤልም ይህን ሰማ፤ ከእጃቸውም አዳነው፤ እንዲህም አለ፦ "ሕይወቱን አናጥፋ።" ፳፪ ሮቤልም፦ "ደም አታፍስሱ፤ በዚች ምድረ በዳ ባለችው ጕድጓድ ጣሉት፤ ነገር ግን እጃችሁን አትጣሉበት" አላቸው። ሮቤልም እንዲህ ማለቱ ከእጃቸው ሊያድነውና ወደ አባቱ ሊመልሰው ነው። ፳፫ እንዲህም ሆነ፤ ዮሴፍ ወደ ወንድሞቹ በቀረበ ጊዜ የለበሳትን በብዙ ኅብር ያጌጠቺውን ቀሚሱን ገፈፉት፤ ፳፬ ወስደውም ወደ ጕድጓድ ጣሉት፤ ጕድጓዱም ውኃ የሌለበት ባዶ ነበረ።

፳፭ እንጀራም ሊበሉ ተቀመጡ፤ ዐይኖቻቸውንም በአነሡ ጊዜ እነሆ፥ ይስማኤላውያን ነጋድያን ከገለዓድ ሲመጡ አዩ፤ ግመሎቻቸውም ሽቱና በለሳን፥ ከርቤም ተጭነው ነበር። ወደ ግብፅ ሀገርም ሊያራግፉ ይሄዱ ነበር። ፳፮ ይሁዳም ወንድሞቹን እንዲህ አላቸው፦ "ወንድማችንን ገድለን ደሙን ብንሸሽግ ጥቅማችን ምንድን ነው? ፳፯ ኑ፥ ለእነዚህ ይስማኤላውያን እንሽጠው፤ እጃችንን ግን በእርሱ ላይ አንጣል፤ ወንድማችን ሥጋችን ነውና።" ወንድሞቹም የነገራቸውን ሰሙት። ፳፰ እነዚያ ይስማኤላውያን

---

[፩] ግእዝ "ወአምጽኡ ላዕለ ዮሴፍ ውዴተ እኪተ ኀበ አቡሆሙ እስራኤል" ይላል።

[፪] ዕብ. "እነርሱም እንደ ገና በብዙ ተጣሉት" የሚል ይጨምራል።

ነጋዴዎችም ሲያልፉ ወንድሞቹ ዮሴፍን ከጕድ
ጓድ ጐትተው አወጡት፤ ለይስማኤላውያንም
ዮሴፍን በሃያ ብር ሸጡት፤ እነርሱም ዮሴፍን
ወደ ግብፅ ወሰዱት።
፳፱ሮቤልም ወደ ጕድጓዱ ተመለሰ፤ እነ
ሆም፥ ዮሴፍን ከጕድጓድ በአጣው ጊዜ ልብ
ሱን ቀደደ። ፴ሮቤልም ወደ ወንድሞቹ ተመ
ልሶ፥ "ብላቴናው በጕድጓድ የለም፤ እንግ
ዲህ እኔ ወዴት እሄዳለሁ?" አለ። ፴፩የዮሴፍ
ንም ቀሚስ ወሰዱ፤ የፍየልም ጠቦት አርደው
ቀሚሱን በደም ነከሩት። ፴፪ብዙ ኅብር ያለበ
ትን ቀሚሱንም ላኩ፤ ወደ አባታቸውም አገ
ቡት፤ እንዲህም አሉት፥ "ይህን ልብስ አገ
ኘን፤ ይህ የልጅህ ልብስ እንደ ሆነ ወይም እን
ዳልሆነ እስኪ እየው?" ፴፫እርሱም ዐውቆ፥
"የልጄ ቀሚስ ነው፤ ክፉ አውሬ በልቶታል፤
ዮሴፍን ቦጫጭቆታል" አለ። ፴፬ያዕቆብም ልብ
ሱን ቀደደ፤ በወገቡም ማቅ ታጥቆ ለልጁ ብዙ
ቀን አለቀሰ። ፴፭ወንዶች ልጆቹና ሴቶች ልጆቹ
ሁሉ ተሰብስበው መጡ። ኀዘኑንም ያስተዉት
ዘንድ አባታቸውን ማለዱት። ኀዘኑንም መተ
ውን እንቢ አለ፥ እንዲህም አላቸው፥ "ወደ
ልጄ ወደ መቃብር እያዘንሁ እወርዳለሁ።"
አባቱም ስለ እርሱ አለቀሰ። ፴፮እነዚያ ይስማኤ
ላውያን[፫] ሰዎች ግን ዮሴፍን በግብፅ ለፈርዖን
ጃንደረባ ለዘበኞቹ አለቃ ለጲጥፋራ ሸጡት።

## ምዕራፍ ፴፰

### ይሁዳና ትዕማር

፩በዚያም ወራት እንዲህ ሆነ፤ ይሁዳ ከወን
ድሞቹ ተለይቶ ወረደ፤ ስሙ ኤራስ በሚባል
በዓዶሎማዊውም ሰው ዘንድ አደረ። ፪ከዚያም
ይሁዳ ያንድ ከነዓናዊ ሰው ሴት ልጅን አየ፤
ስምዋም ሴዋ[፬] ይባላል። ወሰዳትም፤ ወደ እር
ስዋም ገባ። ፫ፀነሰችም፤ ወንድ ልጅንም ወለ
ደች፤ ስሙንም ዔር ብላ ጠራችው። ፬ደግ
ሞም ፀነሰች፤ ወንድ ልጅንም ወለደች፤ ስሙ
ንም አውናን ብላ ጠራችው። ፭እንደገና ደግሞ
ወንድ ልጅን ወለደች፤ ስሙንም ሴሎም ብላ
ጠራችው፤ እነርሱንም በወለደች ጊዜ ኬሴቢ
በሚባል ሀገር ነበረች። ፮ይሁዳም ለበኵር ልጁ
ለዔር ትዕማር የምትባል ሚስት አጋባው። ፯የይ
ሁዳም የበኵር ልጅ ዔር በእግዚአብሔር ፊት
ክፉ ነበረ፤ እግዚአብሔርም ቀሠፈው። ፰ይሁ
ዳም አውናንን፥ "ወደ ወንድምህ ሚስት ግባ፤
አግባትም፤ ለወንድምህም ዘርን አቁምለት"
አለው። ፱አውናንም ዘሩ ለእርሱ እንዳይሆን
ዐወቀ፤ ወደ ወንድሙ ሚስትም በገባ ጊዜ
ለወንድሙ ዘር እንዳይተካ ዘሩን በምድር ያፈ
ስሰው ነበር። ፲ይህም ሥራው በእግዚአብሔር
ዘንድ ክፉ ሆነበት፤ እንዲህ አድርጎአልና እርሱ
ንም ደግሞ ቀሠፈው። ፲፩ይሁዳም ምራቱን ትዕ
ማርን፥ "ልጄ ሴሎም እስኪያድግ ድረስ በአ
ባትሽ ቤት መበለት ሆነሽ ተቀመጪ" አላት፤
እርሱ ደግሞ እንደ ወንድሞቹ እንዳይሞትብኝ
ብሎአልና። ትዕማርም ሄዳ በአባቷ ቤት ተቀ
መጠች።
፲፪ዘመንዋም በተፈጸመ ጊዜ የይሁዳ ሚስት
ሴዋ ሞተች፤ ይሁዳም ተጽናና፤ የበጎቹን
ጠጕር ወደሚሸልቱት ሰዎችም ወደ ተምና
ወጣ፤ እርሱም ዓዶሎማዊው በግ ጠባቂው
ኤራስም። ፲፫ለምራቱ ትዕማርም፥ "እነሆ፥ አማ
ትሽ ይሁዳ የበጎቹን ጠጕር ይሸልት ዘንድ ወደ
ተምና ይወጣል" ብለው ነገሩአት። ፲፬እርስዋም
የመበለትነቷን ልብስ አወለቀች፤ መጐናጸፊያ
ዋንም ለበሰች፤ ተሸፈነችም፤ ወደ ተምናም
በሚወስደው መንገድ ዳር በኤናይም ደጅ ተቀ
መጠች፤ ሴሎም እንደ አደገ፥ ሚስትም ትሆ
ነው ዘንድ እርስዋን ሊሰጠው እንዳልፈለገ አይ
ታለችና። ፲፭ይሁዳም በአያት ጊዜ ዘማ መሰ
ለችው፤ ፊቷን ተሸፍና ነበርና አላወቃትም።
፲፮ወደ እርስዋም አዘነበለ፥ "እባክሽ ወደ አንቺ
ልግባ አላት፤" እርስዋ ምራቱ እንደ ሆነች አላ
ወቀም ነበርና። እርስዋም፥ "ወደ እኔ ብት
ገባ ምን ትሰጠኛለህ?" አለችው። ፲፯"የፍየል
ጠቦት ከመንጋዬ እልክልሻለሁ" አላት። እርስ
ዋም፥ "እስክትልክልኝ ድረስ መያዣ ስጠኝ"
አለችው። ፲፰እርሱም፥ "ምን መያዣ ልስ
ጥሽ?" አላት። እርስዋም፥ "ቀለበትህን፥ ኩፌ
ትህን፥ በእጅህ ያለውን በትር" አለች። እር
ሱም ሰጣትና ከእርስዋ ደረሰ፤ እርስዋም ፀነሰች
ለት። ፲፱እርስዋም ተነሥታ ሄደች፤ መጐናጸፊያ
ዋንም አውልቃ የመበለትነቷን ልብስ ለበሰች።
፳ይሁዳም መያዣውን ከሴቲቱ እጅ ይቀበል
ዘንድ በበግ ጠባቂው በዓዶሎማዊው እጅ የፍ
የሉን ጠቦት ላከላት፤ እርስዋንም አላገኛትም።
፳፩እርሱም የሀገሩን ሰዎች፥ "በኤናይም በመን

---

፫ ግሪክ ሰባ. ሊ.. እና ዕብ. "ምድያማውያን" ይላል።
፬ ዕብ. "ሴዋን" የይሁዳ የሚስቱ አባት ነው ይላል።

ገድ ዳር ተቀምጣ የነበረች ዘማ ወዴት ናት?”
ብሎ ጠየቃቸው። እነርሱም፥ “በዚህ ዘማ አል
ነበረችም” አሉት። ፳፪ወደ ይሁዳም ተመልሶ
እንዲህ አለው፥ “አላገኘኋትም፤ የሀገሩ ሰዎች
ደግሞ፡- ከዚህ ዘማ የለችም” አሉኝ። ፳፫ይሁ
ዳም፡ “እኛ መዘበቻ እንዳንሆን ትውሰደው፤
እነሆ፡ የፍየሉን ጠቦት ላክሁላት፤ አንተም አላ
ገኘሃትም” አለ።

፳፬እንዲህም ሆነ፤ ከሦስት ወር በኋላ ለይ
ሁዳ፡ “ምራትህ ትዕማር ሴሰነች፤ እነሆ፡ በዝ
ሙት ፀነሰች” ብለው ነገሩት። ይሁዳም፥
“አውጡአትና በእሳት ትቃጠል” አለ። ፳፭እር
ስዋም ሲወስዱአት ወደ አማቷ እንዲህ ብላ
ላከች፤ “ተመልከት፡- ይህ ቀለበት፥ ይህ
ኩፌት፥ ይህ በትር የማን ነው? ይህስ ፅንስ
የማን ነው?” ፳፮ይሁዳም አይቶ “ከእኔ ይልቅ
ትዕማር እውነተኛ ሆነች፤ ልጄን ሴሎምን አል
ሰጠኋትምና” አለ። ትገደል ማለትንም ተወ፤[፩]
ደግሞም አላወቃትም። ፳፯መውለጃዋም በደረሰ
ጊዜ እነሆ፥ መንታ ልጆች በሆድዋ ነበሩ።
፳፰ስትወልድም አንዱ እጁን አወጣ፤ አዋላጂ
ቱም ቀይ ፈትል ወስዳ በእጁ አሰረች፥ “ይህ
መጀመሪያ ይወጣል” አለች። ፳፱እንዲህም ሆነ፤
እጁን በመለሰ ጊዜ እነሆ፥ ወንድሙ ወጣ፤ እር
ስዋም፥ “ለምን ጥሰህ ወጣህ? ስትል ስሙን
ፋሬስ” ብላ ጠራችው። ፴ከእርሱም በኋላ ቀይ
ፈትል በእጁ ያለበት ወንድሙ ወጣ፤ ስሙም
ዛራ ተባለ።

## ምዕራፍ ፴፱

### ዮሴፍ በጲጥፋራ ቤት

፩ዮሴፍ ግን ወደ ግብፅ ወረደ፤ የፈርዖን ጃን
ደረባ የመጋቢዎቹም አለቃ የሚሆን የግብፅ
ሰው ጲጥፋራ ወደ ግብፅ ከአወረዱት ከይስማኤ
ላውያን እጅ ገዛው። ፪እግዚአብሔርም ከዮሴፍ
ጋር ነበር፤ ሥራውም የተከናወነለት ሰው ሆነ፤
በግብፃዊው ጌታውም ቤት ተሾመ። ፫ጌታውም
እግዚአብሔር ከዮሴፍ ጋር እንዳለ፥ እርሱ የሚ
ሠራውንም ሁሉ እግዚአብሔር በእጁ እንዲያከ
ናውንለት አየ። ፬ዮሴፍም በጌታው ፊት ሞገስን
አገኘ፤ እርሱንም ደስ ያሰኘው ነበር፤ በቤቱም
ላይ ሾመው፤ ያለውንም ሁሉ በእጁ ሰጠው።
፭እንዲህም ሆነ፤ በቤቱ ባለውም ሁሉ ላይ ከሾ
መው በኋላ እግዚአብሔር የግብፃዊውን ቤት
በዮሴፍ ምክንያት ባረከው። የእግዚአብሔርም
በረከት በቤቱም፥ በእርሻውም ባለው ሁሉ ላይ
ሆነ። ፮ያለውንም ሁሉ ለዮሴፍ በእጁ አስረከ
በው፤ ከሚበላውም እንጀራ በቀር ምንም የሚ
ያውቀው አልነበረም። ዮሴፍም መልኩ ያማረ፥
ፊቱም እጅግ የተዋበ ነበር።

፯ከዚህም በኋላ እንዲህ ሆነ፤ የጌታው ሚስት
በዮሴፍ ላይ ዐይንዋን ጣለችበት፤ “ከእኔም
ጋር ተኛ” አለችው። ፰እርሱም እንቢ አለ፤
ለጌታውም ሚስት እንዲህ አላት፥ “እነሆ፥
ጌታዬ በቤቱ ያለውን ሁሉ ለእኔ በእጄ አስ
ረክቦኛል፤ በቤቱ ያለውንም ምንም የሚያው
ቀው የለም፤ ፱በዚህ ቤት ከእኔ የሚበልጥ ሰው
የለም፤ ሚስቱ ስለሆንሽ ከአንቺ በቀር ያልሰ
ጠኝ ነገር የለም፤ እንዴት ይህን ትልቅ ክፉ
ነገር አደርጋለሁ? በእግዚአብሔር ፊት እንዴት
ኀጢአትን እሠራለሁ?” ፲ይህንም ነገር በየዕ
ለቱ ለዮሴፍ ትነግረው ነበር፤ እርሱም ከእር
ስዋ ጋር ይተኛ ዘንድ፥ ከእርስዋም ጋር ይሆን
ዘንድ አልሰማትም። ፲፩በአንዲትም ቀን እንዲህ
ሆነ፤ በዚያ ቀን ሥራውን እንዲሠራ ዮሴፍ
ወደ ቤቱ ገባ፤ በቤትም ውስጥ ከቤተ ሰዎች
ማንም አልነበረም። ፲፪ልብሱን ይዛ፥ “ና ከእኔ
ጋር ተኛ” አለችው፤ እርሱም ልብሱን በእ
ጅዋ ትቶላት ሸሸ፤ ወደ ውጭም ወጣ። ፲፫እን
ዲህም ሆነ፤ ልብሱን ትቶ ወደ ውጭ እንደ
ሸሸ በአየች ጊዜ፥ ፲፬የቤቷን ሰዎች ወደ እርስዋ
ጠርታ እንዲህ ብላ ነገረቻቸው፥ “እዩ፤ ይህ
ዕብራዊ ባርያ በእኛ እንዲሣለቅ አመጣብን፤
እርሱ ወደ እኔ ገብቶ ከእኔ ጋር ተኚ አለኝ፤
እኔም ድምፄን ከፍ አድርጌ ጮኽሁ፤ ፲፭ድም
ፄንም ከፍ አድርጌ እንደ ጮኽሁ ቢሰማ፥ ልብ
ሱን በእኔ ዘንድ ጥሎ ሸሸ፤ ወደ ውጭም
ወጣ።” ፲፮ጌታው ወደ ቤቱ እስኪገባ ድረስም
ልብሱን ከእርስዋ ዘንድ አኖረች። ፲፯ይህንም
ነገር እንዲህ ብላ ነገረችው፥ “ያመጣኸው ዕብ
ራዊው ባሪያ ሊሣለቅብኝ ወደ እኔ ገባ፤ ከአን
ቺም ጋር ልተኛ አለኝ። ፲፰እኔም ድምፄን ከፍ
አድርጌ ስጮኽ ልብሱን በእጄ ተወና ወደ
ውጭ ሸሸ።”

፲፱ጌታውም፥ “ባሪያህ እንዲህ አደረገኝ”
ብላ የነገረችውን የሚስቱን ቃል በሰማ ጊዜ
እጅግ ተቈጣ። ፳ዮሴፍንም ወሰደው፤ የንጉሡ
እስረኞች ወደሚታሰሩበት ስፍራ ወደ ግዞት
ቤትም አገባው፤ ከዚያም በግዞት ነበረ። ፳፩እግ

---

፩ “ትገደል ማለትንም ተወ” በግእዝ ብቻ ነው።

ዚአብሔርም ከዮሴፍ ጋር ነበረ፤ ምሕረትንም
አበዛለት፤ በግዞት ቤቱም አለቃ ፊት ሞገስን
ሰጠው። ፳፪የግዞት ቤቱም አለቃ በግዞት ያሉ
ትን እስረኞች ሁሉ በዮሴፍ እጅ አሳልፎ ሰጣ
ቸው፤ በዚያም የሚደረገው ነገር ሁሉ እርሱ
የሚያደርገው ነበረ። ፳፫የግዞት ቤቱ ጠባቂ
ዎች አለቃም በግዞት ቤት የሚደረገውን ሁሉ
ምንም አያውቅም ነበር፤ ሁሉን ለዮሴፍ ትቶ
ለት ነበር፤ እግዚአብሔርም ከእርሱ ጋር ነበ
ረና፤ የሚያደርገውንም ሁሉ እግዚአብሔር
በእጁ ያቀናለት ነበር።

## ምዕራፍ ፵

### ዮሴፍ የእስረኞችን ሕልም እንደ ተረጐመ

፩ከዚህ ነገር በኋላም እንዲህ ሆነ፤ የግብፅ
ንጉሥ የጠጅ አሳላፊዎች አለቃና የእንጀራ
አበዛዎች አለቃ ጌታቸውን የግብፅ ንጉሥን
በደሉ። ፪ፈርዖንም በሁለቱ ሹሞች በጠጅ አሳ
ላፊዎቹ አለቃና በእንጀራ አበዛዎቹ አለቃ ላይ
ተቈጣ፤ ፫በእስር ቤት ውስጥም ዮሴፍ ታስሮ
በነበረበት የግዞት ስፍራ አጋዛቸው። ፬የእስር
ቤቱ ዘበኞች አለቃም ለዮሴፍ አሳልፎ ሰጣ
ቸው፤ እርሱም ያገለግላቸው ነበር፤ በግዞት
ቤትም አንድ ዓመት ተቀመጡ። ፭ሁለቱም በአ
ንዲት ሌሊት ሕልምን አለሙ። በግዞት ቤት
የነበሩት የግብፅ ንጉሥ ጠጅ አሳላፊዎች አለ
ቃና የእንጀራ አበዛዎች አለቃ ሁለቱም እየራሳ
ቸው ሕልምን አለሙ። ፮ዮሴፍም ማልዶ ወደ
እነርሱ ገባ፤ እነሆም፥ አዝነው አያቸው። ፯በጌ
ታው ቤት ከእርሱ ጋር በግዞት የነበሩትንም የፈ
ርዖን ሹሞች እንዲህ ብሎ ጠየቃቸው፥ “እና
ንት ዛሬ ስለምን አዝናችኋል?” ፰እነርሱም፥
“ሕልምን አልመን የሚተረጕምልን አጣን”
አሉት። ዮሴፍም አላቸው፥ “ሕልምን የሚ
ተረጕም እግዚአብሔር የሰጠው አይደለምን?
እስቲ ንገሩኝ፤ ሕልማችሁ ምንድን ነው?”
፱የጠጅ አሳላፊዎች አለቃም ለዮሴፍ ሕል
ሙን እንዲህ ብሎ ነገረው፥ “በሕልሜ የወ
ይን ሐረግ በፊቴ ሆና አየሁ፥ ፲በሐረጉም
ሦስት ቅርንጫፎች ወጡ፤ እርስዋም ቅጠልና
አበባ አወጣች፤ ዘለላም አንጠለጠለች፤ የዘለ
ላዋም ፍሬ በሰለ፤ ፲፩የፈርዖንም ጽዋ በእጄ
ነበር፤ ፍሬውንም ወስጄ በፈርዖን ጽዋ ጨመ
ቅሁት፤ ጽዋዉንም ለፈርዖን በእጁ ሰጠሁት።”
፲፪ዮሴፍም አለው፥ “የሕልምህ ትርጓሜው
ይህ ነው፤ ሦስት ቅርንጫፎች ሦስት ቀኖች
ናቸው። ፲፫እስከ ሦስት ቀንም ድረስ ፈርዖን
ሹመትህን ያስባል፤ ወደ ጠጅ አሳላፊዎች አለ
ቃነትህም ይመልስሃል፤ ጠጅ አሳላፊ በነበርህ
በት ጊዜ ስታደርገው እንደ ነበረው እንደ ቀድ
ሞው ሹመትህም የፈርዖንን ጽዋ በእጁ ትሰ
ጣለህ። ፲፬ነገር ግን በጎ ነገር በተደረገልህ ጊዜ
እኔን ዐስበኝ፤ ምሕረትንም አድርግልኝ፤ ስለ
እኔም ለፈርዖን አሳስበህ ከዚህ እስር ቤት አው
ጣኝ፤ ፲፭ሌቦች በስውር ከዕብራውያን ሀገር ሰር
ቀውኛልና፤ በዚህም ደግሞ ምንም ያደረግሁት
ሳይኖር በግዞት ቤት አኑረውኛልና።”
፲፮የእንጀራ አበዛዎቹ አለቃም ሕልሙን በመ
ልካም እንደ ተረጐመለት በአየ ጊዜ ዮሴፍን
እንዲህ አለው፥ “እኔም ደግሞ ሕልም አይች
ነበር፤ እነሆም፥ ሦስት መሶብ ነጭ እንጀራ
በራሴ ላይ ነበረ፤ ፲፯በላይኛውም መሶብ ፈርዖን
የሚበላው ጋጋሪው በያይነቱ የሠራው መብል
ነበረበት፤ ወፎችም በራሴ ላይ ከመሶቡ ይበሉ
ነበር።” ፲፰ዮሴፍም መልሶ እንዲህ አለው፥
“የሕልምህ ትርጓሜው ይህ ነው፤ ሦስቱ
መሶብ ሦስት ቀን ነው፤ ፲፱እስከ ሦስት ቀን
ድረስ ፈርዖን ራስህን ይቈርጥሃል፤ በዕንጨ
ትም ላይ ይሰቅልሃል፤ የሰማይ ወፎችም ሥጋ
ህን ይበሉታል።” ፳እንዲህም ሆነ፤ በሦስተኛው
ቀን ፈርዖን የተወለደበት ዕለት ነበር፤ ለሠራዊ
ቱም ሁሉ ግብር አደረገ፤ የጠጅ አሳላፊዎቹን
አለቃና የእንጀራ አበዛዎቹን አለቃ በአሽከሮቹ
መካከል ዐሰበ። ፳፩የጠጅ አሳላፊዎቹንም አለቃ
ወደ ሹመቱ መለሰው፤ ጽዋውንም በፈርዖን
እጅ ሰጠ፤ ፳፪የእንጀራ አበዛዎቹንም አለቃ በዕ
ንጨት ላይ ሰቀለው፤ ዮሴፍ እንደ ተረጐመላ
ቸው። ፳፫የጠጅ አሳላፊዎች አለቃ ግን ዮሴፍን
አላሰበውም፤ ረሳው እንጂ።

## ምዕራፍ ፵፩

### ዮሴፍ የፈርዖንን ሕልም እንደ ተረጐመ

፩ከሁለት ዓመት በኋላም ፈርዖን ሕልምን
አየ፤ እነሆም፥ በወንዙ ዳር ቆሞ ነበር። ፪እነ
ሆም፥ መልካቸው ያማረ፥ ሥጋቸውም የወ
ፈረ ሰባት ላሞች ከወንዙ ወጡ፤ በወንዙም
ዳር በመስኩ ይሰማሩ ነበር። ፫ከእነርሱም በኋላ
እነሆ፥ መልካቸው የከፋ፥ ሥጋቸውም የከሳ
ሌሎች ሰባት ላሞች ከወንዙ ወጡ፤ በእነዚ
ያም ላሞች አጠገብ በወንዙ ዳር ተሰማርተው
ነበር። ፬መልካቸው የከፋ፥ ሥጋቸውም የከሳ
እነዚያ ሰባት ላሞች መልካቸው ያማረውን፥

ሥጋቸውም የወፈረውን ሰባቱን ላሞች ዋጡአ
ቸው። ፈርዖንም ነቃ፤ ፭ደግሞም ተኛ፤ ሁለ
ተኛ ሕልምንም አየ፤ እነሆም፥ በአንድ አገዳ
ላይ የነበሩ፥ ያማሩና ምርጥ የሆኑ ሰባት እሸ
ቶች ወጡ፤ ፮እነሆም፥ ከእነርሱ በኋላ የሰለቱና
በነፋስ የተመቱ ሰባት እሸቶች ወጡ፤ ፯እነዚ
ያም የሰለቱና ነፋስ የመታቸው እሸቶች ሰባቱን
ያማሩና የጐመሩ እሸቶች ዋጡአቸው። ፈርዖ
ንም ነቃ፤ እነሆም ሕልም ነበር። ፰በነጋም ጊዜ
መንፈሱ ታወከችበት፤ የግብፅ ሕልም ተርጓ
ሚዎችንና ጠቢባንን ሁሉ ልኮ አስጠራቸው፤
ፈርዖንም ሕልሙን ነገራቸው፤ ነገር ግን ከእ
ነርሱ ለፈርዖን ሕልሙን የሚተረጒምለት አል
ተገኘም።

፱የዚያን ጊዜ የጠጅ አሳላፊዎቹ አለቃ እን
ዲህ ብሎ ለፈርዖን ተናገረ፥ "እኔ ኀጢአ
ቴን ዛሬ አስባለሁ፤ ፲ፈርዖን በአገልጋዮቹ ላይ
ተቈጣ፤ እኔንም የእንጀራ አበዛዎቹንም አለቃ
በግዞት ቤት አኖረን፤ ፲፩እኛም በአንዲት ሌሊት
ሕልምን አለምን፤ እኔና እርሱ እያንዳንዳችን
እንደ ሕልማችን ትርጓሜ አለምን። ፲፪በዚያም
የእንጀራ አበዛዎች[፩] አለቃ አገልጋይ የሆነ አንድ
ዕብራዊ ጐልማሳ ከእኛ ጋር ነበር፤ ለእርሱም
ነገርነው፤ ሕልማችንንም ተረጐመልን። ፲፫እንዲ
ህም ሆነ፤ እንደ ተረጐመልን እንደዚያው ሆነ፤
እኔ ወደ ሹመቴ ተመለስሁ፤ እርሱም ተሰ
ቀለ።"

፲፬ፈርዖንም ልኮ ዮሴፍን አስጠራው፤ ከግዞት
ቤትም አወጡት፤ ራሱንም ላጩት፤ ልብሱንም
ለወጡ፤ ወደ ፈርዖንም ገባ። ፲፭ፈርዖንም ዮሴ
ፍን አለው፥ "ሕልምን አየሁ፤ የሚተረጕም
ልኝም አጣሁ፤ ሕልምን እንደ ሰማህ፥ እንደ
ተረጐምህም ስለ አንተ ሰማሁ።" ፲፮ዮሴፍም፥
"እግዚአብሔር ከገለጸለት ሰው በቀር መተ
ርጐም የሚችል የለም" ብሎ ለፈርዖን መለ
ሰለት። ፲፯ፈርዖንም ለዮሴፍ እንዲህ አለው፥
"እነሆ፥ በሕልሜ በወንዝ ዳር ቆሜ ነበር፤
፲፰እነሆም፥ ሥጋቸው የወፈረ፥ መልካቸውም
ያማረ ሰባት ላሞች ወጡ፤ በወንዙ ዳር በመስ
ኩም ይሰማሩ ነበር፤ ፲፱ከእነርሱም በኋላ እነሆ፥
የደከሙ፥ መልካቸውም እጅግ የከፋ፥ ሥጋቸ
ውም የከሳ ሌሎች ሰባት ላሞች ከወንዙ ወጡ፤
በግብፅም ምድር ሁሉ እንደ እነርሱ መልከ ክፉ
ከቶ አላየሁም፤ ፳እነዚያ የከሱትና መልከ ክፉ
ዎቹ ላሞች እነዚያን የመጀመሪያዎቹን ያማሩና
የወፈሩ ሰባት ላሞች ዋጡአቸው፤ በሆዳቸውም
ተዋጡ፤ ፳፩በሆዳቸውም ውስጥ የገባ እንደሌለ
ሆኑ፤ መልካቸውም በመጀመሪያ እንደ ነበረው
የከፋ ነበረ፤ ነቃሁም። ዳግመኛም ተኛሁ፤
፳፪በሕልሜም እነሆ፥ የጐመሩና መልካም የሆኑ
ሰባት እሸቶች ከአንድ አገዳ ሲወጡ አየሁ፤
፳፫ከእነርሱም በኋላ እነሆ የሰለቱና በነፋስ የተ
መቱ ሌሎች ሰባት እሸቶች ወጡ፤ ፳፬እነዚያ
የሰለቱትና በነፋስ የተመቱት እሸቶች እነዚያን
ያማሩትንና የጐመሩትን ሰባቱን እሸቶች ዋጡ
አቸው። ለሕልም ተርጓሚዎችም ሕልሜን ነገ
ርሁ፤ የተረጐመልኝም የለም።"

፳፭ዮሴፍም ፈርዖንን አለው፥ "የፈርዖን
ሕልሙ አንድ ነው፤ እግዚአብሔር ሊያደርገው
ያለውን ለፈርዖን አሳይቶታል። ፳፮እነዚያ ሰባቱ
መልካካሞች ላሞች ሰባት ዓመታት ናቸው፤ እነ
ዚያም ሰባቱ መልካካሞች እሸቶች ሰባት ዓመ
ታት ናቸው፤ የፈርዖን ሕልሙ አንድ ነው።
፳፯ከእነርሱም በኋላ የወጡት እነዚያ የከሱና
መልከ ክፉዎቹ ሰባት ላሞች ሰባት ዓመታት
ናቸው፤ እነዚያም የሰለቱትና ነፋስ የመታቸው
ሰባቱ እሸቶች እነርሱ ራብ የሚሆንባቸው ሰባት
ዓመታት ናቸው። ፳፰ለፈርዖን የነገርሁት ነገር
ይህ ነው፤ እግዚአብሔር ሊያደርገው ያለውን
ለፈርዖን አሳየው። ፳፱እነሆ፥ በግብፅ ምድር ሁሉ
እጅግ ጥጋብ የሚሆንባቸው ሰባት ዓመታት ይመ
ጣሉ፤ ፴ደግሞም ከዚህ በኋላ ሰባት የራብ ዓመት
ይመጣል፤ በግብፅ ሀገር ሁሉ የነበረውንም
ጥጋብ ሁሉ ይረሱታል፤ ራብም ምድርን ሁሉ
ያጠፋል፤ ፴፩በኋላም ከሚሆነው ከዚያ ራብ የተ
ነሣ በምድር የሆነው ጥጋብ አይታወቅም፤ እጅግ
ጽኑ ይሆናልና። ፴፪ሕልሙም ለፈርዖን ደጋግሞ
መታየቱ ነገሩ ከእግዚአብሔር ዘንድ የተቈረጠ
ስለሆነ ነው፤ እግዚአብሔርም ፈጥኖ ያደርገዋል።
፴፫አሁንም ብልህና ዐዋቂ ሰውን ለአንተ ፈልግ፤
በግብፅ ምድር ላይም ሹመው። ፴፬ፈርዖን በግብፅ
ምድር ላይ ሹሞችን ይሹም፤ በሰባቱም የጥጋብ
ዓመታት ከሚገኘው ፍሬ በግብፅ ምድር ሁሉ
ከአምስት እጅ አንደኛውን ይውሰድ። ፴፭የሚ
መጡትን የመልካሞቹን ሰባት ዓመታት እህላ
ቸውን ያከማቹ፤ ስንዴውንም ከፈርዖን እጅ
በታች ያኑሩ፤ እህሎችም በከተሞች ይጠበቁ።
፴፮በግብፅ ምድር ስለሚሆነው ስለ ሰባቱ ዓመ
ታት ራብ እህሉ ለሀገሩ ሁሉ ተጠብቆ ይኑር፥
ምድሪቱም በራብ አትጠፋም።"

---

፩ ዕብ. "የዘብ ጥበቃ አለቃ" ይላል።

### ዮሴፍ በግብፅ አዛዥ እንደ ሆነ

፴፯ነገሩም ፈርዖንንና ሰዎቹን ሁሉ ደስ አሰ
ኛቸው፤ ፴፰ፈርዖንም ሎሌዎቹን እንዲህ አላ
ቸው፥ “በውኑ የእግዚአብሔር መንፈስ ያለበ
ትን እንደዚህ ያለ ሰውን እናገኛለን?” ፴፱ፈር
ዖንም ዮሴፍን አለው፥ “እግዚአብሔር ይህን
ሁሉ ገልጦልሃልና ከአንተ ይልቅ ብልህና ዐዋቂ
ሰው የለም። ፵አንተ በቤቴ ላይ ተሾም፤ ሕዝ
ቤም ሁሉ ለቃልህ ይታዘዝ፤ እኔም ከዙፋኔ
በቀር ከአንተ የምበልጥበት የለም።” ፵፩ፈርዖ
ንም ዮሴፍን፥ “በግብፅ ምድር ሁሉ ላይ ሾም
ሁህ” አለው። ፵፪ፈርዖን ቀለበቱን ከእጁ አወ
ለቀ፤ በዮሴፍም እጅ አደረገው፤ የነጭ ሐር
ልብስንም አለበሰው፤ በአንገቱም የወርቅ ዝር
ግፍን አደረገለት፤ ፵፫የእርሱም በምትሆን በሁ
ለተኛይቱ ሰረገላ አስቀመጠው፤ ስገዱ እያለም
በፊት በፊቱ አዋጅ ነጋሪ እንዲሄድ አደረገ፤[፪]
በግብፅ ምድር ሁሉ ላይም ሾመው። ፵፬ፈርዖ
ንም ዮሴፍን አለው፥ “እኔ ራሴ ፈርዖን ነኝ፤
በግብፅ ሀገር ሁሉ ያለ አንተ ማንም እጁን[፫]
አያንሣ።” ፵፭ፈርዖንም የዮሴፍን ስም “እስፍን
ቶፎኔህ” ብሎ ጠራው፤ የሄልዮቱ ከተማ ካህን
የጴጤፌራ ልጅ የምትሆን አስኔትንም ሚስት
ትሆነው ዘንድ ሰጠው።

፵፮ዮሴፍም በግብፅ ንጉሥ በፈርዖን ፊት
በቆመ ጊዜ ዕድሜው ሠላሳ ዓመት ነበረ። ዮሴ
ፍም ከፈርዖን ፊት ወጣ፤ የግብፅ ምድርንም
ሁሉ ዞረ። ፵፯በሰባቱም የጥጋብ ዓመታት ግብፅ
ያስገኘችው እህል ሁሉ ክምር ሆነ። ፵፰በግብፅ
ምድር ሁሉ ያለውን የሰባቱን የጥጋብ ዓመታት
እህል ሁሉ ሰበሰበ፤ እህልንም በከተሞቹ አደ
ለበ፤ በየከተማይቱም ዙሪያ ያለውን የእርሻ
ውን እህል ሁሉ በዚያው ከተተ። ፵፱ዮሴፍም
እንደ ባሕር አሸዋ እጅግ ብዙ የሆነ ስንዴን
አከማቸ፤ መስፈር እስኪሳናቸው ድረስ፤ ሊሰ
ፈር አልተቻለምና።

፶ለዮሴፍም የሄልዮቱ ከተማ ካህን የጴጤፌራ
ልጅ አስኔት የወለደችለት ሁለት ልጆች የራብ
ዘመን ገና ሳይመጣ ተወለዱለት። ፶፩ዮሴፍም
የበኵር ልጁን ስም ምናሴ ብሎ ጠራው፤ እን
ዲህ ሲል፥ “እግዚአብሔር መከራዬን ሁሉ የአ
ባቴንም ቤት እንድረሳ አደረገኝ፤” ፶፪የሁለተኛ
ውንም ስም ኤፍሬም ብሎ ጠራው፤ እንዲህ
ሲል፥ “እግዚአብሔር በመከራዬ ሀገር አብዝ
ቶኛልና።”

፶፫በግብፅ ምድር የነበረውም ሰባቱ የጥ
ጋብ ዓመት አለፈ፤ ፶፬ዮሴፍም እንደ ተናገረ
ሰባቱ የራብ ዓመት መምጣት ጀመረ። በየሀገ
ሩም ሁሉ ራብ ሆነ፤ በግብፅ ምድር ሁሉ ግን
እህል ነበረ። ፶፭የግብፅ ምድርም ሁሉ ተራበ፤
ሕዝቡም ስለ እህል ወደ ፈርዖን ጮኸ፤ ፈር
ዖንም የግብፅ ሰዎችን ሁሉ፥ “ወደ ዮሴፍ
ሂዱ፤ እርሱ ያላችሁንም ሁሉ አድርጉ” አላ
ቸው። ፶፮በምድርም ሁሉ ላይ ራብ ሆነ፤ ዮሴ
ፍም እህል ያለበትን ጎተራ ሁሉ ከፍቶ ለግብፅ
ሰዎች ሁሉ ይሸጥ ነበር።[፬] ፶፯ሀገሮችም ሁሉ
ከዮሴፍ እህል ይገዙ ዘንድ ወደ ግብፅ ወጡ፤
በምድር ሁሉ ራብ እጅግ ጸንቶ ነበርና።

## ምዕራፍ ፵፪

### የዮሴፍ ወንድሞች ወደ ግብፅ እንደ ሄዱ

፩ያዕቆብም በግብፅ የሚሸመት እህል እንዳለ
ሰማ፤ ልጆቹንም፥ “ለምን ትተክዛላችሁ?”
አላቸው። ፪እንዲህም አለ፥ “እነሆ፥ እህል በግ
ብፅ እንዳለ ሰምቼአለሁ፤ ወደዚያ ውረዱ፤ እን
ድንድንና በራብ እንዳንሞትም ከዚያ ሸምቱ
ልን። ፫የዮሴፍም ዐሥሩ ወንድሞቹ እህልን ከግ
ብፅ ይሸምቱ ዘንድ ወረዱ፤ ፬የዮሴፍን ወንድም
ብንያምን ግን ያዕቆብ ከወንድሞቹ ጋር አልሰደ
ደውም፥ “ምናልባት ክፉ እንዳያገኘው” ብሎ
አልና። ፭የእስራኤልም ልጆች ለእህል ሸመታ
ከመጡት ጋር ገቡ፤ በከነዓን ሀገር ራብ ነበ
ርና። ፮ዮሴፍም በግብፅ ምድር ላይ ገዥ ነበረ፤
እርሱም ለምድር ሕዝብ ሁሉ እህል ይሸጥ
ነበር፤ የዮሴፍም ወንድሞች በመጡ ጊዜ በም
ድር ላይ በግንባራቸው ሰገዱለት። ፯ዮሴፍም
ወንድሞቹን በአያቸው ጊዜ ዐወቃቸው፤ እን
ደማያውቃቸውም ሆነ፤ ክፉ ቃልንም ተናገ
ራቸው፥ “እናንተ ከወዴት መጣችሁ?” አላ
ቸው። እነርሱም፥ “ከከነዓን ምድር እህል ልን
ሸምት የመጣን ነን” አሉት። ፰ዮሴፍም ወንድ
ሞቹን ዐወቃቸው፤ እነርሱ ግን አላወቁትም፤
ዮሴፍም አይቶት የነበረውን ሕልም ዐሰበ።
፱እንዲህም አላቸው፥ “እናንተ ሰላዮች ናችሁ፤

---

[፪] ዕብ. “አዋጅ ነጋሪም ስገዱ እያለ በፊቱ ይጮኽ ነበር” ይላል።

[፫] ዕብ. “እጁንም እግሩንም” ይላል።

[፬] ዕብ. ምዕ. ፵፩ ቍ. ፶፮ መጨረሻ “ራብም በግብፅ ምድር ጸንቶ ነበር” የሚል ይጨምራል።

የሀገሩን ሁኔታ ልታዩ መጥታችኋል።” ፲እነር
ሱም አሉት፥ “ጌታ ሆይ፥ አይደለም፤ ባሪያዎ
ችህስ ስንዴ ሊገዙ መጥተዋል፤ ፲፩እኛ ሁላችን
የአንድ ሰው ልጆች ነን፤ እኛ የሰላም ሰዎች
ነን፤ ባሪያዎችህስ ሰላዮች አይደሉም።” ፲፪እር
ሱም አላቸው፥ “አይደለም፤ ነገር ግን እና
ንተ ሰላዮች ናችሁ፤ የሀገሩንም ሁኔታ ልታዩ
መጥታችኋል።” ፲፫እነርሱም አሉ፥ “ባሪያዎ
ችህ በከነዓን ምድር የምንኖር ዐሥራ ሁለት
ወንድማማቾች ነን፤፩ ታናሹም እነሆ ዛሬ ከአ
ባታችን ጋር ነው፤ ሌላውም ሞቶአል።” ፲፬ዮሴ
ፍም አላቸው፥ “እናንተ ሰላዮች ናችሁ ብዬ
የተናገርሁአችሁም ይህ ነው፤ በዚህ ትታወ
ቃላችሁ፤ ፲፭ታናሽ ወንድማችሁን ከአላመጣ
ችሁ በቀር ‘የፈርዖንን ሕይወት!’ ከዚህ አትወ
ጡም። ፲፮ወንድማችሁን ያመጣ ዘንድ ከእናንት
አንዱን ላኩ፤ እናንተ ግን እውነትን የምትናገሩ
ከሆነ ወይም ከአልሆነ ነገራችሁ እስኪታወቅ
ድረስ ከዚህ ተቀመጡ፤ ይህ ከአልሆነ ‘የፈርዖ
ንን ሕይወት!’ ሰላዮች ናችሁ።” ፲፯ሦስት ቀን
ያህልም በግዞት ቤት ጨመራቸው።

፲፰በሦስተኛው ቀን ዮሴፍ እንዲህ አላቸው፥
“ትድኑ ዘንድ ይህን አድርጉ፤ እኔ እግዚአብሔ
ርን እፈራለሁና። ፲፱እናንተ ሰላማውያን ከሆና
ችሁ ከእናንተ አንዱ ወንድማችሁ በግዞት ቤት
ይታሰር፤ እናንተ ግን ሂዱ፤ የሸመታችሁትን
እህልም ውሰዱ፤፪ ፳ታናሹንም ወንድማችሁን
ወደ እኔ አምጡ፤ ነገራችሁ የታመነ ይሆናልና፤
ይህ ከአልሆነ ግን ትሞታላችሁ።” እንዲህም
አደረጉ። ፳፩እነርሱም እርስ በርሳቸው እንዲህ
ተባባሉ፥ “በእውነት ወንድማችንን በድለናል፤
እኛን በመማጠን ነፍሱ ስትጨነቅ አይተን አል
ሰማነውምና፤ ስለዚህ ይህ መከራ መጣብን።”
፳፪ሮቤልም መልሶ እንዲህ አላቸው፥ “ብላቴና
ውን አትበድሉ ብዬአችሁ አልነበረምን? እኔ
ንም አልሰማችሁኝም፤ ስለዚህ እነሆ፥ አሁን
ደሙ ይፈላለጋችኋል።” ፳፫እነርሱም ዮሴፍ ነገ
ራቸውን እንደሚሰማባቸው አላወቁም፤ በመካ
ከላቸው አስተርጓሚ ነበርና። ፳፬ዮሴፍም ከእነ
ርሱ ዘወር ብሎ አለቀሰ፤ ደግሞም ወደ እነርሱ
ተመልሶ ተናገራቸው፤ ስምዖንንም ከእነርሱ
ለይቶ ወስዶ በፊታቸው አሰረው። ፳፭ዮሴፍም
ዓይበታቸውን እህል ይሞሉት ዘንድ አዘዘ፤ የየ
ራሳቸውንም ብር በየዓይበታቸው ይመልሱት
ዘንድ፥ ደግሞም የመንገድ ስንቅ ይሰጡአቸው
ዘንድ አዘዘ። እንዲህም አደረጉ።

## የዮሴፍ ወንድሞች ወደ ከነዓን መመለሳቸው

፳፮እነርሱም እህሉን በአህዮቻቸው ላይ ጫኑ፤
ከዚያም ተነሥተው ሄዱ። ፳፯ከእነርሱም አንዱ
በአደሩበት ስፍራ ለአህዮቹ ገፈራን ይሰጥ ዘንድ
ዓይበቱን ፈታ፤ ብሩንም በዓይበቱ አፍ ተቋ
ጥሮ አገኘ። ፳፰ለወንድሞቹም፥ “ብሬ ተመለሰ
ችልኝ፤ እርስዋም በዓይበቱ አፍ እነኋት” አላ
ቸው። ልባቸውም ደነገጠ፤ እየታወኩም እርስ
በርሳቸው ተባባሉ፥ “እግዚአብሔር ያደረገብን
ይህ ምንድን ነው?” ፳፱ወደ አባታቸውም ወደ
ያዕቆብ ወደ ከነዓን ምድር መጡ፤ የደረሰባ
ቸውንም ነገር ሁሉ እንዲህ ብለው አወሩ፡-
፴“የሀገሩ ጌታ የሆነው ሰው በክፉ ንግግር ተና
ገረን፤ የምድሪቱም ሰላዮች እንደሆን አድርጎ
ወደ እስር ቤት አስገባን።” ፴፩እኛም እንዲህ
አልነው፥ “ሰላማውያን ሰዎች ነን እንጂ ሰላ
ዮች አይደለንም፤ ፴፪እኛ የአባታችን ልጆች
ዐሥራ ሁለት ወንድማማቾች ነን፤ አንዱ ሞቶ
አል፤ ታናሹም በከነዓን ምድር ዛሬ ከአባታ
ችን ጋር አለ። ፴፫የሀገሩም ጌታ ያ ሰው እንዲህ
አለን፡- ‘ሰላማውያን ሰዎች ከሆናችሁ በዚህ
ዐውቃለሁ፤ አንደኛውን ወንድማችሁን ከእኔ
ጋር ተዉት፤ ለቤታችሁም የሸመታችሁትን
እህል ይዛችሁ ሂዱ፤ ፴፬ታናሹንም ወንድማ
ችሁን አምጡልኝ፤ ሰላማውያን እንጂ ሰላዮች
አለመሆናችሁንም በዚህ ዐውቀዋለሁ፤ ወንድ
ማችሁንም እሰጣችኋለሁ፤ እናንተም በሀገራችን
ትነግዳላችሁ።’ ”

፴፭እንዲህም ሆነ፤ ዓይበታቸውን በፈቱ ጊዜ
እነሆ፥ ከእነርሱ እያንዳንዳቸው ብራቸውን በዓ
ይበታቸው ተቋጥሮ አገኙት፤ እነርሱም አባታ
ቸውም የተቋጠረ ብራቸውን አይተው ፈሩ።
፴፮አባታቸው ያዕቆብም እንዲህ አላቸው፥
“ልጅ አልባ አስቀራችሁኝ፤ ዮሴፍ የለም፤
ስምዖንም የለም፤ ብንያምንም ትወስዱብኛላ
ችሁ፤ ይህ ሁሉ በእኔ ላይ ደረሰ።” ፴፯ሮቤ
ልም አባቱን አለው፥ “ወደ አንተ መልሼ ያላ
መጣሁት እንደሆነ ሁለቱን ልጆችን ግደል፤
ልጅህን በእጄ ስጠኝ፤ እኔም ወደ አንተ እመ
ልሰዋለሁ።” ፴፰እርሱም አለ፥ “ልጄ ከእናንተ
ጋር አይወርድም፤ ወንድሙ ሞቶ እርሱ ብቻ

---

፩ ዕብ. “ባሪያዎችህ ዐሥራ ሁለት ወንድማማቾች በከነዓን ምድር የሚኖር የአንድ ሰው ልጆች ነን” ይላል።

፪ ዕብ. “እህሉንም ለተራቡት ቤተሰቦቻችሁ ውሰዱ።” ይላል።

ቀርቶአልና፤ በምትሄዱበት መንገድ ምናልባት
ክፉ ነገር ቢያገኘው ሽምግልናዬን በኀዘን ወደ
መቃብር ታወርዱታላችሁ።”

## ምዕራፍ ፵፫

### የዮሴፍ ወንድሞች ከብንያም ጋር ወደ ግብፅ እንደ ሄዱ

፩ከዚህም በኋላ ራብ በሀገር ላይ ጸና። ፪ከግብ
ፅም ያመጡትን እህል በልተው ከፈጸሙ በኋላ
አባታቸው፥ “እንደገና ሂዱ፤ ጥቂት እህል ሸም
ታችሁ አምጡልን” አላቸው። ፫ይሁዳም እን
ዲህ አለው፥ “የሀገሩ ጌታ ያ ሰው፦ ‘ወንድ
ማችሁ ከእናንተ ጋር ከአልመጣ ፊቴን አታ
ዩም’ ብሎ በምስክር ፊት አዳኝቶብናል። ፬ወን
ድማችንን ከእኛ ጋር ብትልከው እንወርዳለን፤
እህልም እንሸምትልሃለን፤ ፭ወንድማችንን ከእኛ
ጋር ባትልከው ግን አንሄድም፤ ያ ሰው ‘ታናሽ
ወንድማችሁን ከእናንተ ጋር ካላመጣችሁ ፊቴን
አታዩም’ ብሎናልና።” ፮እስራኤልም አላቸው፥
“በእኔ ላይ ያደረጋችኋት ይህች ክፋት ምንድን
ናት? በዚያውስ ላይ ሌላ ወንድም አለን ብላ
ችሁ ለምን ነገራችሁት? ፯እነርሱም አሉ፥ “ያ
ሰው ስለ እኛና ስለ ትውልዳችን ፈጽሞ ጠየ
ቀን፤ እንዲህም አለን፦ ‘ሽማግሌው አባታችሁ
ገና በሕይወት ነው? ወንድምስ አላችሁን?’
እኛም እንደዚሁ እንደ ጠየቀን መለስንለት፤
በውኑ፦ ‘ወንድማችሁን አምጡ’ እንዲለን እና
ውቅ ነበርን?” ፰ይሁዳም አባቱን እስራኤልን
አለው፥ “እኛና አንተ ልጆቻችንም ደግሞ እን
ድንድን፥ እንዳንሞትም ብላቴናውን ከእኔ ጋር
ላከው፤ እኛም ተነሥተን እንሄዳለን። ፱እኔ እዋ
ሳለሁ፤ ከእጄ ትሻዋለህ፤ ወደ አንተ ባላመ
ጣው፥ በፊትህም ባላቆመው፥ በዘመናት ሁሉ
አንተን የበደልሁህ ልሁን። ፲ባንዘገይስ ኖሮ
አሁን ሁለተኛ ጊዜ በተመለስን ነበር።” ፲፩አባ
ታቸው እስራኤልም እንዲህ አላቸው፥ “ነገሩ
እንዲህ ከሆነስ ይህን አድርጉ፤ ከምድሩ ፍሬ
በዓይበታችሁ ይዛችሁ ሂዱ፤ ለዚያም ሰው እጅ
መንሻ፥ ጥቂት በለሳን፥ ጥቂት ማር፥ ሽቱ፥
ዕጣን፥ ተምር፥ ለውዝ ውሰዱ። ፲፪ብሩን በእ
ጠፌታ አድርጋችሁ በእጃችሁ ውሰዱ፤ በዓይ
በታችሁም አፍ የተመለሰውን ብር መልሳችሁ
ውሰዱ፤ ምናልባት ባለማወቅ ይሆናል። ፲፫ወን
ድማችሁንም ከእናንተ ጋር ውሰዱ፤ ተነሥታች
ሁም ወደዚያ ሰው ውረዱ። ፲፬አምላኬም በዚያ
ሰው ፊት ሞገስን ይስጣችሁ፤ ያን ወንድማች
ሁንና ብንያምንም ይመልስላችሁ፤ እኔም ልጆ
ችን እንዳጣሁ አጣሁ።” ፲፭ሰዎቹም በእጃቸው
ያችን እጅ መንሻና ብራቸውን በእጥፍ፥ ብን
ያምንም ከእነርሱ ጋር ወሰዱ፤ ተነሥተውም
ወደ ግብፅ ወረዱ፤ በዮሴፍም ፊት ቆሙ፤ ሰገ
ዱለትም።

፲፮ዮሴፍም ብንያምን ከእነርሱ ጋር በአየው
ጊዜ የቤቱን አዛዥ እንዲህ ብሎ አዘዘው፥
“እነዚያን ሰዎች ወደ ቤት አስገባቸው፤ እር
ድም እረድ፤ አዘጋጅም፤ እነዚያ ሰዎች በእ
ኩለ ቀን ከእኔ ጋር ይበላሉና።” ፲፯ያም ሰው
ዮሴፍ እንዳለው አደረገ፤ ሰዎቹንም ወደ ዮሴፍ
ቤት አስገባ። ፲፰እነዚያም ሰዎች ወደ ዮሴፍ
ቤት እንደ ገቡ በአዩ ጊዜ እንዲህ አሉ፥ “በዓ
ይበታችን ቀድሞ ስለ ተመለሰው ብር ሊተነኩ
ሉብን፥ ሊወድቁብንም፥ እኛንም በባርነት ሊገ
ዙን፥ አህዮቻችንንም ሊወስዱ ወደዚህ አስገ
ቡን።” ፲፱ወደ ዮሴፍ ቤት አዛዥም ቀረቡ፤ በቤ
ቱም ደጅ ተናገሩት፤ ፳እንዲህም አሉ፥ “ጌታ
ሆይ፥ እንማልድሃለን፤ ቀድሞ እህልን ልንሸ
ምት ወርደን ነበር፤ ፳፩እንዲህም ሆነ፥ ወደም
ናድርበትም ስፍራ በደረስን ጊዜ ዓይበታችንን
ከፈትን፤ እነሆም፥ የየአንዳንዱ ሰው ብር በየዓ
ይበቱ አፍ ነበር፤ አሁንም ብራችንን በእጃችን
እንደ ሚዛኑ መለስነው። ፳፪እህል እንሸምትበት
ዘንድ ሌላም ብር በእጃችን አመጣን፤ ብራች
ንንም በዓይበታችን ማን እንደ ጨመረው አና
ውቅም።” ፳፫እርሱም አላቸው፥ “ሰላም ለእ
ናንተ ይሁን፥ አትፍሩ፤ አምላካችሁ የአባቶቻ
ችሁ አምላክ በዓይበታችሁ የተሰወረ ገንዘብ
ሰጣችሁ፤ ብራችሁንስ መዝኜ ተቀብያለሁ።”
፳፬ስምዖንንም ወደ እነርሱ አወጣላቸው። እግራ
ቸውንም ሊታጠቡ ውኃ አመጣላቸው፤ ለአህ
ዮቻቸውም ገፈራ ሰጣቸው።[፩] ፳፭ዮሴፍም በእ
ኩለ ቀን እስኪገባ ድረስ እነርሱ እጅ መንሻ
ቸውን አዘጋጁ፤ ከዚያ ምሳ እንደሚበሉ ሰም
ተዋልና። ፳፮ዮሴፍም ወደ ቤቱ በገባ ጊዜ በእ
ጃቸው ያለውን እጅ መንሻ በቤት ውስጥ አቀ
ረቡለት፤ ወደ ምድርም በግንባራቸው ወድ
ቀው ሰገዱለት። ፳፯እርሱም ደኅንነታቸውን ጠየ
ቃቸው፤ እንዲህም አለ፥ “የነገራችሁኝ ሽማ

---

፩ ዕብ. ምዕ. ፵፫ በቍ. ፳፬ መጀመሪያ “ሰውየውም እነዚያን ሰዎች ወደ ዮሴፍ ቤት አስገባቸው” የሚል ይጨም
ራል።

ግሌ አባታችሁ ደኅና ነውን? ገና በሕይወት
አለን?” ፳፰እነርሱም አሉት፥ “ባሪያህ ሽማ
ግሌው አባታችን ደኅና ነው፤ ገና በሕይወት
አለ።” ዮሴፍም አለ፥ “ሰውየው እግዚአብሔር
የባረከው ነው።” ራሳቸውንም ዝቅ አድርገው
ሰገዱለት። ፳፱ዮሴፍም ዐይኑን አንሥቶ የእና
ቱን ልጅ ወንድሙ ብንያምን አየው፤ እርሱም
አለ፤ “ወደ አንተ እናመጣዋለን ብላችሁ የነገ
ራችሁኝ ታናሽ ወንድማችሁ ይህ ነውን?” እነ
ርሱም፣ “አዎን” አሉት። እንዲህም አለው፥
“ልጄ ሆይ፥ እግዚአብሔር ይቅር ይበልህ።”
፴ዮሴፍም ታወከ፤ አንጀቱ ወንድሙን ናፍቆ
ታልና፤ ሊያለቅስም ወደደ፤ ወደ እልፍኙም
ገብቶ በዚያ አለቀሰ። ፴፩ፊቱንም ታጥቦ ተጽ
ናንቶም ወጣ። “እንጀራ አቅርቡልን” አለ።
፴፪ለእርሱም ለብቻው አቀረቡ፤ ለእነርሱም
ለብቻቸው፤ ከእርሱ ጋር ለሚበሉት ለግብፅ
ሰዎችም ለብቻቸው፤ የግብፅ ሰዎች ከዕብራ
ውያን ጋር መብላት አይችሉምና፥ ይህ ለግ
ብፅ ሰዎች እንደ መርከስ ነውና። ፴፫በፊቱም
በኵሩ እንደ ታላቅነቱ፥ ታናሹም እንደ ታናሽ
ነቱ ተቀመጡ፤ እነርሱም እርስ በርሳቸው በመ
ደነቅ ተያዩ። ፴፬በፊቱም ከአለው መብል ፈንታ
ቸውን አቀረበላቸው፤ የብንያምም ፈንታ ከሁሉ
አምስት እጅ የሚበልጥ ነበረ። እነርሱም በሉ፤
ጠጡም፤ ከእርሱም ጋር ደስ አላቸው።

## ምዕራፍ ፵፬

### የጠፋው ጽዋዕ

፩ዮሴፍም የቤቱን አዛዥ እንዲህ ብሎ አዘ
ዘው፥ “የእነዚህ ሰዎች ዓይበቶቻቸው መያዝ
የሚችሉትን ያህል እህል ሙላላቸው፤ የሁሉ
ንም ብር በየዓይበታቸው አፍ ጨምረው፤ ፪በታ
ናሹም ዓይበት አፍ የብሩን ጽዋዬንና የእህሉን
ዋጋ ጨምረው።” እርሱም ዮሴፍ እንዳለው
አደረገ። ፫ነግህ በሆነ ጊዜም ሰዎቹ አህዮቻቸ
ውን ይዘው ይሄዱ ዘንድ አሰናበታቸው። ፬ከከ
ተማዪቱም ወጥተው ገና ሳይርቁ ዮሴፍ ለቤቱ
አዛዥ እንዲህ አለ፥ “ተነሥተህ ሰዎቹን ተከት
ለህ ያዛቸው፤ እንዲህም በላቸው፡- በመልካሙ
ፈንታ ስለምን ክፉን መለሳችሁ? ፭ጌታዬ የሚ
ጠጣበትን፥ ምስጢርንም የሚያውቅበትን የብር
ጽዋ ለምን ሰረቃችሁ? ባደረጋችሁት ነገር በደ
ላችሁ።” ፮እርሱም ሂዶ አገኛቸው፤ “ለምን
እንዲህ አደረጋችሁ? ስለ አደረግሁላችሁ መል
ካም ነገር ለምን ክፉ ትከፍሉኛላችሁ? የጌታ
ዬንስ የብር ጽዋ ለምን ሰረቃችሁኝ?” አላ
ቸው።፩ ፯እነርሱም አሉት፥ “ጌታችን እንደዚህ
ለምን ክፉ ትናገራለህ? ይህን ነገር ያደርጉት
ዘንድ ለባሪያዎችህ አግባባቸው አይደለም። ፰በየ
ዓይበታችን አፍ ያገኘነውን ብር እንኳን ይዘን
ከከነዓን ሀገር ወደ አንተ ተመልሰናል፤ ከጌታ
ህስ ቤት ወርቅ ወይስ ብር እንዴት እንሰርቃ
ለን? ፱አሁንም ከባሪያዎችህ ጽዋው የተገኘበት
እርሱ ይሙት፤ እኛም ደግሞ ለጌታችን አገል
ጋዮች እንሁን።” ፲እርሱም አለ፤ “አሁንም እን
ዲሁ እንደ ነገራችሁ ይሁን፤ ጽዋው የተገኘበት
እርሱ ለእኔ አገልጋይ ይሁነኝ፤ እናንተም ንጹ
ሓን ትሆናላችሁ።” ፲፩እየራሳቸውም ፈጥነው
ዓይበታቸውን ወደ ምድር አወረዱ፤ እየራሳ
ቸውም ዓይበታቸውን ፈቱ። ፲፪እርሱም ከታ
ላቁ ጀምሮ እስከ ታናሹ ድረስ በረበራቸው፤
ጽዋውንም በብንያም ዓይበት ውስጥ አገኘው።
፲፫ልብሳቸውንም ቀደዱ፤ ዓይበታቸውንም በየአ
ህዮቻቸው ጭነው ወደ ከተማዪቱ ተመለሱ።
፲፬ይሁዳም ከወንድሞቹ ጋር ወደ ዮሴፍ ገባ፤
እርሱም ገና ከዚያው ነበረ፤ በፊቱም በምድር
ላይ ወደቁ። ፲፭ዮሴፍም፥ “ይህ ያደረጋችሁት
ነገር ምንድን ነው? እንደ እኔ ያለ ሰው ምሥ
ጢርን እንዲያውቅ አታውቁምን?”፪ አላቸው።
፲፮ይሁዳም አለ፡- “ለጌታችን ምን እንመልሳ
ለን? ምንስ እንናገራለን? ወይስ በምን እንነጻ
ለን? እግዚአብሔር የአገልጋዮችህን ኀጢአት
ገለጠ። እነሆ፥ እኛም ጽዋው ከእርሱ ዘንድ የተ
ገኘበትም ደግሞ ለጌታችን አገልጋዮቹ ነን።”
፲፯ዮሴፍም አላቸው፥ “ይህን አደርግ ዘንድ
አይገባኝም፤ ጽዋው የተገኘበት ሰው እርሱ አገ
ልጋይ ይሁነኝ እንጂ፤ እናንተ ግን ወደ አባታ
ችሁ በደኅና ሂዱ።”

### ይሁዳ ስለ ብንያም ዮሴፍን መለመኑ

፲፰ይሁዳም ወደ እርሱ ቀረበ፤ እንዲህም አለ፥
“ጌታዬ ሆይ፥ እኔ አገልጋይህ በፊትህ አንዲት
ቃልን እንድናገር እለምናለሁ፤ እኔን አገልጋይ
ህን አትቈጣኝ፤ አንተ ከፈርዖን ቀጥለህ ነህና።
፲፱ጌታዬ አገልጋዮችህን፡- አባት አላችሁን?
ወይስ ወንድም? ብለህ ጠየቅሃቸው። ፳እኛም

---

፩ ግሪክ ሰባ. ሊ. እና ዕብ. ምዕ. ፵፬ ቍ. ፮ “እርሱም ሄዶ አገኛቸው ይህንም ቃል ነገራቸው” ይላል።

፪ “እንደ እኔ ያለ ሰው ምሥጢርን እንዲያውቅ አታውቁምን?” የሚለው ከግሪክ ሰባ. ሊ. እና ከዕብ. የተወሰደ ነው።

ለጌታዬ እንዲህ አልን፡- ሽማግሌ አባት አለን፤
በሽምግልናው የወለደውም ታናሽ ብላቴና አለ፤
ወንድሙ ግን ሞተ፤ ለእናቱም እርሱ ብቻውን
ቀረ፤ አባቱም ይወድደዋል። ፳፩ አንተም ለአገል
ጋዮችህ፡- ወደ እኔ አምጡት፤ እኔም እጠብ
ቀዋለሁ አልህ። ፳፪ ጌታዬንም፡- ብላቴናው አባ
ቱን መተው አይሆንለትም፤ የተወው እንደ ሆነ
አባቱ ይሞታልና አልንህ። ፳፫ አንተ ጌታችንም
አገልጋዮችህን፡- ታናሽ ወንድማችሁን ከእናንተ
ጋር ከአላመጣችሁት ዳግመኛ ፊቴን አታዩም
አልኸን። ፳፬ ወደ ባሪያህ ወደ አባታችን በተመ
ለስን ጊዜም የጌታችንን ቃል ነገርነው። ፳፭ አባ
ታችንም፡- ዳግመኛ ሄዳችሁ ጥቂት እህል ሸም
ቱልን አለን። ፳፮ እኛም አልነው፡- ታናሹ ወንድ
ማችን ከእኛ ጋር ካልሄደ መሄድ አንችልም፤
ታናሹ ወንድማችን ከእኛ ጋር ከሌለ የዚያን
ሰው ፊት ማየት አይቻለንምና። ፳፯ አገልጋይህ
አባታችንም እንዲህ አለን፡- ሚስቴ ሁለት ወን
ዶች ልጆችን እንደ ወለደችልኝ እናንተ ታው
ቃላችሁ፤ ፳፰ አንዱም ከእኔ ወጣ፤ አውሬ በላው
አላችሁኝ፤ እስከ ዛሬም ገና አላየሁትም፤ ፳፱ ይህ
ንም ከእኔ ለይታችሁ ደግሞ ብትወስዱት በመ
ንገድም ክፉ ቢያገኘው፥ እርጅናዬን በኀዘን
ወደ መቃብር ታወርዱታላችሁ። ፴ አሁንም እኛ
ወደ አባታችን ወደ አገልጋይህ ብንሄድ፥ ብላ
ቴናውም ከእኛ ጋር ከሌለ፥ ነፍሱ በብላቴናው
ነፍስ ታስራለችና ፴፩ ብላቴናው ከእኛ ጋር እን
ደሌለ በአየ ጊዜ ይሞታል፤ አገልጋዮችህም የአ
ገልጋይህን የአባታችንን እርጅና በኀዘን ወደ
መቃብር እናወርዳለን። ፴፪ እኔ አገልጋይህ በአ
ባቴ ዘንድ ስለ ብላቴናው እንዲህ ብዬ ተውሼ
አለሁና፡- እርሱንስ ወደ አንተ መልሼ በፊትህ
ባላቆመው በአባቴ ዘንድ በዘመናት ሁሉ ኀጢ
አተኛ እሆናለሁ። ፴፫ አሁንም እኔ በብላቴናው
ፈንታ የጌታዬ አገልጋይ ሆኜ ልቀመጥ፤ ብላ
ቴናው ግን ከወንድሞቹ ጋር ይሂድ። ፴፬ አለዚ
ያም ብላቴናው ከእኛ ጋር ከሌለ እኔ ወደ አባ
ታችን እንዴት እሄዳለሁ? አባታችንን የሚያገ
ኘውን መከራ እንዳላይ።”

## ምዕራፍ ፵፭

### ዮሴፍ ራሱን ለወንድሞቹ መግለጡ

፩ ዮሴፍም በፊቱ ሰዎች ሁሉ ቆመው ሳሉ
ሊታገሥ አልተቻለውም፥ “ሰዎቹንም ሁሉ
ከፊቴ አስወጡልኝ” ብሎ ተናገረ፤ ዮሴፍ ለወን
ድሞቹ ራሱን በገለጠ ጊዜ በእርሱ ዘንድ የቆመ
ማንም አልነበረም። ፪ ቃሉንም ከፍ አድርጎ አለ
ቀሰ፤ የግብፅ ሰዎችም ሰሙ፤ በፈርዖን ቤትም
ተሰማ። ፫ ዮሴፍም ለወንድሞቹ፥ “እኔ ወንድማ
ችሁ ዮሴፍ ነኝ፤ አባቴ እስከ አሁን በሕይወቱ
ነውን?” አላቸው። ወንድሞቹም ይመልሱለት
ዘንድ አልቻሉም፤ ደንግጠው ነበርና። ፬ ዮሴፍም
ወንድሞቹን፥ “ወደ እኔ ቅረቡ” አላቸው። ወደ
እርሱም ቀረቡ። እንዲህም አላቸው፥ “ወደ
ግብፅ የሸጣችሁኝ እኔ ወንድማችሁ ዮሴፍ ነኝ።
፭ አሁንም ወደዚህ ስለሸጣችሁኝ አትፍሩ፤ አት
ቈርቈሩም፤ እግዚአብሔር ለሕይወት ከእናንተ
በፊት ልኮኛልና። ፮ እነሆ፥ ይህ ሁለቱ ዓመት
በምድር ላይ ራብ የሆነበት ነውና፤ የማይታረ
ስበትና የማይታጨድበት አምስት ዓመት ገና
አለ። ፯ እግዚአብሔርም በምድር ላይ እንድት
ድኑና እንድትተርፉ እመግባችሁ ዘንድ ከእና
ንተ በፊት ላከኝ። ፰ አሁንም እናንተ ወደዚህ
የላካችሁኝ አይደላችሁም፤ እግዚአብሔር ላከኝ
እንጂ፤ ለፈርዖንም እንደ አባት[፩] አደረገኝ፤ በቤ
ቱም ሁሉ ላይ ጌታ፥ በግብፅ ምድርም ሁሉ
ላይ አለቃ አደረገኝ። ፱ አሁንም ፈጥናችሁ ወደ
አባቴ ሂዱ፤ እንዲህም በሉት፡- ልጅህ ዮሴፍ
የሚለው ነገር ይህ ነው፡- እግዚአብሔር በግ
ብፅ ምድር ሁሉ ላይ ጌታ አደረገኝ፤ ወደ እኔ
ና፤ በዚያም አትዘግይ፤ ፲ በዐረብ በኩል በጌሤም
ምድርም ትቀመጣለህ፤ ወደ እኔም ትቀርባለህ።
አንተና ልጆችህ የልጆችህም ልጆች፥ በጎችህና
ላሞችህ፥ የአንተ የሆነው ሁሉ፥ ፲፩ በዚያም አን
ተና የቤትህ ሰዎች የአንተ የሆነው ሁሉ እንዳ
ትቸገሩ እመግብሃለሁ፤ የራቡ ዘመን ገና አም
ስት ዓመት ቀርቶአልና፤ ፲፪ እነሆም፤ ለእናንተ
እኔ ራሴ በአፌ እንደ ተናገርሁአችሁ እናንተ
በዐይኖቻችሁ አይታችኋል፤ ወንድሜ ብንያም
በዐዓይኖቹ አይቶአል። ፲፫ ለአባቴ በግብፅ ምድር
ያለኝን ክብሬን ሁሉ፥ በዐይኖቻችሁ ያያችሁት
ንም ሁሉ ንገሩት፤ አባቴንም ወደዚህ ፈጥና
ችሁ አምጡት።” ፲፬ የወንድሙን የብንያምንም
አንገት አቅፎ አለቀሰ፤ ብንያምም በአንገቱ ላይ
አለቀሰ። ፲፭ ወንድሞቹን ሁሉ ሳማቸው፤ በእነ
ርሱም ላይ አለቀሰ፤ ከዚያም በኋላ ወንድሞቹ
ከእርሱ ጋር ተጫዋወቱ።

፲፮ በፈርዖንም ቤት፥ “የዮሴፍ ወንድሞች
መጡ” ተብሎ ወሬ ተሰማ፤ ፈርዖንና ቤተ

---

[፩] ግእዙ “ልጅ” ይላል።

ሰቡም ሁሉ ደስ አላቸው። ፲፯ፈርዖንም ዮሴ
ፍን አለው፥ "ለወንድሞችህ እንዲህ ብለህ ንገ
ራቸው፦ ይህን አድርጉ፤ ዕቃችሁን ጭናችሁ
ወደ ከነዓን ምድር ሂዱ፤ ፲፰አባታችሁንና ንብ
ረታችሁን ሁሉ[፱] ይዛችሁ ወደ እኔ ኑ፤ እኔም
የግብፅን ምድር በረከት ሁሉ እሰጣችሁአለሁ፤
የምድሪቱንም ድልብ ትበላላችሁ። ፲፱አንተም
ወንድሞችህን፦ እንዲህ አድርጉ በላቸው፤ ከግ
ብፅ ምድር ለሕፃኖቻችሁ፥ ለሴቶቻችሁም ሰረ
ገሎችን ውሰዱ፤ አባታችሁንም ይዛችሁ ኑ፤
፳ለዕቃችሁም ዐይናችሁ ለአየውም ሁሉ አታ
ስቡ፤ የግብፅ በረከት ሁሉ ለእናንተ ነውና።"
፳፩የእስራኤል ልጆችም እንደ አዘዛቸው አደ
ረጉ፤ ዮሴፍም የግብፅ ንጉሥ ፈርዖን እንደ ነገ
ረው ሰረገሎችንና ለመንገድ ስንቅን ሰጣቸው፤
፳፪ለሁሉም ሁለት ሁለት መለወጫ ልብስ ሰጣ
ቸው፤ ለብንያም ግን ሦስት መቶ ብርና አም
ስት መለወጫ ልብስ ሰጠው። ፳፫ለአባቱም እን
ደዚሁ ላከ፤ ከግብፅ በረከት ሁሉ የተጫኑ
ዐሥር አህዮችን፥ ደግሞም በመንገድ ለአባቱ
ስንቅ የተጫኑ ዐሥር በቅሎዎችን። ፳፬ዮሴፍም
ወንድሞቹን አሰናበታቸው፤ እንዲህም አላ
ቸው፥ "በመንገድ እርስ በርሳችሁ አትጣሉ።"
፳፭እነርሱም ከግብፅ ሀገር ወጥተው ሄዱ፤ ወደ
ከነዓንም ምድር ወደ አባታቸው ወደ ያዕቆብ
ደረሱ። ፳፮እንዲህም ብለው ነገሩት፥ "ልጅህ
ዮሴፍ በሕይወቱ ነው፤ እርሱም በግብፅ ምድር
ሁሉ ላይ ገዥ ሆኖአል።" ያዕቆብም ልቡ ደነ
ገጠ፤ አላመናቸውምም፤ ፳፯እነርሱም ዮሴፍ ያላ
ቸውን፥ የተናገራቸውንም ነገር ሁሉ ነገሩት፤
ይወስዱት ዘንድ ዮሴፍ የላካቸውን ሰረገሎች
በአየ ጊዜ የአባታቸው የያዕቆብ ልቡ፥ መንፈ
ሱም ታደሰ። ፳፰እስራኤልም፥ "ልጄ ዮሴፍ
ገና በሕይወት ከሆነ ይህ ለእኔ ታላቅ ነገር
ነው፤ ሳልሞት እንዳየው እሄዳለሁ" አለ።

## ምዕራፍ ፵፮

ያዕቆብ ከቤተ ሰቡ ጋር ወደ ግብፅ መሄዱ.

፩እስራኤልም ለእርሱ ያለውን ሁሉ ይዞ
ተነሣ፤ ወደ ዐዘቅተ መሐላም መጣ፤ መሥዋ
ዕትንም ለአባቱ ለይስሐቅ አምላክ ሠዋ። ፪እግ
ዚአብሔርም በሌሊት ራእይ፥ "ያዕቆብ ያዕ
ቆብ" ብሎ ለእስራኤል ተናገረው። እርሱም
"ምንድን ነው?" አለ። ፫አለውም፥ "የአባቶ
ችህ አምላክ እግዚአብሔር እኔ ነኝ፤ ወደ ግብፅ
መውረድን አትፍራ፤ በዚያ ትልቅ ሕዝብ አደ
ርግሃለሁና። ፬እኔ ወደ ግብፅ አብሬህ እወርዳ
ለሁ፤ ከዚያም ደግሞ እኔ አወጣሃለሁ፤ ልጅህ
ዮሴፍም እጁን በዐይንህ ላይ ያኖራል።" ፭ያዕ
ቆብም ከዐዘቅተ መሐላ ተነሣ፤ የእስራኤልም
ልጆች አባታቸውን፥ ገንዘባቸውን፥ ሚስቶቻ
ቸውንም እነርሱን ያመጡባቸው ዘንድ ዮሴፍ
በላካቸው ሰረገሎች ጭነው ወሰዱ።[፲] ፮ንዛቻ
ውን፥ በከነዓን ሀገርም ያገኙትን ጥሪታቸውን
ሁሉ ይዘው ያዕቆብና ዘሩ ሁሉ ከእርሱ ጋር
ወደ ግብፅ መጡ፤ ፯ወንዶች ልጆቹንና የወን
ዶች ልጆቹን ወንዶች ልጆች፥ ሴቶች ልጆቹ
ንና የሴቶች ልጆቹን ሴቶች ልጆች፥ ዘሩንም
ሁሉ ከእርሱ ጋር ወደ ግብፅ አስገባቸው።
፰ከአባታቸው ከያዕቆብ ጋር ወደ ግብፅ የገ
ቡት የእስራኤል ልጆች ስም ይህ ነው፤ ያዕ
ቆብና ልጆቹ፤ የያዕቆብ በኵር ሮቤል። ፱የሮ
ቤልም ልጆች፤ ሄኖኅ፥ ፍሉስ፥ አስሮን፥
ከርሚ። ፲የስምዖን ልጆች፤ ይሙኤል፥ ያሚን፥
አኡድ፥ ያኪን፥ ሱሐር፥ የከነዓናዊት ልጅ
ሳውል። ፲፩የሌዊም ልጆች፤ ጌድሶን፥ ቀዓት፥
ሜራሪ። ፲፪የይሁዳም ልጆች፤ ዔር፥ አውናን፥
ሴሎም፥ ፋሬስ፥ ዛራ፤ ዔርና አውናን በከነዓን
ምድር ሞቱ። የፋሬስም ልጆች እኒህ ናቸው፤
ኤስሮም፥ ይሞሔል፤ ፲፫የይሳኮርም ልጆች፤
ቶላዕ፥ ፎሓ፥ ያሱብ፥ ስምራ። ፲፬የዛብሎንም
ልጆች፤ ሳሬድ፥ አሎን፥ አሔል። ፲፭ልያ በመ
ስጴጦምያ በሶርያ ለያዕቆብ የወለደቻቸው ልጆ
ችና ሴቲቱ ልጅዋ ዲና እነዚህ ናቸው፤ ወን
ዶችም ሴቶችም ልጆችዋ ሁሉ ሠላሳ አራት[፲፩]
ነፍስ ናቸው። ፲፮የጋድም ልጆች፤ ስፎን፥ ሐጊ፥
ሱኒ፥ አዜን፥ አድ፥ አሮሐድ፥ አርሔል። ፲፯የአ
ሴርም ልጆች፤ ኢያምን፥ ኢያሱ፥ኢዩል፥
በሪዓ፥ እኅታቸው ሳራ፤ የበሪዓ ልጆችም፤
ኮቦር፥ መልኪኤል። ፲፰ላባ ለልጁ ለልያ የሰጣት
የዘለፋ ልጆች እነዚህ ናቸው፤ እርስዋም እነዚ
ህን ዐሥራ ስድስቱን ነፍስ ለያዕቆብ ወለደች።
፲፱የያዕቆብ ሚስት የራሔል ልጆች ዮሴፍና ብን

---

[፱] ዕብ. "ቤተ ሰባችሁን" ይላል።

[፲] ዕብ. "ያዕቆብን ይወስዱ ዘንድ ፈርዖን በላካቸው ሰረገሎች አባታቸውን ያዕቆብንና ሕፃኖቻቸውን፥ ሚስቶቻቸው ንም ወሰዱ" ይላል።

[፲፩] ግሪክ ሰባ. ሊ. እና ዕብ. "ሰላሳ ሦስት" ይላል።

ያም ናቸው። ፳ለዮሴፍም በግብፅ ምድር ልጆች ተወለዱለት፤ እነርሱም የሄልዮቱ ከተማ ካህን የጴጤፌራ ልጅ አስኔት የወለደችለት ምናሴና ኤፍሬም ናቸው። ሶርያዊት ዕቅብቱ የወለደች ለት የምናሴም ልጅ ማኪር ነው። ማኪርም ገለዓድን ወለደ፤ የምናሴም ወንድም የኤፍ ሬም ልጆች ሱታላና ጠኀን ናቸው። የሱታላ ልጅም ኤዴን ነው። ፳፩የብንያምም ልጆች፤ ቤላ፥ ቦኮር፥ አስቤር፤ የቤላ ልጆችም፤ ጌራ፥ ኖሔማን፥ አሒ፥ ሮስ፥ ማንፌን፥ ሑፊም፤ ጌራም አራድን ወለደ። ፳፪ለያዕቆብ የተወለዱ ለት የራሔል ልጆችም እነዚህ ናቸው፤ ሁሉም ዐሥራ አራት[፫] ነፍስ ናቸው። ፳፫የዳንም ልጅ አሳ ነው። ፳፬የንፍታሌምም ልጆች፤ አሴሔል፥ ጎሂን፥ ዮሴር ሴሌም። ፳፭ላባ ለልጁ ለራሔል የሰጣት የባላ ልጆች እነዚህ ናቸው፤ እነዚህ ንም ለያዕቆብ ወለደችለት፤ ባላ የወለደቻ ቸው ሁሉም ሰባት ነፍስ ናቸው። ፳፮ከያዕቆብ ጋር ወደ ግብፅ የገቡት ሰዎች ሁሉ ከጕልበቱ የወጡት፥ ከልጆቹ ሚስቶች ሌላ፥ ሁላቸው ስድሳ ሰባት[፬] ናቸው። ፳፯በግብፅ ምድር የተ ወለዱለት የዮሴፍም ልጆች ሁለት[፭] ናቸው፤ ወደ ግብፅ የገቡት የያዕቆብ ቤተ ሰዎች ሁሉ ሰባ[፮] ናቸው።

### ያዕቆብና ቤተ ሰቡ በግብፅ

፳፰ይሁዳንም ኤሮስ በምትባል በራምሴ ከተማ እንዲቀበለው በፊቱ ወደ ዮሴፍ ላከው፤ ፳፱ዮሴ ፍም ሰረገላውን አዘጋጀ፤ አባቱንም እስራኤ ልን ሊገናኘው ወደ ኤሮስ ከተማ ወጣ፤ በአየ ውም ጊዜ አንገቱን አቀፈው፤ ረዥም ጊዜም አለቀሰ። ፴እስራኤልም ዮሴፍን፥ "አንተ ገና በሕይወት ሳለህ ፊትህን አይችአለሁና አሁን ልሙት" አለው። ፴፩ዮሴፍም ወንድሞቹን እን ዲህ አላቸው፥ "እኔ ሄጄ ለፈርዖን እንዲህ ብዬ እነግረዋለሁ፦ በከነዓን ምድር የነበሩት ወንድሞችና የአባቴ ቤተ ሰዎች ወደ እኔ መጥ ተዋል፤ ፴፪እነርሱም ከብት ጠባቂዎች፥ መንጋ አርቢዎች ናቸው፤ በጎቻቸውንና ላሞቻቸውን፥ ያላቸውንም ሁሉ አመጡ። ፴፫ፈርዖንም ቢጠ ራችሁ ተግባራችሁስ ምንድን ነው? ቢላችሁ፥ ፴፬በግ ጠባቂ ሁሉ ለግብፅ ሰዎች ርኩስ ነውና በዐረብ በኩል በጌሤም እንድትቀመጡ እኛ አገ ልጋዮችህ ከብላቴንነታችን ጀምረን እስከ አሁን ድረስ እኛም አባቶቻችንም እንስሳ አርቢዎች ነን" በሉት።

## ምዕራፍ ፵፯

### ዮሴፍ የዘመዶቹን መምጣት ለፈርዖን መናገሩ

፩ዮሴፍም ገባ፤ ለፈርዖንም እንዲህ ብሎ ነገ ረው፥ "አባቴና ወንድሞች በጎቻቸውም፥ ላሞ ቻቸውም፥ ያላቸውም ሁሉ ከከነዓን ምድር መጡ፤ እነርሱም እነሆ፥ ወደ ጌሤም ምድር ደረሱ።" ፪ከወንድሞቹም አምስት ሰዎችን ወስዶ በፈርዖን ፊት አቆማቸው። ፫ፈርዖንም የዮሴፍን ወንድሞች፥ "ሥራችሁ ምንድን ነው?" አላቸው። እነርሱም ፈርዖንን፥ "እኛ አገልጋዮችህ፥ አባታችንም ከብት ጠባቂዎች ነን" አሉት። ፬ፈርዖንንም እንዲህ አሉት፥ "በምድር ልንቀመጥ በእንግድነት መጣን፤ የአ ገልጋዮችህ በጎች የሚሰማሩበት ስፍራ የለምና፤ ራብም በከነዓን ምድር እጅግ ጸንቶአልና፤ አሁንም አገልጋዮችህ በጌሤም ምድር እንቀ መጥ።" ፭ፈርዖንም ዮሴፍን እንዲህ ብሎ ተናገ ረው፥ "አባትህና ወንድሞችህ መጥተውልሃል፤ እነሆ፥ የግብፅ ምድር በፊትህ ናት፤ ፮በመል ካሙ ምድር አባትህንና ወንድሞችህን አኑራ ቸው፤[፯] ከእነርሱም ውስጥ ዕውቀት ያላቸውን ሰዎች ታውቅ እንደሆነ በእንስሶች ጠባቂዎች ላይ አለቆች አድርጋቸው።"[፰] ፯ዮሴፍም ያዕቆ ብን አባቱን አስገብቶ በፈርዖን ፊት አቆመው፤ ያዕቆብም ፈርዖንን ባረከው። ፰ፈርዖንም ያዕቆ ብን፥ "የኖርኸው ዘመን ስንት ነው?" አለው። ፱ያዕቆብም ለፈርዖን አለው፥ "በእንግድነት የኖ ርሁት የሕይወቴ ዘመንስ መቶ ሠላሳ ዓመት ነው፤ የሕይወቴም ዘመኖች ጥቂትም ክፉም ሆኑብኝ፤ አባቶች በእንግድነት የተቀመጡበት

---

[፫] ግሪክ ሰባ. ሊ. "ዐሥራ ስምንት" ይላል።

[፬] ግሪክ ሰባ. ሊ. እና ዕብ. "ስድሳ ስድስት" ይላል።

[፭] ግሪክ ሰባ. ሊ. "ዘጠኝ" ይላል።

[፮] ግሪክ ሰባ. ሊ. "ሰባ አምስት" ይላል።

[፯] ዕብ. "በጌሤም ምድር ይኑሩ" የሚል ይጨምራል።

[፰] "ከእነርሱም ውስጥ ዕውቀት ያላቸውን ሰዎች ታውቅ እንደሆነ በእንስሶች ጠባቂዎች ላይ አለቆች አድርጋቸው" የሚለው በግሪክ ሰባ. ሊ. የለም።

ንም ዘመን አያህሉም።” ፲ያዕቆብም ፈርዖንን
ባረከው፤ ከፈርዖንም ፊት ወጣ። ፲፩ዮሴፍም
አባቱንና ወንድሞቹን አኖረ፤ ፈርዖን እንዳዘዘ
ላቸውም በግብፅ ምድር በተሻለችው በራምሴ
ምድር ርስትን ሰጣቸው። ፲፪ዮሴፍም ለአባቱና
ለወንድሞቹ፥ ለአባቱም ቤተ ሰዎች ሁሉ ለእ
ያንዳንዱ ሰው እየሰፈረ እህልን ለምግብ ይሰ
ጣቸው ነበር።

### በግብፅ የራብ መጽናትና የዮሴፍ አመራር

፲፫በምድርም ሁሉ እህል አልነበረም፤ ራብ
እጅግ ጸንቶአልና፤ ከራብም የተነሣ የግብፅ
ምድርና የከነዓን ምድር ተጐዳ። ፲፬ዮሴፍም
ከግብፅ ምድርና ከከነዓን ምድር በእህል ሸመታ
የተገኘውን ብሩን ሁሉ አከማቸ፤ ዮሴፍም
ብሩን ወደ ፈርዖን ቤት አስገባው። ፲፭ብሩም
በግብፅ ምድርና በከነዓን ምድር አለቀ፤ የግ
ብፅ ሰዎችም ሁሉ ወደ ዮሴፍ መጡ፤ እንዲህ
ሲሉ፥ “በፊትህ እንዳንሞት እህል ስጠን፤ ብሩ
አልቆብናልና።” ፲፮ዮሴፍም፥ “ከብቶቻችሁን
አምጡልኝ፤ ብር ከአለቀባችሁ በከብቶቻችሁ
ፈንታ እህል እሰጣችኋለሁ” አለ። ፲፯ከብቶቻቸ
ውንም ወደ ዮሴፍ አመጡ፤ ዮሴፍም በፈረሶ
ቻቸው፥ በበጎቻቸውም፥ በላሞቻቸውም፥ በአ
ህዮቻቸውም ፈንታ እህልን ሰጣቸው፤ በዚያች
ዓመትም ስለ ከብቶቻቸው ሁሉ ፈንታ እህልን
መገባቸው። ፲፰ያችም ዓመት ተፈጸመች፤ በሁ
ለተኛዋም ዓመት ወደ እርሱ መጥተው እንዲህ
አሉት፥ “እኛ ለጌታችን ሞተን እንዳናልቅበት
እህል ስጠን፤ ብሩ በፍጹም አለቀ፤ ንብረታ
ችንና ከብታችንም በጌታችን ዘንድ ነው፤ ከሰ
ውነታችንና ከምድራችን በቀር በጌታችን ፊት
አንዳች የቀረን የለም፤ ፲፱እንግዲህ እኛ በፊትህ
እንዳንሞት፥ ምድራችንም እንዳትጠፋ፥ እኛ
ንም፥ ምድራችንንም በእህል ግዛን፤ እኛም ለፈ
ርዖን አገልጋዮች እንሁን፤ ምድራችንም ለእ
ርሱ ትሁን፤ እኛ እንድንድን፥ እንዳንሞትም፥
ምድራችንም እንዳትጠፋ እንዘራ ዘንድ ዘር
ስጠን።” ፳ዮሴፍም የግብፅን ምድር ሁሉ ለፈ
ርዖን ገዛ፤ የግብፅ ሰዎች ሁሉ ራብ ስለጸናባ
ቸው ርስታቸውን ሸጠዋልና፤ ምድሪቱ ለፈር
ዖን ሆነች። ፳፩ሕዝቡንም ሁሉ ከግብፅ ዳርቻ
አንሥቶ እስከ ሌላው ዳርቻዋ ድረስ አገልጋ
ዮች አደረጋቸው። ፳፪ዮሴፍ የካህናትን ምድር
ብቻ አልገዛም፤ ፈርዖን ለካህናቱ ድርጎ ይሰ
ጣቸው ነበርና፥ ፈርዖንም የሰጣቸውን ድርጎ
ይበሉ ነበር፤ ስለዚህም ምድራቸውን አልሸ
ጡም። ፳፫ዮሴፍም የግብፅን ሰዎች ሁሉ እንዲህ
አላቸው፥ “እነሆ ዛሬ እናንተንና ምድራችሁን
ለፈርዖን ገዝቻችኋለሁ፤ ለእናንተ ዘር ውሰዱና
ምድሪቱን ዝሩ፤ ፳፬በመከርም ጊዜ ፍሬውን ከአ
ምስት እጅ አንዱን እጅ ለፈርዖን ስጡ፤ አራ
ቱም እጅ ለእናንተ ለራሳችሁ፥ ለእርሻው ዘርና
ለእናንተ ምግብ፥ ለቤተ ሰባችሁም ሁሉ ሲሳይ
ይሁን።” ፳፭እነርሱም፥ “አንተ አዳንኸን፤ በጌ
ታችንም ፊት ሞገስን አገኘን፤ ለፈርዖንም አገ
ልጋዮች እንሆናለን” አሉት። ፳፮ዮሴፍም ለፈር
ዖን ካልሆነችው ከካህናቱ ምድር በቀር አምስ
ተኛው እጅ ለፈርዖን እንዲሆን በግብፅ ምድር
እስከ ዛሬ ሕግ አደረጋት።

### ያዕቆብ በሀገሩ እንዲቀበር ዮሴፍን መለመኑ

፳፯እስራኤልም በግብፅ ምድር በጌሤም ሀገር
ተቀመጠ፤ እርስዋም ርስታቸው ሆነች፤ በዙ፤
እጅግም ተባዙ። ፳፰ያዕቆብም በግብፅ ምድር
ዐሥራ ሰባት ዓመት ተቀመጠ፤ የያዕቆብም
መላው የሕይወቱ ዘመን መቶ አርባ ሰባት
ዓመት ሆነ። ፳፱የእስራኤልም የሞቱ ቀን ቀረበ፤
ልጁን ዮሴፍንም ጠርቶ እንዲህ አለው፥ “በፊ
ትህ ሞገስን አግኝቼ እንደ ሆንሁ እጅህን በጕ
ልበቴ ላይ አድርግ፤ በግብፅ ምድርም እንዳ
ትቀብረኝ ምሕረትንና እውነትን አድርግልኝ፤
፴ከአባቶችም ጋር በአንቀላፋሁ ጊዜ ከግብፅ
ምድር አውጥተህ ትወስደኛለህ፤ በአባቶችም
መቃብር ትቀብረኛለህ።” እርሱም፥ “እንደ
ቃልህ አደርጋለሁ” አለ። እርሱም፥ “ማል
ልኝ” አለው። ፴፩ዮሴፍም ማለለት፤ እስራኤ
ልም በአልጋው[፫] ራስ ላይ ሰገደ።

## ምዕራፍ ፵፰

### ያዕቆብ ኤፍሬምንና ምናሴን መባረኩ

፩ከዚህም ነገር በኋላ እንዲህ ሆነ፤ “እነሆ፥
አባታችን ደከመ” ብለው ለዮሴፍ ነገሩት፤
እርሱም ሁለቱን ልጆቹን ምናሴንና ኤፍሬ
ምን ይዞ ሄደ። ፪ለያዕቆብም፥ “እነሆ፥ ልጅህ
ዮሴፍ መጥቶልሃል” ብለው ነገሩት፤ እስራኤ
ልም ተጠነካከረ፤ በአልጋውም ላይ ተቀመጠ።
፫ያዕቆብ ዮሴፍን አለው፥ “አምላኬ በከነዓን
ምድር በሎዛ ተገለጠልኝ፤ ባረከኝም። ፬እንዲ

---

[፫] ግሪክ ሰባ. ሊ. “በበትሩ ጫፍ ሰገደ” ይላል።

ህም አለኝ:- እነሆ፥ አበዛሃለሁ፤ አባዛሃለሁም፤
ለብዙም ሕዝብ ጉባኤ አደርግሃለሁ፤ ይህችንም
ምድር ለአንተ፥ ከአንተም በኋላ ለዘለዓለም
ርስት ለዘርህ እሰጣታለሁ። ፭ አሁንም እኔ ወደ
አንተ ከመምጣቴ በፊት በግብፅ ምድር የተወ
ለዱልህ ሁለቱ ልጆችህ ለእኔ ይሁኑ፤ ኤፍሬ
ምና ምናሴ ለእኔ እንደ ሮቤልና እንደ ስምዖን
ናቸው። ፮ ከእነርሱም በኋላ የምትወልዳቸው
ልጆች ለአንተ ይሁኑ፤ በርስታቸው በወንድሞ
ቻቸው ስም ይጠሩ። ፯ እኔም ከሶርያ መስጴጦ
ምያ በመጣሁ ጊዜ፥ ወደ ኤፍራታ ለመግባት
ጥቂት ቀርቶኝ በፈረስ መጋለቢያው መንገድ
ሳለሁ፥ ራሔል በከነዓን ምድር ሞተችብኝ፤
በዚያም በኤፍራታ ወደ ፈረስ መጋለቢያ በሚ
ወስደው መንገድ ላይ ቀበርኋት፤ እርስዋም
ቤተ ልሔም ናት።"
፰ እስራኤልም የዮሴፍን ልጆች ለይቶ፥
"እነዚህ ምኖችህ ናቸው?" አለው። ፱ ዮሴ
ፍም ለአባቱ፥ "እግዚአብሔር በዚህ የሰጠኝ
ልጆች ናቸው" አለው። ያዕቆብም፥ "እባር
ካቸው ዘንድ ወደ እኔ አቅርብልኝ" አለው።
፲ የእስራኤልም ዐይኖች ከሽምግልና የተነሣ
ከብደው ነበር፤ ማየትም አይችልም ነበር፤
ወደ እርሱም አቀረባቸው፤ ሳማቸውም፤ አቀ
ፋቸውም። ፲፩ እስራኤልም ዮሴፍን፥ "ከፊትህ
አልተለየሁም፤[፩] እነሆም፥ እግዚአብሔር ዘር
ህን ደግሞ አሳየኝ" አለው። ፲፪ ዮሴፍም ከጕ
ልበቱ ፈቀቅ አደረጋቸው፤ ወደ ምድርም
በግንባሩ ሰገደ። ፲፫ ዮሴፍም ሁለቱን ልጆቹን
ወሰደ፤ ኤፍሬምንም በቀኙ በእስራኤል ግራ፥
ምናሴንም በግራው በእስራኤል ቀኝ አቆማ
ቸው፤ ወደ አባቱም አቀረባቸው። ፲፬ እስራኤ
ልም ቀኝ እጁን ዘርግቶ በኤፍሬም ራስ ላይ
አኖረው፤ እርሱም ታናሽ ነበረ፤ ግራውንም
በምናሴ ራስ ላይ አኖረ፤ እጆቹንም አስተላ
ለፈ።[፪] ፲፭ ያዕቆብም ባረካቸው፤[፫] እንዲህም
አለ፥ "አባቶች አብርሃምና ይስሐቅ በፊቱ
ደስ ያሰኙት እርሱ እግዚአብሔር፥ ከታናሽ
ነቴ ጀምሮ እስከ ዛሬ ድረስ እኔን የመገበኝ
እግዚአብሔር፥ ፲፮ ከክፉ ነገር ሁሉ የአዳነኝ
መልአክ እርሱ እነዚህን ብላቴኖች ይባርክ፤
ስሜም፥ የአባቶች የአብርሃምና የይስሐቅም
ስም በእነርሱ ይጠራ፤ በምድር ላይ ይብዙ፤
የብዙ ብዙም ይሁኑ፤ ፲፯ ዮሴፍም አባቱ ቀኝ
እጁን በኤፍሬም ራስ ላይ ጭኖ በአየ ጊዜ
ከባድ ነገር ሆነበት፤ ዮሴፍም የአባቱን እጅ
በምናሴ ራስ ላይ ይጭነው ዘንድ ከኤፍ
ሬም ራስ ላይ አነሣው። ፲፰ ዮሴፍም አባቱን፥
"አባቴ ሆይ፥ እንዲህ አይደለም፤ በኵሩ ይህ
ነውና ቀኝህን በራሱ ላይ አድርግ" አለው።
፲፱ አባቱም እንቢ አለ፤ እንዲህ ሲል፥ "አው
ቃለሁ ልጄ ሆይ፥ አውቃለሁ፤ ይህም ደግሞ
ሕዝብ ይሆናል፤ ታላቅም ይሆናል፤ ነገር ግን
ታናሽ ወንድሙ ከእርሱ ይበልጣል፤ ዘሩም
ብዙ ሕዝብ ይሆናል።" ፳ በዚያም ቀን እንዲህ
ብሎ ባረካቸው፥ "በእናንተ እስራኤል[፬] እን
ዲህ ተብሎ ይባረካል:- እግዚአብሔር እንደ
ኤፍሬምና እንደ ምናሴ ይባርክህ።" ኤፍሬም
ንም ከምናሴ ፊት አደረገው። ፳፩ እስራኤልም
ዮሴፍን፥ "እነሆ፥ እኔ እሞታለሁ፤ እግዚአብ
ሔርም ከእናንተ ጋር ይሆናል፤ ወደ አባቶቻ
ችሁም ምድር ይመልሳችኋል፤ ፳፪ እኔም ከአ
ሞራውያን እጅ በሰይፌና በቀስቴ የወሰድሁ
ትን ምርኮ ለአንተ ከወንድሞችህ የተሻለውን
እሰጥሃለሁ" አለው።

## ምዕራፍ ፵፱

### ያዕቆብ ልጆቹን እንደ መረቃቸው

፩ ያዕቆብም ልጆቹን ጠርቶ እንዲህ አላቸው፥
"በኋለኛው ዘመን የሚያገኛችሁን እንድነግራ
ችሁ ተሰብሰቡ። ፪ እናንት የያዕቆብ ልጆች ኑ፥
ተሰብሰቡ፤ ስሙም፤ አባታችሁ እስራኤልንም
አድምጡ።
፫ "ሮቤል እርሱ የበኵር ልጄና ኀይሌ፥ የልጆ
ችም[፭] መጀመሪያ ነው፤ ክፉ ሆነ፤ አንገቱንም
አደነደነ።[፮] ጭንቅ ነገርንም አደረገ። ፬ እንደ
ውኃ የሚዋልል ነው፤ ኀይል የለውም፤[፯] ወደ

---

፩ ዕብ. "ፊትህን አያለሁ ብዬ አላሰብሁም ነበር" ይላል።

፪ ዕብ. "ምናሴ በኵር ነበርና" የሚል ይጨምራል።

፫ ዕብ. "ያዕቆብ ዮሴፍን ባረከ" ይላል።

፬ አንዳንድ የግእዝ ዘርዕ "በእናንተ የእስራኤል አምላክ ይመሰገናል" ይላል።

፭ ዕብ. "የጕብዝናዬ" ይላል።

፮ ዕብ. "የክብር አለቃና የኀይል አለቃ" ይላል።

፯ ዕብ. "አለቅነት ለአንተ አይሁን" ይላል።

አባቱ መኝታ ወጥቶአልና፤ ያን ጊዜ የወጣበ
ትን አልጋ አርክሶአልና።
፭“ስምዖንና ሌዊ ወንድማማቾች ናቸው፤
በጭቅጭቃቸውና በጦራቸው ዐመፅን ፈጸሙ
አት። ፮በምክራቸው ሰውነቴ አትገናኛቸው፤
ዐሳቤም በአመፃቸው አትተባበርም፤ በቍጣ
ቸው ሰውን ገድለዋልና፤ በገዛ ፈቃዳቸውም
የሀገርን ሥር ቈርጠዋልና። ፯ቍጣቸው ርጉም
ይሁን፤ ጽኑ ነበርና፤ ዥርፍታቸውም ብርቱ ነበ
ርና፤ በያዕቆብ እከፋፍላቸዋለሁ፤ በእስራኤልም
እበታትናቸዋለሁ።
፰“ይሁዳ፥ ወንድሞችህ አንተን ያመሰግኑ
ሃል፤ እጅህ በጠላቶችህ ደንደስ ላይ ነው፤ የአ
ባትህ ልጆች በፊትህ ይሰግዳሉ። ፱ይሁዳ የአ
ንበሳ ደቦል ነው፤ ልጄ ሆይ፥ ከመሰማሪያህ
ወጣህ፤ እንደ አንበሳ ተኛህ፤ አንቀላፋህም፤
እንደ አንበሳም ደቦል የሚቀሰቅስህ የለም።
፲መንግሥት ከይሁዳ አይጠፋም፤ ምስፍናም
ከአብራኩ፥ ለእርሱ የሚጠብቀውን እስኪያ
ገኝ ድረስ፤ የአሕዛብ ተስፋቸው እርሱ ነውና፤
፲፩አህያይቱን በወይን ግንድ ያስራል፤ የአህያይ
ቱንም ግልገል በወይን ሐረግ፤ ልብሱን በወይን
ያጥባል፤ መጐናጸፊያውንም በዘለላው ደም።
፲፪ዐይኖቹ ከወይን ይልቅ ደስ ያሰኛሉ፤ ጥርሱም
ከወተት ይልቅ ነጭ ነው።
፲፫“ዛብሎን ጫማውን አዝቦ ይኖራል፤ እር
ሱም እንደ መርከቦች ወደብ ይሆናል፤ ዳርቻ
ውም እስከ ሲዶና ይሰፋል።
፲፬“ይሳኮር መልካም ነገርን ወደደ፤ በተወራ
ራሾቹም መካከል ያርፋል። ፲፭ዕረፍትም መል
ካም መሆንዋን፥ ምድሪቱም የለማች መሆንዋን
በአየ ጊዜ ምድርን ያርሳት ዘንድ ትከሻውን
ዝቅ አደረገ፤ በሥራም ገበሬ ሆነ።
፲፮“ዳን ከእስራኤል ነገድ እንደ አንዱ በወ
ገኑ ይፈርዳል፤ ፲፯ዳን በጎዳና ላይ እንደሚያደባ
እባብ ይሆናል፤ በመንገዱም የፈረሱን ሰኰና
እንደሚናደፍ እንደ ቀንዳም እባብ ነው፤ ፈረሰ
ኛውም ወደኋላው ይወድቃል። ፲፰እግዚአብሔ
ርም ያድነው ዘንድ ይጠብቃል።[፩]
፲፱“ጋድን ሽፍቶች ቀሙት፤ እርሱም ፍለጋ
ቸውን ተከታትሎ ቀማቸው።
፳“የአሴር እንጀራ ወፍራም ነው፤ እርሱም
ለአለቆች ደስ የሚያሰኝ መብልን ይሰጣል።
፳፩“ንፍታሌም በፍሬው ላይ ውበትን የሚ
ሰጥ ሰፊ ዘንባባ ነው።[፪]
፳፪“ዮሴፍ የሚያድግ ልጅ ነው፤ ለእኔ በጣም
የተወደደ የሚቀናልኝና የሚያድግልኝ ልጅ
ነው፤ ወደ እኔ የሚመለስም ጐልማሳ ነው።[፫]
፳፫በምክራቸው የሰደቡት ጌቶች ሆኑበት፤ ቀስ
ተኞችም ወጉት፤ ፳፬ነገር ግን ቀስቶቻቸው በኀ
ይል ተቀጠቀጡ፤ የእጆቻቸው ክንድ ሥርም
በያዕቆብ ኀያል እጅ ዛለ፤ በዚያም በአባትህ
አምላክ ዘንድ እስራኤልን አጸናው።
፳፭“የእኔ አምላክ ረዳህ፤ ከላይ በሰማይ በረ
ከት፥ ሁሉ በሚገኝባት፥ በምድር በረከት፥
በጡትና በማኅፀን በረከት ባረከህ፤ ፳፮የአባት
ህና የእናትህ በረከቶች ጽኑዓን ከሆኑ ከተራ
ሮች በረከቶች ይልቅ ይበልጣሉ፤ ዘለዓለማው
ያን ከሆኑ ከኮረብቶችም[፬] በረከቶች ይልቅ ኀያ
ላን ናቸው፤ እነርሱም በዮሴፍ ራስ ላይ ይሆ
ናሉ፤ በወንድሞቹ መካከል አለቃ በሆነውም
ራስ አናት ላይ ይሆናሉ።
፳፯“ብንያም ነጣቂ ተኵላ ነው፤ በጥዋት ይበ
ላል፤ የማረከውንም ምግቡን በማታ ለሕዝብ
ይሰጣል።” ፳፰እነዚህም ሁሉ ዐሥራ ሁለቱ የያ
ዕቆብ ልጆች ናቸው፤ አባታቸውም ይህን ነገር
ነገራቸው፤ ባረካቸውም፤ እያንዳንዳቸውንም
እንደ በረከታቸው ባረካቸው።

### የያዕቆብ መሞትና መቀበር

፳፱እንዲህም ብሎ አዘዛቸው፥ “እኔ ወደ
ወገኖች እሰበሰባለሁ፤ በኬጢያዊው በኤፍ
ሮን እርሻ ላይ ባለችው ዋሻ ከአባቶች ጋር
ቅበሩኝ፤ እርስዋም በከነዓን ምድር በመምሬ
ፊት ያለች፥ ፴አብርሃም ለመቃብር ርስት ከኬ
ጢያዊው ከኤፍሮን ከእርሻው ጋር የገዛት፥
ባለ ድርብ ክፍል ዋሻ ናት። ፴፩አብርሃምንና
ሚስቱ ሣራንም በዚያ ቀበሩአቸው፤ ይስሐቅ
ንና ሚስቱ ርብቃንም በዚያ ቀበሩአቸው፤ ከዚ
ያም እኔ ልያን ቀበርኋት ፴፪እርሻውና በእር
ስዋ ላይ ያለችው ዋሻ ከኬጢ ልጆች የተገዙ
ናቸው።” ፴፫ያዕቆብም ትእዛዙን ለልጆቹ ተና

---

[፩] ዕብ. “እግዚአብሔር ሆይ መድኀኒትህን እጠብቃለሁ” ይላል።

[፪] ዕብ. “የተፈታ ሚዳቋ ነው መልካም ቃልን ይሰጣል” ይላል።

[፫] ዕብ. “ዮሴፍ ትንሹ የፍሬ ዛፍ ነው፤ በምንጭ አጠገብ የሚያፈራ የፍሬ ዛፍ ነው፤ ሐረጎቹ በቅጥር ላይ ያድጋሉ” ይላል።

[፬] ግእዝ “በረከተ መላእክቲሁ ለእግዚአብሔር” ይላል።

ግሮ በፈጸመ ጊዜ እግሮቹን በአልጋው ላይ ዘር ግቶ ሞተ፤ ወደ ወገኖቹም ተጨመረ።

## ምዕራፍ ፶

፩ዮሴፍም በአባቱ ፊት ወደቀ፤ በእርሱም ላይ አለቀሰ፤ ሳመውም። ፪ዮሴፍም ባለ መድኀኒቶች አገልጋዮቹ አባቱን በሽቱ ያሹት ዘንድ አዘዘ፤ ባለ መድኀኒቶችም እስራኤልን በሽቱ አሹት። ፫አርባ ቀንም ፈጸሙለት፤ ሽቱ የሚቀቡበትን ቀን እንዲሁ ይቈጥራሉና፤[፩] የግብፅም ሰዎች ሰባ ቀን አለቀሱለት።

፬የልቅሶውም ወራት ከተፈጸመ በኋላ ዮሴፍ ለፈርዖን መኳንንት እንዲህ ብሎ ተናገረ፤ "እኔ በፊታችሁ ሞገስን አግኝቼ እንደ ሆንሁ ለፈርዖን እንዲህ ብላችሁ ስለ እኔ ንገሩት፦ ፭አባቴ ሳይሞት አምሎኛል፤ እንዲህ ሲል፦ 'እነሆ እኔ እሞታለሁ፤ በቈፈርሁት መቃብር በከነዓን ምድር በዚያ ቅበረኝ።' አሁንም ወጥቼ አባቴን ልቅበርና ልመለስ።" ፮ፈርዖንም ዮሴፍን አለው፦ "ውጣ፤ አባትህንም እንዳማለህ ቅበረው።" ፯ዮሴፍም አባቱን ሊቀብር ወጣ፤ የፈርዖን ሎሌዎችም ሁሉ፥ የቤቱ ሽማግሌዎችም ሁሉ፥ የግብፅ ምድር ሽማግሌዎችም ሁሉ ከእርሱ ጋር ወጡ፤ ፰የዮሴፍም ቤተ ሰቦች ሁሉ፥ ወንድሞቹም፥ የአባቱም ቤተ ሰቦች ወጡ፤ ልጆቻቸውንና በጎቻቸውን፥ ከብቶቻቸውንም ብቻ በጌሤም ተዉ። ፱ሰረገሎችም፥ ፈረሰኞችም ከእርሱ ጋር ወጡ፤ ሠራዊቱም ብዙ ነበር። ፲በዮርዳኖስ ማዶ ወዳለችው ወደ አጣድ አውድማ ደረሱ፤ እጅግ ታላቅ በሆነ በጽኑ ልቅሶም አለቀሱለት፤ ለአባቱም ሰባት ቀን ልቅሶ አደረገለት። ፲፩በዚያች ምድር የሚኖሩ የከነዓን ሰዎችም በአጣድ አውድማ የሆነውን ልቅሶ በአዩ ጊዜ፥ "የግብፅ ልቅሶ እንዲህ ታላቅ ነውን?" አሉ፤ ስለዚህም የዚያን ቦታ ስም "ላሐ ግብፅ" ብለው ጠሩት፤ እርሱም በዮርዳኖስ ማዶ ነው። ፲፪ልጆቹም እንዳዘዛቸው እንደዚያው አደረጉለት፤ ፲፫ልጆቹም ወደ ከነዓን ምድር መለሱት፤ ባለ ሁለት ክፍል በሆነች ዋሻም ቀበሩት፤ እርስዋም በመምሬ ፊት ያለች፥ አብርሃም ለመቃብር ርስት ከኬጢያዊው ከኤፍሮን ከእርሻው ጋር የገዛት ዋሻ ናት። ፲፬ዮሴፍና ወንድሞቹ፥ አባቱንም ሊቀብሩ ከእርሱ ጋር የወጡት ሰዎች ሁሉ አባቱን ከቀበረ በኋላ ወደ ግብፅ ተመለሱ።

### ዮሴፍ ወንድሞቹን ማረጋጋቱ

፲፭የዮሴፍም ወንድሞች አባታቸው እንደ ሞተ በአዩ ጊዜ እንዲህ አሉ፥ "ምናልባት ዮሴፍ ያደረግንበትን ክፋት ያስብብን ይሆናል፤ ባደረግንበትም ክፋት ሁሉ ብድራት ይመልስብን ይሆናል።" ፲፮ወደ ዮሴፍም መጡ፤ እንዲህም አሉት፥ "አባትህ ገና ሳይሞት እንዲህ ብሎ አዝዟል፦ ፲፯'ዮሴፍን እንዲህ በሉት፦ እባክህ የወንድሞችህን በደል ኀጢአታቸውንም ይቅር በል፤ እነርሱ በአንተ ክፉ አድርገውብሃልና፤' አሁንም እባክህ የአባትህ አምላክ ባሪያዎች የበደሉህን ይቅር በል።" ፲፰ዮሴፍም ይህን ሲሉት አለቀሰ። ወንድሞቹ ደግሞ መጡ፤[፪] "እነሆ፥ እኛ ለአንተ አገልጋዮችህ ነን" አሉት። ፲፱ዮሴፍም አላቸው፥ "አትፍሩ፤ ይህ ከእግዚአብሔር ዘንድ ሆኖአልና።[፫] ፳እናንተ በእኔ ላይ ክፉ መከራችሁ፤ እግዚአብሔር ግን ዛሬ እንደ ሆነው ብዙ ሕዝብ እንዲመገብ ለማድረግ ለእኔ መልካም መከረ። ፳፩አሁንም አትፍሩ፤ እኔ እናንተንና ቤተ ሰቦቻችሁን እመግባችኋለሁ።" አጽናናቸውም፤ በልባቸው የሚገባ ነገርም ነገራቸው።

### የዮሴፍ ሞት

፳፪ዮሴፍም በግብፅ ሀገር ተቀመጠ፤ እርሱና ወንድሞቹ የአባቱም ቤተ ሰብ፤ ዮሴፍም መቶ ዐሥር ዓመት ኖረ። ፳፫ዮሴፍም የኤፍሬምን ልጆች እስከ ሦስት ትውልድ አየ። የምናሴ ልጅ የማኪር ልጆችም በዮሴፍ ጭን ላይ ተወለዱ። ፳፬ዮሴፍም ወንድሞቹን አላቸው፥ "እኔ እሞታለሁ፤ እግዚአብሔርም መጐብኘትን ይጐበኛችኋል፤ ከዚህችም ምድር ያወጣችኋል። ለአባቶቻችን ለአብርሃምና ለይስሐቅ ለያዕቆብም ወደ ማለላቸው ምድር ያገባችኋል።" ፳፭ዮሴፍም የእስራኤልን ልጆች፥ "እግዚአብሔር በጐበኛችሁ ጊዜ አጥንቴን ከዚህ አንሥታችሁ ከእናንተ ጋር አውጡ" ብሎ አማላቸው። ፳፮ዮሴፍም በመቶ ዐሥር ዓመት ዕድሜው ሞተ፤ በሽቱም አሹት፤ በግብፅ ምድርም በሣጥን ውስጥ አኖሩት።

---

፩ ዕብ. "የሽቱ ማድረጊያው ቀን እንዲሁ ይፈጸማልና" ይላል።

፪ ዕብ. "በፊቱም ሰግደው" የሚል ይጨምራል።

፫ ግሪክ ሰባ. ሊ. "እኔ የእግዚአብሔር ነኝና" ዕብ. "እኔ በእግዚአብሔር ፋንታ ነኝን" ይላል።